# መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት።

## በግእዝና ፡ በአማርኛ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ በብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ጳውሎስ ፡ ፓትርያርክ ፡
ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዘአክሱም ፡ ወዕጨጌ ፡ ዘመንበረ ፡
ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በ፲፩ኛው ፡ ዘመነ ፡ ፓትርያርክነት ፡ ለመጀመሪያ ፡
ጊዜ ፡ በግእዝና ፡ በአማርኛ ፡ ታተመ።


<u>አሳታሚ</u> :– ትንሣኤ ፡ ማሳተሚያ ፡ ድርጅት፡
አ.አ. ፲፱፻፺፯ ፡ ዓ.ም


Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡ሌሊት፡ዘሠኑይ

ትብልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ደብር ፡ ፍልስ ፡ እምዝየ ፡ ወበጊዜሃ፡ፍጡነ፡ይሰምዕ፡እምኔክሙ፡ወኢ የዐጽበክሙ፡ምንተኒ።
፳፮፤ እስመ፡ኵሉ፡ይትከሀል፡ለምእመናን።
፳፯፤ ወናጥሪ ፡ ለነ ፡ ተስፋ ፡ ዐቢየ ፡ ወሃይማኖተ ፡ ዘበአማን ፡ ዘእንበለ ፡ ኑፋቄ ፡ ወንትቃሐው ፡ ውስተ፡ፍቅር፡ዘልዕልት፡ላዕለ፡ኵሉ፡እስመ፡ ፍቅር፡ያስተአምን፡በኵሉ።
፳፰፤ ወናዝልፍ ፡ ጸሎተ ፡ ወናፍቅር ፡ ጾመ ፡ ከመ ፡ ንትመጦ፡ተስፋሆሙ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡ መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ ማማቲሁ፡አድኃነነ።
ጸልዩ ፡ በእንተ ፡ ጽንዐ ፡ ዛቲ ፡ በል ፤ ወኵሎ ፡ ከመ፡ቀዳሚ፡አብጽሕ

ሰኞ፡ሌሊት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ተነቀል ፡ ብትሉት ፡ ወዲያው ፡ ፈጥኖ ፡ ይታዘዛችኋል ። ምንም ፡ የሚሳናችሁ ፡ የለም።
፳፮፤ ለሚያምን፡ሁሉ፡ይቻላልና።
፳፯፤ እንግዲህ ፡ ለኛ ፡ ያለ ፡ መጠራጠር ፡ ሃይማ ኖትን፡ ተስፋን ፡ ገንዘብ ፡ እናድርግ ፤ ከሁሉ፡ በላይ፡የሆነች፡ፍቅርን፡ለመያዝ፡እንፎካከር፤ ፍቅር፡በሁሉ፡ዘንድ፡ያስተማምናልና።
፳፰፤ ጸሎትን፡እናዘውትር፤ጾምን፡እንውደድ፤በሃ ይማኖትና ፡ በፍቅር ፡ የሚገኘውን ፡ ተስፋ ፡ እንቀበል፡ዘንድ።
ክርስቶስ ፡ መድኃኒታችን ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ መጥቶ፡ መከራ፡ተቀበለ።በመከራውም፡አዳነን።
በእንተ ፡ ጽንዐ ፡ ዛቲ ፡ በል ፤ ሁሉንም ፡ እንደ፡ በፊቱ፡አድርስ።

ስብሐት፡ለከ፡ተዘከርከ፡በሌሊት፡በል፤ግናይ፡ለከሙ፡ሥሉስ፡ቅዱስ፡አዕማደ፡ብሩህ፡እሳት፡በል። ስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነ፡ዘፈጠረ፡በል፤እስከ፡ተፍጻሜቱ።ጸሎተ፡ሃይማኖት፡ወአቡነ፡ዘበሰማያት፡በል።አ፡ማኅበ ራኒሁ።ነዋ፡በግዑ።ወዕቀቦሙ፡በል።

ይ ፡ ካ ፡ ሑሩ ፡ በሰላም ፡ ወእግዚአብሔር ፡ የሀሉ ፡ ምስሌክሙ ። ወእምዝ ፡ ንዑ ፡ ወተጋብዑ ፡ ውስተ ፡ ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በሰዓተ፡ጽባሕ፡ዘሰኑይ በሰላም።

ካህኑ ፡ በሰላም ፡ ሂዱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ፡ ጋራ ፡ ይሁን ። ሰኞ ፡ ጥዋት ፡ (በነግህ)፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ተሰብሰቡ፡ይበል።

## ምዕራፍ፡፲።
### ትዕዛዝ።

ወይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ ቅድስት ፡ በጊዜ ፡ ነግህ ፡ ዘሰኑይ ፡ ወይጸልዩ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ዘይብል ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ።እስከ፡ኅበ፡ይብል፡ተዐገሡ፡ወአጽንዑ፡ ልበክሙ፡ኵልክሙ፡እለ፡ተወከልክሙ፡በእግዚአ ብሔር ። ወውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ዘሰኑይ ፡ ያብጽሁ ። ወእምዝ ፡ ይበል ፡ መራሒ ፡ በ፫ ፡ ስምዕዎኬ ፡ ዘማርቆስ ። ወይበሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኅቡረ ፡ በሰጊድ ፡ ወበትጋህ፡ዐሠርተ፡ወክልኤተ፡ጊዜ፡ለከ፡ኃይል።.

### ክፍል፡፩።
ምንባብ፡ዘዕለተ፡ሰኑይ፡በጊዜ፡ነግህ።
ኦሪት፡ዘልደት።
ምዕ፤፩፤፩-፲፯።

፩፤ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ።

## ምዕራፍ፡፲።
### ትዕዛዝ።

ሰኞ ፡ በነግህ ፡ ካህናት ፡ በከበረች ፡ በቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ተሰብስበው ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ ይጸልዩ ፤ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢሖረ ፡ ከሚለው ፡ እስከ ፡ ተዐገሡ ፡ ወአጽንዑ ፡ ልበክሙ ፡ እስከ ሚለው ፡ (እስከ ፡ ብፁዓን) ፡ ድረስ ፡ ውዳሴ ፡ ማርያም፡ የሰኞን፡ይበሉ፤መሪ፡በሦስት፡ሃሌታ፡ ስምዕዎኬ ፡ ማርቆስ ፡ ይበል ። ሁሉም ፡ በአን ድነት ፡ በመትጋት ፡ እየሰገዱ ፡ በግራ ፡ በቀኝ ፡ አሥራ፡ሁለት፡ጊዜ፡ለከ፡ኃይል፡ይበሉ።

### ክፍል፡፩።
የሰኞ፡ነግህ፡ንባብ
ኦሪት፡ዘፍጥረት።
ምዕ፤፩፤፩-፲፯።

፩፤ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይና፡ምድርን፡ፈጠረ።

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት/ነግህ። |
|---|---|
| ፪፤ ወምድርሰ፡ዕራቃ፡ትነብር፡ወኢታስተርኢ። ወኢኮነት፡ድሉተ፡ወጽልመት፡መልዕልተ፡ቀላይ፡ወመንፈሰ፡እግዚአብሔር፡ይጼልል፡መልዕልተ፡ማይ። | ፪፤ ምድር፡ግን፡ባዶዋን፡ነበረች፤አትታይም፡ነበር፤አልተዘጋጀችም፡ነበር፤ጨለማውም፡በውኃው፡ላይ፡ነበር፤የእግዚአብሔር፡መንፈስም፡በውኃው፡ላይ፡ይሰፍፍ፡ነበር። |
| ፫፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡ለይኩን፡ብርሃን፡ወኮነ፡ብርሃን። | ፫፤ እግዚአብሔርም፡ብርሃን፡ይሁን፡አለ፡ብርሃንም፡ሆነ። |
| ፬፤ ወርእዮ፡እግዚአብሔር፡ለብርሃን፡ከመ፡ሠናይ፡ውእቱ፡ወፈለጠ፡እግዚአብሔር፡ማዕከለ፡ብርሃን፡ወማዕከለ፡ጽልመት። | ፬፤ እግዚአብሔርም፡ብርሃንን፡መልካም፡እንደሆነ፡አየ።እግዚአብሔርም፡በጨለማና፡በብርሃን፡መካከል፡ድንበር፡ለየ። |
| ፭፤ ወሰመዮ፡እግዚአብሔር፡ለብርሃን፡መዐልተ፡ ወለጽልመት፡ሌሊተ፡ወኮነ፡ሌሊተ፡ወጸብሐ።<br>ወኮነ፡፩፡ዕለተ። | ፭፤ እግዚአብሔርም፡ብርሃኑን፡ቀን፡ጨለማውንም፡ሌሊት፡ብሎ፡ጠራው፤ማታም፡ሆነ፤ነጋም።<br>አንደኛ፡ቀን፡ሆነ። |
| ፮፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡ለይኩን፡ጠፈር፡ማዕከለ፡ማይ፡ከመ፡ይፍልጥ፡ማዕከለ፡ማይ፡ወማይ፡ወኮነ፡ከማሁ። | ፮፤ እግዚአብሔርም፡በውኃ፡መካከል፡ጠፈር፡ይሁን፡አለ፤በውኃና፡በውኃ፡(በውቅያኖስና፡በኃኖስ)፡መካከል፡ይለይ፡አለ።እንዲህም፡ሆነ። |
| ፯፤ ወገብረ፡እግዚአብሔር፡ጠፈረ፡ወፈለጠ፡እግዚአብሔር፡ማዕከለ፡ማይ፡ዘመልዕልተ፡ጠፈር፡ወማዕከለ፡ማይ፡ዘመትሕተ፡ጠፈር። | ፯፤ እግዚአብሔርም፡ጠፈርን፡አደረገ፡ከጠፈር፡በታች፡ባለው፡በውኃ፡(በውቅያኖስ)፡መካከልና፡ ከጠፈር፡በላይ፡ባለ፡ውኃ፡(በኃኖስ)፡መካከል፡ድንበር፡ለየ። |
| ፰፤ ወሰመዮ፡እግዚአብሔር፡ለውእቱ፡ጠፈር፡ሰማየ።ወርእየ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ሠናይ፡ወኮነ፡ሌሊተ፡ወጸብሐ።<br>ወኮነ፡፪ተ፡ዕለተ። | ፰፤ እግዚአብሔር፡ይህን፡ጠፈር፡ሰማይ፡ብሎ፡ጠራው፤እግዚአብሔር፡ያ፡መልካም፡እንደሆነ፡አየ።ማታም፡ሆነ፤ጠዋትም፡ሆነ።<br>ሁለተኛ፡ቀን፡ሆነ። |
| ፱፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡ለይትጋባእ፡ማይ፡ዘመትሕተ፡ሰማይ፡ውስተ፡፩፡መካን፡ወያስተርኢ፡የብስ፡ወኮነ፡ከማሁ፡ወተጋብአ፡ማይ፡ ውስተ፡ምዕላዲሁ፡ወአስተርአየ፡የብስ። | ፱፤ እግዚአብሔር፡ከጠፈር፡በታች፡ያለው፡ውኃ፡ባንድ፡ቦታ፡ይወሰን፡አለ፡ደረቁም፡ይገለጥ፡አለ፤እንዲህም፡ሆነ፤ውኃውም፡በቦታው፡ተወሰነ፤የብሱም፡ተገለጠ። |
| ፲፤ መሰመዮ፡እግዚአብሔር፡ለየብስ፡ምድረ፡ወለምዕላዲሁ፡ለማይ፡ሰመዮ፡ባሕረ፡ወርእየ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ሠናይ። | ፲፤ እግዚአብሔር፡የብሱን፡ምድር፡ብሎ፡ጠራው።የውኃውንም፡መከማቻ፡ባሕር፡ብሎ፡ጠራው፤እግዚአብሔርም፡ያ፡መልካም፡እንደሆነ፡አየ። |
| ፲፩፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡ለታብቊል፡ምድር፡ሐመልማለ፡ሣዕር፡ዘይዘርዕ፡በበዘርዑ፡ወበበ ዘመዱ፡ወበበአርአያሁ፤ወዕፀ፡ዘይፈሪ፡ | ፲፩፤ እግዚአብሔርም፡ምድር፡በየዘርዑ፡በየወገኑ፡በየመልኩ፤የሚዘራውን፡የሣር፡ቡቃያ፡የሚአፈራውን፡ዛፍ፡ፍሬ፡የሚሰጠውን፤ዘሩ፤ |

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ወይገብር ፡ ፍሬሁ ፡ ዘእምውስቴቱ ፡ ዘርዐ ፡ ዘይወፅእ ፡ ወዘይከውን ፡ በበዘመዱ ፡ ዲበ ፡ ምድር፤ወኮነ፡ከማሁ።
፲፪፤ ወአውፅአት ፡ ምድር ፡ ሐመልማለ ፡ ሣዕር ፡ ዘይዘራዕ ፡ በበዘርዑ ፡ ወበበዘመዱ ፡ ወበበአርአያሁ፡ወዕፀ፡ዘይፈሪ፡ወዘይገብር፡ፍሬሁ፡ዘእምውስቴቱ ፡ ዘርዑ ፡ ዘይወፅእ ፡ በበዘመዱ መልዕልተ፡ምድር።ወርእየ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ሠናይ።
፲፫፤ ወኮነ፡ሌሊተ፡ወጸብሐ፤ወኮነ፡፫ተ፡ዕለተ።

፲፬፤ ወይቤ ፡እግዚአብሔር፡ ለይኩኑ ፡ ብርሃናት ፡ ውስተ፡ጠፈረ፡ሰማይ፡ከመ፡ያብርሁ፡ዲበ፡ምድር ፡ ወይፍልጡ ፡ ማዕከለ ፡ መዐልት ፡ ወማዕከለ፡ሌሊት፡ወይኩኑ።

ለትእምርታት፤
ወለአዝማናት፤
ለመዋዕላት፤
ወለዓመታት።
፲፭፤ ወይኩኑ፡ለአብርሆ፡በጠፈረ፡ሰማይ፡ከመ፡ያብርሁ፡ዲበ፡ምድር፡ወኮነ፡ከማሁ።

፲፮፤ ወገብረ፡እግዚአብሔር፡ ክልዔተ፡ብርሃናተ፡ዐበይተ ፡ ዘየዐቢ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ይምልክ ፡ መዐልተ ፡ ወዘይንዕስ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ይምልክ፡ሌሊተ፡ምስለ፡ከዋክብት።

፲፯፤ ወሤሞሙ፡እግዚአብሔር፡ በጠፈረ፡ሰማይ፡ከመ፡ያብርሁ፡ዲበ፡ምድር።

፲፰፤ ወይኰንንዎሙ ፡ ለመዐልት ፡ ወለሌሊት ፡ ወይፍልጡ፡ማዕከለ፡መዓልት፡ወማዕከለ፡ሌሊት ፡ ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ሠናይ።
፲፱፤ ወኮነ ፡ ሌሊተ ፡ ወጸብሐ ፡ ወኮነ ፡ አርባዕተ ፡ ዕለተ።
፳፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡'ለታውፅእ፡ማይ፡ዘይትሐወስ፡ዘቦ፡መንፈሰ፡ሕይወት፡ወአዕዋፈ፡ዘይሰርሩ፡መልዕልተ፡ምድር፡ወመትሕተ፡ሰማይ፤ወኮነ፡ከማሁ።
፳፩፤ ወገብረ፡እግዚአብሔር፡ አናብርተ፡ዐበይተ።

ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

ከውስጡ፡የሚገኘውን፡በየወገኑ፡በምድር፡ላይ፡የሚተከለውን፡የሚበቅለውን፡ተክል፡ታውጣ፡አለ፤እንዳለውም፡ሆነ።
፲፪፤ ምድርም፡በየዘሩ፡በየወገኑ፡በየመልኩ፡የሚዘራውን፡የሣር፡ቡቃያ፡አወጣች፤የሚአፈራውን ፡ ዛፍ ፤ ፍሬ ፡ የሚሰጠውን ፤ ዘሩ፡ከውስጡ፡የሚገኘውን፡በየወገኑ፡በምድር፡ላይ፡የሚበቅለውን፡ተክል፡አስገኘች።እግዚአብሔርም፡ያ፡መልካም፡እንደሆነ፡አየ።
፲፫፤ ማታም፡ሆነ፤ጠዋትም፡ሆነ፤ሦስተኛ፡ቀን፡ሆነ።
፲፬፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ በመዐልትና፡በሌሊትም፡መካከል፡ድንበር፡ይለዩ፡ዘንድ፡እግዚአብሔር ፡ (ማክሰኞ ፡ ማታ ፡ ለረቡዕ፡አጥቢያ)፡ሰማይ፡በሚባል፡ጠፈር፡ብርሃናት፡ይፈጠሩ፡አለ።
ለምልክቶች፤
ለዘመናት፤
ለወራት፤
ለዓመታት፡ይሁኑ።
፲፭፤ በምድር፡ላይ፡ያበሩ፡ዘንድ፡ሰማይ፡በሚባል፡ጠፈር፡ለማብራት፡ይሁኑ፡አለ፤እንዲህም፡ሆነ።
፲፮፤ ትልቁ ፡ ብርሃን ፡ ቀንን ፡ ይመግብ ፡ ዘንድ፡ትንሹ፡ብርሃን፡ከከዋክብት፡ጋራ፡ሌሊትን፡ይመግብ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደጋግ፡የሆኑ፡ ሁለቱን ፡ ብርሃናት ፡ (ፀሐይና ፡ ጨረቃን)፡ፈጠረ።
፲፯፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ፡ ሰማይ ፡ በሚባል ፡ ጠፈር ፡ ላይ ፡ አኖራቸው።
፲፰፤ መዐልትና ፡ ሌሊትንም ፡ ይመግቡአቸው ፡ ዘንድ፡በመዐልትና፡በሌሊትም፡መካከል፡ድንበር፡ይለዩ፡ዘንድ፤እግዚአብሔርም፡ያ፡መልካም፡እንደሆነ፡አየ።
፲፱፤ ማታም፡ሆነ፤ጧትም፡ሆነ፤አራተኛ፡ቀንም፡ሆነ።
፳፤ እግዚአብሔርም ፡ ውኃይቱ ፡ የሚንቀሳቀሰውን ፡ የሕይወት ፡ እስትንፋስ ፡ ያለውን ፡ ከምድር፡በላይ፡ከሰማይ፡በታች፡የሚበሩ፡ወፎችን፡ታውጣ፡አለ።እንዲህም፡ሆነ።
፳፩፤ እግዚአብሔርም ፡ ታላላቅ ፡ አንበሬዎችን።

Scanned by CamScanner

### በ፭፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ወኵሎ ፡ ነፍሰ ፡ ሕይወት ፡ ዘይትሐወስ ፡ ዘአውፅአ፡ማይ፡በበዘመዱ፡ወኵሎ፡አዕዋፈ፡ ዘይሰርሩ ፡ በበዘመዶሙ ፤ ወርእየ ፡ እግዚአብሔር፡ከመ፡ሠናይ።

፳፪፤ ወባረኮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ፡ወምልዕዋ፡ለቀላይ፡ወአዕዋፍኒ፡ ይብዝኁ፡ውስተ፡ምድር።

፳፫፤ ወኮነ፡ሌሊተ፡ወጸብሐ፡ወኮነ፡፭ተ፡ዕለተ።

፳፬፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለታውፅእ ፡ ምድር ፡ ዘመደ ፡ እንስሳ ፡ ወዘይትሐወስ ፡ ወአራዊተ ፡ ምድር፡በበዘመዱ፡ወኮነ፡ከማሁ።

፳፭፤ ወገብረ፡እግዚአብሔር፡እንስሳ፡በበዘመዱ፡ ወኵሎ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ በበዘመዱ ፡ ወአራዊተ ፡ ምድር ፡ በበዘመዶሙ፡ ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ሠናይ።

፳፮፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአርአያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ከመ ፡ ይኰንን ፡ ዓሣተ ፡ ባሕር፡ወአራዊተ፡ምድር፡ወአዕዋፈ፡ሰማይ፡ ወእንስሳኒ ፡ ወኵሎ ፡ ምድረ ፡ ወኵሎ ፡ ዘይትሐወስ፡ዲበ፡ምድር።

፳፯፤ ወገብሮ፡እግዚአብሔር፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡ በአምሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተባዕተ ፡ ወአንስተ፡ገብሮሙ።

፳፰፤ ወባረኮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎሙ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልዕዋ ፡ ለምድር ፡ ወቅንይዋ ፡ ወኰንንዎሙ ፡ ለዓሣተ ፡ ባሕር ፡ ወለአራዊተ ፡ ምድር ፡ ወለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወለኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ወለኵሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ዲበ፡ምድር።

፳፱፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ ወሀብኩክሙ ፡ ኵሎ ፡ ሐመልማለ ፡ ሣዕር ፡ ዘይዘራዕ ፡ ወይበቍል ፡ በበዘርዑ ፡ ወትዘርዕዎ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ፡ምድር፡ወኵሎ፡ዕፀ፡ዘሀሎ፡ውስቴቱ፡ ዘርዑ ፡ ዘይዘራዕ ፡ በበፍሬሁ ፡ ለክሙ ፡ ይኩንክሙ፡መብልዐ።

፴፤ ወለኵሉ፡አራዊተ፡ምድር፡ወለኵሉ፡አዕዋፈ፡

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፭፡ሰዓት።

ውሃ ፡ ያወጣውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሕያው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በየወገኑ ፡ የሚበሩ ፡ ወፎችንም፡ሁሉ፡በየወገናቸው፡ፈጠረ።እግዚአብሔርም፡ያ፡መልካም፡እንደሆነ፡አየ።

፳፪፤ እግዚአብሔርም ፡ ብዙ ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ሁኑ ፤ ባሕርንም ፡ ምሉዋት ፤ አዕዋፍንም ፡ በምድር ፡ ላይ፡ይብዙ፡ብሎ፡ባረካቸው።

፳፫፤ ማታም ፡ ሆነ ፤ ጠዋትም ፡ ሆነ ፤ አምስተኛ ፡ ቀንም፡ሆነ።

፳፬፤ እግዚአብሔር ፡ ሐሙስ ፡ ማታ፡ ለዓርብ፡ አጥቢያ፡ ምድር ፡ የእንስሳን ፡ ወገን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚኖረውን ፡ የምድር ፡ አውሬዎችንም ፡ በየወገኑ፡ታስገኝ፡አለ።እንዲህም፡ሆነ።

፳፭፤ እግዚአብሔርም ፡ እንስሳን ፡ በየወገኑ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚኖረውንም ፡ በየወገኑ ፡ የምድር ፡ አውሬዎችንም ፡ በየወገናቸው ፡ ፈጠረ ። እግዚአብሔርም ፡ ያ ፡ መልካም ፡ እንደሆነ፡አየ።

፳፮፤ እግዚአብሔርም ፡ የባሕር ፡ ዓሣዎችን ፡ የምድር ፡ አውሬዎችንም ፡ የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ እንስሳንም ፡ ምድርንም ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሰውንም ፡ ሁሉ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ በመልካችን ፡ በምሳሌያችን ፡ ሰውን፡(አዳምን)፡እንፍጠር፡አለ።

፳፯፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰውን ፡ በእግዚአብሔርነቱ ፡ አምሳል ፡ ፈጠረው ፤ ሴትና ፡ ወንድም ፡ አድርጎ፡ፈጠራቸው።

፳፰፤ እግዚአብሔርም፡ብዙ፡የብዙ፡ብዙም፡ሁኑ፤ ምድርንም ፡ ምሏት ፤ ግዟትም ፤ የባሕር ፡ ዓሣዎችን፡የምድር፡አውሬዎችን፡የሰማይ፡ ወፎችን ፡ እንስሳንም ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሰውንም ፡ ሁሉ ፡ ግዙአቸው ፡ ብሎ፡እግዚአብሔር፡ባረካቸው።

፳፱፤ እግዚአብሔርም፡የሚዘራውን፡በየዘሩ፡የሚበቅለውን ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የምትዘሩትን፡የእህል፡ፍሬ፡ዘሩ፡በውስጡ፡ያለውን፡ ዛፍ ፡ በየፍሬው ፡ የሚዘራውን ፡ ተክልም ፡ ሁሉ፡ ለእናንተ ፡ ምግብ ፡ ይሆናችሁ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ፡ሰጠኋችሁ፡አለ።

፴፤ ለምድር ፡ አውሬዎችም ፡ ሁሉ ፡ ለሰማይ ።

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሰኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ሰማይ፡ወለኵሉ፡ዘይትሐወስ፡ዲበ፡ምድር፡ ዘቦ፡መንፈሰ፡ሕይወት፡ወኵሉ፡ሐመልማለ፡ ሣዕር ፡ ይኩንክሙ ፡ መብልዐ ፡ ወኮነ ፡ ከማሁ። | ወፎችም ፡ ሁሉ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ደመ ፡ ነፍስ ፡ ያለውም ፡ ሁሉ፡ የበቀለው ፡ የእህል ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ምግብ ፡ ይሁናችሁ፡አለ።እንዲሁም፡ሆነ። |
| ፴፩፤ ወርእየ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ከመ፡ጥቀ፡ሠናይ፡ወኮነ፡ሌሊተ፡ወጸብሐ፡ ወኮነ፡፯ተ፡ዕለተ። | ፴፩፤ **እግዚአብሔር**፡የፈጠረውን፡ፍጥረት፡ሁሉ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ እንደሆነ ፡ አየ። ማታም ፡ ሆነ ፤ ጠዋትም ፡ ሆነ ፤ ስድስተኛ ፡ ቀንም፡ሆነ። |
| ምዕ፤፪፡፩-፬። | ምዕ፤፪፡፩-፬። |
| ፩፤ ወተፈጸመ፡ሰማይ፡ወምድር፡ወኵሉ፡ዘውስ ቴቶሙ። | ፩፤ የሰማይና፡የምድር፡ተፈጥሮ፡ተፈጸመ።በው ስጣቸው፡ያለውም፡ሁሉ። |
| ፪፤ ወፈጸመ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ገቢረ ፡ ግብሮ ፡ በስሱ፡ ዕለት ፡ ወአዕረፈ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በሳብዕት፡ዕለት፡እምኵሉ፡ግብሩ። | ፪፤ **እግዚአብሔር**፡በስድስተኛው፡ቀን፡ሥራውን፡ ሠርቶ ፡ ጨረሰ ፤ **እግዚአብሔርም** ፡ በሰባተ ኛይቱ፡ቀን፡ቅዳሜ፡ከሥራው፡ሁሉ፡አረፈ። |
| ፫፤ ወባረካ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ለዕለት ፡ ሳብዕት ፡ ወቀደሳ። | ፫፤ **እግዚአብሔር**፡ሰባተኛይቱን፡ቀን፡ቅዳሜን፡ ከስድስቱ፡ዕለታት፡ለይቶ፡አከበራት። |
| ፬፤ እስመ ፡ ባቲ ፡ አዕረፈ ፡ እምኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ዘአኃዘ፡ይግበር። | ፬፤ ይሠራ፡ዘንድ፡ከጀመረው፡ሥራ፡ሁሉ፡አርፎ ባታልና። |
| **ዘሰኑይ፡በእሐዱ፡ሰዓተ፡መዓልት።** | **ሰኞ፡ከቀኑ፡በአንድ፡ሰዓት፡የሚነበብ።** |
| ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | የነቢዩ ፡ የኢሳይያስ ፡ በረከት ፡ ለዘለዓለሙ፡ ከሁላችን፡ጋር፡ትሁን፤አሜን። |
| ምዕ፤፭፡፩-፬። | ምዕ፤፭፡፩-፬። |
| ፩፤ አሐሊኬ፡ማሕሌተ፡ለፍቁርየ፡እንዘ፡እብል፡ ዐጸደ ፡ ወይን ፡ ኮነ ፡ ለፍቁርየ ፡ በብሔር ፡ ጥሉል። | ፩፤ ለወዳጄ ፡ (ለእሥራኤል) ፡ በለመለመ ፡ ቦታ፡ (በኢየሩሳሌም) ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ነበረው ። እያልኩ፡ለወዳጄ፡የምስጋና፡መዝሙር፡እዘ ምርለታለሁ፡(አወርድለታለሁ)። |
| ፪፤ ወውስተ ፡ ማዕዘንቱ ፡ ጸቈንኩ ፡ ሎቱ ፡ ጸቈነ ፡ ወአግዘዝኩ ፡ ወተከልኩ ፡ ውስቴቱ ፡ ወይነ ፡ ኀሩየ ፡ ዘሴሬቅ ፡ ወሐነጽኩ ፡ ማኅፈደ ፡ ማእከሎ፡ ወአክረይኩ ፡ ሎቱ ፡ ምክያደ ፡ ወእምገዘ ፡ ጸናሕክዎ ፡ ለወይንየ ፡ ይፍረይ ፡ አስካለ፡ወፈረየ፡አስዋከ። | ፪፤ በዙሪያው ፡ አጽንቼ ፡ ቅጽርን ፡ ቀጸርኩለት ፤ በውስጡም ፡ የተመረጠ ፡ የሴሬቅ ፡ ወይንን ፡ ተከልኹ ፤ በመካከሉ ፡ ግምብ ፡ ሠራሁለት ፤ አውድማንም፡አስቆፈርሁለት፤ከዚህ፡በኋላ፡ ወይኔን ፡ ፍሬን ፡ ያፈራ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቅሁት ፤ ነገር፡ግን፡እሾኽን፡አፈራ። |
| ፫፤ ወይእዜኒ፡ኦ፡ሰብአ፡ይሁዳ፡ወእለኒ፡ትነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፡ፍትሑ፡ማዕከሌየ፡ወማዕከለ፡ ዐጸደ፡ወይንየ። | ፫፤ አሁንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩና ፡ የይሁዳ፡ ሰዎች ፡ በወይኔ ፡ ቦታ ፡ መካከልና ፡ በእኔ፡መካከል፡ፍረዱ። |
| ፬፤ ምንተ፡እንከ፡ዓዲ፡እግበር፡ለወይንየ፡ዘኢገ በርኩ ፡ ሎቱ ፡ ናሁ ፡ ጸናሕክዎ ፡ ይፍረይ ፡ | ፬፤ እንግዲህ፡ወዲህ፡ዳግመኛ፡ለወይኔ፡ያላደረግ ሁለትን ፡ ምን ፡ ላድርግለት? እነሆ ፡ ፍሬን ፡ |

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

አስካለ፡ወፈረየ፡አሥዋከ።

፭ ወይእዜኒ፡እነግረክሙ፡ዘእሬስዮ፡ለወይንየ፡ እነሥት፡ጸቈኖ፡ወይትሐበለይዎ፡ነኪራን፡ ወአአትት፡ጥቅሞ፡ወይከውን፡ምክያደ።

፮ ወአኀድጎ ፡ ወኢይገምዶ ፡ ወኢይከርዮ ፡ ወይበቊል ፡ ሣዕር ፡ ወሦክ ፡ ውስቴቱ ። ወይማስን፡እንከ፡ወእኤዝዝ፡እንከ፡ደመና፡ ከመ፡ኢያዝንም፡ዝናመ፡ላዕሌሁ።

፯ ዓፀደ ፡ ወይኑሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸባኦት ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ውእቱ ፡ ወሰብአ ፡ ይሁዳ ። ውእቱ፡ተክል፡ሐዲስ፡ዘአፍቀሮሙ፡ወጸናሕ ክዎሙ ፡ ይግበሩ ፡ ጽድቀ ፡ ወገብሩ ፡ ዐመፃ ፡ ወአኮ፡ርትዐ፡ዘእንበለ፡ገዐር።

፰ አሌ፡ሎሙ፡ለእለ፡ያስተእኅዙ፡ቤተ፡ምስለ፡ ቤት፡ወለእለ፡ያስተቃርቡ፡ገራህተ፡ምስለ፡ ገራህት፡ከመ፡ይቅስጡ፡ዘኮነ፡እምገራህተ፡ ቢጸሙ፡ወይፈቅዱ፡ያግምርዋ፡ለምድር፡ለባ ሕቲቶሙ።

፱ እስመ፡ተሰምዐ፡ዝንቱ፡ነገር፡ውስተ፡እዝነ፡ እግዚአብሔር፡ጸባኦት።

### ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ኢሳያስ፡ነቢይ።

ይቤ ፡ መተርጕም ፡ አሐሊ ፡ ማሕሌተ ፡ ለፍቁርየ።

፩ ዘንተ፡ዘይቤ፡በእንተ፡አብ፡እመ፡ሰብሐ፡ ለወልዱ፡በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡አ፡አባ፡ ሰብሖ፡ለወልድከ።

፪ ይቤ፡ሰባሕኩከሂ፡ወዓዲ፡እሴብሐከ።

፫ ወብሂሎቱሰ ፡ ፍቁርየ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ በወንጌል፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ወልድየ ፡ ዘቦቱ ፡ ሠመርኩ።

፬ ወብሂሎቱ ፡ ስብሐተ ፡ ለዐፀደ ፡ ወይንየ ፡ ይብል፡ እሎንተ ፡ ስብሐታተ ፡ ክልኤተ ፡ መትልዋነ።

፭ ዘይቤ ፡ ሰባሕኩከሂ ፡ ወዓዲ ፡ እሴብ ሐከ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

ያፈራ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቅሁት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እሾኽን፡አፈራ።

፭ አሁንም ፡ ወይኔን ፡ የማደርገውን ፡ እነግራች ኋለሁ፤ቅጽሩን፡አፈርሳለሁ፤አሕዛብ፡ይበዘ ብዙታል ፤ ቅጽሩንም ፡ አፈርሳለሁ ፤ መመላ ለሻም፡ይሆናል።

፮ እተወዋለሁ ፤ ያወራውን ፡ አልቈርጥለትም ፤ ቅጥሩንም፡ቆፍሬ፡አላወጣለትም፤በውስጡም፡ ሣር፡እሾኽ፡ይበቅልበታል፤ከእንግዲህ፡ወዲህ፡ ይጠፋል ፤ በሱ ፡ ላይ ፡ ዝናምን ፡ እንዳያዘንም ፡ እንግዲህ፡ወዲህ፡ደመናን፡አገዛለሁ።

፯ ይኸውም፡የወይን፡ቦታ፡ያልኹት፡የአሸናፊ፡ እግዚአብሔር፡የሕጉ፡ማደሪያ፡የእስራኤል፡ ወገን ፡ ነው ፤ የወደዳቸው ፡ አዲስ ፡ ተክልም ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ ጽድቅን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቅኋቸው ፤ ድኃ ፡ ከማስጮኽ ፡ በቀር፡የቀና፡ነገር፡ያይደለ፡ዓመፅን፡ሠሩ።

፰ ቤትን፡ከቤት፡ጋራ፡አያይዘው፡ለሚሠሩ፡የባ ልንጀራቸው ፡ እርሻ ፡ የሆነውን ፡ ይሰርቁ ፡ ዘንድ፡እርሻን፡ከእርሻ፡ጋራ፡ለሚአቀራርቡ፡ ምድርንም ፡ ብቻቸውን ፡ ይይዟት ፡ ዘንድ ፡ ለሚወዱ፡ሰዎች፡ወዮላቸው።

፱ ይኽ ፡ ነገር ፡ አሸናፊ ፡ በሚሆን ፡ በእግዚአ ብሔር፡ጆሮ፡ደርሶአልና።

### የነቢዩ፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡ትርጓሜ።

ለወዳጄ፡የምሥጋና፡መዝሙር፡እዘምራለሁ፡ አለ።

፩ በወንጌል፡አባት፡ሆይ፡ልጅህን፡ግለጠው፡ እንዳለ ፡ አብም ፡ ልጁን ፡ በምሥጋና ፡ በገለጠው፡ጊዜ፡ይኸን፡የተናገረው፡ስለአብ፡ ነው።

፪ ገልጬሃለሁ፤እንደገናም፡እገልጥሃለሁ፡አለ።

፫ ወዳጄ ፡ ማለቱም ፡ በወንጌል ፡ በእርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ፡የምወደው፡ለመሥዋዕትነት፡የመረ ጥኩት፡ልጄ፡ይኸ፡ነው፡እንዳለ።

፬ ለወይን፡ዐፀድ፡ምሥጋና፡ማለቱም፡እነዚህ፡ ተከታታዮች ፡ ሁለቱን ፡ ምስጋናዎች ፡ ተናገረ።

፭ ገልጬሃለሁ ፡ እንደገናም ፡ እገልጥሃለሁ ፡ ያለው፡ነው።

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፩፡ ወሰመዮ ፡ ነቢይ ፡ ለወልድ ፡ ዐፀደ ፡ ወይን ፡
በዝየ፡በከመ፡ሰመየ፡እግዚእ፡ርእሶ፡በውስተ፡
ወንጌል ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ። በከመ ፡ ባህሉ ፡ አነ ፡
ውእቱ፡ዐጸደ፡ወይን፡ዘጽድቅ።
፪፡ ወብሂሎቱ፡ካዕበ፡አነ፡ውእቱ፡ዐጸደ፡ወይን፡
ዘጽድቅ፡ወአንትሙ፡አዕጹቂሁ።

፫፡ ወዛቲ ፡ ትንቢት ፡ ቀደመት ፡ በአፈ ፡ ነቢይ ፡
በእንተ፡ዘይቤ፡እግዚእ፡በእንተ፡ርእሱ።
፬፡ ወባህሉሂ ፡ ኮነ ፡ ለፍቁርየ ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ፡
ውስተ፡ማዕዘንቱ።
፲፡ ይብል ፡ ዐጸደ ፡ ወይን ፡ እሥራኤልሃ ፡ ወማእዘ
ንትሂ ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡
ኢነበሩ፡ውስተ፡ኵላ፡ምድር።
፲፩፡ ዳእሙ ፡ ውስተ ፡ ሣቅዕ ፡ ዘውእቱ ፡ ማዕዘንት ፡
እምውስተ፡ምድር።
፲፪፡ ወሰመዮ ፡ ነቢይ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ እንተ ፡
አውረሶሙ፡እግዚአብሔር፡ኪያሃ።

፲፫፡ ወብሂሎቱ፡ለሙ፡ይእቲ፡ዛ፡ምድር፡እንተ፡
ታውኅዝ፡ሐሊበ፡ወመዐረ።
፲፬፡ ዘይቤ፡ወአፆድኩ፡ሎቱ፡ጸቈነ፡ይብል፡ጸቈነ፡
ወእደ፡ሕገ፡አሪት፡ዘሐጸሮሙ፡ቦቱ፡ወረሰየ፡
ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ አረፍት ፡ ዘላዕለ ፡ ሀገር ፡
ከመ፡እመ፡ቦ፡ዘወፅአ፡እምኔሁ፡ይሜሮ።

፲፭፡ ወውእቱኬ ፡ ከመ ፡ ሀገር ፡ ወላዕሌሃ ፡ ጥቅም ፡
ወዐውዳ ፡ ጸላዕት ። እመ ፡ ቦ ፡ እንከ ፡ ዘወፅአ ፡
እምሀገር ፡ ወተዐደወ ፡ ጥቅመ ፡ ይሜሮ ፡ እምጸ
ላዕቱ።
፲፮፡ ከማሁኬ፡ኵሉ፡ዘዐለዋ፡ለሕገ፡እግዚአብሔር፡
ወወፅአ ፡ እምውሳንያቲ ፡ እስመ ፡ ሰያጥንት ፡
ጸላዕቱ፡ይሜርውዎ፡በምግባሪሆሙ፡እኪት።
፲፯፡ ይቤ ፡ ወአንሣእክዎ ፡ ዲበ ፡ ኀለት ፡ ይብል ፡
ከመ፡ ውእቱ ፡ አልዓሎሙ ፡ ዲበ ፡ ጸላዕቶሙ ፡
ወአንገሦሙ፡ዲቤሆሙ።
፲፰፡ ወሰመዮሙ፡ኀለተ፡በእንተ፡ፅበሶሙ፡በኀበ፡
ሕዝበ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡አሕዛብ፡ኮኑ፡
ይጸብኡ ፡ ወአልቦሙ ፡ ረድኤተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ምስሌሆሙ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፩፡ ጌታ፡ በወንጌል ፡ ራሱን ፡ ዐፀደ ፡ ወይን ፡ ብሎ፡
እንደሰየመ ፡ ነቢዩም ፡ በዚህ ፡ ወልድን ፡
የወይን ፡ ዐፀድ ፡ አለው ። እኔ ፡ ዕውነተኛ ፡
የወይን፡ሐረግ፡ነኝ፡እንደማለቱ።
፪፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ዕውነተኛ ፡ የወይን ፡ (አረግ)፡
ግንድ፡ነኝ፡ቅርንጫፎቹም፡እናንተ፡ናችሁ፡
ማለቱ።
፫፡ ጌታችን፡ ስለ፡ራሱ፡የተናገረው፡አስቀድሞ፡
በነቢይ፡የተነገረች፡ትንቢት፡ናት።
፬፡ በቅጽሩም፡ውስጥ፡ለወዳጄ፡የወይን፡ተክል፡
ሆነለት፡ማለቱ።
፲፡ የእሥራኤል፡ልጆች፡በዓለሙ፡ሁሉ፡አልተበ
ተኑም ፡ ነበረና ፡ የወይን ፡ ዐጸድ ፡ እስራኤል፡
እንጂ፡ናቸው፡ይላል።
፲፩፡ በምድር ፡ መዓዝን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይኸውም፡
ከምድር፡ውስጥ፡ያለ፡መዓዝን፡ነው።
፲፪፡ እግዚአብሔር፡ ያወረሳቸው፡እርስዋን፡ኢየሩ
ሳሌምን ፡ ነቢይ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ብሎ፡
ሰየማት።
፲፫፡ ማርና ፡ ወተትን ፡ የምታፈስ ፡ ይቺ ፡ ምድር፡
የእነርሱ፡ናት፡ማለቱ፡ነው።
፲፬፡ ዙሪያውን፡ቅጽር፡ቀጸርሁት፡ያለው፡በኦሪት፡
ሕግ ፡ እንደሚጠብቃቸው ፡ በከተማ ፡ ላይ፡
እንዳለ ፡ ቅጽር ፡ ግምብ ፡ አድርጎ ፡ ስለሚጠብ
ቃቸው ፡ ከቅጽሩ ፡ (ከሕጉ) ፡ የሚወጣ ፡ ቢኖር፡
በጠላት፡እጅ፡እንደሚወድቅ፡ተናገረ።
፲፭፡ ይኸም ፡ በግምብ ፡ እንደ ፡ ታጠረች ፡ ከተማና፡
ምሽግ፡ በዙሪያዋ፡ ዋሻ፡ እንዳላት፡ ነው። እን
ዲህ ፡ ከከተማ ፡ ወጥቶ ፡ ግምቡን ፡ አልፎ ፡ የሄደ፡
ሰው፡ቢኖር፡በጠላት፡ተመትቶ፡ይጠፋል።
፲፮፡ እንደዚሁም፡የእግዚአብሔርን፡ ሕግ ፡ ያፈረሳ
ትንና ፡ ከሥርዓቷም ፡ የወጣውን ፡ ጠላቶቹ፡
ሰይጣናት፡በክፉ፡ሥራቸው፡ያጠፉታል።
፲፯፡ በቀርቃኅ፡ዘንግ፡ላይ፡አነሣሁት፡አለ፤በጠላቶ
ቻቸው፡ላይ፡ከፍ፡ከፍ፡እንዳደረጋቸውና፡በእነ
ርሱም፡ላይ፡እንዳነገሣቸው፡ያስረዳል።
፲፰፡ አሕዛብን ፡ ስለ ፡ ደካማነታቸው ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ወገኖች ፡ ዘንድ ፡ የቀርቃኅ ፡ በትር ፡
ብሎ ፡ ጠራቸው ፤ አሕዛብ ፡ ለጦርነት ፡
(ይሰለፋሉ)፡ይጸራራሉ፤ነገር፡ግን፡የእግዚአ
ብሔር፡ረድኤት፡ከእርሳቸው፡ጋራ፡የለም።

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፲፱፤ ወደቂቀ፡እስራኤልሰ፡እንዘ፡ኀዩላን፡ቀዲሙ፡ እምነበ፡እግዚአብሔር፡ወበእንተ፡ውእቱኬ፡ ሰመዮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጸላዕቶሙ ፡ በአፈ፡ነቢይ፡ኀሊተ፡እስመ፡ጽቡስ፡ውእቱ። | ፲፱፤ የእሥራኤል፡ልጆችስ፡አስቀድሞ፡ከእግዚአ ብሔር፡ዘንድ፡ኃይለኞች፡ሲሆኑ፡ስለዚህ፡ ጠላቶቻቸው፡አሕዛብን፡በነቢይ፡አድሮ፡እግ ዚአብሔር፡የሸንበቆ፡በትር፡አላቸው፤ደካማ፡ ልምሾ፡ነውና። |
| ፳፤ ይቤ፡ወሐነጽኩ፡ማኅፈደ፡ማእከሎ፡ይብል፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ማኅፈድ ፡ መንግሥተ ፡ ዘወሀቦሙ።እስከ፡መንግሥቶሙ፡ኮነ፡ላዕለ፡ ኵሎሙ፡ነገሥት። | ፳፤ በመካከሉ፡ግምብ፡ሠራሁ፡አለ፤ይህም፡ጽኑ፡ መንግሥትን፡ስለሰጣቸው፡ይናገራል።መን ግሥታቸው ፡ ከነገሥታቱ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ሁኗልና። |
| ፳፩፤ ወኢይክል፡መኑሂ፡እምነገሥታተ፡ምድር፡ ይትቃወሞሙ፡ዘእንበለ፡መባሕተ፡እግዚአ ብሔር፡ሎሙ፡ቦቱ። | ፳፩፤ በእርሱ፡በእግዚአብሔር፡ፈቃድ፡ካልሆነ፡ ከምድር፡ነገሥታት፡ማንም፡ሊቃወማቸው፡ ሊአጠቃቸው፡አይችልም። |
| ፳፪፤ ይቤ፡ወገበርኩ፡ውስቴቱ፡ምክያደ፡ይብል፡ በእንተ፡ምክያድ፡ወእደ፡ዝብሖት፡እንተ፡ኮኑ፡ ይገብርዋ፡ለአስተስርዮ፡በእንቲአሆሙ። | ፳፪፤ በውስጡም፡አውድማ፡ሠራሁ፡አለ፤ስለ፡ ኀጢአታቸው፡ማስተስረያ፡ስለሚአደርጉት፡ የእንስሳት፡መሠዊያ፡ስለሆነው፡ይናገራል። |
| ፳፫፤ እስመ፡ብእሲ፡ኮነ፡ለእመ፡ገብረ፡ኀጢአተ፡ ወኢየአምን ፡ ኪያሃ ፡ ለመኑሂ ፡ እምሰብእ ፡ ያበውእ፡እንከ፡ውእቱ፡ዘኮነ፡እምነ፡እንስሳ፡ ወይትአመን፡ኃጢአቶ። | ፳፫፤ ሰው ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ለማንም፡ባይነግር፡እንግዲህ፡ከእንስሳት፡ ወገን፡የሆነውን፡ያቀርባል፤ኀጢአቱንም፡ ይናዘዛል። |
| ፳፬፤ ወይዘብሖ፡ካህን፡ለውእቱ፡እንስሳ፡ፈዳየ፡ በእንተ፡ኃጢአቱ። | ፳፬፤ ካህኑም፡ስለ፡ኀጢአቱ፡ስርየት፡ፈንታ፡ ያንን፡እንስሳ፡ያርደዋል። |
| ፳፭፤ ወዘንተ፡ኢገብሮ፡እግዚአብሔር፡ስቡሕ፡ ዘእንበለ፡ምሕረት፡ሎሙ፡እምኔሁ። | ፳፭፤ የተመሰገነ፡እግዚአብሔር፡ይህን፡ለነሱ፡ ምሕረት፡ከእንስሳው፡በቀር፡ይህን፡አልሠ ራውም። |
| ፳፮፤ ይቤ፡ወጸናሕክዎ፡ከመ፡ይፍረይ፡ወይነ፡ ወአውፅአ ፡ ሦከ ፡ ብሂሎቱ ፡ ወጸናሕክዎ ፡ ይብል። | ፳፮፤ ወይንን፡ያፈራ፡ዘንድ፡ጠበቅሁት፤ግን፡ እሾኽ፡አወጣ፡ማለቱ፡ነው፡አለ፤ጠበቅ ሁትም፡ይላል። |
| ፳፯፤ ዘውእቱ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ያነውኅ፡ መንፈሶ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ወይጸ ንሖሙ። | ፳፯፤ ይኸ ፡ ስለእርሳቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልቡናውን፡አስፍቶ፡በትዕግሥት፡ይጠብቃ ቸዋልና። |
| ፳፰፤ ወይትዔገሥ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘገብረ፡ምስሌሆሙ፡ተአምራተ፡ወመድ ምማተ፡ለአልባብ። | ፳፰፤ ከእነርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሁኖ ፡ ለልቡና ፡ አስደናቂ፡ የሆኑ፡ተአምራትን፡በማድረጉ፡ ስለእነርሳቸው፡ይታገሣል። |
| ፳፱፤ ወአድኀኖሙ፡እግዚአብሔር፡እምፀሮሙ፡ ግብፃውያን፡ወአስጠሞሙ፡ውስተ፡ባሕር፡ ወሐሩ፡እሙንቱሰ፡ማዕከለ፡ማያት፡ዲበ፡ ምድር፡ይብስት። | ፳፱፤ እግዚአብሔርም፡ከጠላቶቻቸው፡ከግብጻ ውያን፡አዳናቸው፤ግብጻውያንን፡በባሕር፡ አሰጠማቸው፤እነርሱ፡ግን፡በውኃ፡ውስጥ፡ በደረቀች፡ምድር፡ተሻገሩ። |
| ፴፤ ወአብልዖሙ፡መና፡በገዳም፡አርብዓ፡ዓመተ፡ ዘአውረደ ፡ እምሰማይ ፡ ወይጼልሎሙ ፡ በደመና፡ወያበርህ፡ሎሙ፡በዐምደ፡እሳት። | ፴፤ በበረሀም ፡ ከሰማይ ፡ ያወረደውን ፡ መና ፡ አርባ፡ ዓመት፡መገባቸው፤በደመና፡ይጋርዳ ቸዋል፤በብርሃን፡ዐምድ፡ያበራላቸዋል። |
| ፴፩፤ ወምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ኮኑ ፡ ይትሄየዩ ፡ | ፴፩፤ ከዚህም፡ሁሉ፡ጋራ፡ችላ፡የሚሉ፡ሆኑ፤ |

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| እምኔሁ ፡ ወይትመየጡ ፡ በአልባቢሆሙ ፡ እምፈቃዱ። | ፈቃዱንም ፡ ከመፈጸም ፡ ከእርሱ ፡ ልቡና ቸውን፡መለሱ። |
| ፴፪፤ ይቤ ፡ ተሰፈውኩ ፡ ከመ ፡ ያውፅእ ፡ ወይነ ፡ ወኣውፅአ ፡ ሦከ ፡ ይብል ፡ እንበይነ ፡ ወይን ፡ ለኅበ፡ምግባራት፡ሠናይት፡ወሦከሰ፡ለኅበ፡ምግባራት፡መንሡት። | ፴፪፤ ወይንን፡ያፈራ፡ዘንድ፡ተስፋ፡አደረግሁ፤ግን፡ እሾኽን ፡ አወጣ ፤ ስለ ፡ ወይን ፡ ሲናገር ፡ ስለ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ይናገራል ፤ ስለ ፡ እሾኽም፡ ሲአወሳ፡ስለ፡ጥፋት፡ሥራ፡ይናገራል። |
| ፴፫፤ ይቤ፡አ፡ሰብአ፡ይሁዳ፡ወእለ፡ትነብሩ፡ኢየሩ ሳሌም ፡ ይእዜኒ ፡ ፍትሑ ፡ ማዕከሌየ ፡ ወማዕከለ፡ዐጸደ፡ወይንየ፡ይብል። | ፴፫፤ በኢየሩሳሌም፡የምትኖሩና፡የይሁዳ፡ሰዎች፡ በወይኔ ፡ ቦታ ፡ መካከልና ፡ በእኔ ፡ መካከል፡ አሁን፡ፍረዱ፡አለ። |
| ፴፬፤ እንበይነ ፡ ሰብአ ፡ ይሁዳ ፡ ነቢያተ ፡ እለ ፡ ፈነዎሙ፡እግዚአብሔር፡ሎሙ፡ከመ፡ያለብ ውዎሙ፡ተዐቅቦተ፡ከመ፡ይትመየጡ፡እምግ ዕዞሙ፡እኩይ፡ወኢተመይጡ። | ፴፬፤ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ከክፉ ፡ ጠባያቸው፡ ይመለሱ፡ዘንድ፡መጠበቅን፡ያሳውቃቸው፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የላከላቸው ፡ ነቢያትን፡ይናገራል፤እነርሱ፡ግን፡አልተመ ለሱም። |
| ፴፭፤ ወበእንተ፡ውእቱ፡ይከውኑ፡በዕለተ፡ደይን፡ ይትፋትሕዎሙ ፡ በስምዕ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በከመ፡ አይድዕዎሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ወአንቅሕዎሙ ፡ ወአግኅሥዎሙ ፡ ወኢተመይጡ፡እምግባራቲሆሙ። | ፴፭፤ ስለዚህም፡በፍርድ፡ቀን፡በእነርሳቸው፡ላይ፡ በመመስከር ፡ የሚፋረዱአቸው ፡ ይሆናሉ፡ ስለ፡እግዚአብሔር፡መንግሥት፡እንዳስተማ ሩአቸው ፡ ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አስወግዱ ዋቸው፤እርሳቸው፡ግን፡ከክፉ፡ሥራቸው፡ አልተመለሱም። |
| ፴፮፤ ይቤ፡ምንተ፡እገብር፡ኀለየ፡በዘይገብር፡ቦቱ፡ ዳግመ። | ፴፮፤ ምን ፡ እሠራለሁ ፡ አለ ፤ የሚአደርግበትን፡ ደግሞ፡አሰበ። |
| ፴፯፤ ወይቤ፡ነቢይ፡ዘንተ፡ቃለ፡በእንተ፡እግዚአ ብሔር ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘየሐትት ፡ ኀሊናሁ ፡ ወያስተነትን፡በእንተ፡ዘይገብር። | ፴፯፤ ስለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ በልቡናው፡ ያለውን ፡ ሐሳቡን ፡ እንደሚመረምር ፡ እንደ ሚያስተነትን ፡ ሰው ፡ ነቢይ ፡ ይህን ፡ ቃል፡ ተናገረ። |
| ፴፰፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ኮነ ፡ ይፈቅዶሙ ፡ ይግበሩ ፡ ፈቃዶ ፡ ወኢይፃኡ ፡ እምሃይማኖት፡ቦቱ። | ፴፰፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃዱን ፡ እንዲ ፈጽሙ ፡ በእርሱ ፡ ከማመን ፡ እንዳይወጡ፡ ይወድ፡ነበረና። |
| ፴፱፤ ወኢፈቀዱ፡ውእተ፡ወበእንተ፡ዝ፡ዘለፎሙ፡ ወንጌል ፡ በብሂሎቱ ፡ ሚ ፡ መጠነ ፡ ፈቀድኩ ፡ አስተጋብእክሙ፡ወኢፈቀድክሙ፡አንትሙ። | ፴፱፤ ይህን ፡ አልወደዱም፤ ልሰበስባችሁ ፡ ምን፡ ያህል፡ወደድሁ፤እናንተ፡ግን፡እምቢ፡አላችሁ፡ በማለቱ፡ስለዚህ፡ወንጌል፡ዘለፋቸው። |
| ፵፤ ወደገመ፡ቃለ፡ውስተ፡ዝ፡ከመ፡ዘይኔስሕ፡ በእንቲአሆሙ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ እምሰብአ ፡ ጽልመት፡አላ፡እምሰብአ፡ብርሃን። | ፵፤ በዚህም፡ውስጥ፡ስለ፡እነርሳቸው፡እንደሚ ጸጸት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ ተናገረ ፤ እነር ሳቸው፡ከብርሃን፡ሰዎች፡እንጂ፡ከጨለማ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ፡ የሚወድ፡አይደለምና። |
| ፵፩፤ ይቤ ፡ ተሰፈውኩ ፡ ከመ ፡ ያውፅእ ፡ ወይነ ፡ ወአውፅአ፡ሦከ፤ይብል፡ለለ፡ኵሉ፡አናኅከ፡ መንፈስየ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወተዓገሥክዎሙ ፡ ከመ ፡ ይነስሑ ፡ ወይትመየጡ ፡ እምእከይ ፡ ኀበ፡ኂሩት፡ወኢተመይጡ። | ፵፩፤ ወይንን፡ያፈራ፡ዘንድ፡ተስፋ፡አድርጌ፡ነበር፡ ነገር ፡ ግን ፡ እሾኽን ፡ አወጣ ፡ አለ ፤ ለየአን ዳንዱ፡ ልቡናየን ፡ አስፍቼ ፡ ወደ ፡ ንስሐ፡ ከክፋት፡ወደ፡በጎነት፡ይመለሱ፡ዘንድ፡ታገ ሥኳቸው፤ግን፡አልተመለሱም፡ይላል። |

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፺፪፤ ይቤ ፡ አንሰ ፡ እነግረክሙ ፡ ምንተ ፡ እገብር ፡ ዘንተ ዐጸደ ፡ ወይንየ ፡ ይብል ፡ ለእመሰ ፡ አዝለፉ፡ላዕለ፡ግዕዘሙ፡ሙሱን፡ወኢገብኡ፡ እምዘ፡እሙንቱ፡ላዕሌሁ።

፺፫፤ ይቤ፡አአትት፡ጸቄኖ፡ይብል፡ከመ፡ውእቱ፡ ያአትት ፡ እምኔሆሙ ፡ መንግሥተ ፡ ወይሁብሙ፡ለምእመናን።

፺፬፤ ይቤ ፡ ወእሬስዮሙ ፡ ለተበርብሮ ፡ ይብል ፡ ከመ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ምእመናን ፡ ቦቱ ፡ ይነሥኡ፡መንግሥተ፡ዘውስተ፡እደዊሆሙ፡ እምሕግ፡ዘተወፈይዎ፡እምእግዚአብሔር፡ ልዑል።

፺፭፤ ይቤ፡ወእነሥእ፡ጥቅሞ፡ይብል፡ከመ፡እግዚ አብሔር፡ልዑል፡ያበጥላ፡ለሕጎሙ፡በካልእ፡ ሕግ። ወያወፍያ፡ለካልአን፡አሕዛብ፡እለ፡ የአምኑ ፡ በስሙ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሕግ ፡ ፍጽምት።

፺፮፤ ይቤ ፡ ወይከውን ፡ ምክያደ ፡ ይብል ፡ ከመ ፡ ኵሉ፡ዘይትርፍ፡እምደቂቀ፡እስራኤል፡ወኢ የአምን፡በክርስቶስ፡ዘይሴፈውዎ፡ይከውን፡ እንከ፡ውእቱ፡ምኑነ፡ወጽሉአ፡እምኵሉ፡ አሕዛብ።

፺፯፤ ይቤ፡ወኢይከውን፡ለዐጸደ፡ወይንየ፡ሕንጻ።

፺፰፤ ይብል፡እስመ፡እምድኅረ፡ፍጹም፡ሕግ፡ ኢይከውና፡ለሕገ፡ብሊት፡ሐድሶ፡ካልእ፡ ሕግ።

፺፱፤ አኮ፡በከመ፡ተምዐ፡ላዕሌሆሙ፡ወዔወ ውዎሙ፡ከለዳውያን፡ካዕበ፡ገብአ፡ ወመሐሮሙ፡ወአግብአሙ፡ኀበ፡ርስቶሙ፡ ወተሐደሱ፡ምዕረ።

፻፤ ወባሕቱ፡እምድኅረ፡ምጽአተ፡ክርስቶስ፡ ዘውእቱ፡ተፋጻሜት፡ኢተርፈ፡ለሕገ፡ኦሪት፡ ካልእ፡ተሐድሶት።

፻፩፤ ይቤ፡ወይበቍል፡ሦክ፡ውስቴቱ፡ከመ፡ሣዕር።

፻፪፤ ዘውእቱ፡እመ፡ቦ፡ዘይትርፍ፡እምኔሆሙ፡ዘኢ የአምን፡በክርስቶስ፡እስመ፡ሰይጣን፡ይዘርዕ፡ ውስቴቱ ፡ ኀሊና ፡ እኪተ ፡ ወምንንተ ፡ ወመዋቲተ።

፻፫፤ ወባቲ፡ያስሕቶሙ፡አልባቢሆሙ፡ወኢየኀ ድጎሙ፡ይእመኑ፡ከመ፡ይድኃኑ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፺፪፤ ይህን፡የወይን፡ቦታ፡ምን፡እንደማደርገው፡ እነግራችኋለሁ፡አለ፤ከከፉ፡ጠባያቸው፡ካል ተመለሱ፡በዚያው፡ላይ፡ለዘወትር፡ከጸኑ፡ እነርሱ፡ካልተመለሱ፡ይላል።

፺፫፤ ቅጽሩን፡አፈርሳለሁ፡አለ፤ከእነርሳቸው፡ መንግሥትን ፡ አስወግዶ ፡ ለምእመናን ፡ አሕዛብ፡እሰጣለሁ፡ማለቱ፡ነው።

፺፬፤ ለመበዝበዝ ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ አለ ፤ ከአሕዛብ፡ወገን፡ያመኑበት፡መንግሥትን፡ (ልጅነትን)፡በኦሪት፡ሕግ፡ከልዑል፡እግዚአ ብሔር፡ዘንድ፡የተቀበሉትን፡እንደሚወስዱ ባቸው፡ይናገራል።

፺፭፤ ቅጽሩን፡አፈርሳለሁ፡አለ፤ልዑል፡እግዚአ ብሔር፡ሕጋቸው፡ኦሪትን፡በሌላ፡ሕግ፡ በወንጌል ፡ እንደሚአፈልሳትና ፡ በስሙ ፡ ለሚአምኑ ፡ ለሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ እንደሚ ሰጣት፡ይችም፡ፍጽምት፡ሕግ፡እንደሆነች፡ ይናገራል።

፺፮፤ አውድማ ፡ ይሆናል ፡ አለ ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች፡ ተስፋ፡በሚአደርጉት፡በክርስቶስ፡ ሳያምን ፡ የቀረውን ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከአሕዛብ፡ሁሉ፡የተጠላና፡የተናቀ፡እንደ ሚሆን፡ይናገራል።

፺፯፤ ለወይኔ፡ቦታ፡ግምብ፡አይሠራም፡አለ።

፺፰፤ ከፍጹም፡ሕገ፡ወንጌል፡በኋላ፡ለሕገ፡ኦሪት፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ እድሳት ፡ እንደማይደረግ ፡ ይናገራል።

፺፱፤ በእነርሳቸው፡ላይ፡ተቆጥቶ፡ከለዳውያን፡እን ደማረኳቸውና፡ሁለተኛም፡ተመልሶ፡እንደ ራራላቸው ፡ ወደ ፡ ርስታቸው ፡ እንደመለ ሳቸው፡አንድ፡ጊዜ፡እንደታደሱ፡አይደለም።

፻፤ ነገር፡ግን፡ከክርስቶስ፡ሰው፡መሆን፡በኋላ፡ ይኸውም፡የሕግ፡ፍጻሜ፡ነው።ለኦሪት፡ሕግ፡ ሌላ፡እድሳት፡አልቀረም።

፻፩፤ በውስጡ፡እሾኽ፡እንደሣር፡ይበቅላል፡አለ።

፻፪፤ ይኸም፡ከእርሳቸው፡በክርስቶስ፡ሳያምን፡ የሚቀር፡ቢኖር፡በውሳጤ፡ልቡናው፡የከፋ፡ የተናቀ፡የረከሰ፡ሐሳብ፡ሰይጣን፡ስለሚዘ ራበት፡ነው።

፻፫፤ በእርሷም ፡ ልባቸውን ፡ የሚያስትበት ፡ በእርሱ፡በጌታ፡አምነው፡ይድኑ፡ዘንድ፡አይ ተዋቸውም።

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፶፬፤ ወእኤዝዝ፡ደመና፡ከመ፡ኢያውርድ፡ዝናመ፡ ይብል ፡ እምድኅረ ፡ ምጽአተ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢተርፈ፡ሎሙ፡ኢቍርባን፡ወኢትምህርት፡ ወኢትንቢት። | ፶፬፤ ዝናብ፡እንዳያወርድ፡ደመናን፡አዛለሁ፡አለ፤ ከክርስቶስ፡ሰው፡መሆን፡በኋላ፡ቍርባንም፡ ቢሆን ፡ ትምህርትም ፡ ቢሆን ፡ ትንቢትም፡ ቢሆን፡አልቀረላቸውምና። |
| ፶፭፤ ይቤ፡አሌ፡ሎሙ፡ለእለ፡ያስተእኅዙ፡ቤተ፡ ምስለ፡ቤት፡ወገራህተ፡ምስለ፡ገራህት፡ከመ፡ ይንሥኡ ፡ ደወለ ፡ ቢጾሙ ፤ ቦኑ ፡ ትነብሩ ፡ ውስተ፡ምድር፡ባሕቲትክሙ። | ፶፭፤ ቤትን፡ከቤት፡ጋራ፡አያይዘው፡ለሚሠሩ፡የባ ልንጀራቸውን ፡ ድርሻ ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ፡ እርሻን፡ከእርሻ፡ለሚአቀራርቡ፡ወዮላቸው፤ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ብቻቸውን ፡ ይኖራሉን? አለ። |
| ፶፮፤ ዝንቱ፡ይትሜሰል፡በእንተ፡አፍቅሮ፡ዓለም፡ ኮነት፡ሞት፡ላዕሌሆሙ። | ፶፮፤ ይህን፡ዓለም፡ስለመውደድ፡ሞት፡በላያቸው፡ እንዳለችባቸው፡ይመስላል። |
| ፶፯፤ ወአስተዓደመ፡ሎሙ፡ሰይጣን፡ከመ፡ኵሉ፡ ዘኮነ፡ኮኖሙ፡ሎሙ። | ፶፯፤ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ የእርሳቸው ፡ እንደሆነ፡ ሰይጣን፡ያስመስልላቸዋል። |
| ፶፰፤ ወኮኑ ፡ ይትዓመፁ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወይት ቀሐዉ፡በእንተ፡ዘኮነ፡ወኢኮነ፡ሎሙ። | ፶፰፤ ለእርሳቸው ፡ በሆነ ፡ ባልሆነው ፡ እርስበር ሳቸው፡ይከዳዳሉ፡ይከራከራሉ። |
| ፶፱፤ ይቤ ፡ ቦኑ ፡ ትነብሩ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ባሕቲ ተክሙ። | ፶፱፤ በውኑ፡በዓለም፡ውስጥ፡ብቻችሁን፡ትኖራላ ችሁን?አለ። |
| ፷፤ ይብል፡ብእሲ፡ለእመ፡ኮነ፡ፈራሄ፡እግዚአ ብሔር፡ወየኀሥሥ፡ሥምረቶ፡ወሥርዓቶ፡ እስመ ፡ የአክሎ ፡ ዘወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ፡በውስተ፡ዝ፡ዓለም። | ፷፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሕጉን፡ ሥርዓቱን፡የሚሻ፡ከሆነ፡በዚህ፡ዓለም፡እግ ዚአብሔር፡የሰጠው፡የሚበቃው፡እንደሆነ፡ ይናገራል። |
| ፷፩፤ ወያፈቅሮሙ፡ለአኀዊሁ፡ወይፈቱ፡ከመ፡ ሎሙ ፡ ዘያፈትዎ ፡ ለርእሱ ፡ ወኢኀረየ ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢ ፡ ለነቢረ ፡ ምድር ፡ ወለካል እትኒ። | ፷፩፤ እርሱም፡የተፈጥሮ፡ወንድሞቹን፡ይወዳቸዋል፤ ለእርሱ፡የሚያሻውንም፡ለእርሳቸው፡እንደሚ ያሻቸው ፡ አድርጎ ፡ ይመኝላቸዋል ፤ በምድር፡ መኖርንም ፡ ቢሆን ፡ ሌላውንም ፡ ሀብትና፡ ክብርም፡ቢሆን፡ለራሱ፡አይመርጥም። |
| ፷፪፤ በእንተ፡ዝንቱመ፡ትርጓሜ፡ካልእኒ፡ወውእቱኬ፡ እስመ፡አመረ፡ገራህተ፡ለኀበ፡ዓለም። | ፷፪፤ ስለዚህም፡ትርጓሜ፡ስለ፡ሌላውም፡እርሱ፡ እርሻ፡ያለው፡ዓለምን፡ሲያመለክት፡ነውና። |
| ፷፫፤ ወውስተ፡ዓለም፡ቦ፡ማእምራን፡ወእለኒ፡ኢ፡ ማእምራን። | ፷፫፤ በዓለም፡ውስጥ፡አዋቂዎች፡አላዋቂዎችም፡ አሉ፤ይኖራሉ። |
| ፷፬፤ ወማእምራን፡እንከ፡ለእመ፡ኢያርብሕዎሙ፡ ለሰብእ ፡ ትሩፋተ ፡ በቅንአት ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ትሩፋነ ፡ ይከውኑ፡ወይነሥኡ፡ርስተ፡እሙንቱ። | ፷፬፤ እንግዲህ፡አዋቂዎች፡በቅንዓት፡ተይዘው፡ ሰዎችን፡በትሩፋት፡የማይረቧቸው፡የማይጠ ቅሟቸው ፡ ከሆነ ፡ ከእነርሱ ፡ ይልቅ፡ ብቻቸውን፡በበጎ፡ሥራ፡ፍጹማን፡ሁነው፡ ርስተ፡መንግሥተ፡ሰማያትን፡ይወርሳሉ። |
| ፷፭፤ እልክቱ፡ኢ፡ማዕምራን፡ለጥንቃቄ፡አእም ሮታት፡በዑቀቶሙ፡ዘዚአሆሙ፡ይኩን፡ ሎሙ፡በቅንአቶሙ፡ወውእቱ፡በጽልአተ፡ አእምሮተ፡ዚአሆሙ። | ፷፭፤ እነዚያ ፡ አላዋቂዎች ፡ በእውቀታቸው፡ በጥንቃቄ ፡ ተራቀቅን ፡ ሲሉ ፡ በመቅናት፡ የራሳቸው፡ለራሳቸው፡ይሁንላቸው፡ይህም፡ እነሱን፡ማወቅን፡መጥላታቸው፡ነው። |
| ፷፮፤ ይቤ፡ቦኑ፡ትነብርዋ፡ለምድር፡ባሕቲተክሙ፡ ይብል፡በእንተ፡ምድርኒ፡ለኀበ፡ነገሥት። | ፷፮፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ብቻችሁን ፡ ትኖራላችሁን? አለ፤ ምድር፡ሲል፡በነፍሳቸው፡ነገሥታት፡ ወደሆኑት፡ያመለክታል። |

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፳፯፤ ወኮኑ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡አመ፡ኮኑ፡ሕዝበ፡እግዚአብሔር፡ ወአምኑ፡ በእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኮኑ፡ይትሔዘዙ፡በነፍሳቲሆሙ፡ ከመ፡ ኢይከውን፡ ሎሙ፡ ጸጋ፡ ለአሕዛብ፡ወኢይወርሱ፡መንግሥተ፡እግዚአብሔር፡ወለእመኒ፡አምኑ፡አላ፡ውእቶሙ፡ባሕቲቶሙ። | ፳፯፤ የእስራኤል፡ልጆች፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምነው፡የእግዚአብሔር፡ቤተ፡ሰብእ፡ከሆኑ፡ልጅነት፡ለእነርሳቸው፡ብቻ፡እንጂ፡ለአሕዛብ፡እንደማትሆን፡የእግዚአብሔርንም፡ መንግሥት፡ አሕዛብ፡ እንደማይወርሱ፡ብቻቸውን፡ከእነርሳቸው፡እንደሚወርሷት፡በማሰብ፡የሚጸኑ፡ሆኑ። |
| ፳፰፤ ወዘለፎሙ፡ እንከ፡ ነቢይ፡ ወይቤ፡ ቦኑ፡ ትነብርዋ፡ለምድር፡ባሕቲተክሙ። | ፳፰፤ በውኑ፡ምድርን፡ለብቻችሁ፡ይዛችኋት፡ትኖራላችሁን፡ብሎ፡ነቢይ፡ዘለፋቸው። |
| ፳፱፤ ይብል፡ እስመ፡ እምድኅረ፡ ምጽአተ፡ክርስቶስ፡ኢኮነ፡ሕዝብ፡ዘይኄይስ፡እምነ፡ሕዝብ፡በእንተ፡ብሂሎቱ፡ለአርዳኢሁ፡ሑሩ፡ወመሐሩ፡ ኵሎ፡ አሕዛበ፡ ወዘአምነ፡ እምኔሆሙ፡ሎቱ፡ጸጋ። | ፳፱፤ ከእርሳቸው፡ ከአሕዛብ፡ ውስጥ፡ ለአመነ፡ ይች፡ ልጅነት፡ ለእርሱ፡ ናትና፡ ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ ሂዳችሁ፡ አሕዛብን፡ ሁሉ፡ አስተምሩ፡በማለቱ፡ክርስቶስ፡ሰው፡ከሆነ፡ በኋላ፡ሕዝብ፡ከሕዝብ፡አይሻልም፤አይበልጥም። |
| ፴፤ ይቤ፡ከመ፡በጽሐ፡ዝንቱ፡ውስተ፡ምስማዐ፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት። | ፴፤ ይህ፡ወደ፡አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡ጆሮ፡እንደደረሰና፡እንደተሰማ፡ተናገረ። |
| ፴፩፤ ይብል፡ እስመ፡ ኵሉ፡ ዘኮነ፡ ክሡተ፡ወክቡተ፡ በቅድሜሁ፡ ወውእቱ፡ ማእምረ፡ኵሉ፡ኅጣውእ፡ክሡት፡ወክቡት፡ወውእቱ፡ሰማዔ፡ ጽራሕ፡ ለዘይትመሐፀን፡ ኅቤሁ፡ እምኵሉ፡ልቡ። | ፴፩፤ በፊቱ፡የተገለጸው፡የተሸሸገ፡የተሸሸገው፡የተገለጸ፡ነውና፡እርሱም፡የተገለጸውንና፡የተሠወረውን፡ ኃጢአት፡ ያውቃል፤ በፍጹም፡ ልቡም፡ለሚማፀን፡ልመናውን፡የሚሰማ፡እሱ፡ነው፡ይላል። |
| ሎቱ፡ ስብሐት፡ እስከ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን። | ለዘላለሙ፡ለርሱ፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፡አሜን። |
| ጥበበ፡ሲራክ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | ሲራክ፡በምሳሌ፡የተናገረው፡ጥበብ፡ይህ፡ነው።በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን። |
| ምዕ፡፩፡፩–፲፱። | ምዕ፡፩፡፩–፲፱። |
| ፩ ቀዳሚሃ፡ ለኵላ፡ ጥበብ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር፡ይእቲ፡ወምስሌሁ፡ትሄሉ፡ለዓለም። | ፩፤ የጥበብ፡ ሁሉ፡ መገኛዋ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ነው፤ ከእርሱ፡ ጋርም፡ ለዘላለሙ፡ትኖራለች። |
| ፪፤ ኆፃ፡ባሕር፡ወነጠብጣበ፡ዝናም፡ወመዋዕለ፡ዓለም፡መኑ፡ኈለቈ። | ፪፤ የባሕር፡ አሸዋን፡ የዝናብ፡ ጠብታን፡ የዘላለምን፡ትንሽ፡ቀን፡ማን፡ቈጠረ። |
| ፫፤ ሉዓሌ፡ሰማይ፡ወራኅበ፡ምድር፡ወዕመቀ፡ቀላይ፡ወለጥበብ፡መኑ፡ሰፈሮሙ። | ፫፤ የሰማይን፡ምጥቀት፡የምድርን፡ስፋት፤የውቅያኖስን፡ ጥልቅነት፡ እስከዚህስ፡ ሁሉ፡ ጥበብንም፡መርምሮ፡ማን፡አገኛቸው? |
| ፬፤ ቀዳሜ፡ኵሉ፡ተፈጥረት፡ጥበብ። | ፬፤ ከሁሉም፡አስቀድሞ፡ጥበብ፡ተገኘች። |
| ፭፤ ወኀሊናሃ፡ለጥበብ፡ዘእምፍጥረተ፡ዓለም። | ፭፤ የጥበብ፡መታሰቢያ፡ዓለም፡ሳይፈጠር፡ነው። |
| ፮፤ ሥርዋ፡ለጥበብ፡ለመኑ፡ተከሥተ። | ፮፤ የጥበብ፡ሥሯ፡ለማን፡ተገለጠ? |
| ፯፤ ወመኑ፡አእመረ፡ምክራ። | ፯፤ ምክሯንስ፡ማን፡አወቀ? |

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ፰፤ አሐዱ፡ውእቱ፡ጠቢብ፡ወፈድፋደ፡ግሩም፡ውእቱ፡ወይነብር፡ላዕለ፡መንበሩ፡ውእቱ። | ፰፤ ጥበብ፡አንድ፡ነው፤እጅግም፡ግሩም፡ነው፤እሱ፡በዙፋኑ፡ላይ፡ይኖራል። |
| ፱፤ ወእግዚአብሔር፡ለሊሁ፡ፈጠራ፡ወርእያ፡ወሰፈራሂ። | ፱፤ እርሱ፡እግዚአብሔር፡ሠራት፤አያት፤ሠፈራትም። |
| ፲፤ ወሦጣ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ግብሩ፡ምስለ፡ኵሉ፡ዘሥጋ፡በከመ፡ሀብቱ፡ወወሀቦሙ፡ለኵሎሙ፡እለ፡ያፈቅርዋ። | ፲፤ በሥራው፡ሁሉ፡ላይ፡አሳደራት፤እርሷም፤እንደስጦታው፡ከሥጋው፡ሁሉ፡ጋር፡ናት፤ለሚወዱአትም፡ሁሉ፡እርሷን፡ሰጣቸው። |
| ፲፩፤ ፈሪሃ፡እግዚአብሔር፡ክብር፡ውእቱ፡ወምክህ፡ወትፍሥሕት፡ውእቱ፡ወአክሊለ፡ሐሤት። | ፲፩፤ እግዚአብሔርን፡መፍራት፡ክብር፡ነው፤የሚያስመካም፡ደስ፡የሚያሰኝም፡ነው፤የደስታም፡ዘውድ፡ነው። |
| ፲፪፤ ፈሪሃ፡እግዚአብሔር፡ትፍሥሕተ፡ልብ፡ውእቱ፡ወይሁብ፡ሐሤተ፡ወያስተፌሥሕ፡ወያነውኅ፡መዋዕለ፡ሕይወት። | ፲፪፤ እግዚአብሔርን፡መፍራት፡የልብ፡ደስታ፡ነው፤ደስታም፡ይሰጣል፤ደስ፡ያሰኛል፡የሕይወትንም፡ዕድሜ፡ያስረዝማል። |
| ፲፫፤ ለፈራሂ፡እግዚአብሔር፡ይሤኒ፡ደኅሪቱ፡ወይትባረክ፡አመ፡ዕለተ፡ሞቱ። | ፲፫፤ እግዚአብሔርን፡የሚፈራ፡ሰው፡ፍጻሜው፡ያምርለታል፤በሞቱ፡ጊዜ፡ይከብራል። |
| ፲፬፤ ቀዳሚሃ፡ለጥበብ፡ፈሪሃ፡እግዚአብሔር፡ወተፈጥረት፡ምስለ፡ምእመናን፡እምከርሠ፡እሞሙ። | ፲፬፤ የጥበብ፡(የዕውቀት)፡መጀመሪያ፡እግዚአብሔርን፡መፍራት፡ነው፤ጥበብ፡ከናታቸው፡ማሕፀን፡ጀምሮ፡ከምዕመናን፡ጋራ፡ልትኖር፡ተፈጠረች። |
| ፲፭፤ ወምስለ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ተፈጥረት፡መሠረተ፡ዓለም፡ወተአምነት፡ምስለ፡ዘርዖሙ። | ፲፭፤ ከሰዎችም፡ጋር፡የዓለምን፡መሠረት፡ፈጠረች፤ከልጆቻቸውም፡(ከዘራቸው፡)ጋራ፡ልትኖር፡የታመነች፡ሆነች። |
| ፲፮፤ ጸጊቦታ፡ለጥበብ፡ፈሪሃ፡እግዚአብሔር፡ወታረውዮሙ፡እምነ፡ቀምሓ። | ፲፮፤ እግዚአብሔርን፡መፍራት፡ጥበብን፡(ዕውቀትን)፡መጥገብ፡ነው፤ከፍሬዋም፡ታጠግባቸዋለች። |
| ፲፯፤ ምሉዕ፡ትፍሥሕት፡ውስተ፡አብያቲሃ፡ወውስተ፡አዕፃዲሃ፡ምሉዕ፡ፍሬ። | ፲፯፤ በቤቶቿም፡ደስታ፡ሞልቷል፤በቦታዎቿም፡ፍሬ፡አለ። |
| ፲፰፤ አክሊላ፡ለጥበብ፡ፈሪሃ፡እግዚአብሔር፡ወያመጽእ፡ለሰላም፡ወይፌውስ፡ወያሐዩ። | ፲፰፤ የጥበብ፡(የዕውቀት)፡ዘውዷ፡ፍጻሜዋ፡እግዚአብሔርን፡መፍራት፡ነው፤ሰላምን፡ያመጣታል፤ፈጽሞም፡ያድናል። |
| ፲፱፤ ወርእያ፡ፈጣሪሃ፡ወሠፈራ፡ወከሠታ፡ለእጓለ፡እመሐያው። ወአውኀዘ፡ነቅዐ፡አእምሮ፡ወምክር፡ወጥበብ፡ወአዕበዮሙ፡ለእለ፡ያጸንዕዋ፡ወአክበሮሙ። | ፲፱፤ ፈጣሪዋ፡አያት፤ሠፈራትም፤የምክርንና፡የዕውቀትን፡የጥበብንም፡ምንጭ፡አፈሰሰ፤አጽንተው፡የያዙአትንም፡ፈጽሞ፡አከበራቸው። |

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡አሐዱ፡አምላክ።

ድርሳን፡ዘቅዱስ፡ወብፁዕ፡ዮሐንስ፡አፈወርቅ፡ዘይትነበብ፡በዕለተ፡ሰኑይ፡ነግሀ።
በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ ነዋ፡ሰማዕነ፡ይእዜኒ፡ከመ፡እለ፡ይትሜሰሉ፡በፆም፡ዘዕሩቅ፡እምጸዊረ፡ፍሬያት፡ይወርድ፡ላዕሌሆሙ፡መቅሠፍት፡ዐቢይ፡እምእግዚአብሔር፡ወመድምምም፡እምእለ፡ይኔጽሩ።

፪፡ እፎኬ፡ንሕነ፡አ፡አኀው፡ኢንጠናቀቅ፡ለዐቂበ፡ነገራተ፡ሥርዐትነ፡ወኢንሌቡ፡በተዐቅቦ፡ጽኑዕ፡ፍካሬ፡ቃላት፡ዘተነበ፡ላዕሌነ።

፫፡ ወንትጋደል፡በአስተናጽሖ፡ምድረ፡አልባቢነ፡እምነ፡ሦክ፡ዘየሐንቅ፡ወመሥገርት፡ዘያማስን።

፬፡ ወንዕቀባ፡በልቡና፡እምነ፡አራዊት፡ወአዕዋፍ፡ወኀለፍተ፡ፍኖት፡ከመ፡ንፍረይ፡ፍሬ፡ንጹሐ፡ወንደሎ፡ለፍግዓ፡ዘውስተ፡ገነት፡እስመ፡እለ፡ሰምዕዎ፡እምቅድሜነ፡ሶበ፡ኢትወክፍዎ፡በጥበዐት፡ወድቁ፡እምርስቶሙ፡ወተዐቅፉ፡በጽልመተ፡ኅሊናሆሙ፡ወስሕቱ፡እምፍኖተ፡ርትዕ፡ወተሐንቁ፡በፍቅረ፡ፍትወት፡ወትፍግዕት።

፭፡ ወአያሮሙ፡ቅንአት፡ወተእኅዘ፡በኀሢሠ፡ሢመታት፡ወወድቁ፡ውስተ፡ማዕምቅት፡እኪት።

፮፡ ንስማዕኬ፡ይእዜኒ፡በከመ፡ይነግር፡መጽሐፍ፡አምላካዊ፡አስተንቲኖ፡ፈጣሬ፡ኵሉ፡ለዘመደ፡ዕጓለ፡እመሕያው።

፯፡ ከመ፡ዘያስተኑትን፡ለንጉሥ፡ጊዜ፡ምጽአቱ፡ውስተ፡ሀገር፡እስመ፡እለ፡ይኄልዩ፡በአምኃ፡ወያስተዳልዉ፡በምጽንሐት፡ክቡራት፡

ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ሰኞ፡በነግህ፡የሚነበብ፡ክቡር፡ብፁዕ፡ዮሐንስ፡አፈወርቅ፡የተናገረው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።
የፈጣሪው፡በረከት፡በሁላችን፡ላይ፡ለዘላለሙ፡ትደር፡አሜን።

፩፡ እነሆ፡ፍሬ፡በሌለው፡ዛፍ፡በሚመሰሉ፡ሰዎች፡ለሚያዩት፡የሚአስገርም፡ታላቅ፡መቅሠፍት፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡እንደሚወርድባቸው፡አሁን፡ሰማን።

፪፡ ወንድሞች፡ሆይ፡የሥርዓታችንን፡ነገር፡ለመጠበቅ፡እኛ፡እንዴት፡አንጠነቀቅም? በእኛ፡ላይ፡የሚነበበውን፡ጽኑዕ፡የሆነ፡የቃሉን፡ምሥጢር፡በመጠበቅ፡እንዴት፡አናስተውልም?

፫፡ ምድር፡ልቡናችንን፡አንቆ፡ከሚይዝ፡እሾኽ፡ከሚያጠፉ፡አሽክላ፡ለማንጻት፡እንታገል።

፬፡ በገነት፡ለሚገኘው፡ተድላ፡ደስታ፡ንጹሕ፡ፍሬ፡አፍርተን፡የተዘጋጀን፡እንሆን፡ዘንድ፡ከአራዊት፡ከአዕዋፍ፡ከመንገድ፡አላፊ፡በማስተዋል፡እንጠብቃት፡ከእኛ፡የቀደሙት፡ሰምተው፡ስላልተቀበሉት፡ከርስታቸው፡ገነት፡ወጡ፤በልቡናቸውም፡ድንቁርና፡ተሰናከሉ፡ከእውነተኛው፡መንገድ፡ሳቱ፤በዓለማዊ፡ፍቅርና፡ፍትወት፡በዓመጽ፡ሥራም፡ታነቁ።

፭፡ ቅንዓትም፡አሳወራቸው፤ሹመትን፡በመፈለግ፡ምክንያት፡ተያዙ፤ወደከፋች፡አዘቅትም፡ወደቁ።

፮፡ የሁሉ፡ፈጣሪ፡ለሰው፡ባሕርይ፡(ወገን)፡ሁሉ፡እንደሚስማማ፡አድርጎ፡እንደፈጠረው፡አምላካዊ፡መጽሐፍ፡አቅናንቶ፡እንደሚናገር፡አሁንም፡እንስማ።

፯፡ ንጉሥ፡ወደ፡አገር፡በሚመጣ፡ጊዜ፡የከበረ፡አቀባበል፡ስለሚአስቡ፡እጅ፡መንሻውን፡በማዘጋጀት፡ስለሚያስተናትኑ፡ከመምጣቱ፡

### በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ያቀድሙ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአቱ ፡ ኀቤሃ ፡
በአንጽሮ፡ምግባራት፡ወጥብሓተ፡እንስሳ፡
ወአስተዳልዎ ፡ መባልዕት ፡ ወቅድሐተ ፡
መስቴ፡ወኵሎ፡ጽጌያተ፡ወፍሬያተ፡ከመ፡
ሶበ፡ቦአ፡ንጉሥ፡ውስተ፡ሀገሮሙ፡ይረከብ፡
ኵሎ፡ድልወ፡ዘከመ፡ይፈቅድ፡በቅሩብ፡ወይ
ትፌጋዕ ፡ በፍሥሓ ፡ ወበሐሤት ፡ ለኵላ ፡
ይእቲ፡ሥርዐት፡ሠናይት።
፰፤ ወከማሁኬ፡ገብረ፡እግዚአ፡ኵሉ፡ጽድቅ፡
ሶበ፡ኀለየ፡ይፍጥሮ፡ለአዳም፡ቀዳማዊ፡አዘዘ፡
ቅድመ፡ወአርአየ፡ዘሀሎ፡እምኀበ፡ኢሀሎ፡
በኂሩት፡ዘኢይትከሀል፡ልዕልና፡ረኪቦቱ፡
ወለፍጻሜ፡ፍድፍድናሁ፡ወብዝኀ፡ሣሀሉ፡
ወጽንዐ፡ሠናይቱ፡ወዕዘዘ፡ሀብቱ፡ወዕበየ፡
ፍቅሩ፡ለዕጓለ፡እመሕያው።
ወበእንተ፡ዝ፡ሐነጸ፡ቤተ፡ሥርግወ፡በዘዘ፡
ዚአሁ፡ሠናይት፡ወርሱይ፡በዘዘ፡ዘኢሁ፡
ክብራት።
፱፤ ወፈጠረ፡ሎቱ፡ለየብስ፡ምድር፡ወለማይ፡
ጠፈረ።
፲፤ ወአሠርገዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቤት ፡ በብር
ሃናት ፡ ዘያጸድሉ ፤ ወላሕይ ፡ ዘያን
ጸበርቅ ፡ በከመ ፡ ፀሐይ ፡ ወወርኅ ፡ ወከ
ዋክብት ፡ በውላጤ ፡ ራእያት ፡ ወአሠ
ንዮ ፡ ላሕያት ፡ ወአውፅአ ፡ እምድር ፡ ሠር
ፃተ ፡ ወጽጌያተ ፡ ወሙብቍላተ ፡ ወእን
ስሳ ፡ ወሰራሪተ ፡ ወዘይድህክ ፡ ወዘእን
በለዝ ፡ እምኵሉ ፡ ዘይትፈቶ ፡ ለዕጓለ ፡
እመሕያው።
፲፩፤ ወሶበ፡አሠነየ፡አስተናብሮ፡ማኅደር፡ሠናይ፡
ወአስተጣእጦአ፡ወፈጸመ፡እምኵሉ፡ተድላ፤
፲፪፤ ውእተ፡ጊዜ፡ይቤ፡ንግበር፡ሰብአ፡በአርኢያነ፡
ወበአምሳሊነ፡ከመ፡ይሥልጥ፡ወከመ፡ይኩን፡

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

በፊት ፡ ቦታውን ፡ በማጽዳት ፡ ምንጣፎችን
በማንጠፍ ፡ መቀመጫዎችን ፡ በማስጌጥ ፡
ሶችን፡በማረድና፡ሙብል፡መጠጥ፡በማዘጋ
አበባዎችን ፡ ፍራፍሬዎችን ፡ በማቅረ
ሁሉንም፡እንደሚፈለግ፡በማድረግ፡ይተጋ
ንጉሡ፡ወደ፡አገራቸው፡በገባ፡ጊዜ፡ፈጽሞ
ብሎት ፡ ባደረጋት ፡ መልካም ፡ የአቀባ
ሥርዓት፡ተድላ፡ደስታ፡ይሆንለት፡ዘንድ።
፰፤ የእውነት፡ሁሉ፡ጌታም፡ቀዳማዊ፡አዳ
ይፈጥረው፡ዘንድ፡ባሰበ፡ጊዜ፡እንደዚ
አደረገ፤የመገኘቱ፡ከፍታ፡የማይቻለው
ካለመኖር፡ወደ፡መኖር፡እንዲገለጥ፡በ
ርታው፡ብዛትና፡በልግስናው፡ፍጹም
በጸናች ፡ በጎነቱና ፡ ስጦታው ፡ ሰው
በመውደድ ፡ ልዕልናው ፡ በቸርነ
አስቀድሞ፡አዘዘ፤ስለዚህ፡ለሰው፡ቤ
ሠራ፤በየራሱም፡አስገጤው፤ልዩ፡
በሆነ፡ክብርም፡ሸለመው።
፱፤ ለየብሱ ፡ ምድርን ፡ ለውኃው ፡ ጠፈ
ፈጠረለት።
፲፤ ይኸንንም፡ቤት፡ጸዳል፡ባላቸው፡ብርሃ
የሚያንጸባርቅ ፡ ላህይ ፡ ባለው ፡ በፀሐ
ተለዋዋጭ፡መልክ፡ባላቸው፡በጨረቃና
ዋክብት ፡ ደም ፡ ግባት ፡ እትክልቱን ፡
እቱን ፡ አበባውን ፡ ቡቃያውን ፡ ከምድ
በማውጣት ፡ እንስሳትን ፡ አዕዋፍን ፡ በ
የሚሳበውን ፡ በእግር ፡ የሚሽከረከረው
ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ለሰው ፡ የሚአስፈልገው
በማስገኘት፡አስጌጠው።
፲፩፤ ከተድላው ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡
ያውን፡አሳምሮ፡አከናውኖ፡በፈጸመ፡
፲፪፤ ያን፡ጊዜ፡በአርአያችንና፡በምሳሌያችን፡
እንፍጠር ፤ በፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ይሠ

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ሥልጣኑ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ዘገበርን።
፲፫፤ ትሬእዩኑ ፡ እፎ ፡ ነበረ ፡ እግዚእ ፡ ኵሉ ፡
ፍጥረት፡ ሰዱሰ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡ ያስተዴሉ ፡
አምኃ፡ለገብሩ።
፲፬፤ ርኢክሙኑ ፡ ኦ ፡ አኀወየ ፡ ዕበየ ፡ ዝንቱ ፡
አስተንትኖ ፡ ነጸርክሙኑ ፡ ካዕበ ፡ ዕበየ ፡
ዝንቱ፡ምሳሕ፡ሰማዕክሙኑ፡እፎ፡ኀለየ፡በበ፡
አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኵሉ ፡ ዘዘ ፡ ዘኢሁ ፡
መባልዕተ ፡ ወዘዘ ፡ ዚአሁ ፡ መስቴ ፡ ወፍግዓ ፡
ወተድላ።
፲፭፤ ወፈከራ ፡ ለሊሁ ፡ በአስተአድሞ ፡ በበ
ሂሎቱ፡ወርእየ፡እግዚአብሔር፡ከመ፡ሠናይ፡
ውእቱ።
፲፮፤ ለበውክሙኑ ፡ ዘይቤ ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ በአር
አያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ከመ ፡ ይሥልጥ ፡ ላዕለ ፡
ዓሣተ ፡ ባሕር ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወአራዊተ ፡
ገዳም።
፲፯፤ ርኢክሙኑ ፡ ከመ ፡ እግዚእ ፡ በአርዓያሁ ፡
ዘይሥዕል ፡ ገብሮ ፡ ወይገብር ፡ ከመ ፡ ዝ ፡
ለገብሩ።
፲፰፤ ወእፎኑ ፡ ይደሉ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ዘልፈ ፡
ንነጽር ፡ ኀበ ፡ እሉ ፡ ሠናያት ፡ በዐይነ ፡ ልብነ ፡
እንዘ ፡ ነአኵት ፡ እማዕምቀ ፡ ኀሊናነ ፡
ወንሴብሕ ፡ ለዘአሠነየ ፡ ለዘመድነ ፡ ወንት
ቀነይ ፡ ለዘጸገወነ ፡ ዘመጠነ ፡ ዝ ፡ ክብረ ፡ ከመ ፡
ኢንኩን ፡ ከመ ፡ እሉ ፡ ዐላውያን ፡ እለ ፡
ጸንሐሙ፡ ከመ ፡ ያውዕእ ፡ ሥርዎሙ ፡ ወይነ ፡
ወአውፅአ፡ሦከ።
፲፱፤ ሰማዕኬ ፡ ዘይብል ፡ ልዑል ፡ እንዘ ፡
ይወቅሦሙ፡ ወይዜክር ፡ ዕልወቶሙ ፡
ወይፌክር ፡ እከየ ፡ ምግባሮሙ ፡ ሶበ ፡ ይቤ ፡
ተከለ ፡ ሎሙ ፡ ጸቈነ ፡ ወሐነጸ ፡ ውስቴቱ ፡
ጥቅመ፡ወምክያደ።
፳፤ ወመጠዎሙ፡ለእለ፡ይትጌበሩ፡ዘውእቶሙ፡
አይሁድ ፡ ወተሰፈወ ፡ ይፍረይ ፡ ወይነ ፡
ወፈረየ፡አሥዋከ።
፳፩፤ ወይቤ፡እስመ፡አውፅአ፡ፍሬ፡እኩየ፡እነሥት፡
ጸቈኖ፡ወእአትት፡ጥቅሞ፡ወእሬስዮ፡ሕብልያ፡
ወኢይትርፍ፡ለወይንየ፡ዘይጌሞዶ።
፳፪፤ ወአበቍል ፡ ውስቴቱ ፡ ሦከ ፡ ዐበርት ፡
ወእኤዝዝ ፡ ደመና ፡ ከመ ፡ ኢያውርድ ፡
ላዕሌሁ፡ዝናመ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

ዘንድ፡አለ።
፲፫፤ የሁሉ ፡ ጌታ ፡ ለባሪያው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡
ስድስት፡ቀን፡ሙሉ፡እያዘጋጀ፡እንደቆየ፡ታያ
ላችሁን?
፲፬፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ የዚህን ፡ ዝግጅት ፡
ታላቅነት፡ ታያላችሁን ፤ ሁለተኛ ፡ የዚህን ፡
ታላቅ፡የምሳ፡ግብዣ፡ትመለከታላችሁን?በየ
አንዳንዱ ፡ የመብሉን ፡ የመጠጡን ፡ የተድላ ፡
ደስታውን፡ነገር፡እንዴት፡እንደ፡አሰበና፡እን
ዳዘጋጀ፡ሰምታችኋልን?
፲፭፤ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በማዘጋጀት ፡ እግዚአብሐርም ፡
መልካም ፡ እንደሆነ ፡ ተመለከተ ፡ በማለቱ ፡
ተረጒማት።
፲፮፤ በባሕር ፡ ዓሣዎችና ፡ በሰማይ ፡ ወፎች ፤ በዱር ፡
አራዊቶች ፡ ላይ ፡ ይሠለጥን ፡ ዘንድ ፡ በመልካ
ችንና በምሳሌአችን ፡ ሰውን ፡ እንፍጠር ፡
ያለውን፡አስተውላችኋልን?
፲፯፤ ጌታ ፡ በመልኩ ፡ ባሪያውን ፡ እንደፈጠረው ፡
ታያላችሁን ? ለፈጠረው ፡ ለባሪያውስ ፡
እንዲህ፡ያደርጋል።
፲፰፤ ወደ ፡ እነዚህ ፡ መልካም ፡ ነገሮች ፡ ሁልጊዜ ፡
በዐይነ ፡ ልቡናችን ፡ በመመልከት ፡ ከጥልቅ ፡
አሳባችንም ፡ እያመሰገን ፡ ለባሕርያችን ፡
አስማምቶ ፡ ለፈጠረልንና ፡ ይህን ፡ ያህል ፡
ክብር፡ለሰጠን፡እንገዛ፡ዘንድ፡ለእኛ፡ምንኛ፡
ይገባል?ወይን፡ያፈሩ፡ዘንድ፡የጠበቃቸው፡
እሾክ፡እንዳወጡ፡እንደነዚያ፡ወንጀለኞች፡
እንዳንሆን።
፲፱፤ እየወቀሰና ፡ ክዳታቸውንም ፡ እያወሳ ፡ ክፉ ፡
ሥራቸውንም ፡ እየገለጠ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡
ያለውን ፡ ስማ ፤ በወይኑ ፡ቦታ ፡ ወይን ፡ ተከለ፡
ዙሪያውን ፡ ግምብ ፡ ሠራለት ፡ አውድማም ፡
አዘጋጀ።
፳፤ ለሠራተኞችም ፡ ሰጣቸው ፤ እነርሱም ፡
አይሁድ፡ናቸው፤ወይን፡ያፈራልኛል፡ብሎ፡
ተስፋ፡አደረገ፤ነገር፡ግን፡እሾኽን፡አፈራ።
፳፩፤ ክፉ ፡ ፍሬ ፡ አውጥቷልና ፡ አጥሩን ፡ አፈር
ሳለሁ፤ግምቡንም፡አስወግጄ፡ብዝበዛ፡አደር
ገዋለሁ፤የሚገዝረውም፡አይኖርም።
፳፪፤ በውስጡም፡የሰሌን፡እሾኽ፡አበቅልበታለሁ፡
በላዩም ፡ ዝናም ፡ እንዳያወርድ ፡ ደመናን ፡
አዝዛለሁ፡አለ።

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ጽ፫፤ ይደልወነኬ፡ይእዜኒ፡ንትገበር፡ዐጸደ፡ወይን፡ ዘተውህበ፡ለነ፡ሠናየ፡ወንርሐቅ፡እምትካዝ፡ ዘየኀልፍ። | ጽ፫፤ አሁንም ፡ የተሰጠንን ፡ መልካም ፡ የወይን፡ ቦታ ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ፤ ከሚ ልፍም፡ትካዜ፡እንራቅ። |
| ጽ፬፤ ወኢንትአኀዝ ፡ በአፍቅሮ ፡ ሢመታት ፡ በከመ፡ ተእኀዙ ፡ እሉ ፡ ሕሡማን ፡ ወያራ ፡ አዕይንተ ፡ ኀሊናሆሙ ፡ ወጸልመ ፡ ብርሃነ ፡ አልባቢሆሙ፡ ወወድቁ ፡ እምጸታ ፡ ኀሩያን ፤ አላ ፡ ንትጋደልኬ፡ ወትረ ፡ ከመ ፡ ንቅረብ ፡ ኀበ ፡ **እግዚእነ** ፡ በምሒረ ፡ ነዳያን ፡ አኀዊነ። | ጽ፬፤ የልቡናቸው ፡ ዕውቀት ፡ እንደጠፋባቸው፡ ዓይነ፡ሕሊናቸው፡እንደታጠረባቸው፡እንደ ነርሱ ፡ በሹመት ፡ ፍቅር ፡ እንዳንያዝ፡ከተመ ረጡት፡ወገን፡ተለይተው፡እንደ፡ወደቁ፡እን ዳንወድቅ ፡ ለወንድሞቻችን ፡ ለድኆች፡ በመራራት፡ወደ፡**ጌታችን**፡እንቀርብ፡ዘንድ፡ ተጋድሎ፡እናድርግ፡እንጂ። |
| ጽ፭፤ ወንትመየጥ፡ኀበ፡ጽኑሳን፡ከመ፡ንትባላሕ፡ በምሕረቱ ፡ **ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ** ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወለእመ፡ኮነ፡ውስተ፡ኀሢሠ፡ሢመታት፡ ንበጽሕ፡ውስተ፡ሞት። | ጽ፭፤ የክብር፡ባለቤት፡በሆነ፡በጌታችንና፡**በመድ ኃኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ በቸርነቱ፡ ከመከራ፡እንድን፡ዘንድ፡ችግረኞችን፡ወደ፡ መጐብኘት፡እንመለስ፤ግን፡ሹመት፡ወደ፡ መፈለግ፡ከሆነ፡ወደ፡ሞት፡እንደርሳለን። |
| ጽ፮፤ አ፡ፍቁራንየ፡ንኅየይ፡እምአፍቅሮ፡ሢመት፡ ከመ፡ንረስ፡መንግሥተ፡ዘኢይበሊ፡በኀበ፡ **እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት፡ወክብር፡ወዕበይ፡ይደሉ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን። | ጽ፮፤ ወድሞቼ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ ሹመትን፡ ከመውደድ፡እንራቅ፤ **በጌታችን ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ**፡ዘንድ፡የማይጠፋውን፡መንግሥት፡ እንወርስ ፡ ዘንድ ፡ ለርሱም ፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ልዕልና፡ይገባል፤ለዘላለሙ፡አሜን። |
| **በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ድርሳን ፡ ዘቅዱስ ፡ ወብፁዕ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ** ፡ በእንተ፡ዕፀ፡በለስ፡ዘይ ትነበብ ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ ነግሀ ፡ ዘዕለተ ፡ ሕማማት። | **አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ስም ፡ በሕማማት ፡ ሰሞን፡ ሰኞ ፡ በነግህ ፡ ስለ ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ የሚነበብ፡ **ክቡር ፡ ንዑድ ፡ የሆነ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ**፡የተ ናገረው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው። |
| ፩፤ ወሶበ ፡ ነጸረት ፡ ዐይን ፡ ኀበ ፡ ዖም ፡ ዘባቲ ፡ ዘዘዚአሁ፡አንቅዕተ፡ማይ፡እስመኬ፡በእንቲአሃ፡ ይትፌሣሕ፡ልብ፡ወየሐውር፡ኀቤሃ፡ብእሲ፤ | ፩፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ የውኃ ፡ ምንጮች ፡ አጠገብ፡ ወዳለ፡ዛፍ፡ዓይን፡በተመለከተች፡ጊዜ፡ስለርስዋ፡ ልብ፡ደስ፡ብሎት፡ሰው፡ወደርስዋ፡ይሄዳል። |
| ፪፤ ከማሁ ፡ አስተማስል ፡ ለእለ ፡ ይሰምዑ ፡ አንብቦ፡መጻሕፍት፡ቅዱሳት። | ፪፤ መጻሕፍትን ፡ በማንበብ ፡ ለሚያስተውሉ፡ እንዲሁ፡ምሳሌ፡እመስላለሁ። |
| ፫፤ እስመ፡ውእቶሙ፡በልቦሙ፡ወበኀሊናሆሙ፡ ይሰምዑ ፡ ውእተ ፤ ወለእለሰ ፡ ሃለዉ ፡ በሥጋ ፡ ከማነ። | ፫፤ እነርሱም ፡ በልቡናቸውና ፡ በሃሳባቸው፡ ይህንን፡ ያስተውሉታልና ፡ እንደ ፡ እኛም፡ በሥጋ፡ያሉትን፡ይሰማሉ። |
| ፬፤ እስመ ፡ ኀሊናሆሙ ፡ ወልቦሙ ፡ ስቁላን ፡ ለአንብቦ፡መጻሕፍት፡ክቡራት። | ፬፤ የከበሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ ለማንበብ ፡ ልባቸው፡ ይሰቀላልና። |
| ፭፤ ከማሁኬ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ ፍቁራንየ ፡ ይእዜኒ ፡ ስምዑ ፡ ዘኮነ ፡ በቢታንያ ፡ **እምእግ ዚእነ ፡ ክርስቶስ** ። ወበእንተ ፡ ዘገብረ ፡ መንክረ፡በዕፀ፡በለስ። | ፭፤ ወንድሞቼ ፡ እንዲሁ ፡ ልትሆኑ ፡ ይገባል ። አሁንም ፡ **ከጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ**፡ ዘንድ፡በቢታንያ፡በዕፀ፡በለስ፡ላይ፡የተደረ ገውን፡ድንቅ፡ተአምር፡ስሙ። |

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፮፤ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ለእመኒ ፡ ኢሀሎኩ ፡ በሥጋ፡አእምር፡በልብየ፡ወኀሊናየ፡ውእተ፡ግብረ፡ወአነ፡አንብብ፡ዘገብረ፡ፈቃዱ፡ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በይእቲ ፡ ዕፀ ፡ በለስ።

፯፤ እስመ፡ኮነት፡ይእቲ፡እምቅድመ፡ምጽአቱ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኀቤሃ፡አሚሃ፡በቈለት፡ወአሥረጸት፡ቈጽለ።

፰፤ ወበጊዜ፡ይቤላ፡እግዚእነ፡ኢይኩን፡በውስቴትኪ፡ፍሬ፡የብሰት፡ወተሠረወት።

፱፤ ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡በዛቲ፡ዕለት፡ጸቢሖ፡እንዘ፡የዓርግ፡እግዚእነ፡ክርስቶስ፡ርኅበ፤ ወርእየ፡ለበለስ፡እሐቲ፡ውስተ፡መንገድ፡ወሖረ፡ኀቤሃ፡ወአልቦ፡ዘረከበ፡በውስቴታ፡ፍሬ፡ዘእንበለ፡ቈጽል፡ባሕቲታ።

፲፤ ወይቤላ፡እንከ፡ኢይኩን፡ፍሬ፡በውስቴትኪ፡ለዓለም፡ወየብሰት፡በጊዜሃ፡ይእቲ፡በለስ።

፲፩፤ ይቤ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ሶበ፡ኀለይኩ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ግብር፡እደነግፅ፡ወይትከፈል፡ልብየ፡ሶበ፡ኀለይኩ፡እኄሥሥ፡ዘንተ፡ቃለ፡ወዘንተ፡መንክረ።

፲፪፤ ወሶበ፡እኔጽር፡ኀበ፡ዝንቱ፡መንክር፡እረክብ፡ኅሊና፡ውሉጠ።

፲፫፤ ወበከመ ፡ ዘይሬኢ ፡ ብእሲ ፡ ኀበ ፡ አስከሬነ ፡ ወርቅ ፡ ዘውስቴቱ ፡ ባሕርያት ፡ ክቡራት ፡ ዘብዙኅ ፡ ሤጠሙ ፡ ወዘቦቱ ፡ ጽሑፍ ፡ ምሥጢር፡ኀቡእ።ወይፈቅድ፡እምዝ፡ከመ፡ይርአይ፡ኀበ፡ውእቱ፡አስከሬን፡ዘያንጸበርቅ፡እምብርሃን፡እሉ፡ባሕርያት፡ዘውስቴቱ።

፲፬፤ ካዕበ፡ይጔጕዕ፡ከመ፡ይርአይ፡ኀበ፡ውእቱ፡አስከሬን፡ወሠናይቶ፡ይፈቱ፡ይርአይ፡ወያእምር፡ውእተ፡ምሥጢረ፡ዘጽሑፍ፡ውስቴቱ።

፲፭፤ ከማሁኬ፡አነኒ፡አ፡አኀውየ፡ሶበ፡ርኢኩ፡ኀበ፡ዘይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡በዛቲ፡ዕለት፡ወውእቱ፡ያጤይቅ፡ለኵሉ።

፲፮፤ ወርኢኩ፡በልብየ፡ኀበ፡ውእቱ፡ወፈቀድኩ፡ነፍስየ፡ኀበ፡ውእቱ፡አእምሮ፡መንክር፡ወዜና፡ዘባቲ፡ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ወጸቢሖ፡እንዘ፡የዐርግ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ሀገረ፡ርኅበ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፮፤ ቅዱስ፡ዮሐንስም፡በሥጋ፡በዚያ፡ባልኖርም፡ያንን ፡ ሥራ ፡ በልቤና ፡ በመንፈሴ ፡ አውቃለሁ። የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈቃድ፡በዚያች፡በበለስ፡ዕንጨት፡ላይ፡ያደረገውን፡እኔ፡አነባለሁ፡አለ።

፯፤ ያቺ ፡ በለስ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደርስዋ ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ ለምልማ ፡ ቅጠል፡አውጥታ፡ነበር።

፰፤ ጌታችንም፡በውስጥሽ፡ፍሬ፡አይሁን፡ባላት፡ጊዜ፡ወዲያው፡ደረቀች፤ከሥርዋም፡ተነቀለች።

፱፤ ቅዱስ፡ወንጌል፡እንዲህ፡አለ፤በዚች፡ቀን፡በነጋ፡ጊዜ፡ወደ፡ከተማ፡ሲወጣ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ተራበ፤በመንገድም፡የበለስን፡ዛፍ፡አይቶ፡ወደርስዋ፡ሄደ፤ግን፡በውስጥዋ፡ያገኘው፡ፍሬ፡የለም፤ከብቻዋ፡ከቅጠል፡በቀር።

፲፤ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለዘላለም ፡ ፍሬ ፡ አይገኝብሽ፡አላት፤ያቺም፡በለስ፡ወዲያውኑ፡ደረቀች።

፲፩፤ ቅዱስ፡ዮሐንስም፡ይህን፡ሥራ፡ባሰብኩት፡ጊዜ፡እደነግጣለሁ፤ይህንን፡ቃልና፡ይህን፡ድንቅ፡ሥራ፡ለመመርመር፡ባሰብኩ፡ጊዜ፡ልቤ፡ይከፈላል፡አለ።

፲፪፤ ወደዚህም ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ በተመለከትኩ ፡ ጊዜ፡ልዩ፡የሆነ፡ሐሳብ፡አገኛለሁ።

፲፫፤ የተሠወረ ፡ ጽሑፍ ፡ ተጽፎበት ፡ ዋጋቸው ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ የከበሩ ፡ አዕናቍን ፡ ወደ ፡ ያዘ ፡ የወርቅ፡ሣጥን፡እንደሚመለከትና፡በውስጡ፡ካሉት፡አዕናቍ፡ብርሃን፡የተነሣ፡ወደሚያንጸባርቀው ፡ የወርቅ ፡ ሣጥን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚሻ፡ሰው።

፲፬፤ ዳግመኛም፡አይቶ፡መልካምነቱን፡ያውቅ፡ዘንድ፡በውስጡ፡የተጻፈውንም፡ምሥጢር፡ይረዳ፡ዘንድ፡እንደሚቸኩል።

፲፭፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ የከበረ ፡ ወንጌል፡ያለውንና፡ለሁሉ፡የሚያስረዳውን፡በአየሁ፡ጊዜ፡እኔም፡እንዲሁ፡ነኝ።

፲፮፤ በልቤም ፡ ወደርሱ ፡ ተመለከትኩ ፤ የከበረ ፡ ወንጌል ፡ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሲወጣ ፡ ተራበ ፤ የሚል ፡ ዜናንና ፡ ድንቅ፡ሥራን፡ማወቅን፡ሰውነቴ፡ወደደች።

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፯፤ አ፡ገ፡መንክር፡ገ፡እንግዳ፡ዘይሴሲ፡ለኵሉ፡ ብሔር፡ወዘአጽገበ፡እምኀምስቱ፡ኅብስት፡ ለኀምሳ፡ምእት፡ርኅቡ፡ዘአዘዘ፡ማየ፡ይኩን፡ ወይነ፡ርኅቡ።

፲፰፤ ዘከሠተ፡አዕይንተ፡ዕውር፡በጽቡር፡ከመ፡ ይርአይ፡ርኅቡ።

፲፱፤ ዘኬደ፡ዲበ፡ማዕበል፡ወሖረ፡ላዕለ፡ማይ፡ ወኢ.ርሕሳ፡እገሪሁ፡ርኅቡ።

፳፤ ዘገሠጸ፡ነፋሳተ፡ወተአዘዙ፡ሎቱ፡ለግብሩ፡ ወዘይእኅዝ፡በቃሉ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ርኅቡ።

፳፩፤ ወእሮ፡ይቤ፡ኢሳይያስ፡እግዚአብሔር፡ ዘለዓለም፡ኢይርኀብ፤ወኢይጸምእ፤ወኢይ ደክም።

፳፪፤ ወመጻሕፍት፡ቅዱሳት፡ስምዕ፡ላዕሌሁ፡ ከመ፡ክርስቶስ፡አምላክ፡ውእቱ፡በከመ፡ ይቤ፡ዮሐንስ፡ወንጌላዊ፡ቀዳሚሁ፡ቃል፡ ውእቱ፡ወውእቱ፡ቃል፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ ውእቱ፡ወእግዚአብሔር፡ውእቱ፡ቃል።

፳፫፤ ወእሮ፡ርኅበ፡አምላክ፡በእንተ፡አርአያ፡ ግብር፡ዘአጽገበ፡ኀምሳ፡ምእተ፡በመለኮቱ፤ ወበፈቃዱ፡መጽአ፡ኀበ፡ዕፀ፡በለስ፡ከመ፡ ሰብእ፡ወሎቱ፡ክሡት፡ውስተ፡ኵሉ፡መካን፡ ዘበመለኮቱ፡ምሉዕ።

፳፬፤ መጽአ፡ኀበ፡ዕፅ፡ዘአልቦ፡ፍሬ፡ከመ፡ ሰብእ፡ወአይበሳ፡በቃሉ፡ከመ፡አም ላክ።

፳፭፤ ወይቤላ፡ኢይኩን፡ፍሬ፡እምውስቴትኪ፡ እስከ፡ለዓለም፡ወወዕአ፡ትእዛዝ፡ምስለ፡ ብሂል። ወእምዝ፡የብሰት፡ይእቲ፡በለስ፡ በጊዜሃ።

፳፮፤ ቃልሰ፡ቃለ፡ብእሲ፡ውእቱ፡ወምግባር፡ ግብረ፡አምላክ፡ውእቱ።

፳፯፤ ወባሕቱ፡አ፡አኀውየ፡ብዙኃን፡እምፈካ ርያን፡ወኀጣውያን፡ተናገሩ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ ዕፀ፡በለስ።

፳፰፤ በከመ፡እብል፡ዓዲ፡አንሰ፤ወአኮ፡ዘአ ኀብእ፡እምኔክሙ፡ምንተኒ።

፳፱፤ እምዘእፈቅድ፡አድርስ፡ለክሙ፡ወእዜ ኑክሙ፡በከመ፡ክህልክሙ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፲፯፤ ምን፡ይረቅ! ምን፡ይደንቅ! ይህ፡እንግዳ፡ ነው፤ዓለምን፡ሁሉ፡የሚመግብና፡ከአምስት፡ እንጀራም፡አምስት፡ሺህ፡ሕዝብ፡ያጠገበ፡ተራበ? ውኃው፡ወይን፡ይሆን፡ዘንድ፡ያዘዘ፡ተራበ?

፲፰፤ ያይለት፡ዘንድ፡የዕውሩን፡ዓይን፡ጭቃ፡ ቀብቶ፡ያበራለት፡ተራበን?

፲፱፤ በማዕበል፡ላይ፡የሄደ፡እግሮቹም፡ያልራሱ፡ ተራበን?

፳፤ ነፋሳትን፡የገሠጸ፤ለቃሉም፡የታዘዙለት፡ ይህን፡ሁሉ፡በቃሉ፡የያዘ፡እርሱ፡ተራበን?

፳፩፤ ኢሳይያስ፡እግዚአብሔር፡ለዘላለም፡ አይራብም፤አይጠማም፤አይደክምም፡ እንዴት፡አለ?

፳፪፤ ክርስቶስ፡አምላክ፡እንደሆነ፡የከበሩ፡መጻሕ ፍቶች፡ይመሰክራሉ፤ወንጌላዊው፡ዮሐንስ፡ ያ፡ቃል፡ቀዳማዊ፡ነው፤ያ፡ቃል፡በእግዚአ ብሔር፡ዘንድ፡ነበረ፤ያም፡ቃል፡እግዚአ ብሔር፡ነው፡ብሎ፡እንደ፡ተናገረ።

፳፫፤ በመለኮቱ፡አምስት፡ሺህ፡ሕዝብ፡ያጠገበ፡ አምላክ፡በሰው፡አርዓያ፡እንዴት፡ተራበ! ለእርሱ፡ሁሉ፡የተገለጠና፡በመለኮቱም፡ በሁሉ፡ቦታ፡ምሉ፡ሲሆን፡ወደ፡ዕፀ፡በለስ፡ በፈቃዱ፡እንዴት፡መጣ።

፳፬፤ እንደማያውቅ፡ሰው፡ፍሬ፡ወደሌላት፡በለስ፡ መጥቶም፡አምላክ፡እንደመሆኑም፡በቃሉ፡ ረግሞ፡አደረቃት።

፳፭፤ እስከ፡ዘላለሙ፡በውስጥሽ፡ፍሬ፡ አይገኝብሽ፡ አላት፤ትእዛዝም፡ከነገር፡ ጋር፡ወጣ፤ወዲያውኑ፡ያች፡በለስ፡ ደረቀች።

፳፮፤ ቃሉስ፡የሰው፡ቃል፡ነው። ሥራው፡ግን፡ የአምላክ፡ሥራ፡ነው።

፳፯፤ ወንድሞቼ፡ሆይ፡ነገር፡ግን፡ከተርጓሚ ዎችና፡ከተመራማሪዎች፡ስለዚች፡የበለስ፡ ዛፍ፡ብዙዎች፡ተናገሩ።

፳፰፤ እኔ፡እንደተናገርኩ፡ደግሞ፡ከእናንተ፡ ምንም፡ምን፡የምሸሽገው፡የለም።

፳፱፤ እናንተ፡እንደምትችሉት፡መጠን፡እነግራ ችሁና፡አደርስላችሁ፡ዘንድ፡እንደምፈቅድ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፴፩፤ እስመ፡ኢኮነ፡ገዘንቱ፡ቃል፡ሕፁፀ፡እምቃል፡ ዘይቤ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ አላ ፡ እምብዝኅ ፡ ምሥጢር ፡ ኅቡእ ፡ ዘአብርሀ ፡ ሊተ ፡ ተናገርኩ፡በዘፈቀድኩ፡እንብብ።

፴፪፤ አኮኑ ፡ ዘይቤ ፡ ዛቲ ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ትይበስ ፡ ወየብሰት ፡ ኢይክልኑ ፡ ከመ ፡ ይበላ ፡ ታፍሪ ፡ በጊዜሃ ፤ ወባሕቱ ፡ ምንተ ፡ ዘአበሰት ፡ ዛቲ ፡ ዕፅ፡እስመ፡ኢኮነ፡መዋዕለ፡ፍሬ፡አሚሃ።

፴፫፤ በከመ፡ስምዐ፡ኮነ፡ማርቆስ፡ወንጌላዊ፡ከመ፡ መዋዕለ፡ክረምት፡ውእቱ።

፴፬፤ ወባሕቱ፡ኮነ፡ዐቢየ፡እስመ፡ንሕነ፡ረከብነ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስሃ ፡ ያከብርዎ ፡ እምገጽ ፡ ወያዐቅፍዎ ፡ እምገጽ ፤ ያከብርዎ ፡ በእንተ ፡ ቃሉ ፡ ዘይቤ ፡ የብሰት ፡ ወያስተሐቅርዎ ፡ በእንተ፡ተምዖቱ፡ኪያሃ።

፴፭፤ ወባሕቱ ፡ አ ፡ አኀውየ ፡ ዓቢይ ፡ ምስጢር ፡ ውእቱ፡ጥቀ።

ወዝንቱ ፡ ግብር ፡ ሰማያዊ ፡ ዘይትሌዓል ፡ እምልብ።

፴፮፤ ወብዙኃን ፡ እምፈካርያን ፡ ይቤሉ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ጉባኤ ፡ አይሁድ ፡ ሶበ ፡ መጽአ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይኅሥሥ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፍሬ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኢረከበ ፡ ዘእንበለ ፡ መጻሕፍት ፡ ወነቢያት ፡ በከመ ፡ ቈጽል፡ዘአቍጸለት።

፴፯፤ ወይቤላ ፡ ኢይኩን ፡ እምውስቴትኪ ፡ ፍሬ ፡ ለዓለም፤ወየብሰት።

፴፰፤ ወአንሰ፡አ፡ፍቁራንየ፡ፈራህኩ፡እምዝንቱ፡ ፍካሬ ፤ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘይከልአኒ ፡ ወኢን ስቲተ፡ለለብዎ፡እምኔሃ።

፴፱፤ እፎኑ ፡ ረገመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ጉባኤ ፡ አይሁድ፡ወውእቱሰ፡ዘይቤለነ፡ባርኩ፡ወኢ ትርግሙ፡በእፎኬ፡ረገመ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ዘንተ፡ጉባኤ፡አይሁድ፡ወአህጕለ።

፵፤ ወውእቱ ፡ ዘይቤ ፡ ኢመጽአ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ለሀጕል ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ይኅሥሥ ፡ ወያድኅን፡ዘተሀጕለ።

፵፩ ወለእመ፡ይቤለከሙ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ወኢም ንተኒ፡ወአብዝኀ፡ነቢበ፡ከመ፡ፍካሬ፡ይእቲ፡ ንብሎ፡በእፎኬ፡ትከውን፡ጉባኤ፡አይሁድ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓትነግህ።

፴፩፤ ይህ፡ቃል፡የከበረ፡ወንጌል፡ከተናገረው፡አይ ጐድልምና፡እናገር፡ዘንድ፡እንደምፈልገው፡ የተሠወረ ፡ ምሥጢር ፡ የገለጠልኝን ፡ ተናገርኩ፡እንጂ።

፴፪፤ ያቺ፡የበለስ፡ዕንጨት፡ትድረቅ፡ብሎ፡የደረቀች፡ አይደለምን? ወዲያውኑ፡ታፍራ፡ይላት፡ዘንድ፡ አይችልምን? ነገር፡ግን፡ይቺ፡ዕፅ፡ምን፡በደለች? ያን፡ጊዜ፡የፍሬ፡ወራት፡አልነበረምና።

፴፫፤ የክረምት ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወንጌላዊ ፡ ማርቆስ፡መስክሮአልና።

፴፬፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንደሆነ ፡ አይ ተናልና ፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስን ፡ በአንድ ፡ ወገን፡ ሲያከብሩት ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ይነቅ ፉታል ፤ ደረቀች ፡ ስለሚለው ፡ ቃል ፡ ያከብ ሩታል፡እርሷን፡በመቆጣቱ፡ይነቅፉታል።

፴፭፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሞቼ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ምሥጢር፡ነው።

ይህም ፡ ሥራ ፡ ከልብ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚል ፡ ሰማያዊ፡ሥራ፡ነው።

፴፮፤ ከተርጓሚዎች፡ብዙዎች፡የአይሁድ፡ጉባዔ፡ እንደሆነች ፡ ተናገሩ ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ የሃይማኖት ፡ ፍሬ ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ወደ፡ እነርሳቸው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እንደለመ ለመች ፡ ቅጠል ፡ ከመጻሕፍተ ፡ ኦሪት ፡ ከነቢያት፡በቀር፡አላገኘም፡ይላሉ።

፴፯፤ ለዘላለሙ ፡ ፍሬ ፡ አይገኝብሽ ፡ አላት ፤ ወዲያውኑ፡ደረቀች።

፴፰፤ ወንድሞቼ፡ሆይ፡ከዚህ፡ትርጓሜ፡የተነሣ፡ እኔ፡ፈራሁ፤ከርሷ፡ጥቂት፡ብመራመር፡የሚ ከለክለኝ፡የለምና።

፴፱፤ የአይሁድን፡ጉባዔ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡እንዴት፡ ረገመ? እርሱ ፡ መርቁ ፡ እንጂ ፡ አትራገሙ ፡ የሚለን ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ የአይሁድ ፡ ጉባዔ ፡ እንዴት፡ረግሞ፡ያጠፋል?

፵፤ እርሱ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ ለማጥፋት ፡ አልመጣሁም ፤ የጠፋውን ፡ ለመፈለግና ፡ ለማዳን፡እንጂ፡ብሎ፡የተናገረ፡ሲሆን።

፵፩፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡ እንደዚች ፡ አተረጓጐም ፡ ምንም ፡ ነገርን ፡ ቢአበዛ ፡ የአይሁድ ፡ ጉባኤ ፡ ከሥርዋ ፡ ተነቅላ ፡ ደርቃ ፡ እንዴት ፡ ጠፋች ፡

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት፡ነግሀ። |
| --- | --- |
| ዘየብስት፡እምሥረዊሃ፡ወተሀጒለት። | ቢላችሁ። |
| ፵፩፤ ወወዕአ ፡ ለነ ፡ ዝንቱ ፡ ዐጽቅ ፡ ሠናየ ፡ ፍሬ ፡ ጳውሎስ፡ሐዋርያ። | ፵፩፤ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ዐጽቅ ፡ ሐዋርያው፡ ጳውሎስ፡ከአይሁድ፡ጉባዔ፡ወጣልን፡እንለዋለን። |
| ፵፪፤ ወብዙኃን ፡ እምኀልአን ፡ ተመይጡ ፡ እምጉባኤ፡አይሁድ፡ዘነአምሮሙ፡አኮኑ፡እስጢፋኖስ ፡ ቀዳሚ ፡ ሰማዕት ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘተወግረ፡እምኀበ፡አይሁድ። | ፵፪፤ ብዙዎች፡የምናውቃቸው፡ከአይሁድ፡ጉባኤ፡ የተመለሱ ፡ አይደለምን ? ከርሳቸውም፡ አይሁድ፡የወገሩት፡የሰማዕታት፡መጀመሪያ፡ እስጢፋኖስ፡የተገኘ፡አይደለምን? |
| ፵፫፤ ወኮነ፡ይትናገር፡በጉባኤሆሙ። | ፵፫፤ በጉባኤያቸውስ፡ውስጥ፡የሚከራከር፡የነበረ፡ አይደለምን? |
| ፵፬፤ አውይንሂ ፡ ረድእ ፡ ወሲኮር ፡ ረድእ ፡ ወካልአንሂ ፡ ብዙኃን ፡ ዘእሙራን ፡ አስማቲሆሙ ፡ በኀቤነ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ይጼዐሉ ፡ ምስሌነ። | ፵፬፤ አውይንና ፡ ሲኮር ፡ የተባሉ ፡ አርድእት፡ ሌሎችም ብዙዎች፡ስማቸው፡በእኛ፡ዘንድ፡ የታወቁ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንደኛ ፡ መከራ፡ የሚቀበሉ፡የተጠሉ፡አይደሉምን? |
| ፵፭፤ ወባሕቱ፡አንሰ፡እብለክሙ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ኢኀደገ፡ጸውዖ፡ሕዝበ፡አይሁድ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ስምዕ፡በውስተ፡መልእክቱ፡እንዘ፡ይብል። | ፵፭፤ ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ መጥራትን ፡ አልተወም፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡መስክሮአልና። |
| ፵፮፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢኀደገ ፡ ሕዝቦ ፡ ሐሰ ፡ አኮኑ ፡ አነሂ ፡ እስራኤላዊ ፡ አነ ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ ወነገደ ፡ ብንያም ፤ ኢገደፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቦ ፡ ዘአቅደመ ፡ አእምሮ። | ፵፮፤ እግዚአብሔር፡ወገኖቹን፡ጣላቸውን?አልጣ ላቸውም ፡ እኮን ፤ እኔ ፡ ከብንያም ፡ ወገን፡ የምሆን፡የአብርሃም፡ዘር፡እስራኤላዊ፡አይደ ለሁምን ? እንኪያስ ፡ አስቀድሞ ፡ የወደ ቻቸውን፡ሕዝቡን፡እግዚአብሔር፡አልጣለም፡ |
| ፵፯፤ ወባሕቱ ፡ አሰፈዎሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሶበ ፡ ተፈጸመ፡ኵሉ፡ወአሕዛብ፡አምኑ፡ወከመዝ፡ ይድኅኑ፡ኵሉ፡እስራኤል። | ፵፯፤ ነገር፡ግን፡ሁሉም፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡አሕዛብ፡ አመኑ ፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ ሰጣቸው፡ እንዲሁም፡እስራኤል፡ሁሉ፡ይድናሉ። |
| ፵፰፤ እስመ ፡ አኮ ፡ ዘኮኑ ፡ በእንቲአነ ፡ አይሁድ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምኑናነ ፡ እስከ ፡ ለነ ፡ በጌጋዮሙ፡ይሣሃለነ። | ፵፰፤ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ስለእኛ ፡ አይሁድ፡ የተጣሉ ፡ አይደለም ፤ በነሱ ፡ በደል ፡ እኛን፡ ይቅር፡እስኪለን፡ድረስ። |
| ፵፱፤ ለሊሁ ፡ ጳውሎስ ፡ ስምዐ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እመንገለ፡ኅሬስ፡ፍቁራን፡እሙንቱ፡በእንተ፡ አበዊሆሙ ፡ እስመ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጽዋዔሁ፡ኢኀደጎሙ። | ፵፱፤ ራሱ፡ጳውሎስ፡እንዲህ፡ሲል፡መስክሮአል፡ አባቶቻቸው ፡ ስለመመረጣቸው ፡ ወንድሞ ቻችን ፡ ናቸው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ፡ እነርሱን፡መጥራት፡አልተወምና። |
| ፶፤ ወእፈቅድ ፡ ይእዜኒ ፡ አ ፡ አኀውየ ፡ እፈጽም፡ለክሙ፡ቃለ፡በእንተ፡አዳም፡ይቤ፡ እንዘ፡ሀሎ፡ዕራቀ፡በውስተ፡ገነት፡በአይኑ፡ ቈጽል ፡ ሰፍየ ፡ ዘተከድነ ፡ ወለብሰ ፡ እምኔሃ ፡ ዐጽፈ። | ፶፤ ወንድሞቼ፡ሆይ፡አሁንም፡ስለ፡አዳም፡የም ግራችሁን፡ቃል፡ልፈጽምላችሁ፡እወዳለሁ፡ አለ ፤ አዳም ፡ በገነት ፡ ዕርቃኑን ፡ ሁኖ ፡ ሳለ፡ በየትኛው ፡ ቅጠል ፡ ነበር ፡ መሸፈኛ ፡ ሠፍቶ፡ ዕርቃኑን፡የሸፈነ? |
| ፶፩፤ ርኢከኑ፡እፎ፡የብሰት፡ቈጽል፡አኮኑ፡ይእቲ፡ ቈጽለ፡በለስ፡ዘተከድነ፡ባቲ፡አዳም፡ወከደነ፡ ኃፍረቶ። | ፶፩፤ ይህች ፡ ቅጠል ፡ እንዴት ፡ እንደደረቀች፡ አየህን ? አዳም ፡ የለበሳት ፡ ዕርቃኑን ፡ የሸፈ ነባት፡አይደለችምን? |
| ፶፪፤ ወመጽአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ ዕፀ | ፶፪፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ለመለመችው ፡ የበለስ፡ |

### በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

በለስ ፡ እንተ ፡ ሠረጸት ፡ ለይእቲ ፡ ቈጽል ፡ ዘተከድነ ፡ ባቲ ፡ አዳም ፡ አይበሳ ፡ በቃሉ ፡ እስመ፡ረከቦ፡ንዱየ፡ወወሀቦ፡ብርሃነ፡ንጹሐ፡ ወውእቱ ፡ ብርሃን ፡ እኑም ፡ እማይ ፡ ወእመ ንፈስ፡ቅዱስ።

፶፫፤ አይበሰ፡ቈጽለ፡በለስ፡ወወሀቦ፡መድኃኒተ፡ ነፍስ።

፶፬፤ እሄሊ ፡ እፎ ፡ ተባልሐ ፡ ዘአዕቀጸቶ ፡ ከይሲ ፡ በውስተ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘኮነ ፡ ሕያወ ፡ ከመ ፡ መላእክት ፡ በአልባሰ ፡ ፍሥሓ ፡ ወሐሤት፡ወበጽድቅ።

፶፭፤ ወባሕቱ፡አ፡ፍቁራንየ፡ንትመየጥ፡ኀበ፡ዘአቅ ደምነ፡ዘክሮ፡ቀዳሚ።

፶፮፤ ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ወጸቢሖ፡እንዘ፡የዐርግ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ሀገረ ፡ ርኅበ ፡ ጸቢሖ ፡ እምድኅረ፡ሌሊት፡መጽአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ በጽባሕ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያንሥእ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ከመ ፡ ጎሕ ፡ ድልወ ፡ ንረክቦ።

፶፯፤ ወበጽባሕ ፡ መጽአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ።

ጸቢሖ፡እምድኅረ፡ልብሰቱ፡ጽልመተ፡ሞት፡ በፈቃዱ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሐር ፡ አጽንዖሙ፡ወሐሩ።

፶፰፤ ወአብርሀ ፡ ፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡ ውስተ ፡ አልባበ ፡ ሰብእ፡ዘሠረቀ፡ጽልመት።

፶፱፤ ጸቢሖ ፡ ሶበ ፡ ሙቀተ ፡ መለኮት ፡ መጽአ ፡ ኀበ ፡ ነፍሳተ ፡ ሰብእ ፡ ዘአሞቆሙ ፡ ሰይጣን ፡ ወአመ ከሮሙ ፤ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መኑ ፡ ይትቃወሞ፡ለቊሩ።

፷፤ እስመ ፡ ቊረ ፡ ኃጢአት ፡ ዘሰይጣን ፡ እሞተ ፡ ነፍሳተ ፡ ሰብእ ፡ በእንቲአሁ ፤ ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ፍትን፡ልብየ፡ወኵልያትየ።

፷፩፤ እስመ፡ኮኑ፡በዐሊዎቶሙ፡ውስተ፡ኃጕል።

፷፪፤ ወበእንተ፡ውእቱ፡ተጋብኡ፡ኵሎሙ፡ነቢያት፡ በውስተ ፡ ጸሎቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ እግዚእ ፡ ሚጥ ፡ ፄዋነ ፡ ከመ ፡ ውኂዝ ፡ ውስተ ፡ አዜብ ፤ ወከመ፡ነፋስ፡አዜብ፡ዘይነፍኅ፡ምስለ፡ውዕየት፤ ወይመስዎሙ ፡ ለማያት ፡ እለ፡ ረግዑ ፡ ወይመ ይጠን፡ኀበ፡ዘቀዳሚ፡ፍጥረቶን።

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት፡ነግህ።

ዛፍ፡መጥቶ፡አዳም፡ዕርቃኑን፡የሸፈነባትን፡ ቅጠል ፡ በቃሉ ፡ አደረቃት ፤ አዳምን ፡ ድኃ ፡ ሁኖ ፡ ስለ ፡ አገኘው ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ የብርሃ ንንም ፡ ልብስ ፡ ሰጠው ፤ ይኸውም ፡ ብርሃን ፡ ከውኃና፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡የተሠራ፡ነው።

፶፫፤ የበለስን፡ቅጠል፡አድርቆ፡የነፍሱን፡ድኅነት፡ ሰጠው።

፶፬፤ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ባለባት ፡ ገነት ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ የተድላ ፡ ደስታ ፡ ልብስ ፡ ተጐናጽፎ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ሕያው ፡ ሁኖ ፡ ሲኖር ፡ ከይሲ ፡ ያሳተኘው፡አዳም፡እንዴት፡እንደ፡ዳነ፡አስባለሁ።

፶፭፤ ወዳጆቼ፡ሆይ፡አስቀድመን፡ወደ፡ተናገርነው፡ ነገር፡እንመለስ።

፶፮፤ የከበረ ፡ ወንጌል ፡ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሲወጣ ፡ ተራበ ፡ አለ ፤ ሌሊቱ ፡ አልፎ ፡ ሲነጋ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ መጣ ፤ ዓለምንም ፡ ሊአነሣው ፡ ወደደ ፤ ነቢይ ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እናገኘዋለን ፡ እንዳለ።

፶፯፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በነግህ ፡ መጣ።

ዓለም፡ጨለመ፡ሞትን፡ከለበሰ፡በኋላ፡በነጋ፡ ጊዜ ፡ በፈቃዱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የጌትነቱ ፡ ብርሃን፡አጸናቸው፤በዚያው፡ጸኑ።

፶፰፤ ጨለማ፡ባደረበት፡በሰው፡ልቡና፡ዕውነተኛ፡ ብርሃን፡በራ።

፶፱፤ ሰይጣን ፡ ወደፈተናቸውና ፡ ወደለያቸው ፡ የሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ነግቶ ፡ የመለኮት ፡ ሙቀት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ነቢይ ፡ ዳዊት ፡ ቅዝቃዜውን ፡ ማን፡ይቃወመዋል፡እንዳለ።

፷፤ ከሰይጣን ፡ የሚገኝ ፡ የኃጢአት ፡ ቅዝቃዜ ፡ የሰዎችን፡ነፍሳት፡ሊይቶአልና፡ስለዚህም፡ነቢይ፡ ውስጣዊ፡ልቡናዬንና፡ኵላሊቴን፡ፈትን፡አለ።

፷፩፤ እነዚያ፡በክዳታቸው፡ጠፍተዋልና።

፷፪፤ ስለዚህም ፡ ነቢያት ፡ ሁሉም ፡ ተሰ ብስበው ፡ አቤቱ ፡ ምርኮአችንን ፡ መልስ ፡ እያሉ ፡ ጸለዩ ፤ ከአዜብም ፡ ከሙቀት ፡ ጋራ ፡ እንደሚነፍስ ፡ ነፋስ ፡ በረዶ ፡ የሆነውንም ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡ ቀደመ፡ ፍጥረቱ ፡ እንደ ሚመልስ።

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፫፤ ከማሁኬ ፡ ንሕነኒ ፡ እለ ፡ ነበርነ ፡ መዊተነ ፡ በጌጋየ ፡ ሰይጣን ፤ መጽአ ፡ ኀቤነ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ነፋስ ፡ አዜብ ፡ ወሜጠነ ፡ ኀበ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ፍጥረትነ ፡ ዘኢ.ት መውት።

፳፬፤ ወዝ ፡ ዋዕይ ፡ ዘዘከርነ ፡ በእንተ ፡ አዜብ ፡ ወመርዓት ፡ ክርስቶስኒ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውስተ ፡ ጥበበ ፡ ሰሎሞን ፡ ዛ ፡ ይእቲ ፡ መኃልየ ፡ መሓልይ ፡ ተንሥሥ ፡ ወትብል ፡ ተንሥእ ፡ ሰሜን ፡ ወነዐ ፡ ደቡብ ፡ ንፋኅ፡ገነትየ፡ለየኀዝ፡አፈዋተ፡ዚአየ።

፳፭፤ ወጸቢሖ፡ቦአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡እሮ፡ሠናይ፡ ውእቱ፡ዘይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ከመ፡ውእቱ፡ መጽአ።

፳፮፤ ወገቦንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዜናሁ ፡ ለአዳም ፡ ዘወድቀ ፡ እምገነት፡ወመጽአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኀበ፡ውእቱ፡ መካን፡እንተ፡ወድቀ፡ውስቴቱ፡ኀበ፡ሀገር።

፳፯፤ ወሶበ ፡ ሰማዕከ ፡ አ ፡ ፍቁር ፡ ሀገረ ፡ ኢት ርአይ ፡ ኀበ ፡ መትሕት ፡ አላ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ልዕልት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ማኅደረ ፡ ሰማያ ውያን።

፳፰፤ በከመ፡ይቤ፡ጳውሎስ፡ሐዋርያ፡እስመ፡ማኅ ደርክሙ፡ይእቲ፡ውስተ፡ሰማያት።

፳፱፤ ወጸቢሖ ፡ ቦአ ፡ ሀገረ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወርኀበ ፤ ዘርኀበሰ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ መብልዐ ፡ ሰብእ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒተ ፡ ሰብእ፤

፴፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ለሊሁ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ ሊተሰ ፡ መብልዕየ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ፈቃዶ ፡ ለአቡየ ፡ ዘፈነወኒ ፡ ከመ ፡ ትእመኑ ፡ አንትሙ ፡ በዘፈነወኒ ፡ ከመ ፡ ትእመኑ ፡ አንትሙ፡ በዘፈነወኒ፤እስመ፡ዘየአምን፡ቦቱ፡ ኢይመውት፡ለዓለም፡ለዝሉፉ።

፴፩፤ ወጸቢሖ ፡ ቦአ ፡ ሀገረ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወርኀበ ፡ ወርእያ ፡ ለዕፀ ፡ በለስ ፡ ወበጽሐ፡ኀቤሃ።

፴፪፤ ሠናይኬ ፡ ውእቱ ፡ ዘበጽሐ ፡ ኀቤሃ ፡ እስመ ፡ ለእመ ፡ ተዓደዋ ፡ እምኮነት ፡ ዛቲ ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ማኅደረ፡ከይሲ፡ዘኢይመውት።

፴፫፤ ወባሕቱ፡መጽአ፡ኀበ፡ዛቲ፡ዕፀ፡በለስ፡ገዘማ፡ ወአሞታ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት፡ነግሀ።

፳፫፤ እንደዚሁም ፡ ሰይጣን ፡ ባመጣው ፡ በደል፡ ሁላችንም ፡ ሙታኖች ፡ ሁነን ፡ ሳለን ፡ እንደ፡ አዜብ ፡ ነፋስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መጥቶ፡ ወደማትሞተው ፡ ወደ ፡ ቀደመችው ፡ ፍጥረ ታችን፡መለሰን።

፳፬፤ አስቀድመን ፡ ያስታወስነው ፡ ይህ ፡ ሙቀት፡ ስለ ፡ አዜብ ፡ ሲሆን ፡ የክርስቶስ ፡ ሙሽራ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፤ ሰሎሞን ፡ የምስጋና፡ ምስጋና ፡ በተባለች ፡ መጽሐፉ ፡ ሰሜናዊ፡ ነፋስ፡ተነሣ፤ደቡባዊ፡ነፋስም፡ና፡ለተክሌ፡ ቦታ፡ነፋስ፡ሽቱዬ፡ይፍሰስ፡ትላለች።

፳፭፤ ሲነጋ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡መጣ፤የከበረ፡ወንጌል፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሲናገር ፡ ምንኛ፡ መልካም፡ነው።

፳፮፤ ከገነት፡የተሰደደ፡የአዳም፡ነገሩ፡ይህ፡ነው፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ አዳም ፡ ወደ ፡ ወደቀበት፡ ቦታ፡ወደዚያ፡አገር፡መጣ።

፳፯፤ ወዳጅ፡ወንድም፡ሆይ፡ሀገር፡ሲል፡በሰማ ጊዜ፡ምድራዊት፡እንደሆነች፡አታስብ፤የ ማያውያን ፡ ማደሪያ ፡ ኢየሩሳሌም፡ ሰማያዊት፡እንደሆነች፡እንጂ።

፳፰፤ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መኖሪያችሁ፡ ሰማያዊት፡ሀገር፡ናት፡እንዳለ።

፳፱፤ በነጋ፡ጊዜ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወደ፡ ሀገር፡ሲገባ፡ተራበ፤መራቡም፡ሰው፡ስለሚ በላው ፡ መብል ፡ አይደለም ፤ ስለ ፡ ሰው፡ ድኅነት፡ነው፡እንጂ።

፴፤ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ የኔስ፡ መብል ፡ የላከኝን ፡ ያባቴን ፡ ፈቃድ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ እናንተም ፡ በላከኝ፡ በአባቴ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ እ ዳለ ፡ ያመነበት ፡ ለዘላለሙ ፡ አይሞ ትምና።

፴፩፤ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ገብቶ፡ ተራበ፤የበለስንም፡ዛፍ፡አይቶ፡ወደእርሷ ሄደ።

፴፪፤ ወደርሷም ፡ መሄዱ ፡ መልካም ፡ ነው፡ አልፎዋት፡ሂዶ፡ቢሆን፡ለማይሞት፡ከይሲ፡ ዲያብሎስ፡ማደሪያ፡ሁና፡በኖረች፡ነበርና።

፴፫፤ ነገር፡ግን፡ወደዚያች፡የበለስ፡ዛፍ፡መጥቶ፡ ፈጽሞ፡አጠፋት።

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፸፬፤ በኀበ ፡ ዛቲ ፡ ዕፀ ፡ ርእዮ ፡ ለናትናኤል ፡ ወይቤሎ፡እግዚእነ፡እምቅድመ፡ይጸውዕከ፡ ፊልጶስ፡ርኢኩከ፡በታሕተ፡ዕፀ፡በለስ።

፸፭፤ ወለዛቲ ፡ ዕፅ ፡ ዘከራ ፡ ዕንባቆም ፡ ነቢይ ፡ ኢየዐርግ ፡ ኀበ ፡ አሕዛብ ፡ ካልአን ፡ እስመ ፡ በለስኒ፡ኢትፈሪ።

፸፮፤ ወላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ዐርገ ፡ ዘኬዎስ ፡ ወርእዮ፡ለእግዚእነ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ይቤሎ፡ እግዚእነ ፡ ረድ ፡ ፍጡነ ። ሠናይኬ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቤ ፡ ወንጌል ፤ ሠናይ ፡ ይእቲ ፡ ለርእይ ፡ በለስ።

፸፯፤ ወባሕቱ፡ታርኢ፡ኵሎ፡ለዘዐርገ፡ውስቴታ፡ ዘኬዎስ።

፸፰፤ ወዛቲኬ፡ትእምርት፡ከመ፡ፍኖት፡ስፍሕት፡ ወርሕብት፡ወሙፋር፡ይእቲ፡ዘይትወለድ፡ እምኔሃ፡እከይ፡ወኃጢአት።

፸፱፤ መጽአ ፡ እግዚእነ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ ፍኖት ፡ ርሕብት፡ወስፍሕት፡ወአህጐላ።

፹፤ እስመ፡ቈጽለ፡በለስ፡ስፍሕት፡ወሠናይት፡ ከማሁኬ ፡ ለኃጢአትኒ ፡ ፍኖታ ፡ ርሕብት ፡ ወስፍሕት፡ዘትወስድ፡ውስተ፡ኃጕል።

፹፩፤ እስመ፡ፍሬ፡በለስ፡ጥዑም፡በጊዜ፡በሊዕ፡ ወሐይክ።

፹፪፤ ከማሁኬ ፡ ኀጢአትኒ ፡ ጥዕምት ፡ በጊዜ ፡ ሐይክ፡ወታጸሙ፡እምድኅረ፡በሊዕ።

፹፫፤ ጐየይ፡እምዛቲ፡ሕይክት፡እስመ፡ጥዕምት፡ ይእቲ ፡ በጊዜ ፡ ሐይክ ፡ ወመራር ፡ ይእቲ ፡ ድኅረ፡ገቢሮታ።

፹፬፤ ወይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ ጥበበ ፡ ሰሎሞን ፡ እስመ ፡ መዐር፡ያንጸፈጽፍ፡እምከናፍረ፡ብእሲት፡ዘማ፡ ወእምዝ፡ይበልኅ፡እመላጺ፡ዘክልኤ፡አፉሁ።

፹፭፤ ወሶበ ፡ ጥዕምከ ፡ ውእተ ፡ መዐረ ፡ እምኔሃ ፡ ወስተ ፡ አፉከ ፡ ወጕርዔከ ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ትረክብ፡ዕፁበ፡ወመሪረ፡ወማህጐሌ።

፹፮፤ ብእሲት፡ዘማ፡ዕብስት፡ይእቲ፡እስመ፡ትት ናገረከ፡ነገረ፡ዘይጥዕም፡እመዐር፡ወሶከር፡ ወፍጡነ ፡ ይውኅዝ ፡ ለከ ፡ እምቃላ ፡ መሪር ፡ ሞት።

፹፯፤ ከማሁኬ፡ኮነት፡አርዌ፡ምድርኒ፡ጥዕምተ፡ ንባብ፡በጕሕሉታሰ፡መራር።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፸፬፤ በዚችም ፡ የበለስ ፡ ዕንጨት ፡ ዘንድ ፡ ናትና ኤልን ፡ አየውና ፡ ጌታችን ፡ ፊልጶስ ፡ ሳይጠራህ፡ከበለስ፡በታች፡አየሁህ፡አለው።

፸፭፤ ይችንም ፡ ዕፀ ፡ በለስ ፡ ነቢይ ፡ ዕንባቆም ፡ ወደሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ አልወጣም ፤ በለስም ፡ አታፈራምና፡ብሎ፡አስታውሷታል።

፸፮፤ በዚችም ፡ ዕፅ ፡ ላይ ፡ ዘኬዎስ ፡ ወጥቶ ፡ ጌታችንን ፡ አየው ፤ ስለዚህም ፡ ጌታችን ፡ ፈጥነህ ፡ ውረድ አለው ። ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ መልካም ፡ ብሎአል ፤ በለስ ፡ ለማየት ፡ መልካም፡ናት።

፸፯፤ ነገር ፡ ግን ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ለወጣ ፤ ለዘኬዎስ፡ ሁሉን፡ታሳየዋለች።

፸፰፤ እርሷም ፡ የክፋትና ፡ የኀጢአት ፡ መገኛ ፡ መሠማሪያ ፡ ለምትሆን ፡ ለሰፊ ፡ መንገድ ፡ (ፈቃደ፡ሥጋ)፡ምልክት፡ናት።

፸፱፤ ጌታችንም፡ወደዚች፡ሰፊ፡መንገድ፡መጥቶ፡ አጠፋት።

፹፤ የበለስ፡ቅጠል፡ሰፊ፡ደስ፡የምታሰኝ፡ናት፤ እንዲሁም ፡ የኃጢአት ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ጥፋት፡የምትወስድ፡ሰፊ፡በር፡ናትና።

፹፩፤ የበለስ፡ፍሬ፡በመብላትና፡በማላመጥ፡ጊዜ፡ ጣፋጭ፡ነውና።

፹፪፤ እንዲሁ፡ኀጢአት፡ሲሠርዋት፡ደስ፡ታሰኛለች፤ ከሠርዋት፡በኋላ፡ግን፡መከራ፡ታመጣለች።

፹፫፤ በሚሠሩዋት ፡ ጊዜ ፡ ጣፋጭ ፡ ከሠሩዋት ፡ በኋላ ፡ መራር ፡ ናትና ፡ እርሷን ፡ ከመሥራት ፡ ሽሽ።

፹፬፤ የሰሎሞን፡የጥበብ፡መጽሐፍ፡ከአመንዝራ፡ ሴት፡አፍ፡ማር፡ይፈሳል፤ከዚያ፡ወዲያ፡ግን፡ ሁለት፡አፍ፡ካለው፡ምላጭ፡ይሰላል፡አለ።

፹፭፤ ያንንም ፡ ማር ፡ በቀመስከ ፡ ጊዜ ፡ ለአፍህና ፡ ለጕሮሮህ፡ጣፋጭ፡ሁኖ፡ሳለ፡ከዚያ፡በኋላ፡ እጅግ፡የሚጎዳ፡መራረ፡ሁኖ፡ታገኘዋለህ።

፹፮፤ አመንዝራ፡ሴትም፡አንደበተ፡ለስላሳ፡ናት፤ ከማር ፡ ከስኳር ፡ የሚጣፍጥ ፡ ነገርን ፡ ትናገር ሃለች፤ወዲያውኑ፡መራራ፡ሞትም፡ከእርሷ፡ ያገኝሃል።

፹፯፤ እንዲሁም ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ በአነጋገርዋ ፡ የጣፈ ጠች፡ናት።በሽንገላዋ፡ግን፡መራራ፡ሆነች።

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፶፰፤ ጥዑም፡ውእቱ፡መብልዕ፡ወመሪር፡ውእቱ፡ወዲቅ።

፶፱፤ ጐየይኬ፡እምዛቲ፡ብእሲት፡ዘማ፡ዘትትና ገረከ፡በበጥዑም፡ወትቀትለከ፡በሕምዘ፡ኃጕል።

፷፤ ጕየይኬ፡እምሕማም፡ዘውእቱ፡ኃጢአት፡በከመ፡ጐየ፡ኤልያስ፡እምገጸ፡ኤልዛቤል፡ዘማ።

፷፩፤ መጽአ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እምሰማይ፡በእንተ፡ርኅበቶሙ፡ለሰብእ፡እም ሕይወት፡ረከበ፡ፍኖተ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ስፉሐ፡ወርሒበ፡ወይእቲ፡ሠናይት።

፷፪፤ ወመጽአ፡ኀቤሃ፡ወረከባ፡ብቍልተ፡ወቍጽልተ፡ወሥርጽተ፡እንተ፡ኮነት፡ይእቲ፡ፍኖተ፡ኃጢአት፤ወአልቦ፡ውስቴታ፡ፍሬ፡ሞት፡ወኢኮነ፡ፍሬ፡በመዋዕላ፡በከመ፡ይቤ፡ወንጌል፡ወአልቦ፡ውስቴታ፡ፍሬ፡እስመ፡ኢኮነ፡መዋዕለ፡ፍሬ፡አሚሃ።

፷፫፤ ወበእንተዝ፡እፎኬ፡ትክል፡ዛቲ፡ዕፅ፡ተሀብ፡ፍሬ፡ሞት።

፷፬፤ ወእግዚእነ፡መድኅን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መጽአ፡ውስተ፡ዓለም፡ለአንሥኦ፡በእንተ፡ዓለም፡ከመ፡ይቀድሶሙ።

፷፭፤ ወበእንተ፡ውእቱኬ፡ኮነት፡ዘአልባቲ፡ፍሬ፡እስመ፡ሞት፡ቀነየ፡በከመ፡ይቤ፡ጳውሎስ፡ሐዋርያ፡እምአዳም፡እስከ፡ሙሴ፡ቀነዮሙ፡ሞት።

፷፮፤ ወሙሴሰ፡ሕግ፡ውእቱ፡ወስምዐ፡ኮነ፡በእንተ፡ውእቱ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡ቦሙ፡ሙሴ፡ወነቢያት፡ይስምዑ፡እምኔሆሙ።

፷፯፤ ወበእንተ፡ዝ፡መጽአ፡ኀቤሃ፡እግዚእነ፡ክርስቶስ፡እንዘ፡ይብል፡ኢይኩን፡ፍሬ፡እም ውስቴትኪ፡ለዓለም።

፷፰፤ እስመ፡ዛቲ፡ዕፅ፡እምቅድመ፡ምጽአተ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ኮነት፡እንከ፡ዘአፍረየት፡ፍሬ፡ሞት፤መጽአ፡እግዚእነ፡ዘውእቱ፡መንሥኢ፡ወይቤላ፡ኢይኩን፡ፍሬ፡በውስቴትኪ፡ለዓለም።

፷፱፤ ወእምዝ፡የብሰት፡ይእቲ፡ዕፅ፡ወተፈጸመ፡ዘይቤ፡መጽሐፍ፡ተሞአ፡ሞት፤ወአይቴ፡እንከ፡ሙአትከ፡ሞት፡ወአይቴ፡እንከ፡ቀኖትከ፡ሲኦል።

## ሰኞ፡ቀን፡በ፩፡ሰዓት።

፶፰፤ መብል፡ጣፋጭ፡ነው፤መውደቅ፡ግን፡መራራ፡ነው።

፶፱፤ በሚጣፍጥ፡ቃል፡ተናግራህ፡በሚአጠፋ መርዝ፡ከምትገድልህ፡ከዚያች፡አመንዝራ ሴት፡ሽሽ።

፷፤ ከበሽታ፡ሽሽ፤ይኸውም፡ኃጢአት፡ነው ኤልያስ፡ከአመንዝራይቱ፡ኤልዛቤል፡ፊት እንደሸሸ።

፷፩፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሕይወትን ስለተራቡ፡ሰዎች፡ከሰማይ፡ወርዶ፡ሰው፡ሁኖ መጣ፤የዚህንም፡ዓለም፡መንገድ፡እጅግ፡ሰፊ ሁኖ፡ለሰው፡መልካም፡መስሎ፡አገኘው።

፷፪፤ ወደርሷም፡መጥቶ፡ቅርንጫፉዋ፡ሰፍቶ ለምልማ፡የኃጢአት፡መንገድ፡ሁና፡አገኛት የሞት፡ፍሬ፡ግን፡ገና፡አላፈራችም፡ነበር ወራቱ፡የፍሬ፡አይደለምና፡በወንጌል፡እንደ ተባለ፡ፍሬ፡የለባትም፤ያን፡ጊዜ፡የፍሬ ወራት፡ስላልሆነ።

፷፫፤ ስለዚህ፡ይቺ፡ዕፅ፡የሞተ፡ፍሬ፡ትሰጥ፡ዘንድ እንዴት፡ትችላለች።

፷፬፤ አዳኝ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሰዎችን ለማንሣትና፡ይቀድሳቸው፡ዘንድ፡ወደ ዓለም፡መጣ።

፷፭፤ ስለዚህም፡ፍሬ፡የሌላት፡ሆነች፤ሐዋርያ ጳውሎስ፡ከአዳም፡እስከሙሴ፡ሞት፡ሠለጠነ ባቸው፡እንዳለ፡ሞት፡ሰልጥኖባቸዋልና።

፷፮፤ ሙሴም፡ማለት፡ሕግ፡ነው፤ስለዚህም፡ቅዱስ ወንጌል፡ምስክር፡ሆነ፤ሙሴና፡ነቢያት አሏቸው፡ከእርሳቸው፡ይስሙ፡በማለቱ።

፷፯፤ ስለዚህም፡በውስጥሽ፡ለዘላለሙ፡ፍሬ፡አይ ኝብሽ፡እያለ፡ጌታችን፡ክርስቶስ፡ወደርሷ መጣ።

፷፰፤ ይቺም፡ዕፅ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ ከመምጣቱ፡አስቀድሞ፡የሞት፡ፍሬ አፍርታ፡ነበር፤ጌታችንም፡መጣ፤እርሱም የሚአነሣን፡ነው፤እንጨቷንም፡ለዘላለም ፍሬ፡አይገኝብሽ፡አላት።

፷፱፤ ያች፡እንጨት፡ወዲያውኑ፡ደረቀች መጽሐፍ፡ሞት፡ድል፡ተነሣ፤ሞት ሥልጣንህ፡የት፡አለ? መቃብርስ መውጊያህ፡ወዴት፡ነው፤ያለው፡ተፈጸመ።

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፡ ወይቤ ፡ ወንጌላዊ ፡ እስመ ፡ ክረምት ፡ ውእቱ ፡ መዋዕል ፡ በጊዜ ፡ አቀጽለት ፡ ዕፅ ፡ ዘበለስ ፡ ዘበቈለ ፡ ውስቴታ ፡ ኃጢአተ ፡ ሰይጣን፡ ዘኮነ ፡ ኤልያስ ፡ ነገሮሙ ፡ ከመ ፡ ክረምት፡ውእቱ።

፲፩፡ እስመ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮኑ ፡ እንከ ፡ መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ አድከምዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ በተቀንዮ ፡ ለአማልክት።

፲፪፡ ወበቅተለተ ፡ ሰብእ ፡ ለበሊዕ ፡ ወለሰትይ ፡ ወበገቢረ፡ርኩስ።

፲፫፡ ወእምዝ፡መጽአ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መድኃኒነ ፡ ወሰላምነ ፡ ለገሙመ ፡ መናፍስተ ፡ ርኩሳነ፡ጸላኢያነ፡ሠናያት፡እለ፡የሀውኩ፡ዘንተ፡ዓለመ፡በአፍቅሮ፡ትፍግዕታት፡በበሊዖቱ፡ወበሰትዮቱ፤ወበተሰጥሞቱ፡ውስተ፡ባሕረ፡ሀጕል፡መሪር፡ዘያጠፍእ፡በእበድ።

፲፬፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ወአጥፍአ ፡ ማዕበላቲሁ ፡ ወሁከቶ ፡ አህድአ ፡ ወአይበሳ ፡ ለዕፀ ፡ በለስ ፤ ወተከለ ፡ ለነ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ዘበቈለ ፡ ለነ ፡ በሃይማኖት ፡ ወበሕይወት ፡ ብሩህ።

፲፭፡ ዝንቱ ፡ መስቀል ፡ ስፉሕ ፡ ወስቡሕ ፡ እንተ ፡ በምድር ፡ ሥረዊሁ ፡ ወበሰማይ ፡ አዕጹቂሁ ፡ እንተ፡ኢይትነገፍ፡ቈጽሉ፡እንተ፡ኢኮነ፡ጽጌሁ፡ለሀጕል፡ወፍሬሁኒ፡ዘኢኮነ፡ለመዊት።

፲፮፡ ዝንቱ፡ዘይቤ፡ዳዊት፡ነቢይ፡በእንቲአሁ፡ዕፅ፡እንተ፡ትክልት፡ኀበ፡ሙሓዘ፡ማይ፡ዘትሁብ፡ፍሬሃ፡በበጊዜሃ፡ወቈጽላኒ፡ኢይትነገፍ።

፲፯፡ ለዝንቱ፡ዕፅ፡ትቤ፡ጥበብ፡በእንቲአሁ፡ዕፀ፡ሕይወት፡ውእቱ፡ለኵሉ፡ዘየአምን፡ቦቱ።

፲፰፡ ይቤ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ዕፅ፡በጊዜ፡ርእዮ፡በአዕይንቲሁ፡በኀበ፡አይሁድ፡እንዘ፡ይብሎሙ፡ትብሉ፡ንዑ፡ንደይ፡ዕፀ፡ውስተ ፡ መብልዑ ፡ ወንሥዐሮ ፡ እምድረ ፡ ሕያዋን።

፲፱፡ ወዕፀ፡ሕይወት፡ውእቱ፡ኀብስት፡ሥጋሁ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፲፡ ወንጌላዊ ፡ እንጨቲቱ ፡ የለመለመችበት ፡ ጊዜው ፡ ክረምት ፡ ነው ፡ አለ ፤ ኤልያስም ፡ ክረምት ፡ እንደሆነ ፡ የነገራቸው ፡ ሰይጣን ፡ ያመጣው፡ኀጢአት፡በውስጥዋ፡ስለ፡በቀለ፡ነው፡አለ።

፲፩፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ምጣቱ ፡ በፊት ፡ ለጣዖታት ፡ በማስገዛት ፡ መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ ሰዎችን ፡ አድክመ ዋቸው፡ነበርና።

፲፪፡ ሰውን፡በመግደል፡በመብል፡በመጠጥ፡በመ ቀማጠል፡የረከሰ፡ኃጢአትን፡በመሥራት።

፲፫፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ሰላማችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መጥቶ፡የበጎ፡ሥራ፡ጠላቶች፡የሆኑና፡በመብል፡በመጠጡ፡በመቀማጠሉ ፡ በማስወደድ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ባሕር ፡ የሚአሰጥሙ ፡ ርኵሳን ፡ መናፍስትን ፡ አጠፋ።

፲፬፡ መጥቶም፡ፍትወታት፡እኩያትን፡ኃጣውዕ፡ርኩሳንን፡አጠፋ፤ሁከቱንም፡ጸጥ፡አደረገ፤ ዕፀ ፡ በለስንም ፡ አድርቆ ፡ ብሩህ ፡ በሆነ ፡ ሕይወት ፡ በሃይማኖት ፡ የበቀለውን ፡ ዕፀ ፡ መስቀልን፡ተከለልን፤

፲፭፡ ይህ ፡ የከበረ ፡ የተዘረጋ ፡ መስቀል ፡ ሥሩ ፡ በምድር፡ጫፉ፡በሰማይ፡ያለ፡ቅጠሉ፡የማይ ረግፍ ፡ አበባው ፡ ለጥፋት ፡ ፍሬው ፡ ለሞት ፡ ያልሆነ፡ነው።

፲፮፡ ይህ፡ነቢይ፡ዳዊት፡ስለርሱ፡ሲናገር፡በውኃ፡ዳር፡የተተከለ፡በየጊዜው፡ፍሬውን፡የሚሰጥ፡ቅጠሉም፡የማይረግፍ፡ያለው፡ነው።

፲፯፡ ይኸንንም ፡ ዕንጨት ፡ ጥበብ ፡ ስለርሱ ፡ ስትናገር ፡ ለሚአምንበት ፡ ሁሉ ፡ የሕይወት ፡ ዕፅ፡ነው፡አለች።

፲፰፡ ነቢይ ፡ ኤርምያስም ፡ ስለዚህ ፡ ዕፅ ፡ ተናገረ ፤ በአይሁድ፡ዘንድ፡በአየው፡ጊዜ፡ኑ፡በምግቡ፡ውስጥ ፡ ዕፅን ፡ እንጨምር ፤ ከሕያዋን፡ምድርም፡እናጥፋው፡ትላላችሁ፡ሲላቸው።

፲፱፡ በኅብስት ፡ የሚሰጥ ፡ የክርስቶስ ፤ ሥጋው ፤

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ለክርስቶስ፡እስመ፡እግዚእነ፡ውእቱ፡ነሥአ፡ኀብስተ፡ወይቤ፡ዝ፡ውእቱ፡ሥጋየ፡ዘይትፌተት፡በእንቲአክሙ፡ለሥርየተ፡ኃጢአት፡በላዕለ፡አቅርንተ፡መስቀል፡ወአውደቆሙ፡ለኀያላን፡እለ፡ይሰሩ፡በነፋሳት፡ወአስተዳለወ፡ለነ፡ፍኖተ፡ለኀበ፡መንግሥተ፡ሰማያት። | የሕይወት፡ዕፅ፡ይባላል፤ጌታችን፡እርሱ፡ኅብስቱን፡አንሥቶ፡ስለ፡እናንተ፡ለኃጢአት፡ማስተሥረያ፡በመስቀል፡ላይ፡የሚፈተተው፡ሥጋዬ፡ይህ፡ነው፤በነፋስ፡የሚበሩ፡ኃያላን፡አጋንንትን፡ያጠፋ፡የመንግሥተ፡ሰማያትን፡መንገድ፡ያዘጋጀልን። |
| ፻፲፡ ወገብረ፡ዘንተ፡ዕፀ፡ሰዋስወ፡ኀበ፡ሰማያት፡ለእለ፡የአምኑ፡ቦቱ። | ፻፲፡ ለሚያምኑበትም፡ይህን፡ዕፅ፡ወደ፡ሰማያት፡ለመውጣት፡መሰላል፡አደረገው። |
| ፻፲፩፡ ሶበ፡ሰማዕክሙ፡አ፡ፍቁራንየ፡ዘንተ፡ግብረ፡ዕጹበ፡ወመንክራተ፡ውእቱ፡ዕፀ፡መስቀል፡ዘሰፍሐ፡በላዕሌሁ፡ዘበአማን፡ዐጸደ፡ወይን፡ወኮነ፡ዝንቱ፡ዕፀ፡መስቀል፡ለሰይጣን፡ሞተ፡ወሀጕለ፡ወለነሰ፡ለእለ፡አመነ፡ዕፀ፡ሕይወትነ፡ወደምሳሴ፡አባስነ፡ወተከደነ፡ቦቱ፡ልብሰ፡ዕረፍት። | ፻፲፩፡ ወንድሞቼ፡ሆይ፡ይህን፡ዕፁብ፡ድንቅ፡የሆነ፡ሥራ፡በሰማችሁ፡ጊዜ፡ዕውነተኛው፡የወይን፡ተክል፡ክርስቶስ፡በላዩ፡የተዘረጋበት፡ይህ፡ዕ መስቀል፡እንደሆነ፡ዕወቁ፤እርሱም፡ለሰይጣን፡ሞትና፡ጥፋት፡ለእኛ፡ለአመነው፡የሕይወት፡ዕፅ፡በደላችንን፡የሚደመስስ፡የዕረፍት፡ልብስንም፡የተጐናጸፍንበት፡ነው፡ |
| ፻፲፪፡ ወይቤ፡ዜናዊ፡ምሥጢሩ፤ወውእቱ፡ሰሎሞን፡ጠቢብ፡ይብል፡በውስተ፡መሓልየ፡መሓልይ፡ታሕተ፡ጽላሎቱ፡ፈተውኩ፡ወነበርኩ። | ፻፲፪፡ ምሥጢሩንም፡የሚናገር፡ይህም፡ጥበበኛው፡ሰሎሞን፡ነው፤መሓልየ፡መሓልይ፡በተባለው፡መጽሐፍ፡ከጥላው፡በታች፡ማደርን፡ወደድሁ፡ይላል፡አለ። |
| ፻፲፫፡ ንብላዕ፡ጣዕመ፡ፍሬሁ፡በመዋዕሊነ፡ወፈተዋ፡ለዛቲ፡ሕይወት። | ፻፲፫፡ ጣፋጭ፡ፍሬውንም፡በዘመናችን፡እንመገ ይችንም፡ሕይወት፡ወደዳት። |
| ፻፲፬፡ ወዳዊት፡ነቢይ፡ይብል፡ወበጽላሎተ፡ክንፊክ፡ክድነኒ፡ከመ፡ይርሐቅ፡እምኔየ፡እኩይ። | ፻፲፬፡ ነቢይ፡ዳዊትም፡ክፉ፡ከእኔ፡ይርቅ፡ዘንድ በክንፈ፡ረድኤትህ፡ሠውረኝ፡አለ። |
| ፻፲፭፡ አ፡ዝ፡መንክር፡ዐቢይ፡ወዝንቱ፡ምሥጢር፡ሐዲስ፡እስመ፡ውሕዘት፡ፈልፈል፡እምዕፅ። | ፻፲፭፡ ወዮ፡ይህ፡ድንቅ፡ታላቅ፡ሥራ፡ነው ይህም፡ምሥጢር፡ሐዲስ፡ነው፤ከዚህ፡ዕ የሕይወት፡ምንጭ፡ይፈሳልና። |
| ፻፲፮፡ ወኮነ፡መስቀል፡ይሰቲ፡እምኔሃ፡በጊዜ፡ተረግዘ፡ገቦሁ፡ወወፅአ፡እምኔሁ፡ደም፡ወማይ። | ፻፲፮፡ ይህም፡መስቀል፡ጌታ፡ጎኑን፡ተወግቶ ውኃና፡ደም፡ከእርሱ፡በወጣ፡ጊዜ የሚጠጣ፡ሆነ። |
| ፻፲፯፡ ወደምሰ፡ልብሰ፡መስቀል፡ውእቱ፡ወማይኒ፡ዘውሕዘ፡እምኔሁ፡አስተርአየ፡በሥጋሁ፡ከመ፡ያፍሪ ለምእመናን፡ዘኢይመውት፡ፍሬ። | ፻፲፯፡ ደም፡ግን፡መስቀል፡የለበሰው፡ልብስ፡ነው ከጎኑ፡የፈሰሰው፡ውኃም፡ለምእመናን የማይጠፋ፡ፍሬ፡ያፈራ፡ዘንድ፡በሥጋው የታየው፡ነው። |
| ፻፲፰፡ ወበእንተዝ፡ይደሉ፡ለመስቀል፡ሰጊድ። | ፻፲፰፡ ስለዚህም፡ለመስቀል፡መስገድ፡ይገባል። |
| ፻፲፱፡ አ፡ዝንቱ፡ዕፅ፡ስቡሕ፡ብፁዓዊ፡ዘያከብርዎ፡ኵሎሙ፡ነገሥታት፡ወመሳፍንት፡ወመኳንንት። | ፻፲፱፡ ወዮ፡ይኸ፡የተመሰገነ፡የከበረ፡ዕፅ ነገሥታት፡መኳንንት፡መሳፍንት፡ሁሉም የሚአከብሩት፡ነው። |
| ፻፳፡ አ፡ዝንቱ፡ዕፅ፡ስቡሕ፡ዘውእቱ፡መድንኂ፡ | ፻፳፡ ወዮ፡ይኸ፡ዕፅ፡የሰውን፡ፍጥረት፡ሁሉ |

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ለኵሉ ፡ ፍጥረተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወማዕተብ ፡ ዘይገሥፆ ፡ እምኔሁ ፡ አጋንንት ፡ ወይደነግፅ ፡ እምኔሁ ፡ ርጉም ፡ ሰይጣን።

፻፳፩፤ ወመላእክት ፡ ይሴብሕዎ ፡ ወሰማዕት ፡ ይባርክዎ ፡ ወሐዋርያት ፡ ይዜንዉ ፡ ዕበዮ ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትሰረገዎ ፡ ዘተጸልበ ፡ ላዕሌሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወክሂል፡ ወዕበይ ፡ ወጽንዕ ፡ ወሰላም ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወእስከ፡ መዋዕል ፡ ደኃሪት ፡ አሜን ፡ ወአሜን።

፻፳፪፤ አ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘነሠተ ፡ ምክረ ፡ ሰቃልያን ፡ ወአስተጋብአ ፡ ማኅበረ ፡ መሐይምናን ፡ እመ ፡ ይነግሥ ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ መካን ፡ ይደምረነ ፡ አሜሃ ፡ ምስለ ፡ አግብርቲሁ ፡ ኄራን፡ንጹሐን፡ወቅዱሳን፡ለነ፡ለኃጥአን፡ወአባስያን፡በጸሎታ፡ለእግዝእትነ፡ማርያም፡እመ ፡ ብርሃን ፡ ይዕቀበነ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእ ፡ ዘመን ፡ ምስለ ፡ አቡነ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ኖላዌ ፡ አባግዕ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፪።

ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፡፴፫፡፳፱—፴፬።

፳፱፤ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ኤጲስቆጳስ ፡ ዘኑሲስ ፡ እኁሁ ፡ ለባስልዮስ ፡ ዐቢይ ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ በውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ፊልጵስዩስ።

፴፤ ኀልዩ ፡ ዘንተ ፡ በአልባቢክሙ ፡ ዘኮነ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘውእቱ ፡ አርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኮ ፡ ሐይዶ ፡ ዘኮነ ፡ ዕሩየ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላ ፡ አትሒቶ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ገብር ፡ ነሥአ ፡ አርአያ፡ገብር።

፴፩፤ ምንት፡ውእቱ፡ንዴት፡ዘይከውን፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡ፈድፋደ፡እምግብርናት፡ወባሕቱ፡ኢኮነ፡ሕፁፀ፡ቅድመ፡እግዚአብሔር፡ግሙራ፡

ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

የሚያጸና ፡ የተመሰገነ ፡ ክቡር ፡ መስቀል ፡ ነው። በርሱም ፡ በማማተብ ፡ አጋንንት ፡ የሚሸሹበት ፡ የተረገመ ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚደነግጥበት፡ነው።

፻፳፩፤ መላእክትም፡ያከብሩታል፤ሰማዕታት፡ያመሰግኑታል፤ሐዋርያትም፡ክብሩን፡ይናገራሉ፤ቤተ፡ክርስቲያንም፡ሽልማቷ፡ጌጧ፡ታደርገዋለች፤ እርሱም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ክርስቶስ ፡ የተሰቀለበት ፡ ነው ፤ ለርሱም ፡ ከሃሊነት ፡ ገናናነት ፡ ጽንዕ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ከባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ከአብ ፡ ከባሕርይ፡ሕይወቱ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ጋር፡ዛሬም፡ዘወትርም፡እስከ፡መጨረሻዪቱም፡ቀን፡ለዘላለሙ፡በእውነት፡ይሁን፡አሜን።

፻፳፪፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሰቃዮችን ፡ ምክር ፡ ያጠፋ ፡ የምእመናንንም ፡ ማኅበር ፡ የሰበሰበ ፡ በደብረ ፡ ጽዮንም ፡ በተለገጸ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከበጎ ፡ አገልጋዮቹ ፡ ንጹሐን ፡ ክቡራን ፡ ከሆኑት ፡ ጋራ ፡ እኛን ፡ በደለኞች ፡ ኃጢአተኞቹን ፡ አንድ ፡ ያድርገን ፤ የብርሃን ፡ እናት ፡ በምትሆን ፡ በእመቤታችን ፡ ማርያም፡ ጸሎት ፡ ይጠብቀን ፤ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ቢሆን ፡ በሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን፡ አባግዕ ፡ ከሚጠብቅ ፡ ከአባታችን ፡ ከአባ፡ሰላማ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡አሜን።

ክፍል፡፪።

የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፡፴፫፡፳፱—፴፬።

፳፱፤ የደገኛው ፡ የባስልዮስ ፡ ወንድም ፡ የሚሆን ፡ ክቡር ፡ አባት ፡ የኑሲስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ስለተናገረው ፡ ነገር፡እንዲህ፡አለ።

፴፤ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ የሆነበትን ፡ ሥራ ፡ በልቡናችሁ ፡ ዕወቁ ፤ ሽቶ ፡ ቀምቶ ፡ ከእግዚአብሔር፡ ጋራ ፡ የተካከለ ፡ አይደለም ፤ ራሱን ፡ ገዝቶ ፡ አድርጎ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ የተገኘ፡ባሕርይን፡ተዋሕዶ፡ነው፡እንጂ።

፴፩፤ ሥጋን ፡ ከመዋሐድ ፡ በቀር ፡ የበለጠ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ድኅነት ፡ አለ? ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ነገሥታትን ፡ መኳንንትን ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ሶበ ፡ ወረደ ፡ ውስተ ፡ ሱታፌ ፡ ዚአነ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወእግዚአ ፡ አጋዕዝት፡ወለብሰ፡አርአያ፡ገብር።

፴፪፤ ለዘይኴንና ፡ ለምድር ፡ ተቃፀብዎ ፡ ክቡራን ፡ ዘመድ ፡ ወእግዚአ ፡ ኵሉ ፤ ፍጥረት ፡ ኢረከበ ፡ መካነ ፡ ኀበ ፡ የኀድር ፡ ውስቴቱ ፡ አላ ፡ ሶበ ፡ ተወልደ ፡ በሥጋ ፡ አስከብዎ ፡ በጎለ፡እንስሳ።

፴፫፤ ወንጹሕ ፡ ዘኢይማስን ፡ ተወክፈ ፡ ሕላዌ ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው ፡ ዘይማስን ፡ ወተወክፈ ፡ ንዴተ ፡ ወኢያትረፈ ፡ እምንዴት ፡ እስከ ፡ በጽሐ፡ለሞት።

፴፬፤ ወለመኰንን ፡ አብጽሕዎ ፡ ውስተ ፡ ዐውደ ፡ ምኵናን ፡ ንጉሠ ፡ ኵሉ ፡ ኀይላት ፡ ሰማያት ፡ ገብአ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ኃጥአን ፡ ወሕይወት ፡ ጥዕመ ፡ ሞተ።

### ፊልክስ።

ምዕ፤፴፰፡፩–፬።

፩፤ ይቤ፡ቅዱስ፡ፊልክስ፡ሰማዕት፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ በውስተ ፡ ድርሳኑ ፡ ዘደረሰ ፡ በእንተ ፡ ትስብእት፡ወሃይማኖት።

፪፤ ንሕነሰ ፡ ናወግዝ ፡ እለ ፡ ይኄልዩ ፡ ሕማመ ፡ አው፡ሞተ፡ለመለኮት።

፫፤ እመቦ፡ዘይብል፡እስመ፡ክርስቶስ፡ዘተሰቅለ፡ ብእሲ ፡ ውእቱ ፡ እንበለ ፡ መለኮት ፡ ወኢየ አምን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አሐዱ ፡ አካል ፡ እምሠለስቱ ፡ አካላት ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወብእሲ፡ኀቡር፡ዘከመ፡ነአምን፡ንሕነ።

፬፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ኢየሐምም ፡ በመለኮት ፡ ወሕማም ፡ ዘሥጋ ፡ ተኈለቈ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡ ይቤሉ ፡ አበዊነ፡ንጹሐን።

ተግሣጽ ፡ ዘአቡነ ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡ የሃሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፩፤ አ ፡ አኀውየ ፡ ሶበ ፡ ፈቀድነ ፡ ናምሥጥ ፡ እምዐተ፡እግዚአብሔር፡ወንርከብ፡ምሕረተ፡ እምኀቤሁ።

፪፤ ንንበር ፡ በምሴት ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ባሕቲተነ ፡ እምድኅረ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ዕለት ፡ ወንሕትት ፡ ነፍሳቲነ ፡ ከመ ፡ ምንተ ፡ አቅረብነ፡ ለመልአክ፡ ዘየዓቅበነ ፡ ዘያቄርቦ ፡ ለእግዚአብሔር።

፫፤ ወሶበ ፡ ተፈጸመ ፡ ሌሊት ፡ ዓዲ ፡ ሶበ ፡ ይሠርቅ ፡ ብርሃን ፡ ንሕትት ፡ ነፍሳተነ ፡ ወናእምር ፡ ምንተ ፡ አቅረብነ ፡ ለመልአክ ፡ ዘየዓቅበነ ፡ ዘያዐርግ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

የሚገዛ፡ሲሆን፡እኛን፡ወደመምሰል፡በመጣ፡ ጊዜ፡የተገኘ፡ባሕርይንም፡በተዋሐደ፡ጊዜ፡ ከአብ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡አላነሰም።

፴፪፤ ምድርን፡የፈጠረ፡እርሱን፡በትውልድ፡እንበል ጣለን ፡ የሚሉ ፡ ሐና ፡ ቀያፋ ፡ ዘበቱበት ፤ ፍጥረትን፡ሁሉ፡የሚገዛ፡እርሱ፡የሚአርፍበት፡ ቦታ፡አላገኘም፤በሥጋ፡በተወለደ፡ጊዜ፡ላሞች፡ በሚአድሩበት፡በረት፡አስተኙት፡እንጂ።

፴፫፤ የማይለወጥ፡ንጹሕ፡አካላዊ፡ቃል፤የሚለወጥ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሰውን ፡ ሥራ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ እስከ፡ መለየትም፡ደርሶ፡ትሕትናን፡አብዝቶ፡ሠራ።

፴፬፤ በነፍስ፡በሥጋ፡የሚፈርድ፡እርሱን፡ይሙት፡ በቃ፡ወደሚፈረድበት፡አደባባይ፡አወጡት፡ ሊቃነ፡መላዕክትን፡ሁሉ፡ፈጥሮ፡የሚገዛ፡ እርሱ ፡ በኀጥአን ፡ እጅ ፡ ተያዘ ፤ ሕይወት፡ የሚሆን፡እርሱ፡ሞትን፡ቀመሰ።

### ፊልክስ።

ምዕ፤፴፰፡፩–፬።

፩፤ የከበረ ፡ ሰማዕት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፊልክስ፡ የምስጢረ ፡ ሥላሴን ፡ የምስጢረ ፡ ሥጋዌን፡ ነገር፡በተናገረበት፡ድርሳኑ፡እንዲህ፡አለ።

፪፤ እኛስ፡ሕማም፡ሞት፡ለመለኮት፡የባሕርዩ፡ እንደሆነ፡የሚአስቡትን፡እናውግዛለን።

፫፤ የተሰቀለው፡ክርስቶስ፡መለኮት፡የተለየው፡ ዕሩቅ፡ብእሲ፡ነው፡የሚል፡በተዋሕዶ፡ሰው፡ የሆነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከሦስቱ፡ አካላት፡አንዱ፡አካል፡እንደሆነ፡እኛ፡እንደ ምናምን፡የማያምን፡ቢኖር፡እናወግዘዋለን።

፬፤ እግዚአብሔር፡ቃል፡በመለኮት፡ሕማም፡ሳይ ኖርበት ፡ በሥጋ ፡ ታሚልና ፡ ንጹሓን ፡ አባቶ ቻችን ፡ እንደተናገሩ ፡ የሥጋ ፡ ሕማም ፡ ሞት፡ ለርሱ፡ተነግሮለታልና።

የፈጣሪው ፡ በረከት ፡ ለዘላለሙ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡ ይኑርና፡አባታችን፡አባ፡ሲኖዳ፡የተናገረው፡ ምክር፡እገሥናት፡ይህ፡ነው።

፩፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቁጣ፡ አምልጠን ፡ ምሕረትን ፡ ከእርሱ ፡ ማግኘት፡ ከወደድን።

፪፤ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቀኑ ፡ ተፈጽሞ ፡ ምሽት ፡ ሲሆን፡ ብቻችንን ፡ ሁነን ፡ ለሚጠብቀን ፡ መልአክ፡ እርሱ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡የሚአቀርበውን፡ እኛ፡ምን፡እንዳቀረብንለት፡ራሳችንን፡እንመ ርምር።

፫፤ ሌሊቱም ፡ ተፈጽሞ ፡ ደግሞ ፡ ብርሃን፡ ሲታይ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያሳ ርግልንን ፡ ለሚጠብቀን ፡ መልአክ ፡ ምን፡ እንዳቀረብንለት ፡ ራሳችንን ፡ እን መርምር።

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፩፤ ወኢትትዐቀፉ ፡ በዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ፡እንዘ፡ሕያውክሙ።

፪፤ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተባዕተ ፡ አው ፡ አንስተ ፡ አው ፡ ንዑሰ ፡ አው ፡ ዐቢየ ፡ ሶበ ፡ ተጠምቀ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገብረ ፡ ሎቱ ፡ መልአክ ፡ ዘየዐቅቦ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ወያዐርግ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ምግባራቲሁ ፡ መዐልተ ፡ ወሌሊተ።

፫፤ ወአኮ ፡ ዘኢየአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ምግባራቲነ ፡ ሐሰ ፡ አላ ፡ ውእቱሰ ፡ የአምር፡ኵሎ፡ምግባራቲነ፡እስመ፡ጽሑፍ፡በነቢይ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ እኪተ ፡ ወኄራተ።

፬፤ አላ ፡ ለመላእክትሰ ፡ ሤሞሙ ፡ ላእካነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ለዝንቱ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይረሱ ፡ ድኂነ።

፭፤ ዝንቱ፡ተግሣጽ፡ዘአቡነ፡አባ፡ሲኖዳ፡ተናገረ፡ምስሌነ፡በእንተ፡መድኃኒተ፡ነፍሳቲነ።

ስብሐት ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ምንተኑ ፡ አዓሥየኪ ፡ በል ። ወመቅድመ ፡ ተአምር፡ከመ፡ቀዳሚ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ድቅስት፡ድንግል፡በ፪ኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።ዘከመ፡ቀብዐት ፡ ቅብዐ ፡ በረከት ፡ ወፈወሰት ፡ እገሪሆሙ፡ለእንስሳ።

፮፤ ይቤ ፡ እንጦንዮስ ፡ ዘደብረ ፡ ቍስቋም ፡ እነግር፡ እሙነ ፡ ከመ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም፡ህየ፡ሀለወት፡እኮ፡ይእቲ፡ባሕቲታ፡ዳእሙ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ምስሌሃ ። ወመንበሩ ፡ ድልው ፡ ማዕከለ ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ ይሬእዩ ፡ ዘይደልዎሙ፡ወእለ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ ዘቍስቋም።

፯፤ ኀድጉሰ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘርእያ ፡ አላ ፡ ትወዕእ ፡ ለቀበላነ ፡ ይእቲ ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ፡ እንዘ ፡ ውስተ ፡ እደዊሃ ፡ ንዋይ ፡ ምስለ ፡ ቅብዕ፡

ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፩፤ በሕይወተ፡ሥጋ፡ሳላችሁ፡አንዱም፡አንዱ፡በዚህ፡ሁሉ፡አትሰነካከሉ።

፪፤ ወንድም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ታናሽም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በተጠመቀ ፡ ጊዜ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሥራውን ፡ የሚአሳርግ ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ የሚጠብቀው ፡ መልአክ ፡ ይታዘዝለታል።

፫፤ የምንሠራውን ፡ ሥራችንን ፡ እግዚአብሔር ፡ የማያውቅ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፤ እርሱስ ፡ ሥራችንን፡ሁሉ፡ያውቃል፤በነቢይ፡የእግዚአብሔር ፡ ዓይኖቹ ፡ ክፉም ፡ በጎም ፡ ወደሚሠሩ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እንዲህ ፡ ተጽፎአልና።

፬፤ ሁሉን፡የፈጠረ፡እግዚአብሔር፡ሕይወትን፡ይወርሱ፡ዘንድ፡ስለ፡አላቸው፡ሰዎች፡መላእክትን ፡ አገልጋዮች ፡ አድርጎ ፡ ሹሟቸዋል ፡ እንጂ።

፭፤ ይህ፡ምክር፡እዝናት፡አባታችን፡አባ፡ሲኖዳ፡ስለ፡ነፍሳችን፡ድኅነት፡የተናገረው፡ነው።

ልዩ ፡ ሦስት ፡ ለሆነ ፡ ለእርሱ ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይሁን፡አሜን።

ምንተኑ ፡ በል ፡ የተአምር ፡ መቅድም ፡ እንደ ቀድሞ፡በል።

ለመናኛ ፡ በረከቷ ፡ ይደርብንና ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ የሆነች ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ ክብርት፡ እመቤታችን ፡ የበረከት፡ቅባት ፡ ቀብታ ፡ የእንስሶችን ፡ እግሮቻቸውን ፡ እንደ፡ፈወሰች።

፮፤ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ በዚያ ፡ በደብረ ፡ ቍስቋም ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ የደብረ ፡ ቍስቋሙ፡ሰው ፡ እንጦንስ ፡ በእውነት ፡ እናገራለሁ ፤ እርስዋም ፡ ብቻዋን ፡ አልነበረችም ፤ ልጅዋ ፡ አምላክ ፡ከእርስዋ፡ጋር፡ነበረ፡እንጂ፤ወደዚህ፡ወደቍስቋም፡ቦታ፡ለመመጣጠና፡ማየት፡የሚገባቸው፡እስከ፡ማየት፡ድረስ፡ዙፋኑ፡በሕዝቡ፡መካከል፡ተዘጋጅቶ፡ነበር።

፯፤ ያየት ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ መሆኑንን ፡ ተዉትና ፡ የበረከት ፡ ሁሉ ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባረከው ፡ የበረከት ፡ ቅባት ፡

Scanned by CamScanner

## በ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ዘባረኮ ፡ በዐለ ፡ ኵሉ ፡ በረከታት ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ትፌቅድ፡ትቅብዐነ፡በረከት።

፫፤ ባሕቱ ፡ ትረክበነ ፡ ጽዑናነ ፡ ዲበ ፡ እንስሳ ፡ በተመክኖ ፡ ወበትዝኅርት ፡ ወበዕረፍተ፡ሥጋ።

፬፤ ወትሬእዮሙ ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ለእሉ ፡ እንስሳ ፡ ዘከመ ፡ ጻመዉ ፡ እምእለ ፡ ይቀሥፍዎሙ ፡ ወትቀብዮሙ ፡ እስከ ፡ እግሮሙ ፡ ለእንስሳ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ርኅርኅተ ፡ ልብ ፡ በቅብዐ ፡ በረከት፡ወትፌኑ፡በረከተ፡ዲቤሆሙ፡ለእንስሳ፡እለ፡አልቦሙ፡ልብ።

፭፤ እፎ ፡ መድምም ፡ አ ፡ እግዝእትየ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ ኂሩትኪ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ወኢመስፈርት ፡ ዘትገብሪ ፡ በላዕለ ፡ ኀጥአን ፡ ወዘማውያን፡ወበላዕለ፡ጽኑሳን፡ወሐካያን።

፮፤ ብፁዓን ፡ እለ ፡ አእመሩ ፡ ጣዕመኪ ፡ ወእለ ፡ ይነብሩ፡በፍቅርኪ፡እስመ፡ኮልነ፡ሕይወተ፡ነሐዩ፡በእንቲአኪ።

፯፤ ብፁዕ ፡ ኪያኪ ፡ ዘዴገነ ፡ በኵሉ ፡ ልቡ ፡ ወበኵሉ ፡ ኀይሉ ፡ ወበኵሉ ፡ ነፍሱ ፡ ከመ ፡ ይርከብ ፡ ረድኤተኪ ፡ በከመ ፡ አስተርአየ ፡ ተአምርኪ፡በላእለ፡እንስሳ።

ጸሎትኪ ፡ ወበረከትኪ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር ፡ ወመንክር ፡ ዘገብረ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘከመ ፡ አደንገፆሙ ፡ ለመወልጣን ፡ ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፰፤ ወሶበ ፡ ቦአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አኀዘሙ ፡ ፍርሃት ፡ ወረዓድ ፡ ለኵሎሙ፡ሰብአ፡ኢየሩሳሌም።

፱፤ ወተጋብኡ ፡ እምእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እለ ፡ ይሠይጡ ፡ ወይሣየጡ ፡ ወእለ ፡ ይነሥኡ ፡ አሥራተ።

፲፤ ወገብረ ፡ ጥብጣቤ ፡ ዘሐብል ፡ ወቀሠፎሙ ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

ያለበትን፡ዕቃ፡በእጀቿ፡ይዛ፡ልትቀባን፡ወዶ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ድንግል ፡ ልትቀበለን፡ ትወጣ፡ነበር፡እንጂ።

፫፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእንስሶች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን፡ ሥጋችንን፡ከድካም፡በማሳረፍ፡በኩራትና፡ በመመካት፡ታገኘናለች።

፬፤ የአምላክ ፡ እናት ፡ ድንግልም ፡ እንስሶቹን፡ በላያቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ከሚገርፉአቸው፡ ሰዎች፡እንደ፡ደከሙ፡ተመልክታ፡የልቡና፡ ርኅራኄ ፡ ያላት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም፡ የበረከቱን፡ቅባት፡እስከ፡እግራቸው፡ድረስ፡ እንስሶቹን፡ቀባቻቸው፤አእምሮ፡ለሌላቸው፡ እንስሶችም፡ኃይል፡ብርታትን፡ሰጠቻቸው፡

፭፤ እመቤቴ ፡ ማርያም ፡ ሆይ ፡ በኀጢአተኞችና፡ በአመንዝራዎች ፡ ላይ ፡ በችግረኞችና፡ በታካቾች፡ላይ፡ስፍር፡ቍጥር፡የሌለው፡የቸ ርነትሽ፡ዜና፡ምንኛ፡ድንቅ፡ነው።

፮፤ ጣዕምሽን ፡ ያወቁና ፡ በፍቅርሽም ፡ ጸንተው፡ የሚኖሩ ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፤ ሁላችንም፡ ስለአንቺ፡በሕይወት፡እንኖራለን።

፯፤ ረድኤትሽን፡ያገኝ፡ዘንድ፡በፍጹም፡ልቡናው፡ በፍፁም፡ኃይሉ፡ብፍፁም፡ዕውቀቱ፡አንቺን፡ የተከተለ፡ተአምራትሽ፡በእንስሶች፡ላይ፡እንደ ተገለጸ፡ያመነ፡የተመሰገነ፡ነው።

በረከትሽና፡ጸሎትሽ፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው ፡ ቸርነቱ ፡ በእኛ ፡ ለዘለዓለሙ፡ ይደርና ፡ ጌታችን ፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒ ታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለዋጮችን፡ እንደ፡ አስደነገጣቸው፡የሚናገረው፡ድንቅ፡ ተአምር፡ይህ፡ነው።

፰፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ፡ ፍርሀትና፡መንቀጥቀጥ፡ያዛቸው።

፱፤ የሚሸጡ ፡ የሚገዙ ፡ የሚቀርጡ፡ በመቅደሱ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ከጌታ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፊት ፡ የተነሣ፡ ተሸሸጉ።

፲፤ ከገመድ ፡ የተሠራ ፡ አለንጋ ፡ ይዞ ፡ እየገረፈ፡

### በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ወሰደዶሙ ፡ እምቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወገፍትዐ ፡ ማዕዳቲሆሙ ፡ ለመወልጣን ፡ ወአውፅአሙ ፡ እምቤተ፡መቅደስ።

፲፯፤ ወይቤሎሙ፡ቤትየሰ፡ቤተ፡ጸሎት፡ይሰመይ፡ አንትሙሰ ፡ ረሰይክምዎ ፡ በአተ ፡ ፈያት ፡ ወሠረቅት ፡ ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ወኵሉ፡ሥርዐቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፸፩፡፲፰–፲፱።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል። ዘገብረ ፡ መንክረ ፡ ባሕቲቱ ። ወይትባረክ፡ስመ፡ስብሐቲሁ።

ይ፡ሕ፡ከማሁ።

ይ፡ዲ፡ቁሙ፡ወአጽምዑ፡በል።

ይ ፡ ካ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘዜነወ ፡ ማርቆስ ፡ ቃለ፡ወልደ፡እግዚአብሔር።

ይ፡ሕ፡ስብሐት፡ለከ፡ክርስቶስ።

ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፡፲፩፡፲፪–፳፮።

፲፪፤ ወበሳኒታ፡ወፂአ፡እምቢታንያ፡ርኅበ።

፲፫፤ ወርእየ ፡ በለሰ ፡ እምርኁቅ ፡ ወባቲ ፡ ቈጽል ፡ ወሖረ ፡ ይርአይ ፡ እመቦ ፡ ዘይረክብ ፡ ፍሬ ፡ በውስቴታ፡ወበጺሖ፡ኀቤሃ፡አልቦ፡ዘረከበ፡ ዘእንበለ ፡ ቈጽል ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ጊዜሁ፡ለበለስ።

፲፬፤ ወአውሥአ፡ወይቤላ፡አልቦ፡ዘይበልዕ፡ፍሬ፡ እምኔኪ፡ለዓለም፡ወሰምዕዎ፡አርዳኢሁ።

፲፭፤ ወበጺሖ፡ኢየሩሳሌም፡ቦአ፡ቤተ፡መቅደስ፡ ወአኀዘ፡ይስድድ፡እለ፡ይሠይጡ፡ወይሣየጡ፡ በምኵራብ፡ወገፍትዐ፡ማዕዳቲሆሙ፡ለመወልጣን፡ወመናብርቲሆሙ፡ለእለ፡ይሠይጡ፡ ርግበ።

፲፮፤ ወከልአ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘያኃልፍ ፡ ንዋየ ፡ እንተ፡ምኵራብ።

፲፯፤ ወመሀሮሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አኮኑ ፡ ጽሑፍ ፡ ዘይብል ፡ ቤትየሰ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ይኩን ፡ ለኵሉ፡አሕዛብ፡ወአንትሙሰ፡ረሰይክምዎ፡ በአተ፡ፈያት፡ወሰረቅት።

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

ከምኵራቡ ፡ አባረራቸው ፤ የለዋጮችንም ፡ ድርድራቸውን ፡ ገለበጠ ፤ ከምኵራብም ፡ አስወጣቸው።

፲፯፤ ቤቴ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ይባላል ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ የሌባ ፡ ዋሻ ፡ የቀማኛ ፡ ጋሻ ፡ አደረጋችሁት ፡ አላቸው ። ይቅርታው ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ሥርዐቱ፡ሁሉ፡እንዳለፈው፡ነው።

ክፍል፡፫።

ዲያቆን፡ወንጌል፡በፊት።

መዝ፡፸፩፡፲፰–፲፱።

የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር፡ ይመስገን፤ብቻውን፡ድንቅ፡ሥራ፡ያደረገ፤ የጌትነቱም፡ስም፡ይክበር፡ይመስገን፡ይበል።

ሕ፡ከማሁ፡ይበሉ።

ዲያቆኑ፡ቁሙ፡ወአጽምዑ፡ይበል።

ካህኑ ፡ ማርቆስ ፡ ያስተማረው ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል፡ይበል።

ሕዝቡ፡ምሥጋና፡ላንተ፡ይገባል፡ይበሉ።

የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፲፩፡፲፪–፳፮።

፲፪፤ በነጋውም፡ከቢታንያ፡በወጣ፡ጊዜ፡ተራበ።

፲፫፤ በለስንም፡ከሩቅ፡አየ፤ቅጠል፡ነበራት፤በውስጥዋም ፡ የሚአገኘው ፡ ፍሬ ፡ እንዳለ ፡ ሊያይ ፡ ሄደ፤ወደሷም፡በደረሰ፡ጊዜ፡ከቅጠል፡በቀር፡ ያገኘው ፡ የለም ፤ ጊዜው ፡ የበለስ ፡ አልነበረምና።

፲፬፤ ጌታም፡መልሶ፡ለዘላለም፡ካንቺ፡የሚበላ፡ፍሬ፡ አይኑር፡አላት።ደቀመዛሙርቱም፡ሰሙት።

፲፭፤ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስ፡ገብቶ፡በምኵራቡ፡የሚሸጡትንና፡ የሚገዙትን ፡ ያባርራቸው ፡ ጀመር ፤ የለዋጮችንም ፡ መደብርና ፡ ርግብ ፡ የሚሸጡትን ፡ ወንበሮች፡ገለበጠ።

፲፮፤ በምኵራቡም ፡ በኩል ፡ ገንዘብን ፡ የሚአስተላልፍ፡እንዳይኖር፡ከለከለ።

፲፯፤ እንዲህ ፡ ብሎም ፡ አስተማራቸው ፤ ቤቴ ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ይሁን ፡ የሚል፡ተጽፎ፡የለምን?እናንተ፡ግን፡የሌቦች፡ ዋሻ፡የቀማኞች፡ጋሻ፡አደረጋችሁት።

Scanned by CamScanner

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፰፤ ወሰምዑ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወጸሐፍት ፡ ወኀሠሡ፡እንተ፡ኀበ፡ይቀትልዎ፡ወፈርህዎ፡ እስመ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ያነክሩ፡ምህሮቶ።

፲፱፤ ወሶበ፡መስየ፡ወፅአ፡አፍአ፡እምሀገር።

፳፤ ወበግብአቶሙ ፡ በነግህ ፡ ረከብዋ ፡ ለይእቲ ፡ በለስ፡ይብስተ፡እምሥርዋ።

፳፩፤ ወተዘከረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤሎ ፡ ሊቅ ፡ ነያ ፡ እንታክቲ፡በለስ፡እንተ፡ረገምካ፡የብሰት።

፳፪፤ ወአውሥአ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡**ወይቤሎሙ፡ ይኩን ፡ ውስቴትክሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ **እግዚአ ብሔር።**

፳፫፤ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ለእመ ፡ ትብልዎ ፡ ለዝንቱ፡ ደብር ፡ ተንሥእ ፡ ወተወረው ፡ ውስተ፡ ባሕር ፡ ወኢናፈቅሙ ፡ በልብክሙ ፡ ወተአመንክሙ ፡ ከመ ፡ ዘነበብክሙ ፡ ይከውን፡ወትረክቡ።

፳፬፤ ወበእንተ፡ዝንቱ፡እብለክሙ፡ወሰአልክሙ፡ እንዘ፡ትትአመኑ፡ከመ፡ትረክቡ፡ወይከውን፡ ለክሙ።

፳፭፤ ወሶበሂ፡ትጼልዩ፡ኅድጉ፡ለቢጽክሙ፡ዘተሐ የሰክምዎ፡ከመ፡ይኅድግ፡ለክሙ፡አቡክሙ፡ ዘበሰማያት፡አበሳክሙ።

፳፮፤ ወእመሰ፡አንትሙ፡ኢኃደግሙ፡አቡክሙኒ፡ ሰማያዊ፡ኢየኀድግ፡ለክሙ፡አበሳክሙ፡

**ይ፡ካ፡**ዘቦ፡እዝነ፡ሰሚዐ፡ለይስማዕ።

ድኅረ ፡ ወንጌል ፡ በአሐዱ ፡ ሰዓት ፡ ዘዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ እምግብረ ፡ ሕማማት ፡ ቅድስት ፡ ስብሐት፡ዘይደሉ።

፩፤ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፤ ወአሰርገዎሙ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ በንመፈሰ፡አፉሁ።

፪፤ ወከደነ ፡ ጽልመተ ፡ ወአምጽአ ፡ ብርሃነ ፡ ወፈለጦሙ፡በአስማት፡ሐዲሳን።

ወሰመዮ፡ለብርሃን፡መዓልተ፡ከመ፡ውእቱ፡ መዐልት ፤ ወሰመዮ ፡ ለጽልመት ፡ ሌሊተ ፡ ከመ፡ውእቱ፡ሌሊት።

፫፤ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ፈጠረ ፡ እልክተ ፡ በከመ ፡ ጥበቡ፡ወዕመቀ፡አእምሮቱ።

፬፤ ወበዳግምኒ፡ፈጠረ፡**እግዚአብሔር**፡ምድረ፡ ወአጽንዓ፡መልዕልተ፡ማይ።

፭፤ ወበሣልስት ፡ አጽንዐ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ማየ

ሰኞ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፲፰፤ የካህናት፡አለቆችና፡ጸፎች፡ሰምተው፡የሚገ ድሉበትን፡ፈለጉ፤ግን፡ፈሩት፤ሕዝቡ፡ሁሉ፡ ትምህርቱን፡ያደንቁ፡ነበርና።

፲፱፤ በመሸም፡ጊዜ፡ከከተማ፡ወደ፡ውጭ፡ወጣ።

፳፤ በነጋውም ፡ ተመልሰው ፡ ያችን ፡ በለስ፡ ከሥርዋ፡ደርቃ፡አገኟት።

፳፩፤ ጴጥሮስም፡አስታውሶ፡መምህር፡እነሆ፡ያቺ፡ የረገምካት፡በለስ፡ደርቃለች፡አለው።

፳፪፤ **ጌታ ፡ ኢየሱስም** ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው፤**እግዚአብሔርን**፡ማመን፡በእናንተ፡ ይኑር።

፳፫፤ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡ ተነስተህ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተወ ርወር ፡ ብትሉት ፡ በልቡናችሁ ፡ ባትጠራ ጠሩና ፡ ብታምኑ ፡ እንደ፡ ተናገራችሁት፡ ሁኖ፡ታገኛላችሁ።

፳፬፤ ስለዚህ ፡ አምናችሁ ፡ የለመናችሁት ፡ ሁሉ ፡ እንደሚሆንላችሁም ፡ እነግራ ችኋለሁ።

፳፭፤ በምትጸልዩበትም ፡ ጊዜ ፡ የተነቃቀፋችሁ በትን፡ ለወንድማችሁ ፡ ተዉ ፤ ሰማያዊ ፡ አባታችሁ፡በደላችሁን፡ይቅር፡እንዲላችሁ።

፳፮፤ እናንተ ፡ ይቅር ፡ ካላላችሁ ፡ ሰማያዊ ፡ አባታ ችሁም፡ይቅር፡አይላችሁም።

**ካህኑ፡**ጆሮ፡ያለው፡መስማትን፡ይስማ፡ይበል፡

ሰኞ ፡ ጠዋት ፡ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ ከከበረች፡ ግብረ፡ ሕማማት ፡ ውስጥ ፡ ከወንጌል ፡ በኋላ፡ ሊነበብ፡የሚገባ፡ምሥጋና።

፩፤ በመጀመሪያ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ፈጠረ ፤ እንደዚህም ፡ በሥልጣኑ፡ አከናወናቸው።

፪፤ በጨለማ ፡ ሸፍኖ ፡ ብርሃንንም ፡ አምጥቶ ፡ በአዲስ፡ስሞች፡ለያቸው።

ብርሃንን ፡ ቀን ፡ እንደሞሆኑ ፡ መጠን ፡ ቀን፡ አለው ፤ ጨለማንም ፡ ሌሊት ፡ እንደመሆኑ፡ መጠን፡ሌሊት፡አለው።

፫፤ እንደ ፡ ጥበቡና ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ ጥልቀት፡ መጠን፡በዚህ፡ቀን፡እነዚህን፡ፈጠረ።

፬፤ በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ምድርን፡ገለጠ፤በውኃ፡ላይም፡አጸናት።

፭፤ በሦስተኛውም ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ውኃን ፡

Scanned by CamScanner

| በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት በ፩፡ሰዓት። |
|---|---|
| ላዕላዊተ፡ወሰመያ፡ሰማየ። | አጽንቶና፡ጠፈር፡አድርጎ፡ሰማይም፡ብሎ፡ጠራት። |
| ፲፩፡ ትዝምደ፡ዕፀው፡ወአዝርዕተ፡ሐቅል፡ወሐመልማለ፡ዘርዕ፡ዘይፈሪ፡ፍሬ፡በዕለተ፡ሠሉስ፡ፈጠረ። | ፲፩፡ የዕፅዋትን፡ወገንና፡በዱር፡የሚዘሩትን፡ፍሬ፡የሚአፈሩትን ፡ የእህልና ፡ የአትክልትን ፡ ወገን፡ሁሉ፡በሦስተኛው፡ቀን፡ፈጠረ። |
| ፲፪፡ ፀሐየ፡ወወርኀ፡ወከዋክብተ፡ፈጠረ፡እግዚአብሔር፡በዕለት፡ራብዕት። | ፲፪፡ ፀሐይና ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትንም ፡ እግዚአብሔር፡በአራተኛዪቱ፡ቀን፡ፈጠረ። |
| ፲፫፡ ተሐዋስያነ ፡ ወአራዊተ ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወዓሣተ ፡ አበይተ ፡ ወእንስሳ ፡ ሐቅል ፡ በዕለተ፡ ሐሙስ ፡ ፈጠረ። | ፲፫፡ ተንቀሳቃሽ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አራዊትን ፡ የሰማይ፡ወፎችን፡ታላላቅ፡ዓሣዎችን፡(ብሔሞትንና፡ሌዋታንን)፡የዱር፡እንስሳትንም፡ሁሉ፡በአምስተኛው፡ቀን፡ፈጠረ። |
| ፲፬፡ በዕለተ ፡ ሰዱስ ፡ ፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንስሳ ፡ ዐቢየ ፡ አዳምሃ ፡ ቀዳማየ ፡ ብእሴ ፡ ወረዳኢቶ ፡ እንተ ፡ ተነሥአት ፡ እምኔሁ ፡ ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ገብሮሙ ፡ በከመ ፡ ሥርዐተ ፡ እልክቱ ፡ ኀደጎሙ፡ ይኩኑ ፡ መኳንንተ ፡ ላዕለ ፡ ምግባራቲሁ፡ዘፈጠሮሙ። | ፲፬፡ በስድስተኛው፡ቀን፡ታላቁን፡ፍጥረት፡የመጀመሪያውን ፡ ሰው ፡ አዳምንና ፡ ከጎኑ ፡ አጥንት ፡ ተወስዳ ፡ የተፈጠረች ፡ ረዳቱን ፡ ሔዋንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠረ ፤ እንደ ፡ ሥርዐቱም ፡ ይበዙ ፡ ዘንድ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ፡ሠራቸው፤በፈጠራቸው፡ፍጥረቶቹ፡ላይ፡ገዥዎች፡ይሆኑ፡ዘንድ፡ሾማቸው። |
| ፲፭፡ ወአዕረፈ፡በዕለት፡ሳብዕት። | ፲፭፡ በሰባተኛይቱም፡ቀን፡ከመፍጠር፡አረፈ። |
| ፲፮፡ ወባቲ፡ፈጸመ፡ኵሎ፡ግብሮ፤ወባረካ፡እግዚአብሔር፡አምላክ፡ዛቲ፡ሥርዐት፡መሠረት፡ይእቲ፡ለኵሎሙ፡እለ፡የኀድሩ፡ውስተ፡የብስ። | ፲፮፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ በርስዋ ፡ ፈጸመ ፤ ባረካት ፤ ይቺ ፡ ሥርዐት ፡ በምድር ፡ ለሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ መሠረት፡ናት። |
| ፲፯፡ ንሰብሖ፡ወናልዕል፡ስሞ፡እስመ፡ውእቱ፡ገብረ፡ለነ፡ምሕረተ። ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ። | ፲፯፡ እናመስግነው፤ስሙንም፡ከፍ፡ከፍ፡እናድርገው፤እርሱ፡ይቅርታ፡አድርጎልናልና። መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሁኖ፡መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን። |

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል፤ክርስቶስ፡አምላክነ፡በል፤ሰላም፡ለኪ፡ማርያም፡ሐረገ፡ተድላ፡በል፤ስብሐት፡ለከ፡ከመ፡ንንግር፡ኵሎ፡በል።ግናይ፡ለክሙ፡ሥሉስ፡ቅዱስ፡መዋዕያነ፡፪ኤ፡አእምሮ፡በል፤ስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነ፡ዘፈጠረ፡በል፤ጸሎተ፡ሃይማኖት፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ሐመ።ለዛቲ፡ግብረ፡ሕማማት።አ፡ማኅበራኒሁ።(ነዋ፡በግዑ።)፡(ወዕቀበሙ)፡በል፤ይ፡ካ፡ሑሩ፡በሰላም፤እግዚአብሔር፡የሀሉ፡ምስሌክሙ።ወንዑ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በጊዜ፡ሠለስቱ፡ሰዓት፡ዘመዐልት።

## ምዕራፍ፡፲፭።

ትእዛዝ ፡ ወእምገዘ ፡ ይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ በጊዜ ፡ ሠለስቱ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘሰኑይ ፡ ወይጸልዩ ፡ መዝሙረ፡ዳዊት፡ዘይቤ፡ብፁዓን፡እለ፡ተኀድገ፡ሎሙ፡ኀጢአቶሙ፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ከመ፡ተሀበኒ፡ተምኔትየ፡ኵሎ፡አሚረ፡ወውዳሴሃ፡ለእግዝእትነ፡ማርያም፡ዘይትነበብ፡በዕለተ፡ሠሉስ።

## ምዕራፍ፡፲፭።

ከእንግዲህ ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ በከበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ካህናቱ ፡ ይሰብሰቡ ። የዳዊትንም ፡ መዝሙር ፡ ብፁዓን ፡ እለ ፡ ተኃድገ ፡ ሎሙ ፡ የሚለውን ፡ ከመ ፡ ተሀበኒ ፡ ተምኔትየ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ እስከሚለው ፡ ይጸልዩ ። ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ የማክሰኞን፡ይድገሙ።

| በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት። |
|---|---|

ወይበል፡መራሂ፡በ፲፡ሃሌታ፡ስምዕዎኬ፡**ለእግዚእነ**፡ኵልክሙ፡አብያተ፡ክርስቲያናት፡ከመ፡ዘአክበሮሙ፡ለአሪት፡ወለነቢያት፡በወንጌለ፡መንግሥት፡እንዘ፡ይብል፡**ክርስቶስ፡ወልደ፡ዳዊት**፡አሜን፡አሜን፡እብለክሙ፡እስከ፡አመ፡የኀልፍ፡ሰማይ፡ወምድር፤የውጣ፡እንተ፡አሐቲ፡ቅጽረታ፡**(ቅርጸታ)**፡ወአሐቲ፡ሕርመታ፡ኢተኀልፍ፡እምኦሪት፡ወእምነቢያት፡እስከ፡ሶበ፡ኵሉ፡ይትገበር፡ወይከውን፡ይቤ፡**እግዚእ**፡ዘበዕብራይስጢ፡ልሳን፡በወንጌለ፡ማቴዎስ፡ብርሃን፡ዘእምብርሃን።

ክፍል፡፩።

**ምንባብ፡ዘሠለስቱ፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።**

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፭፡፳፩–፳፮።

፳፩፤ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይጠበቡ ፡ ለእከይ ፡ ወይብሉ፡ንሕነ፡ከመ፡ጠቢባን።

፳፪፤ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለጽኑዓን ፡ እለ ፡ ይሰትይዎ፡ለወይን፡ወለኀያላን፡እለ፡ይቶስሕዎ፡ለሜስ።

፳፫፤ ወያጸድቅዎ፡ለኃጥእ፡ወይነሥኡ፡ሕልያነ፡ወይዔምፅዎ ፡ ለጻድቅ ፡ ወይሜውርዋ ፡ ለጽድቁ።

፳፬፤ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ይነድድ ፡ ኀሠር ፡ በአፍሐመ ፡ እሳት ፡ ወይውዒ ፡ በነበልባል ፡ ከማሁ ፡ ይትበላዕ ፡ ሥርዎሙ ፡ ወርእሶሙ ፡ እስከ፡ የዐርግ ፡ ጢስ ፡ እምኔሆሙ፡እስመ፡ኢፈቀዱ፡ሕገ፡**እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት** ፡ ወአምዕዕዎ ፡ ለቅዱሰ ፡ እስራኤል።

፳፭፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተምዐ ፡ **እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት** ፡ ዐቢየ ፡ መዐተ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝቡ ፡ ወአንሥአ፡እዴሁ፡ላዕሌሆሙ፡ወቀሠፎሙ፡ወተምዐ፡መዐተ፡ላዕለ፡አድባር፡ወኮነ፡አብድንቲሆሙ፡ከመ፡መሬት፡ማእከለ፡ፍኖት፡ወምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ኢተመይጠት ፡ እዴሁ፡**ለእግዚአብሔር**፡ልዕልት።

፳፮፤ ወይእዜኒ ፡ ይገብር ፡ ተአምረ ፡ ለአሕዛብ ፡ ርኁቃን፡ወይስሕቦሙ፡እምአጽናፈ፡ምድር፡ወናሁ፡ይመጽኡ፡ፍጡነ፡እንዘ፡ይረውጹ።

ክፍል፡፩።

**ሰኞ፡ከቀኑ፡በሦስት፡ሰዓት፡የሚነበብ።**

የነቢዩ፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፭፡፳፩–፳፮።

፳፩፤ ለክፉ ፡ ነገር ፡ ለሚራቀቁ ፡ እኛ ፡ እንደ፡ጠቢባን፡ነን፡ለሚሉ፡ወዮላቸው።

፳፪፤ የወይንን፡ጠጅ፡ለሚጠጡ፡ኃያላን፡የሚያሰክረውንም፡(አረቂ)፡ለሚደባልቁ፡ጨካኞች፡ለሆኑ፡ወዮላቸው።

፳፫፤ ኃጥኡን ፡ ጻድቅ ፡ ለሚሉ ፡ ማማለጃ ፡ ተቀብለው ፡ ጻድቁን ፡ ለሚበድሉ ፡ እውነትንም፡ለሚያጠፉአት፡ወዮላቸው።

፳፬፤ ስለዚህ፡ነገር፡ገለባ፡በእሳት፡ፍም፡በነበልባልም፡እንዲቃጠል፡ከጥፋታቸው፡የተነሣ፡የጥፋታቸው ፡ ወሬ ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ፡ ራሳቸውና ፡ ልጆቻቸው ፡ እንደዚሁ ፡ ይጠፋሉ፤ አሸናፊ ፡ የሚሆን ፡ **የእግዚአብሔርን**፡ሕግ፡አልወደዱምና፡በእስራኤልም፡ዘንድ፡የተመሰገነውን፡አሳዝነውታልና።

፳፭፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ **አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር** ፡ በወገኖቹ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ቁጣን ፡ ተቈጣ፤እጁ፡መዐቱንም ፡ በእሳቸው ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ ቀሠፋቸው፤በተራሮችም፡ተቆጣ፤ሬሳቸውም፡በጐዳና ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ አፈር ፡ ሆነ፤ ከዚህም፡ሁሉ፡ጋራ፡ከፍ፡ከፍ፡ያለች፡**የእግዚአብሔር**፡እደ፡መዐቱ፡ገና፡አልተመለሰችም።

፳፮፤ አሁንም፡በሩቅ፡ላሉ፡አሕዛብ፡ተአምራትን፡ያደርጋል፤ከምድር፡ዳርቻም፡ስቦ፡ያመጣቸዋል፤እነሆ፡እየሮጡ፡ፈጥነው፡ይመጣሉ።

Scanned by CamScanner

| በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ፯፤ ኢይርኅቡ ፡ ወኢይጸምዑ ፡ ወኢይደክሙ ፡ ወኢይዴቅሱ ፡ ወኢይፈትሑ ፡ ቅናውቲሆሙ፡ ወኢይትበተክ ፡ ቆታን ፡ አሣእኒሆሙ፡እምእገሪሆሙ። | ፯፤ አይራቡም፡አይጠሙም፡አይደክሙም፡አያንቀላፉም ፤ ዝናራቸውንም ፡ ከወገባቸው ፡ አይፈቱም፤የጫሞቻቸውም፡ማዘቢያ፡ከእግራቸው፡አይበጠስም። |
| ፰፤ ወበሊሕ፡መዐብሊሆሙ፡ወውሱቅ፡አቅስስቲሆሙ፡ወከመ፡እብን፡ጽኑዕ፡እግረ፡አፍራሲሆሙ ፡ ወመንኰራኵረ ፡ ሠረገላቲሆሙ ፡ ይረውፅ፡ከመ፡ዓውሎ። | ፰፤ ሰይፋቸው ፡ የተሳለ ፡ ነው ፤ ቀስታቸውም ፡ የተሳበ፡ነው፤የፈረሶቻቸውም፡እግር፡እንደደንጊያ፡የጸና፡ነው፤የሠረገሎቻቸውም፡መንኰራኵር፡እንደ፡ዐውሎ፡ነፋስ፡ፈጥኖ፡ይደርሳል። |
| ፱፤ ይጥሕሩ ፡ ከመ ፡ አናብስት ፡ ይቀውሙ ፡ ወከመ፡ ዕጓለ ፡ አናብስት ፡ ይመስጡ ፡ ወይጥሕሩ፡ከመ፡አርዌ፡ዘይወፅእ፡እምግቡ፡ወአልቦ፡ዘያድኅኖሙ። | ፱፤ እንደ፡አንበሳ፡ይጮሃሉ፤ይቆማሉ፤እንደ፡አንበሶችም፡ግልገል፡ቁመው፡ይነጥቃሉ፤ከጉድጓዱ፡እንደሚወጣ፡ዘንዶም፡ይጮሃሉ፤የሚያድናቸውም፡የለም። |
| ፲፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ የዐወይዉ ፡ በበይናቲሆሙ፡ ከመ ፡ ድምፀ ፡ ባሕር ፡ ዘይትሀወክ ፡ ወይኔጽሩ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወይሬእዩ ፡ ጽልመተ፡ጽፉቀ፡ወይትመነደቡ። | ፲፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እርስበርሳቸው ፡ ይጮኻሉ ፤ ባሕር ፡ ከነፋስ ፡ የተነሣ ፡ እንዲታወክ ፡ ይታወካሉ፤አንገታቸውን፡ደፍተው፡ወደ፡ምድር፡ያያሉ፤በመከራውም፡ይጨነቃሉ። |
| ዘኢዩኤል፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | የነቢዩ፡ኢዩኤል፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትሁን፡አሜን። |
| ምዕ፪፡፳፩–፳፬። | ምዕ፪፡፳፩–፳፬። |
| ፳፩፤ ተአመኒ ፡ ምድር ፡ ተፈሥሒ ፡ ወተሐሠዪ ፡ እስመ፡አዕበየ፡እግዚአብሔር፡ግብሮ፡ከመ፡ይግበር፡ላዕሌኪ። | ፳፩፤ ቤተ፡እስራኤል፡እመኚ፡ይቅርታው፡ይደረግልሽ፡ዘንድ፡እግዚአብሔር፡ይቅርታውን፡ከፍ ፡ ከፍ (ፍጹም) ፡ አድርጎልሻልና ፡ ፈጽሞም፡ደስ፡ይበልሽ። |
| ፳፪፤ ተአመኑ፡እንስሳ፡ገዳም፡እስመ፡ብዕሉ፡አሕቃላተ፡በድው፡ወፈረዩ፡ዕፀው፡ወይን፡ወበለስ፡ወሀቡ፡ኃይሎሙ። | ፳፪፤ በምድረ፡በዳ፡ያሉ፡አዝርዕት፡አትክልት፡ዕፀዋት፡አብበዋል፤አፍርተዋልና፡ወደ፡ምድረ፡በዳ፡የምትሠማሩ፡እንስሳት፡እንጠግባለን፡ብላችሁ፡እመኑ፤ወይንና፡በለስም፡ፍሬያቸውን፡ሰጡ። |
| ፳፫፤ ተፈሥሑ፡ወተሐሠዩ፡በእግዚአብሔር፡አምላክክሙ፡ደቂቀ፡ጽዮን፡እስመ፡ወሀበክሙ፡ሲሳየ፡ጽድቅ፡ዘበአማን፡ወያዘንም፡ለክሙ፡ጸደየ፡ወመጸወ። | ፳፫፤ እውነተኛ፡ምግባችሁን፡(በሰባ፡ዘመን)፡ሰጥቷችኋልና፡የጽዮን፡ልጆች፡በፈጣሪያችሁ፡በእግዚአብሔር፡አምናችሁ፡ፈጽሞ፡ደስ፡ይበላችሁ፤የበልጉን፡ዝናም፡የበጋውንም፡ዝናም፡ያዘንምላችኋልና። |
| ፳፬፤ ከመ ፡ ትካት ፡ ይመልዕ ፡ ዓውደ ፡ እክል ፡ ወይትከዓው ፡ ምክያዳተ ፡ ወይን ፡ ወዘይት። | ፳፬፤ የእህሉንም ፡ ዓውድማ ፡ እንደቀድሞው ፡ ይሞላል ። የዘይቱና፡የወይኑም፡ዓውድማ፡መልቶ፡ይፈሳል። |

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፮፤ ወእፈድየክሙ ፡ ህየንተ ፡ ዓመት ፡ ዘበልዐ ፡ አንበጣ ፡ ወደጎብያ ፡ ወዕፄ ፡ ወአናኰዕ ፡ ኀይልየ፡ዘፈኖኩ፡ላዕሌክሙ።

፳፯፤ ተሴሰዩ፡ወብልዑ፡ወጽገቡ፡ወሰብሑ፡ስመ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ እስመ ፡ ገብረ ፡ ለክሙ ፡ መንክረ ፡ ወኢትትኀፈሩ ፡ እንከ ፡ ሕዝብየ፡ለዓለም።

፳፰፤ ወተአምሩ፡እንከ፡ከመ፡ሀሎኩ፡አነ፡ማእከሌክሙ ፡ ወአነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ፡ወአልቦ፡ባዕድ፡አምላክ፡ዘእንበሌየ፡ ወኢትትኀፈሩ፡እንከ፡ኵልክሙ፡ሕዝብየ፡ ለዓለም።

፳፱፤ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ እክዑ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ዘሥጋ፡ወይትኔበዩ፡ ደቂቅክሙ ፡ ወአዋልዲክሙ ፡ ወሊቃውንቲክሙ፡ሕልመ፡የሐልሙ፡ወወራዙቲክሙ፡ ራእየ፡ይሬእዩ።

፴፤ ወላዕለ ፡ አግብርትየ ፡ ወአእማትየ ፡ ይእተ ፡ አሚረ፡እክዑ፡እምነ፡መንፈስየ።

፴፩፤ ወእገብር ፡ ተአምረ ፡ በሰማይ ፡ በላዕሉ ፡ ወበምድር፡በታሕቱ፡ደመ፡ወእሳተ፡ወተየ፡ ወጢሰ።

፴፪፤ ፀሐይኒ፡ይጸልም፡ወወርኅኒ፡ደመ፡ይከውን፡ ዘእንበለ ፡ ትብጻሕ ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓባይ፡እንተ፡ታስተርኢ።

፴፫፤ ወኵሉ ፡ ዘፀውዐ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይድኅን ፡ በደብረ ፡ ጽዮን ፡ ወበኢየሩሳሌም ፡ ይድኅኑ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእለሂ፡ ይሜህሩ ፡ እለ ፡ ጸውዖሙ ፡ እግዚአብሔር።

ምዕ፤፫፡፩–፳፩።

፩፤ እስመ ፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡ አነ ፡ በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ እመይጥ ፡ ፄዋ ፡ ይሁዳ ፡ ወኢየሩሳሌም።

፪፤ ወአስተጋብአሙ፡ለኵሎሙ፡አሕዛብ፡ወአወርዶሙ ፡ ቈላተ ፡ ዮሳፍጥ ፡ ወእትዋቀሶሙ ፡ በሀየ ፡ በእንተ ፡ ሕዝብየ ፡ ወበእንተ ፡ ርስትየ ፡

## ስኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፳፮፤ ተምቹና ፡ አንበጣው ፡ ኩብኩባውና ፡ ትሉ፡ ስለ፡ በላው ፡ ፈንታ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እሰጣችኋለሁ፡አለ።

፳፯፤ ይህንን ፡ በልታችሁ ፡ ጥገቡ ፤ ድንቅ ፡ ተአምራቱን ፡ አድርጎላችኋልና ፤ የፈጣሪያችሁን፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አመስግኑ ፤ እናንተም ፡ ወገኖቼ ፡ ለዘላለሙ ፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡አታፍሩም።

፳፰፤ በመካከላችሁ፡በረድኤት፡አድሬ፡እንዳለሁ፡ ታውቃላችሁ ፤ ፈጣሪያችሁም ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ ያለኔ ፡ ምንም ፡ ሌላ ፡ ባዕድ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ ሁላችሁ ፡ ወገኖቼ ፡ ለዘላለሙ፡አታፍሩም።

፳፱፤ ከዚህ፡በኋላ፡ሥጋ፡በለበሰ፡ሁሉ፡መንፈሴን፡ አሳድራለሁ፤ሴቶች፡ልጆቻችሁና፡ወንዶች፡ ልጆቻችሁ ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፤ አለቆቻችሁም ፡ ሕልም ፡ ያልማሉ ፤ ጐልማሶቻችሁም፡ራዕይ፡ያያሉ።

፴፤ በሴቶቹና፡በወንዶቹ፡ባሮቼ፡ላይ፡ያን፡ጊዜ፡ መንፈሴን፡አሳድርባቸዋለሁ።

፴፩፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባለ ፡ በምድር ፡ ከምድር፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በሰማይ ፡ ምልክት ፡ አደርጋለሁ፤ ደማቸው ፡ ይፈሳል ፤ ቤታቸው ፡ ይተኰሳል፤ (ይቃጠላል)፡የጢስም፡ተን፡ይታያል።

፴፪፤ የምትነገር፡ታላቅ፡የሆነች፡የእግዚአብሔር፡ ቀን፡ሳትደርስ፡ፀሐይ፡ይጨልማል፤ጨረቃ፡ ደም፡ይሆናል።

፴፫፤ እግዚአብሔር፡ይድናሉ፡ብሎ፡እንደተናገረ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ፡ ይድናሉ ፡ ብሎአልና ፡ የእግዚአብሔርን፡ ስም፡ የጠራ፡ ሁሉ፡ ይድናል ፤ እስራኤልንም፡ የሚአስተምሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተምሩ፡ ያላቸው፡(ነቢያት፡ካህናት)፡ናቸው።

ምዕ፤፫፡፩–፳፩።

፩፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ እኔ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከይሁዳ፡ የተማረኩትን፡እመልሳቸዋለሁ።

፪፤ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ በሚጠፉበት ፡ ቦታ ፡ እሰበስባቸዋለሁ፤ዮሳፍጥም፡ወደሚባል፡ቈላ፡አወርዳቸዋለሁ ፤ ምድሬን ፡ በተካፈሉበትና ፡ በተማረ

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

እስራኤል ፡ በኀበ ፡ ተዘርዉ ፡ በውስተ ፡
አሕዛብ፡ወተካፈሉ፡ምድርየ።

፫፡ ወተዐፀዉ ፡ ዲበ ፡ ሕዝብየ ፡ ወወሀቡ ፡
ደቂቆሙ፡ ለዘማት ፡ ወሤጡ ፡ አዋልዲሆሙ ፡
ለወይን፡ወሰትዩ።

፬፡ ምንት ፡ ብየ ፡ ምስሌክን ፡ ጢሮስ ፡ ወሲዶና ፡
ወኵሉ ፡ ገሊላ ፡ ዘኢሎፍሊ ፡ በቀለ ፡ እትቤቀ
ለክሙ ፡ ወቂመ ፡ እትቄየመክሙ ፡ ፍጡነ ፡
ወበጕጕዓ ፡ እፈድየክሙ ፡ ፍዳክሙ ፡ ዲበ ፡
ርእስክሙ።
፭፡ ናሁ ፡ ነሣእክሙ ፡ ወርቅየ ፡ ወብሩርየ ፡ ወዐሥ
ራትየ፡ወመሠንየ፡አባእክሙ፡ቤተክሙ።

፮፡ ወሤጥክምዎሙ፡ለደቂቀ፡ይሁዳ፡ወለደቂቀ፡
ኢየሩሳሌም፡ኀበ፡ደቂቀ፡አረሚ፡ከመ፡ታጥ
ፍእዎሙ፡እምብሔሮሙ።
፯፡ ናሁ ፡ አነ ፡ እነሥእሙ ፡ እምውእቱ ፡ ብሔር ፡
ኀበ ፡ ሤጥክምዎሙ ፡ ህየ ፡ ወእፈድየክሙ ፡
ፍዳክሙ፡ዲበ፡ርእስክሙ።
፰፡ ወእትቤቀሎሙ ፡ ለደቂቅክሙ ፡ ወለአዋል
ዲክሙ፡በእደሆሙ፡ለደቂቀ፡ይሁዳ፡ወእት
ቤቀለክሙ፡በኀበ፡ፄወውክምዎሙ፡በውስተ፡
አሕዛብ፡ርኁቃን፡ወነዋኃን፡እስመ፡እግዚአ
ብሔር፡ነበበ፡እንዘ፡ይብል።

፱፡ ስብኩ ፡ ዘንተ ፡ ውስተ ፡ አሕዛብ ፡ ወዓሥሩ ፡
ፀብዐ ፡ ወአንሥኡ ፡ መስተቃትላነ ፡ ወአውፅ
እዎሙ ፡ ወይዕርጉ ፡ ኵሎሙ ፡ እደው ፡ መስተ
ቃትላን።

፲፡ ወማሕረሰክሙኒ፡አግብሩ፡ኵያንወ፡ወማዕፀ
ደክሙኒ፡አግብሩ፡ረምሐ፡ድኩምኒ፡ለይበል፡
ጽኑዕ፡አነ።
፲፩፡ ወይትጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወይሑሩ ፡
ወይዕግቱ፡ወይትጋብኡ፡ህየ፡የዋሃን፡ይኩኑ፡
መስተባእሳነ።

፲፪፡ ወይትነሥኡ ፡ ኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወይዕርጉ ፡
ቈላተ፡ዮሳፍጥ፡እስመ፡ህየ፡እነብር፡ወእትዋ
ቀሥሙ፡ለኵሎሙ፡አሕዛብ።

ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ኩበትም፡በአሕዛብ፡አገር፡ስለ፡ርስቴና፡ስለ፡
ወገኖቼ፡እስራኤል፡ብዬ፡በዚያ፡ቦታ፡እዋቀ
ሳቸዋለሁ።
፫፡ በወገኖቼ ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ በተጣጣሉበት ፡
ወንዶች፡ ልጆቻቸውን ፡ ለጋለሞታ ፡
በሰጡበት፡ሴቶች፡ልጆቻቸውን፡ለመሸታ፡
ሸጠው፡በጠጡበት፡ቦታ፡አጠፋቸዋለሁ።
፬፡ ጢሮስና ፡ ሲዶና ፡ የኢሎፍሊ ፡ አውራጃ ፡
ገሊላም፡ ሁሉ፡ከናንተ፡ጋራ፡ምን፡አንድነት፡
አለኝ? እናንተንስ፡ፈጽሜ፡በቀልን፡እበቀላች
ኋለሁ፤ፈጥኜም፡ቂምን፡እቀየማችኋለሁ፤ችኵ
ዬም፡ፍዳውን፡በራሳችሁ፡አመጣባችኋለሁ።
፭፡ እነሆ ፡ ብሬን ፡ ወርቄን ፡ እሥራቴንም ፡
ወስዳችሁ፡ከዚህም፡መልካም፡መልካሙን፡
መርጣችሁ፡ወደቤታችሁ፡አገባችሁ።
፮፡ ከአገራቸውም ፡ ልታጠፏቸው ፡ የኢየሩሳሌ
ምንና፡የይሁዳን፡ልጆች፡ለአረመኔ፡ልጆች፡
ሸጣችኋቸው።
፯፡ እኔ፡ግን፡እነሱን፡ከሸጣችሁበት፡አገር፡አመ
ጣቸዋለሁ፤በናንተም፡ፍዳችሁን፡በራሳችሁ፡
አመጣባችኋለሁ።
፰፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁንና ፡ ወንዶች ፡ ልጆቻ
ችሁን ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አጠፋቸ
ዋለሁ፤ እናንተንም ፡ ማርካችሁ ፡ በወሰዳች
ኋቸው፡ፈጽመው፡በራቁ፡በአሕዛብ፡አገር፡
ተበቅዬ ፡ አጠፋችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ተናግሮአልና።
፱፡ በአሕዛብ ፡ አገር ፡ ይህንን ፡ አዋጅ ፡ ንገሩ ፤
ሰልፍንም ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ይሁን ፡ ብላችሁ ፡
ቅጠሩ፤አርበኞችንም፡አሥነስታችሁ፡አው
ጡአቸው፤አርበኞችም፡ሁሉ፡አንድ፡ሁነው፡
ይገዘመቱ።
፲፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ማረሻችሁን ፡ ጦር ፡ አሠሩ ፤
ማጭዳችሁንም ፡ ዘገር ፡ አሠሩ ፤ ደካማውም ፡
እኔ፡ጽኑዕ፡ነኝ፡ይበል።
፲፩፡ ሕዝብም፡ሁሉ፡ወደዚያ፡ቦታ፡ተሰብስበው፡
ሂደው ፡ በጦር ፡ ይክበቡ ፤ ጸበኞች ፡ ኀረኞች ፡
ያልነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጸበኞች ፡ ኀረኞች ፡
ይሁኑ።
፲፪፡ በዚያ፡ተቀምጬ፡አሕዛብን፡ሁሉ፡እወቅሳቸ
ዋለሁ፤አሕዛብ፡ሁሉ፡ተነሥተው፡ወደሚጠ
ፉበት፡ቦታ፡ይውጡ።

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፫፤ ወእለ፡ አድያም፡ ፈንዉ፡ ማዕፀደ፡ እስመ፡ በጽሐ፡ ማእረር፡ ባኡ፡ ወእኪዱ፡ እስመ፡ መልአ፡ ምክያድ፡ ወተክዕወ፡ እምነ፡ ምክያዳት።

፲፬፤ ናሁ፡ በዝኀ፡ እከዮሙ፡ ወወውዑ፡ በቈላተ፡ ቅስት፡ ወድምፁ፡ እስመ፡ አልጸቀት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ በውስተ፡ ቈላተ፡ ቅስት።

፲፭፤ ፀሐይ፡ይጸልም፡ወወርኀኒ፡ደመ፡ይከውን፡ ወለከዋክብት፡የዓርብ፡ብርሃኖሙ።

፲፮፤ ወይኬልሕ፡እግዚአብሔር፡እምጽዮን፡ወእም ኢየሩሳሌም፡ይሁብ፡ቃሎ፡ወያድለቀልቁ፡ ሰማይ፡ ወምድር፡ ወእግዚአብሔርሰ፡ ይምህክ፡ሕዝቦ፡ወያጸንዖሙ፡እግዚአብሔር፡ ለደቂቀ፡እስራኤል።

፲፯፤ ወተአምሩ፡እንከ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፡ አምላክክሙ፡ ዘአኀድር፡ ውስተ፡ ጽዮን፡ደብረ፡መቅደስየ፡ወትከውን፡ኢየሩሳሌም፡ሀገረ፡ቅድስተ፡ወኢየኀልፍ፡እንከ፡ እንተ፡ውስቴታ፡ዘእምካልእ፡ሕዝብ፡ያጸንዕ፡ ሕዝበ፡በርትዕ፡ወበጽድቅ።

፲፰፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ያንጸፈጽፍ፡ መዐር፡እምአድባር፡ወይውኅዝ፡ሐሊብ፡እም አውግር፡ ወይነቅዕ፡ ማይ፡ እምዢሉ፡ በሐውርተ፡ ይሁዳ፡ ወይፈለፍል፡ ነቅዕ፡ ወይወፅእ፡እምቤተ፡እግዚአብሔር።

፲፱፤ ወይሰቂ፡ፈለገ፡ሰኪኖን፡ወይማስን፡ብሔረ፡ ግብጽ፡ ወይከውን፡ በድወ፡ ወኤዶምያስኒ፡ ይጠፍኡ፡ በኃጣውኢሆሙ፡ በእደዊሆሙ፡ ለደቂቀ፡ይሁዳ፡እስመ፡ከዐዉ፡ደመ፡ጻድቅ፡ ውስተ፡ምድሮሙ።

፳፤ ወይሁዳሰ፡ ለዓለም፡ ትነብር፡ ወኢየሩሳሌምኒ፡ለትውልደ፡ትውልድ።

፳፩፤ ወእትቤቀል፡ ደሞሙ፡ ወኢያነጽሖሙ፡ እስመ፡ አነ፡ እግዚአብሔር፡ ዘአኀድር፡ ውስተ፡ጽዮን፡ለዓለመ፡ዓለም።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፲፫፤ መከሩ፡ደርሷልና፡በአውራጃው፡ያላችሁ፡ሁሉ፡ ማጭዱን፡ ስደዱ፤ የሰው፡ ጥፋት፡ ነው፤ ዓውድማው፡ መልቷልና፡ ከዓውድማውም፡ ተርፎ፡ፈሶአልና፡ገብታችሁ፡አሂዱ፡(አበራዩ)።

፲፬፤ እነሆ፡ ክፉታቸው፡ በዝቶ፡ ተሠራ፤ ዐብ፡ ክርክር፡በአለበት፡በአሕዛብ፡አገር፡እግዚአብሔር፡ሚጠትን፡የሚአደርግበት፡ቀን፡ደርሶአልና፡ሰልፍ፡በተሰለፉበት፡ቈላ፡ድምፃችሁን፡አሰምታችሁ፡ደንፉ።

፲፭፤ ፀሐይ፡ ይጨልማል፤ ጨረቃም፡ ደም፡ ይሆናል፤ የከዋክብትም፡ ብርሃናቸው፡ ይጠፋል።(ንጉሥ፡ቢትወደድ፡መኳንንት)።

፲፮፤ እግዚአብሔርም፡ በካህናት፡ አድሮ፡ ያስተምራል፤ በነቢያትም፡ አድሮ፡ ያናግራል፤ ሰማይና፡ምድር፡ይነዋወጣሉ፤(ትሑታንና፡ ልዑላኑ፡ በሞት)፡ እግዚአብሔር፡ ግን፡ ለወገኖቹ፡ያዝናል፤ይራራል፤እግዚአብሔር፡ የእስራኤልን፡ልጆች፡በረድኤት፡ያጸናቸዋል፡ በእውነትና፡በቅን፡ፍርድ፡ሕዝቡን፡ያጸናል።

፲፯፤ በምስጋናዬ፡ ማደሪያ፡ በጽዮን፡ አድሬባት፡ የምኖር፡ ፈጣሪያችሁ፡ እግዚአብሔር፡ እኔ፡ እንደሆንሁ፡ከዚህ፡በኋላ፡ታውቃላችሁ፤ኢየሩሳሌምም፡የከበረች፡አገር፡ትሆናለች፤ከአሕዛብም፡ የተወለደ፡ ወገን፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ወደሷ፡አይሄድም።

፲፰፤ ያን፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤ ከተራራው፡ ማር፡ ከኮረፍታውም፡ ወተት፡ ይፈሳል፤ በቤተ፡ እግዚአብሔር፡ አጠገብ፡ ካሉ፡ ከይሁዳ፡ አገሮች፡ ሁሉ፡ ምንጩ፡ ከላይ፡ ወደታች፡ይፈሳል።

፲፱፤ ፈሳሹ፡ ተክሉን፡ ያጠጣል፤ የግብጽ፡ አገር፡ ይጠፋል፤ ምድረ፡ በዳም፡ ይሆናል፤ ኤዶምያስም፡ የድኃውን፡ ደም፡ በሀገራቸው፡ አፍሰዋልና፡ ስለ፡ ኃጢአታቸው፡ በይሁዳ፡ ልጆች፡ እጅ፡ይጠፋሉ።

፳፤ ይሁዳ፡ ግን፡ ለዘላለሙ፡ ትኖራለች፤ ኢየሩሳሌምም፡ለልጅ፡ልጅ፡ዘመን፡ትኖራለች።

፳፩፤ በጽዮን፡በረድኤት፡ለዘላለም፡አድሬባት፡የምኖር፡ እኔ፡እግዚአብሔር፡ ነኝና፡ በግፍ፡ ባፈሰሱት፡ ደም፡ እበቀላቸዋለሁ፤ከፍዳም፡አላነጻቸውም።

Scanned by CamScanner

### በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ዘኤርምያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፱፡፲፪–፲፰።

፲፪፤ መኑ፡ብእሲ፡ጠቢብ፡ዘይሌብዎ፡ለዝንቱ፡ወቃለ፡አፉሁ፡ለእግዚአብሔር፡ኀቤሁ፡ይንግርክሙ፡ወዘየአምር፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ያይድዕ፡ወይንግርክሙ፡በእንተ፡ምንት፡ተሀጕለት፡ምድር፡ወጠፍአት፡ከመ፡በድው፡እስመ፡አልቦ፡ዘየሐውራ።

፲፫፤ ወይቤለኒ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡ኀደጉ፡ሕዝብየ፡ሕግየ፡ዘወሀብክዎሙ፡በቅድመ፡ገጾሙ፡ወኢሰምዑኒ፡ቃልየ።

፲፬፤ ሖሩ፡ወተለዉ፡ፍትወተ፡ልቦሙ፡ወተለዉ፡ጣዖተ፡ዘመሀርዎሙ፡አበዊሆሙ።

፲፭፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡አምላከ፡እስራኤል፡ናሁ፡አነ፡አበልዖሙ፡ፃዕረ፡ወአሰትዮሙ፡ሐሞተ።

፲፮፤ ወእዘርዎሙ፡ውስተ፡በሐውርት፡ኀበ፡ኢየአምሩ፡ኢእሙንቱ፡ወኢ፡አበዊሆሙ፡ወእፌኑ፡ላዕሌሆሙ፡ረኀበ፡ወመጥባሕተ፡እስከ፡አኀልቆሙ።

፲፯፤ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡ተደለዉ፡ወጸውዕዎን፡ለመስቆቅዋት፡ወይምጽኣ፡ወኀበ፡ጠቢባት፡ለአኩ፡ይምጽኣ፡ወይንግራክሙ፡ፍጡነ።

፲፰፤ ወያስቆቅዋክሙ፡ወያንብዓ፡አዕይንቲክሙ፡ወየኀዝ፡ማየ፡ዓንብዕ፡እምነ፡ቀራንብቲክሙ፡እስመ፡ተሰምዐ፡ቃለ፡ብካይ፡ውስተ፡ጽዮን።

### ክፍል፡፪።
### አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዓቱ።

እመጽሐፈ፡ዲድስቅልያ፡ዘአበዊነ፡ቅዱሳን፡ሐዋርያት፡በረከቶሙ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ በእንተ፡ከመ፡መፍትው፡ይዕቀቡ፡ወይፈጽሙ፡ዕለተ፡በዓላት፡በፍሥሓ፡መንፈሳዊት።

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

የነቢዩ፡የኤርምያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፱፡፲፪–፲፰።

፲፪፤ ይህን፡ነገር፡ልብ፡የሚለው፡ብልህ፡ሰው፡ማነው? የእግዚአብሔር፡አፍ፡የተናገረውን፡ቃል፡በሱ፡ዘንድ፡ያለ፡ሰው፡ይንገራችሁ፤ የሚኖርበት፡ሰው፡የለምና፡ የእግዚአብሔርን፡ቃል፡የሚአውቅ፡ሰው፡ምድር፡እንደ፡ምድረ፡በዳ፡ስለምን፡ፈጽማ፡እንደጠፋች፡ይንገራችሁ።

፲፫፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለኝ፤ በፊታቸው፡የሠራሁላቸው፡ሕጌን፡ወገኖቼ፡ትተዋልና፡ቃሌንም፡አልሰሙኝምና።

፲፬፤ ልቡናቸው፡የወደደውንም፡ነገር፡ተከትለው፡ሂደዋልና፡አባቶቻቸው፡ያስተማሩአቸውን፡ጣዖት፡አምልከዋልና።

፲፭፤ ስለዚህ፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤እነሆ፡መከራውን፡አመጣባቸዋለሁ፤ ሐሞትም፡አጠጣቸዋለሁ፡አለ።

፲፮፤ እነሱ፡አባቶቻቸውም፡በማያውቋቸው፡አገሮች፡አስማርኬ፡እበትናቸዋለሁ፤ጨርሼ፡እስካጠፋቸው፡ድረስ፡ጦርና፡ረኃብንም፡አመጣባቸዋለሁ፡አለ፡በላቸው፡አለኝ።

፲፯፤ አሸናፊ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ ለመከራው፡ተዘጋጁ፤አልቃሾችን፡ጥሩአቸው፡ይምጡ፡ወደብልሆችም፡ሴቶች፡ላኩ፤ መጥተውም፡ፈጥነው፡ነገሩን፡ይንገሩአችሁ።

፲፰፤ በጽዮን፡ልቅሶ፡ተሰምቷልና፡ሙሾ፡ያሙሹላችሁ፤ ዐይኖቻችሁ፡ያልቅሱ፤ ከቅንድቦቻችሁም፡የዕንባ፡ጐርፍ፡ይፍሰስ።

### ክፍል፡፪።
### ሃያ፡ዘጠነኛ፡አንቀጽ።

አባቶቻችን፡ቅዱሳን፡ሐዋርያት፡ከሠሩት፡ከዲድስቅልያ፡የመጣ፡የሥርዓት፡መጽሐፍ፡ይህ፡ነው። በረከታቸው፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

፩፤ በመንፈሳዊ፡ደስታ፡የበዓላትን፡ቀን፡ይጠብቁና፡ይፈጽሙ፡ዘንድ፡ስለሚገባ።

| በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፩፤ ዕቀቡ፡እንከ፡ዕለተ፡በዓላት፡በፍሥሐ፡መንፈሳዊት፡ኦፍቁራን፡አኀው። | ፩፤ የተወደዳችሁ፡ወንድሞች፡ሆይ፡እንግዲህ፡በመንፈሳዊ፡ደስታ፡ደስ፡እያላችሁ፡የበዓላትን፡ቀን፡ጠብቁ። |
| ፪፤ ቀዳሚ፡በዓል፡ዘውእቱ፡ልደቱ፡ለክርስቶስ፡ግበሩ፡አመ፡ዕሥራ፡ወኀሙሱ፡ለታሥዕ፡ወርኀ፡በኍልቈ፡ሀሳበ፡ዕብራውያን። | ፪፤ የመጀመሪያ፡በዓል፡የጌታችን፡የክርስቶስ፡ልደት፡ነው፡። ይኸውም፡በዕብራውያን፡አቈጣጠር፡በዘጠነኛ፡ወር፡በሃያ፡አምስት፡ሲሆን። |
| ፫፤ ወበኍልቈ፡ሐሳበ፡ግብጻውያን፡አመ፡ዕሥራ፡ወተስዑ፡ለወርኀ፡ታኅሣሥ፡ዘውእቱ፡ራብዓይ፡ወርኀ። | ፫፤ በግብጻውያን፡አቈጣጠር፡በታኅሣሥ፡ሃያ፡ዘጠኝ፡ይሆናል፤ይኸውም፡አራተኛ፡ወር፡ነው። |
| ፬፤ ወእምድኅሬሁ፡ግበሩ፡በዓለ፡ኤጲፋንያ፡በዘቦቱ፡አርአየ፡እግዚእ፡ስብሐተ፡መለኮቱ፡በውስተ፡ጥምቀት፡በቅድመ፡ዮሐንስ፡በፈለገ፡ዮርዳኖስ፡ወግበሩ፡አመ፡ሰቡዑ፡ለዓሥራይ፡ወርኀ፡በኍልቈ፡ሐሳበ፡ዕብራውያን፡ወበሐሳበ፡ግብጻውያንሰ፡አመ፡ዐሡሩ፡ወአሚሩ፡ለወርኀ፡ጥር፡ዘውእቱ፡ጦቢ፡በኀምሳይ፡ወርኀ። | ፬፤ ከዚህም፡በኋላ፡ጌታ፡በዮርዳኖስ፡ወንዝ፡በዮሐንስ፡ፊት፡የመለኮቱን፡ክብር፡የገለጸ በትን፡የጥምቀቱን፡የኤጲፋንያን፡በዓል፡አክብሩ፤በዕብራውያን፡አቈጣጠር፡በዓሥ ረኛው፡ወር፡በሰባት፡ቀን፡ሲሆን፡በግብጸ ውያን፡አቈጣጠር፡ግን፡ጥር፡አሥራ፡አንድ፡ቀን፡ይኸውም፡ጦቢ፡ማለት፡ጥር፡ነው።በአ ምስተኛ፡ወር፡አክብሩ። |
| ፭፤ ወእምድኅሬሁ፡ዕቀቡ፡በንጽሕ፡አርብዓ፡ዕለተ፡ጾመ፡ቅድስተ፡እንተ፡ይእቲ፡ትሜህረነ፡ዕሙና፡ወትዕግሥተ፡በጾም፡ወበጸሎት፡ዘታቀርበነ፡ኀበ፡ክርስቶስ። | ፭፤ ከዚህ፡በኋላም፡የከበረች፡የዓርባውን፡ቀን፡ጾም፡ጠብቁ፤እርሷም፡ጽሙናንና፡(ጸጥታን)፡ትዕግሥትን፡በማስተማር፡በጾምና፡በጸሎት፡ወደ፡ክርስቶስ፡የምታቀርበን፡ናት። |
| ፮፤ ወትትፌጸም፡ዛቲ፡ጾም፡ቅድስት፡እምቅድመ፡ፋሲካ፡በዘባቲ፡ኮነ፡መድኃኒት። | ፮፤ ይችም፡የከበረች፡ጾም፡በርሷ፡ድኅነት፡ከተደ ረገባት፡ከፋሲካ፡በፊት፡ትፈጸማለች። |
| ፯፤ ወባሕቱ፡ይኩን፡ቀዳሜ፡ጾምክሙ፡በሰኑይ፡ዕለት፡ወተፍጻሜቱሰ፡በዕለተ፡ዓርብ፡ዘቅድመ፡ፋሲካ። | ፯፤ ነገር፡ግን፡የጾማችሁ፡መጀመሪያ፡ሰኞ፡ቀን፡ይሁን፤ፍጻሜውም፡ከፋሲካ፡አስቀድሞ፡ዓርብ፡ቀን፡ይሁን። |
| ፰፤ እስመ፡በሳኒታ፡ሆሣዕና፡በሰኑይ፡ዕለት፡ተጋብኡ፡ዕልዋነ፡ሃይማኖት፡ወሕግ፡እኩያን፡አይሁድ፡ወተማከሩ፡ላዕለ፡እግዚእነ። | ፰፤ በሆሣዕና፡ማግስት፡ሰኞ፡ቀን፡ሃይማኖትና፡ሕግ፡አፍራሾች፡ክፉዎች፡አይሁድ፡በጌታችን፡ላይ፡ሊገሉት፡ተማከረዋልና። |
| ፱፤ በቀዳሚ፡ወርኀ፡ብሩህ፡ዘውእቱ፡ሚያዝያ፡እስመ፡መጽአ፡እግዚእነ፡ወእሙንቱሰ፡ኢአምኑ፡ቦቱ፡ወኢተወክፉ፡ተግሣጸ፡ወበእንተዝ፡ሀጕሉ፡መድኃኒቶሙ። | ፱፤ ብሩህ፡በሆነ፡በመጀመሪያው፡ወር፡ይኸውም፡ሚያዝያ፡ነው፤ጌታችንም፡ሥጋ፡ለብሶ፡ተገለጠ፤እነርሱ፡ግን፡አላመኑበትም፡ምክሩን፡ትምህርቱንም፡አልተቀበሉትም፤ስለዚህም፡ድኅነታቸውን፡አጡ። |
| ፲፤ ወአንትሙሰ፡ብፁዓን፡ወዘመድ፡ቅዱስ፡እስመ፡ኢኮንክሙ፡ከመ፡ትካት፡ሕዝብ፡አላ፡ድኅንክሙ፡እምዕልወት፡ወእምአምልኮ፡ጣዖት። | ፲፤ እናንተ፡ግን፡የተመሰገናችሁ፡ልዩ፡ወገ ናችሁ፤እንደ፡ቀድሙት፡ወገኖች፡አልሆና ሁምና፤ከክህደትና፡ከአምልኮ፡ጣዖት፡ ድናችኋል፡እንጂ። |
| ፲፩፤ አንትሙሰ፡ሕዝበ፡እግዚአብሔር፡ወለክሙ፡ | ፲፩፤ እናንተም፡የእግዚአብሔር፡ወገኖች፡ናችሁ፡ |

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ተርኅወ፡አንቀጸ፡ሕይወት፡እንዘ፡ቀዲሙ፡
ጽሉዓን፡ወምኑናን፡አንትሙ። ይእዜሰ፡
ኮንክሙ፡ኅሩያኒሁ፡ወፍቁራኒሁ፡ወሕዝበ፡
ቅዱስ፡ለእግዚአብሔር፡እለ፡ድልዋን፡
ትስብኩ፡መንክራቲሁ፡ለመድኃኒን።

፲፫፡ እስመ፡ይቤ፡ረከቡኒ፡እለ፡ኢኀሠሡኒ፡ወአስ
ተርአይኩ፡ለእለ፡ኢኀለዩኒ።

፲፬፡ ወእቤሎሙ፡ለሕዝብ፡ለእለ፡ኢየአምኑ፡
ስምየ፡ናሁ፡አነ፡ኀሠሥኩክሙ፡ወአኮ፡
አንትሙ፡ዘኀሠሥክሙኒ፡አላ፡ዳእሙ፡
አመንክሙ፡ብየ፡ወሰማዕክሙ፡በቤተ፡ክርስ
ቲያንየ፡ሕግየ፡ወድኅንክሙ፡እምስህተተ፡
አማልክት፡ወተለውክምዎ፡ለእግዚአብሔር፡
አብ፡አኀዜ፡ኵሉ፡ወወልዱ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ።

፲፭፡ ወኮንክሙ፡ኊሉቃነ፡ምስለ፡እለ፡አምኑ፡
ብየ፡እልፍ፡አእላፍ፡ወትእልፌተ፡አእላፋት።

፲፮፡ ወአንትሙሰ፡ኢኮንክሙ፡ከመ፡እስራኤል፡
እለ፡ኢአምኑ፡ብየ።

፲፯፡ ወበእንቲአሆሙ፡እቤ፡ኵሎ፡አሚረ፡
አንሥእ፡እደውየ፡ኀበ፡ሕዝብ፡ዐላውያን፡
እለ፡ኢይሰምዑ፡ወኢይትኤዘዙ፡ወየሐውሩ፡
ፍኖተ፡እኪተ፡እንተ፡ኢኮነት፡ሠናይተ።

፲፰፡ አላ፡ባሕቱ፡ሕዝብ፡ዘይተሉ፡ኀጢአተ፡ወያ
ምዕዑኒ፡ወትረ፤ናሁኬ፡ርኢክሙ፡ከመ፡
እሙንቱ፡ዐለውዎ፡ለእግዚአብሔር፡
ወኢአምኑ፡ቦቱ።

፲፱፡ ወበእንተዝ፡ይቤ፡ከመ፡እሉ፡አምዕዕዎ፡
ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ፆረ፡ልበሙ፡ወተወሰከ፡
ዲቤሆሙ፡መቅሠፍት፡በእከየ፡ኀሊናሆሙ።
እስመ፡ይቤሉ፡ነአምን፡በክርስቶስ፡ወእሙ
ንቱሰ፡ኢአምኑ፡ከመ፡ውእቱ፡እግዚአ
ብሔር፡አምላክ፡ዘተወልደ፡እምነበ፡አብ፡
እምቅድመ፡ፍጥረት፡ወልድ፡ዋሕድ፡ቃለ፡
አብ።

፳፡ ወእሙንቱሰ፡ኢየአምርዎ፡ሕጹጻነ፡
ሃይማኖት፡ወኢለበዉ፡ትንቢተ፡ነቢያት፡
ዘተጽሕፈ፡በእንቲአሁ፡ከመ፡ይትወለድ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ለእናንተም፡የሕይወት፡በር፡ተከፈተ፤
ቀድሞ፡የተጠላችሁ፤የተናቃችሁ፡ስትሆኑ፡
ዛሬ፡ግን፡የመድኃኒታችንን፡ተአምራቱን፡
ለማስተማር፡የተዘጋጃችሁ፡በመሆናችሁ፡
ምርጦቹና፡ወዳጆቹ፡የተለየ፡የእግዚአ
ብሔር፡ወገን፡ሁናችኋል።

፲፫፡ ያልፈለጉኝ፡አገኙኝ፤ላላሰቡኝም፡ተገለጽኩ
ላቸው፡ብሏልና።

፲፬፡ በስሜ፡ያላመኑትንም፡ሕዝብ፡እነሆ፡እኔ፡ፈለ
ግኋችሁ፤እናንተ፡የፈለጋችሁኝ፡አይደለም፤
ነገር፡ግን፡አመናችሁብኝ፡እንጂ፡በቤተ፡ክር
ስቲያኔም፡ሕጌን፡ሰምታችሁ፡ከጣዖታት፡
ስሕተት፡ዳናችሁ፤ሁሉን፡የያዘ፡እግዚአ
ብሔር፡አብን፡ልጁንም፡ኢየሱስ፡ክርስ
ቶስን፡ተከተላችሁት፡እላችኋለሁ።

፲፭፡ የብዙ፡ብዙ፡እልፍ፡አእላፋት፡ሁነው፡
ካመኑብኝ፡ጋር፡የተቈጠራችሁ፡ሆናችሁ።

፲፮፡ እናንተም፡እንደ፡አላመኑብኝ፡እስራኤል፡
አልሆናችሁም።

፲፯፡ ስለእርሳቸውም፡ሁል፡ጊዜ፡በከዳተኞች፡
ሕዝቦች፡ላይ፡እጄን፡እነሣለሁ፡አልሁ፤እርሳ
ቸውም፡የማይታዘዙ፡የማይሰሙ፡በጎ፡
ባልሆነች፡በክፉ፡መንገድ፡የሚጓዙ፡ናቸው።

፲፰፡ ነገር፡ግን፡ኀጢአትን፡ተከታትለው፡
በመሥራት፡ዘወትር፡ያስቆጡኛል፡እንጂ፤
እነሆ፡እርሳቸው፡እግዚአብሔርን፡እንደ
ካዱት፡እንዳላመኑበትም፡አያችሁ።

፲፱፡ ስለዚህም፡መንፈስ፡ቅዱስን፡እንዳሳዘኑት፡
ተናገረ፤ልባቸው፡ታወረ፤አስበው፡ስለሠ
ሩትም፡ክፋት፡መቅሠፍት፡ተጨመረ
ባቸው። በክርስቶስ፡እናምናለን፡ይላሉ፤ነገር፡
ግን፡የአብ፡አካላዊ፡ቃል፡አንድ፡ልጅ፡
ከዓለም፡ፍጥረት፡በፊት፡ከአብ፡የተወለደ፡
እግዚአብሔር፡አምላክ፡እንደ፡ሆነ፡አያም
ኑምና።

፳፡ ከነርሱም፡ ሃይማኖት፡ የጐደላቸው፡ ክርስ
ቶስ፡ ከድንግል፡እንደሚወለድ፡እያነበቡ፡
እየሰሙ፡ ስለእርሱ፡የተጻፈውን፡የነቢያት፡

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ክርስቶስ ፡ እምድንግል ፡ እንዘ ፡ ያነብቡ ፡ ወይሰምዑ።

፳፩፤ ዘይቤ፡ናሁ፡ድንግል፡ትጸንስ፡ወትወልድ፡ወልደ፡ወይሰመይ፡ስሙ፡ዐማኑኤል፡እስመ፡ሕፃን፡ተወልደ፡ለነ፡ወልድ፡ተውህበ፡ለነ፡ወሕይወት ፡ ኮነ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ። ወይሰመይ፡ስሙ፡ዐቢየ፡ምክር፡ወመልአከ፡ሰላም።

፳፪፤ እስመ፡አነ፡አመጽእ፡ሰላመ፡ለመላእክት፡ወሕይወትሰ፡ዚአሁ፡ወዕበይ፡ቅድሜሁ፡ወአልቦ፡ማኅለቅት፡ለሰላሙ።

በረከቶሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፴፡፯–፳።

ይቤ፡መምህረ፡ሃይማኖት፡ወትሩፋት፡አባ፡አቡሊዲስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡በውስተ፡መልእክቱ፡ኀበ፡ኵሎሙ፡ኤጲስቆጶሳት፡ውስተ፡መካናት።

፯፤ አአምን፡ርደቶ፡እምሰማያት፡ለአሐዱ፡ዘእምቅድስት፡ሥላሴ፡ወተሠግዎቶ፡እምእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ወአስተርእዮቶ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል፡መድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እምኔሃ፡ወአንሶስዎቶ፡ማእከለ፡ሰብእ፡እንዘ፡ውእቱ፡አምላክ፡ወሰብእ፡ኅቡረ።

፰፤ ወኢይቤ፡አሐዱ፡አምላክ፡ወካልኡ፡ብእሲ፡ኅቡረ፡አላ፡አሐዱ፡አካል፡ወአሐዱ፡ህላዌ፡ውእቱ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ምስለ ፡ ሥጋሁ፡ዘውእቱ፡እምእግዝእትነ፡ማርያም፡ወዝንቱ፡ውእቱ፡፩ዱ፡እምእግዚአብሔር፡ወውእቱ፡እምብእሲት።

፱፤ ወእንዘ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ የሐምም ፡ ወኢየሐምም ፡ የሐምም ፡ ወይትዌከፍ ፡ ሕማመ ፡ በሥጋሁ ፡ ወበመለኮቱ ፡ ይስእር ፡ ሕማመነ ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

### ትንቢት፡አላወቁም፤አላስተዋሉም።

፳፩፤ እነሆ ፡ ድንግል ፡ በድንግልና ፡ ትፀንሳለች፤ ወልድን፡ትወልዳለች፤ስሙም፡ዐማኑኤል፡ይባላል ፤ ሕፃን ፡ ተወልዶልናልና፤ ልጅም፡(ለልብሰተ፡ሥጋ)፡ተሰጠልን፤ሕይወትም፡በትከሻው፡ላይ፡ሆነ፤ስሙም፡ዐቢየ፡ምክር፡አበ፡ዓለም፡ንጉሠ፡ሰላም፡ይባላል፤ያለውን፡አላስተዋሉም።

፳፪፤ እኔ ፡ ለአለቆች ፡ ሰላምን ፡ አመጣለሁና፡ሕይወትም፡ገንዘቡ፡ነው፤በፊቱም፡ሥርዓተ፡መንግሥት ፡ ይሠራል ፤ በዘመኑም ፡ ለሚ[illegible] ረገው፡ተድላ፡ደስታ፡ፍጻሜ፡የለውም።

የሐዋርያት ፡ በረከታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡ ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፴፡፯–፳።

ሃይማኖትንና ፡ ትሩፋትን ፡ የሚያስተምር፡ የሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ አቡሊዲስ፡ በየቦታው ፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጶሳት፡ በላከው፡መልእክቱ፡እንዲህ፡አለ።

፯፤ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ከሰማይ፡ መውረዱን ፤ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ነፍስና ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መድ[illegible] ኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከእርሷ፡ ተወልዶ ፡ መገለጡን ፤ በተዋሕዶ ፡ ሰው፡ የሆነ፤ አምላክ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ መመ[illegible] ለሱን፡አምናለሁ።

፰፤ አንዱ፡አምላክ፡ነው፤አንዱ፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ነው፡አልልም፤እግዚአብሔር፡ቃል፡ከእመ ቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም፡ ከነሣው፡ሥጋው፡ጋር፡አንድ፡አካል፡አንድ፡ ባሕርይ፡ነው፡እንጂ፤ከእግዚአብሔር፡የተወ ለደው ፤ ከድንግል ፡ የተወለደው ፡ ይኸው፡ አንዱ፡ነው።

፱፤ አንድ፡ሲሆንም፡ይታመማል፡አይታመምም፡ በሥጋው ፡ ይታመማል ፤ ሕማማችንንም፡ ገንዘብ ፡ ያደርጋል ። በመለኮቱ ፡ ሕማ[illegible]

Scanned by CamScanner

| በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት። |
|---|---|
| ወበሞቱ ፡ ያበጥል ፡ ሞተነ ፡ ወውእቱ ፡ ዘጸገወነ፡ፈውሰ፡ለአግብርቲሁ። | ችንን ፡ ያርቃል ፤ በሞቱም ፡ ሞታችንን ፡ ያጠፋል ፡ ለእኛ ፡ ለአገልጋዮቹ ፡ ድኅነትን ፡ የሰጠን፡እርሱ፡ነው። |
| ፲፩ ወአብርሀ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ፡ ወወሀቦሙ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ፡ ወተድላ ፡ ሠናይተ፡እንተ፡ሀለዋ፡ትኩን፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡በርስት፡መለኮታዊ። | ፲፩ ለአመኑበትም ፡ ትንሣኤን ፡ ገለጠላቸው ፤ የዘላለም ፡ ሕይወትን ፡ በጌትነቱ ፡ በሚያወ ርሳት፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ትሰጥ፡ዘንድ፡ያላት፡ተድላ፡ነፍስንም፡ሰጣቸው። |
| ምዕ፤፵፩፡፲፪–፳። | ምዕ፤፵፩፡፲፪–፳። |
| ፲፪ ወካዕበ፡ይቤ፡እመቦ፡ዘይፈልጦ፡ለመድኅን፡ በእንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ወሕማማቲሁ ፡ ወይሰግድ፡ ለብእሲ ሀየንተ ፡እግዚአብሔር ፡ ወይብል ፡ እስመ ፡ ዘተሰቅለ ፡ ብእሲ ፡ ዕሩቅ ፡ እመለኮት ፡ ወያፈልስ ፡ መለኮተ ፡ ለከዊነ ፡ ትስብእት ፡ ኢይረክብ ፡ መድኃኒተ ፡ዘእግዚአ ብሔር፡ዘኮነ፡በትስብእቱ። | ፲፪ ዳግመኛም ፡ ሰው ፡ ስለመሆኑ ፡ መከራ ፡ ስለመ ቀበሉ ፡ መድኅንን ፡ የሚከፍለው ፡ ለእግዚአ ብሔር፡በመስገድ፡ፈንታ፡ለሰው፡የሚሰግድ፡ የተሰቀለውንም ፡ከመለኮት ፡ የተለየ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መለኮትንም ፡ ሥጋ ፡ ወደመሆን ፡ የሚለውጥ ፡ ቢኖር ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ሰው ፡ በመሆን ፡ ያደረገለትን ፡ ድኅነት፡አያገኝም፡አለ። |
| ፲፫ እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ሐመ ፡ ወሞተ፡ውእቱ፡አድኀነነ፡ወብእሲትሂ፡ሶበ፡ ወለደት ፡ አምላከ ፡ አምጽአት ፡ ሕይወተ ፡ ለዓለም ፡ ወዝንቱ ፡ ሶበ ፡ ተዘከረ ፡ በሰብእ ፡ አብጽሐ ፡ ለሰብእ ፡ ኀበ ፡ ሱታፌ ፡ ሕይወት ፡ ባሕቲቱ። | ፲፫ ከድንግል ፡ የተወለደው ፡ ታሞ ፡ ሙቷልና ፡ እርሱ ፡ አዳነን ፤ ድንግልም ፡ አምላክን ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ አስገኘች፤ይኸም፡በሰው፡ልቡና፡ቢታሰብ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ ወደ፡መምሰል፡አደረሰው። |
| ፲፬ ወበሞቱ፡አብጠለ፡ሞተ፡እምኔሆሙ፡ወበትን ሣኤሁ፡አፍለሶሙ፡ውስተ፡ሕይወት። | ፲፬ በሞቱ ፡ ሞትን ፡ ከእነርሱ ፡ አጠፋ ፤ በትንሣ ኤውም፡ወደ፡ሕይወት፡መለሳቸው። |
| ፳ እመሰ፡መድኃኒት፡ኮነ፡እምእግዚአብሔር፡ ወአኮ፡እምካልእ፡ወተሐደሰ፡ዓለም፡ዳግመ፡ ዘሂ ፡ ተወልደ ፡ ተሰቅለ ፡ ወሐመ ፡ መድኅን ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ዘወለደቶ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ብእሲ ፡ ዕሩቅ ፡እመለኮት ፡ ወኢዘሰ ቀልዎ ፡ አይሁድ ፡ ብእሲ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ አምላክ ፡ ዘተወልደ ፡ በሥጋ ፡ እምብእሲት ፡ ወኪያሁ፡ሰቀሉ፡አይሁድ። | ፳ ድኅነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከተገኘ ፡ ከሌላ ፡ ካልተገኘ ፡ ዳግመኛ ፡ ዓለምም ፡ በርሱ ፡ ከታደሰ፡ የተወለደው ፡ የተሰቀለው ፡ መከራ ፡ የተቀበለው ፡ መድኅን ፡ ነው ።እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የወለደችው ፡ ከመለኮት ፡ የተለየ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አይደለም። ከድንግል ፡ በሥጋ ፡ የተወለደ ፡ አምላክ፡ ነው፡እንጂ፤አይሁድም፡የሰቀሉት፡ እርሱ፡ነው፡እንጂ። |
| በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። | በረከቱ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑር ፡ አሜን። |
| ምንተኑ ፡ በል ፡ ወዙሉ ፡ ሥርዓቱ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ። | ምንተኑ ፡ በል ፡ ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አለፈው፡ነው። |

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ ወሀሎ፡አሐዱ፡ብእሲ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡ቊስጥንጥንያ፡ዘስሙ፡ዮሐንስ፡አፈወርቅ።

፪፤ ወእንዘ፡ሀሎ፡ውእቱ፡እምቅድመ፡ይንሣእ፡ሢመተ፡ቅስና፡ወሊቀ፡ጵጵስና፡ወሀቦ፡ጴጥሮስ፡መራኁተ፡ወዮሐንስ፡ወንጌለ፡ወሀቦ።

፫፤ ወይቤልዎ፡ኢትፍራህ፡ዘአሰርከ፡በምድር፡ይኩን፡እሱረ፡በሰማያት፡ወዘፈታሕከ፡በምድር፡ይኩን፡ፍቱሐ፡በሰማያት።

፬፤ አእምር፡አ፡ዳንኤል፡ሐዲስ፡ዘኀደረ፡ውስቴትከ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡እስመ፡ንሕነ፡ተፈኖነ፡ኀቤከ፡እመምህርነ፡ዐቢይ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፭፤ ወአነ፡ውእቱ፡ጴጥሮስ፡ዘተውህበኒ፡መራኁተ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ወናሁ፡ወሀብኩከ፡መራኁተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡እለ፡ውስተ፡ኵሉ፡ዓጽናፈ፡ዓለም።

፮፤ ወይቤሎ፡ካልኡኒ፡አነ፡ውእቱ፡ዮሐንስ፡ዘተናገርኩ፡በጥንተ፡ስብከትየ፡በወንጌል፡ወእቤ፡በቀዳሚ፡ሀሎ፡ቃል፡ውእቱ፡ሀሎ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ወእግዚአብሔር፡ውእቱ፡ቃል፡ወኮነ፡ውእቱ፡ከመ፡ሰይፈ፡እሳት፡ላዕለ፡ጸላዕያን።

፯፤ ካዕበ፡ናሁ፡ተውህበ፡ለከ፡ዝ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወአእምሮ፡ዘበአማን፡ከመ፡ትሕፅኖሙ፡ለሕዝብ፡በርትዕት፡ሃይማኖት።

፰፤ ወእንዘ፡ይጼሊ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡በአሐቲ፡ሌሊት፡ናሁ፡አስተርአየቶ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ምስለ፡መልአክ፡በልብስ፡ጸዐዳ፡ከመ፡በረድ፡ናዘዞቶ፡ወአጽንዐቶ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ልመናዋ፡በረከቷ፡በእኛ፡ላይ፡ለዘላለሙ፡ይደርብንና፡በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የምትሆን፡እመቤታችን፡ቅድስት፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ የቊስጥንጥንያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡የሆነ፡ስሙ፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡የሚባል፡አንድ፡ሰው፡ነበረ።

፪፤ እርሱም፡የቅስናና፡የሊቀ፡ጵጵስና፡ሹመት፡ከመቀበሉ፡በፊት፡ጴጥሮስ፡መክፈቻ፡ሰጠው፤ዮሐንስም፡ወንጌልን፡ሰጠው።

፫፤ አትፍራ፡አይዞህ፡በምድር፡ያሰርከው፡በሰማያት፡የታሰረ፡ይሁን፤በምድርም፡የፈታኸው፡በሰማይ፡የተፈታ፡ይሁን፡አሉት።

፬፤ መንፈስ፡ቅዱስ፡ያደረብህ፡አዲስ፡ዳንኤል፡ሆይ፡እኛ፡ከታላቁ፡መምህራችን፡ከኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘንድ፡ወደአንተ፡እንደተላክን፡ዕወቅ፡አሉት።

፭፤ የመንግሥተ፡ሰማይ፡መክፈቻ፡የተሰጠኝ፡እኔ፡ጴጥሮስ፡ነኝ፤እነሆ፡በዓለም፡ዳርቻ፡ሁሉ፡ላለች፡ቤተ፡ክርስቲያን፡መክፈቻ፡ሰጠሁህ፡አለው።

፮፤ ሁለተኛውም፡በጥንተ፡ስብከቴ፡በወንጌል፡ውስጥ፡ቃል፡አስቀድሞ፡አለ፤ያ፡ቃልም፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ነበረ፤እርሱም፡እግዚአብሔር፡ነው፡ብዬ፡የተናገርኩ፡እኔ፡ዮሐንስ፡ነኝ፤ይኸውም፡በመናፍቃን፡ላይ፡እንደ፡እሳት፡ሰይፍ፡ሁኖአል።

፯፤ ዳግመኛም፡እነሆ፡ከእግዚአብሔር፡አብ፡ከጌታችን፡ከኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘንድ፡ይህ፡እውነተኛ፡ዕውቀት፡ተሰጠህ፤በትክክለኛ፡በቀናች፡ሃይማኖት፡ምእመናንን፡ታጸናቸው፡ዘንድ።

፰፤ በአንዲት፡ሌሊትም፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ሲጸልይ፡እነሆ፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ቅድስት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ከመልአክ፡ጋራ፡ብሩህ፡ልብስ፡በመያዝ፡ተገልጻ፡አረጋጋችው፤አጸናችው።

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፱፤ ርእዩኬ ፡ ደቂቀ ፡ ወንጌል ፡ ዘከመ ፡ ታስተር እዮሙ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ወትናዝዞሙ፡ለቅዱሳን።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
ለተአምርኪ፡ማርያም፡ቅንኢ፡ቅንአተ፡በል።
ሃሌ፡ሉያ፡በብዝኀ፡ኂሩትኪ፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘከመ ፡ ተናገረ ፡ ሥራዌ ፡ ክህነቶሙ ፡ ወፍልሰተ ፡ መንግሥቶሙ ፡ ወጥፍአቶሙ ፡ ለአይሁድ፡በአፈ፡ኒቆዲሞስ፡ሊቆሙ።
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሃሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ ይቤሎሙ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ለአይሁድ ፡ እምይእዜሰ ፡ ትጠፍኡ ፡ ወትዘረዉ ፡ ውስተ ፡ አጽናፈ፡ምድር።

፪፤ ወትከውኑ ፡ ጽሉአነ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ፡ ወታኀስሩ፡እምኵሎሙ፡አሕዛብ፡ወይረግመክሙ፡ኵሉ፡ዘርእየክሙ።

፫፤ ወትከውኑ፡ትሑታነ፡ወፍሉጣነ፡እምኵሉ፡ወትትመዘበር ፡ ሀገርክሙ ፡ ወትፈልስ ፡ እምኔክሙ ፡ መንግሥት ፡ ወክህነት ፡ ወትንቢት ፡ ወመሥዋዕት ፡ በከመ ፡ እቤለክሙ፡ ቀዲሙ፡ወይነሥእዋ፡ለጽዮን፡እምኔክሙ።

፬፤ ወትከውን ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ማኀደረ ፡ አራዊት ፡ ወእንስሳ ፡ ወአእዱግ ፡ ገዳም ፡ ወበዓተ፡ፈያት።

፭፤ ወሀየንተ ፡ ዝክረ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክቡር፡ ይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሔስዉ፡ግብሮ።

፮፤ ፍርሀዎ፡ለእግዚአብሔር፡በኵሉ፡ልብክሙ፡ወተጋደሉ፡ከመ፡ኢይቅድሙክሙ፡አሕዛብ፡ርኁቃን ፡ በዊአ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፱፤ የወንጌል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ቅዱሳንን ፡ ተገልጻ ፡ እንደምታረጋጋቸው፡እንደምታጽናናቸው፡እዩ።
ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር፡አሜን።
ለተአምርኪ፡በል።
ሃሌ፡ሉያ፡በብዝኀ፡ኂሩትኪ፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

መንግሥት ፡ ክህነት ፡ ከአይሁድ ፡ እንደሚፈልስ፡እነርሱም፡እንደሚጠፉ፡በአለቃቸው፡በኒቆዲሞስ ፡ አፍ ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ አምላካችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የተናገረውና፡ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
ይቅርታው ፡ ቸርነቱ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር፡አሜን።

፩፤ ኒቆዲሞስም፡እንዲህ፡አላቸው፤ከእንግዲህ፡ትጠፋላችሁ፤በምድር፡ዳርቻ፡ሁሉ፡ትበተናላችሁ።

፪፤ በአሕዛብ፡ሁሉ፡ዘንድ፡የተጠላችሁ፡ትሆናላችሁ፤ከሕዝቡ፡ሁሉ፡የጐሰቈላችሁ፡ትሆናላችሁ፤ያያችሁም፡ሁሉ፡ይረግማችኋል።

፫፤ በሁሉ፡ዘንድ፡የተዋረዳችሁና፡የተለያችሁ፡ትሆናላችሁ ፤ ሀገራችሁም ፡ ትጠፋለች ። አስቀድሜ ፡ እንደነገርኳችሁ ፡ መንግሥት ፡ ክህነት ፡ ትንቢት ፡ መሥዋዕት ፡ ከእናንተ ፡ ይቀራል ። ጽዮንንም ፡ ከእናንተ ፡ ይወስድዋታል።

፬፤ ቅድስት ፡ ሀገር ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የአራዊት ፡ የእንስሳ ፡ የበረሀ ፡ እህያ ፡ መሰማሪያ ፡ የወንበዴ፡ዋሻ፡ትሆናለች።

፭፤ የከበረ፡የእግዚአብሔርን፡ስም፡በመጥራት፡ፈንታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሰድባሉ ፤ ሥራውንም፡ሐሰት፡ነው፡ይላሉ።

፮፤ በፍጹም፡ልቡናችሁ፡እግዚአብሔርን፡ፍሩት፤ርቀው፡ያሉ፡አሕዛብ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡መግባትን ፡ እንዳይቀድሟችሁ ፡ ታገሉ።

በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ወትርኅቁ ፡ አንትሙ ፡ ደቂቀ ፡ መንግሥት ፡
እምኔሃ።
፯፡ ወይወድዩክሙ ፡ ውስተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘለዓለም ፡
ወይከውን ፡ ክፍልክሙ ፡ ምስለ ፡ ከይሲ ፡
ዘይጸንሕ ፡ ፍኖተ ፡ ወርስትክሙ ፡ ምስለ ፡
ወልደ ፡ ኀጕል ፡ ዘይሰሚ ፡ ነፍሶ ፡ በስመ ፡
ክርስቶስ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

እመ፡ትመጽእ፡በል፤ወኵሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡
ቀዳሚ።

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፻፳፩፡፩-፫።

ተፈሣሕኩ፡እስመ፡ይቤሉኒ፡ቤተ፡እግዚአ
ብሔር፡ነሐውር። ወቆማ፡እገሪነ፡ውስተ፡
አዕጻድኪ ፡ ኢየሩሳሌም ። ኢየሩሳሌምሰ ፡
ሕንጽት፡ከመ፡ሀገር።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፤፳፩፡፲፰-፳፪።

፲፰፡ ወጸቢሖ፡እንዘ፡የዓርግ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ሀገረ፡ርኅበ።
፲፱፡ ወርእየ፡ዕፀ፡በለስ፡በፍኖት፡ወሖረ፡ኀቤሃ፡
ይንሣእ ፡ ፍሬ ፡ እምኔሃ ፡ ወአልቦ ፡ ዘረከበ ፡
ውስቴታ፡ዘእንበለ፡ቈጽል፡ባሕቲቱ፡ወይቤላ፡
ኢይኩን፡እንከ፡ፍሬ፡እምውስቴትኪ፡ለዓለም፡
ወየብሰት፡በጊዜሃ፡ይእቲ፡በለስ።
፳፡ ወርእዮሙ ፡ አርዳኢሁ ፡ አንከሩ ፡ ወይቤሉ ፡
እፎ፡በጊዜሃ፡የብሰት፡ዛቲ፡በለስ።
፳፩፡ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡
አማን፡እብለክሙ፡እመ፡ብክሙ፡ሃይማኖት፡
ወኢትናፍቁ ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ ዕፀ ፡ ባሕቲቶ ፡
ዘትገብሩ ፡ አላ ፡ ለዝንቱ ፡ ደብር ፡ ለእመ ፡
ትብልዎ ፡ ተንሥእ ፡ ወተወረው ፡ ውስተ ፡
ባሕር፡ይከውን፡ለክሙ።

እናንተም ፡ የመንግሥት ፡ ልጆች ፡ ስትሆኑ፡
ከእርሷ፡ትርቃላችሁ።
፯፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሥቃይ ፡ ይጨምሩአችኋል፤
ዕድል ፡ ፈንታችሁም ፡ በመንገድ ፡ ላይ፡
ከሚጠብቅ፡ከይሲ፡ጋራ፡ርስታችሁም፡እግዚ
አብሔርነቱ፡በሥጋ፡በአከበረው፡በክርስቶስ፡
ስም ፡ ክርስቶስ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ከሚመጣው፡
ከሐሳዊ፡መሲሕ፡ጋር፡ይሆናል።
ቸርነቱ፡ይቅርታው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡በል፤ሥርዓቱ፡ሁሉ፡እንደ
ለፈው፡ነው።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፻፳፩፡፩-፫።

ወደ፡እግዚአብሔር፡ቤት፡እንሄዳለን፡ብለው
ኛልና፡ደስ፡አለኝ። ኢየሩሳሌም፡ሆይ፡እግሮ
ቻችን፡በዓጸዶችሽ፡ቁመዋልና፡ደስ፡አለኝ፡
ኢየሩሳሌምም፡እንደ፡ ሀገርነቷ፡የታነጸች፡
ናት፡ይበል።

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፩፡፲፰-፳፪።

፲፰፡ በነጋም፡ጊዜ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ከሀገር፡ሲወጣ፡
ተራበ።
፲፱፡ በመንገድም፡የበለስ፡ዛፍ፡አይቶ፡ከርሷ፡ፍሬ፡
ሊአገኝ፡ወደርሷ፡ሄደ፤ግን፡ከቅጠል፡በቀር፡
ያገኘባት፡የለም፤እንግዲህ፡ወዲህ፡ለዘላለም፡
ፍሬ ፡ አይገኝብሽ ፡ አላት ፤ ያችም ፡ በለስ፡
ወዲያውኑ፡ደረቀች።
፳፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ አይተው ፡ በለሲቱ፡
እንዴት ፡ ወዲያውኑ ፡ ደረቀች ፡ ብለው፡
አደነቁ።
፳፩፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡መልሶ፡ሃይማኖት፡ቢኖራ
ችሁና ፡ ባትጠራጠሩ ፡ በበለስ ፡ እንደተደ
ረገው፡ ብቻ ፡ የምታደርጉ ፡ አይደለም፤
ይህንንም፡ተራራ፡ተነሥተህ፡ወደ፡ባሕር፡
ተወርወር፡ብትሉት፡ይደረግላችኋል፡እንጂ፡
አላቸው።

Scanned by CamScanner

## በ፫፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፱፤ ወኵሎ ፡ ዘሰአልክሙ ፡ በጸሎት ፡ እንዘ ፡ ትትአመኑ፡ትነሥኡ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በሠለስቱ፡ሰዓት፡ዘሰኑይ።

፩፤ በሠርክ፡ዕለት፡ቡሩክ፡ወፅአ፡አፍአ፡ሀገር፡ ምስለ፡አርዳኢሁ።

፪፤ ክርስቶስ ፡ እምላክነ ፡ ርህበ ፡ ወኀሠሠ ፡ መንገለ፡መብልዕ፡ወርእየ፡በለስ፡እምርኁቅ፡ ወሖረ፡ኀቤሃ፡ከመ፡ይኅሥሥ፡በውስቴታ፡ ፍሬ፡ወኢረከበ፡ዘእንበለ፡ቈጽል፡ባሕቲቱ፡ ወረገማ፡ወየብሰት፡እምሥረዊሃ።

፫፤ ወአርዳኢሁ ፤ አንከሩ ፡ ወይቤልዎ ፡ ለእግዚእነ፡ናሁ፡የብሰት፡ዛ፡በለስ።

፬፤ ይቤ ፡ ለሊሁ ፡ ረስዩ ፡ ለክሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ ውስተ ፡ አልባቢክሙ ፡ ወኵሉ ፡ ይትኤዘዘክሙ።

፭፤ ኢታንክሩ፡በእንተ፡ዛቲ፡ዕፀ፡በለስ፡እስመ፡ በአሐቲ፡ቃል፡የብሰት፡እምጕንዳ።

፮፤ ለእመ፡ብክሙ፡ሃይማኖት፡ይከውን፡ለክሙ፡ ከመ፡ታፍልሱ፡ዛተ፡ደብረ፡እመካና።

፯፤ ንዑ፡ርእዩ፡አ፡አብዳን፡ዘኮነ፡እምዛቲ፡በለስ። ግበሩ፡ሠናየ፡ፍሬ፡ለእግዚአብሔር፡ግበሩ፡ ንስሓ ፡ አ ፡ ሀካያን ፡ ከመ ፡ ትትመጠዉ ፡ ሥርየተ።

፰፤ ኀፅቡ፡ገጸቲክሙ፡በአንብዕ፡ብዙኅ፡እስመ፡ በአንብዕ፡ይደመሰስ፡አበሳ። አኀትዉ፡መኃትዊክሙ፡በትሩፋት፡ከመ፡ያብርህ፡ለክሙ፡ በውስተ፡መካነ፡ፍትሕ።

፱፤ ሕምም ፡ በእንተ ፡ እጉከ ፡ ወርኢ ፡ ከመ ፡ እግዚእ ፡ ኵሉ ፡ ሐመ ፡ በእንቲአከ ፡ ከመ ፡ ያድኅንከ።

፲፤ ለንሰብሕ ፡ ስሞ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ገብረ ፡ ምስሌነ፡ምሕረተ፡በከመ፡ዕበየ፡ምሕረቱ። ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል፤ ወኵሉ፡ ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

፳፱፤ አምናችሁ፡በጸሎት፡የለመናችሁትን፡ሁሉ፡ ታገኛላችሁ።

ሰኞ፡በሦስት፡ሰዓት፡ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ።

፩፤ ዕለቱ፡ሲመሽ፡ቡሩክ፡ጌታ፡ከከተማው፡ወደ፡ ውጭ፡ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡ወጣ።

፪፤ ፈጣሪያችን ፡ ክርስቶስ ፡ ተርቦ ፡ ምግብን ፡ ፈለገ፤ ከሩቅም ፡ በለስን ፡ አይቶ ፡ በውስጥዋ ፡ ፍሬን ፡ ሊሻ ፡ ወደርሷ ፡ ሄደ ፤ ከቅጠል ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ያገኘው ፡ የለም ፤ ረገማትም ፡ ከሥርዋ ፡ ጭምር፡ደረቀች።

፫፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ አድንቀው ፡ ጌታችንን ፡ እነሆ፡ይቺ፡በለስ፡ደረቀች፡አሉት።

፬፤ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ጌታ ፡ ለእናንተ ፡ በልቡናችሁ ፡ ፍጹም ፡ ሃይማኖትን ፡ አሳድሩ ፤ ይህ ፡ ከሆነ ፡ ሁሉም፡ይታዘዝላችኋል፡አለ።

፭፤ ስለዚችም ፡ የበለስ ፡ ዕንጨት ፡ አታድንቁ ፤ በአንዲት ፡ ቃል ፡ ከግንዷ ፡ ጀምሮ ፡ ስለደረቀች።

፮፤ ሃይማኖት፡ካላችሁ፡ይቺን፡ተራራ፡ከቦታዋ፡ ትንቅሉ፡ዘንድ፡ይደረግላችኋል።

፯፤ ሰነፎች፡ሆይ፡በበለሲቱ፡ላይ፡የተደረገውን፡ ኑ ፡ እዩ ። ለእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ በጎ፡ፍሬ፡አድርጉ ፤ ታካቾች ፡ ሆይ ፡ ለኃጢአታችሁ፡ስርየት፡ታገኙ፡ዘንድ፡ንስሓ፡ግቡ።

፰፤ ፊታችሁንም፡በብዙ፡ዕንባ፡እጠቡ፤ በዕንባ፡ በደል፡ይደመሰሳልና፤ ትሩፋት፡በመሥራት፡ መብራታችሁን፡አብሩ፤ በፍርድ፡ቦታ፡ያበራላችሁ፡ዘንድ።

፱፤ ስለ ፡ ወንድምህ ፡ መከራ ፡ ተቀበል ፤ ያድንህ ፡ ዘንድ፡የሁሉ፡ጌታ፡ስላንተ፡መከራ፡እንደተቀበለ፡አስተውል።

፲፤ ስሙን፡እናክብር፤ እናመስግን፤ እርሱ፡እንደርኅራኄው፡ገናናነት፡ከእኛ፡ጋራ፡ቸርነትን፡አድርጓልና። መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሁኖ፡ መከራ፡ተቀበለ፤ በመከራውም፡አዳነን።

በእንተ ፡ ጽንዐ ፡ ዛቲ፡ በል ፤ ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ይ፡ካ፡ሑሩ፡ወዕትዉ፡በሰላም።
እግዚአብሔር ፡ የሃሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ ንዑ ፡
ወተጋብኡ፡በጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓተ፡መዐልት፡
ለጸሎት።

## ምዕራፍ፡፲፪።

ትእዛዝ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡ በስድስቱ ፡
ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘሰኑይ ፡ ወይጸልዩ ፡
መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ዘይቤ ፡ አኮኑ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ትገኒ፡ነፍስየ፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ወአ
ጽገቦሙ፡መዓረ፡እምኰኵሕ።
ውዳሴ፡ማርያም፡ዘረቡዕ።

ሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ካህኑ ፡ በሰላም ፡ ሂዱ ፡ እግዚአብሔር ፡
ክእናንተ፡ ጋር ፡ ይሁን ፤ ከቀኑ ፡ በስድስት ፡
ሰዓት፡ለጸሎት፡ኑ፤ተሰብሰቡ፡ይበል።

## ምዕራፍ፡፲፪።

ካህናት፡ሰኞ፡ከቀኑ፡በስድስት፡ሰዓት፡ተሰብ
ስበው ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ አኮኑ ፡
የሚለውን ፡ ወአጽገቦሙ ፡ መዓረ ፡
እምኰኵሕ፡እስከሚለው፡ይጸልዩ።

የረቡዕን ውዳሴ፡ማርያም፡ይድገሙ።

ወይበል ፡ መራሒ ፡ በ፩ ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በወንጌል ፡ ለዘመሀረነ ፡ በኦሪት ፡ ወበነ
ቢያት ፡ ለዘናዘዘነ ፡ በከመ ፡ መሀረነ ፡ እግዚእነ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ናምልኮ ፡ ለዘፈጠረነ ። ወእምዝ፡
ይበሉ፡ለከ፡ኃይል፡ዐሥርተ፡ወክልኤተ፡ጊዜ።

### ክፍል፡፩።

ምንባብ፡ዘስድስቱ፡ሰዓት፡ዘሠኑይ።

ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፤፴፪፤፯–፲፰።

፯፤ ወነበቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ወይቤሎ ፡
ሑር ፡ ወአፍጥን ፡ ወሪደ ፡ እምዝየ ፡ እስመ ፡
አበሱ ፡ ሕዝብከ ፡ ዘአውፃእከ ፡ እምድረ ፡
ግብጽ፡ወወፅኡ፡እምፍኖት፡ዘአዘዝክዎሙ።
፰፤ ወገብሩ፡ላሕመ፡ወሰገዱ፡ወሦዑ፡ሎቱ።
፱፤ ወይቤሉ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ አማልክቲከ ፡
እስራኤል፡ዘአውጽኡከ፡እምድረ፡ግብጽ።
፲፤ ወይእዜኒ ፡ ኅድገኒ ፡ እጥስዮሙ ፡ በመዐትየ ፡
ወእሰይመከ፡ላዕለ፡ሕዝብ፡ክቡድ፡ወዐቢይ።
፲፩፤ ወሰአለ ፡ ሙሴ ፡ ቅድመ ፡ አምላኩ ፡ ወይቤ ፡
ለምንት ፡ እግዚእ ፡ መዐተ ፡ ትትመዐዕ ፡ ላዕለ ፡
ሕዝብከ ፡ ዘአውፃዕከ ፡ እምድረ ፡ ግብጽ ፡
በኃይል ፡ ጽኑዕ ፡ ወበመዝራዕት ፡ ልዑል ፡
ወዓቢይ።
፲፪፤ ከመ፡ኢይበሉ፡ግብጽ፡በእኩይ፡አውፅአሙ፡
ከመ፡ይቅትሎሙ፡በውስተ፡አድባር፡ወከመ፡
ያጥፍአሙ ፡ እምድር ፡ አቍርር ፡ መዐተከ ፡

### ክፍል፡፩።

ሰኞ፡በስድስት፡ሰዓት፡የሚነበብ።

ኦሪት፡ዘፀአት።

ምዕ፤፴፪፤፯–፲፰።

፯፤ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ነገረው ፤ ከምድረ፡
ግብጽ፡ያወጣኋቸው፡ወገኖችህ፡በድለዋልና፡
ካዘዝኳቸውም፡ሕግ፡ወጥተዋልና።
፰፤ ላምንም ፡ ሠርተው ፡ ሰግደውለታልና ፡ መሥ
ዋዕትም፡ሠውተውለታልና።
፱፤ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ያወጡህ ፡ ፈጣሪዎችህ፡
እኒህ፡ናቸው፡ብለዋልና።
፲፤ አሁንም ፡ ተቈጥቼ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ፡
ተወኝ፤ አንተንም ፡ ፈጽሞ ፡ ብዙ ፡ በሆነ፡
ሕዝብ፡ላይ፡እሾምሃለሁ፡ብሎ፡ነገረው።
፲፩፤ ሙሴም ፡ አቤቱ ፡ በጽኑ ፡ ኃይልና ፡ በታላቅ፡
እጅ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣሃቸው፡
ወገኖችህ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ጽኑ ፡ ቁጣን፡
ትቆጣለህ፡ብሎ፡በፈጣሪው፡ፊት፡ለመነ።
፲፪፤ በተራራ፡ላይ፡ይገላቸው፡ዘንድ፡ከምድርም፡ፊት፡
(ከኢየሩሳሌምም)፡ያጠፋቸውም፡ዘንድ፡የግብጽ፡
ሰዎች፡በክፉ፡ነገር፡አወጣቸው፡እንዳይሉ፡የተቆ

Scanned by CamScanner

## በ፯፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ዘተማዕከ፡ወመሐሬ፡ኩን፡ላዕለ፡እከዮሙ፡
ለሕዝብከ።
፲፫፤ ተዘከር፡አብርሃምሃ፡ወይሥሐቅሃ፡ወያዕ
ቆብሃ፡አግብርቲከ፡ዘመሐልከ፡ሎሙ፡
በርእስከ፡ወትቤሎሙ፡ብዙኀ፡አበዝኖ፡ለዘር
እክሙ፡ከመ፡ከዋክብተ፡ሰማይ፡ብዙኀ፡
ወኵሎ፡ዘንተ፡እሁብ፡ለዘርእክሙ፡ወይመ
ልክዋ፡ለዓለም።
፲፬፤ ወሰረየ፡እግዚአብሔር፡በእንተ፡እኪት፡
ዘይቤ፡ይግበር፡ላዕለ፡ሕዝብ።
፲፭፤ ወተመይጠ፡ሙሴ፡ወወረደ፡እምደብር፡
ወ፪ኤቱ፡ጽላት፡ዘትእዛዝ፡ውስተ፡እደዊሁ፡
ጽላት፡ዘእብን፡ወጽሑፋት፡እንተ፡ክልኤ፡
ገበዋቲሆን።

ጥበበ፡ሰሎሞን፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፩፡፩–፯።

፩፤ አፍቅርዋ፡ለጥበብ፡አ፡መኳንንተ፡ምድር፡
ወኀልዩ፡ኃይለ፡እግዚአብሔር፡በአእምሮ፡
ሠናይ፡ወበስፉሕ፡ልብ፡ኅሥዎ።
፪፤ እስመ፡ውእቱ፡ይትረከብ፡በኀበ፡እለ፡ኢያሜ
ክርዎ፡ወያስተርኢ፡በኀበ፡እለ፡ኢይክ
ህድዎ።
፫፤ እስመ፡ጠዋይ፡ኀሊና፡ያርኁቅ፡እምእግዚአ
ብሔር፡ኃይል፡ፍትንት፡ትዘልፎሙ፡
ለአብዳን።
፬፤ እስመ፡ውስተ፡ምይንት፡ነፍስ፡ኢትበውዕ፡
ጥበብ፡ወኢተኀድር፡ውስተ፡ሥጋ፡ዘቅኑይ፡
ለኃጢአት።
፭፤ እስመ፡መንፈስ፡ተግሣፅ፡ቅዱስ፡ያጕይይ፡
ትምህርተ፡ዘእከይ፡ወይትነሣእ፡በመዊዕ፡
እምኀሊናሆሙ፡ለአብዳን፡ወይዘልፍ፡እኩየ፡
ሶበ፡ይመጽእ።
፮፤ እስመ፡መፍቀሬ፡ሰብእ፡መንፈሰ፡ጥበብ፡
ወኢያነጽሕ፡ፀራፌ፡እምከናፍሪሁ፡እስመ፡
እግዚአብሔር፡ስምዕ፡ላዕለ፡ኵልያቲሁ፡
ወሐዋፂ፡ህልው፡ይሔውፅ፡ልቦ፡ወልሳኖ፡
ሰማዒ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

ጣኸው፡ቍጣህን፡አብርድ፤የወገኖችህን፡
ኃጢአት፡ይቅር፡የምትል፡ሁን።
፲፫፤ ልጆቻችሁን፡ብዙ፡እንደሆኑ፡እንደ፡ሰማይ፡
ከዋክብት፡ፈጽሜ፡ማብዛትን፡አበዛዋለሁ፤
ይኸንንም፡ሁሉ፡ለልጆቻችሁ፡እሰጣለሁ፤
ዓለምንም፡ይገዟታል፡ብለህ፡በራስህ፡የማል
ክላቸው፡ባሮችህን፡አብርሃምንና፡
ይሥሐቅን፡ያዕቆብንም፡አስብ፡አለ።
፲፬፤ እግዚአብሔርም፡በሕዝቡ፡ያደርገው፡ዘንድ፡
የተናገረውን፡ክፉ፡ነገር፡ይቅር፡አለ።
፲፭፤ ሙሴም፡ተመልሶ፡ከደብረ፡ሲና፡ወረደ፤
በወዲያና፡በወዲህ፡በሁለት፡ወገን፡ዐሠርቱ፡
ቃላት፡የተጻፉባቸው፡ሁለት፡የዕንቍ፡
ጽላቶች፡በእጆቹ፡ነበሩ።

የሰሎሞን፡የጥበብ፡ነገር፡ይህ፡ነው።
የፈጣሪው፡በረከት፡ከሁላችን፡ጋራ፡
ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ምዕ፤፩፡፩–፯።

፩፤ ይህን፡ዓለም፡የምትገዙ፡መኳንንት፡ጥበብን፡
ውደዱት፤የእግዚአብሔርን፡ኃይል፡አስቡ፤
በበጎ፡ዕውቀት፡በሰፊ፡ልቡና፡ፈልጉት።
፪፤ በማይፈታተኑት፡ሰዎች፡ዘንድ፡ይገኛልና፡
በማይክዱት፡ሰዎችም፡ዘንድ፡ይገለጣልና፡
ፈልጉት።
፫፤ ጠማማ፡ልቡና፡ከእግዚአብሔር፡ያርቃልና፡
የተፈተነች፡ኃይል፡አላዋቆችን፡ትዘልፋቸ
ዋለች።
፬፤ በተንኰለኛ፡ሰውነት፡ውስጥ፡ጥበብ፡
አትገባም፤ለኃጢአት፡ከምትገዛ፡ሰውነትም፡
ውስጥ፡አታድርምና።
፭፤ ምክር፡እዝናት፡የሚገልጽ፡የከበረ፡መንፈስ፡
ቅዱስ፡ክፉ፡የሚሆን፡(የዲያብሎስን)፡
ትምህርት፡ያርቃልና፡ከአላዋቆችም፡ልቡና፡
ድል፡ነሥቶ፡ይሂዳልና፡በመጣ፡ጊዜ፡
ክፉውን፡ይዘልፈዋል።
፮፤ ጥበብን፡የሚገልጽ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ሰው፡
ወዳጅ፡ነውና፡በከንፈሩ፡የሚሳደበውን፡ከፍዳ፡
አያነጻውም፤እግዚአብሔር፡ኵላሊት፡በሚያ
ጤሰው፡ነገር፡ምስክር፡ነውና፡ነዋሪ፡ጉበኛ፡
የሚሆን፡እርሱ፡ልቡናውን፡ይመረምረዋል፤
በአንደበቱም፡የተናገረውን፡ነገር፡ይሰማዋል።

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፩ እስመ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልዐ ፡ ዓለመ፡ ወዘይእኅዝ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ያገምር ፡ አእምሮ፡ቃሎሙ።

፳፪ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይትኀባእ ፡ እምኔሁ ፡ ወኢምንትኒ፡እምዘይትነገር፡ቃለ፡ዓመፃ።

፳፫ እስመ ፡ ኢይትዓደዎ ፡ ኵነኔሁ ፡ በከሢተ ፡ ግብሩ ፡ እስመ ፡ ለረሲዓን ፡ የሐትቶሙ ፡ በምክረ ፡ ኀሊናሆሙ ፡ ወድምፀ ፡ ንባቦሙ ፡ ይበጽሕ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዝልፈተ ፡ አበሳሆሙ።

### ክፍል፡፪።
### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፵፫፡፩–፯።

፩ ይቤ፡መጥሊሳን፡ኮኑ፡ሕጉላነ፡ኢማእምራነ፡ርትዕተ፡ሃይማኖት፡ከመ፡አሐዱ፡ህላዌሁ፡ለወልድ፡ምስለ፡ሥጋሁ።

፪ ለእመ፡ኮነ፡አሐደ፡ህላዌ፡በአማን፡ውእቱ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡ዘተወልደ፡በዘኢይትረከብ፡አምሳል፡ወሶበሂ፡ነሥአ፡ሥጋነ፡ኢነሥአ፡ሥጋ፡ዘእንበለ፡ነፍስ፡አላ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡ለባዊት፡ወነባቢት፡ወአስተርአየ፡ብእሲ፡ወሂእ፡እምብእሲት።

፫ ወበዝሂ፡ግብር፡ኢይትከፈል፡ኀበ፡፪ኤ፡አካል፡ወኢይትበሃል፡፪ኤተ፡አላ፡አሐዱ፡ግብሩ፡ዘከመ፡ትካት፡እንበለ፡ፍልጠት።

፬ ወአኮ፡ውእቱ፡እንበለ፡ሥጋ፡ወኢሂ፡ሥጋሁ፡በምትሐት፡አላ፡ውእቱ፡ሥጋሁ፡እሙነ፡በተዋሕዶ፡ዘእንበለ፡ፍልጠት፡ወዘእንበለ፡ውላጤ፡ወኢክፍለት፡ወዘኢየአምን፡ዘንተ፡ያጤይቀነ፡ከመ፡ውእቱ፡ንፉቅ።

፭ ወዓዲ፡ንብል፡አልቦቱ፡ቱሳሔ፡ወኢካልእ፡ነገር፡ዘከመዝ፡ወኢይተልዎ፡ንባበ፡ቱሳሔ፡በእንተ፡ነገረ፡ተዋሕዶቱ፡ዘበአማን።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፳፩ የእግዚአብሔር፡ሕይወቱ፡መንፈስ፡ቅዱ[ስ] በዓለም ፡ መልቷልና ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ፡ በመሐል፡እጁ፡የሚይዝ፡እርሱ፡ነገራቸውን፡ ፈጽሞ፡ያውቃልና።

፳፪ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ከሚነገር ፡ ከሐሰት፡ ነገራቸው፡ምንም፡ምን፡ከሱ፡አይሠወርም፡

፳፫ በልቡናቸው፡በመከሩት፡ምክር፡ሕገ፡እግዚ አብሔርን፡የዘነጉ፡ሰዎችን፡ስለሚመረም ራቸው፡የተናገሩትም፡ነገራቸው፡በኃጢአ ታቸው፡ዘለፋ፡ሊሆንባቸው፡ወደ፡እግዚአ ብሔር፡የሚደርስ፡ስለሆነ፡ሥራውን፡ በመግለጽ፡በፍርድ፡አይተላለፍምና።

### ክፍል፡፪።
### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፵፫፡፩–፯።

፩ መጥሊሳን ፡ የወልድ ፡ ባሕርዩ ፡ ከሥጋው፡ ጋር፡አንድ፡አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡እንደሆነ፡ የቀናች፡ሃይማኖትን፡የማያውቁ፡የተሳ[ሳቱ] ሆኑ፡አለ።

፪ አንድ፡አካል፡አንድ፡ባሕርይም፡ከሆነ፡በማ[ይ] መረመር፡ግብር፡የተወለደ፡በውነት፡የእግዚአ ብሔር፡ቃል፡ነው። ሥጋችንንም፡በተዋሐደ ጊዜ፡ነፍስን፡ትቶ፡ሥጋን፡ብቻ፡አልተዋ ሐደም፤የምታውቅ፡የምትናገር፡ነፍስ፡ግንዘ[ብ] የምትሆን፡ሥጋን፡ተዋሐደ፡እንጂ፤ሰው፡ሆኖ፡ ከድንግል፡ማርያም፡ተወልዶ፡ተገለጠ።

፫ በዚህም፡በመዋሐዱ፡ሁለት፡አካል፡ሁለት፡ ባሕርይ፡ወደ፡መሆን፡አይከፈልም፤ሁለት፡ ባሕርይም፡አይባልም፤እንደ፡ቀደመው፡ያ[ለ] መለየት፡ሥራው፡አንድ፡ነው፡እንጂ።

፬ ሥጋን ፡ ያልነሣ ፡ አይደለም ፤ ሥጋውም፡ በምትሐት ፡ አይደለም ፤ ያለመለየት፡ያለ ለወጥ፡ያለ፡መከፈል፡በተዋህዶ፡እውነተኛ ሥጋው ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ይህንን ፡ የማያም[ን] ተጠራጣሪ፡መናፍቅ፡እንደሆነ፡ያስረዳልና።

፭ ዳግመኛም፡መቀላቀል፡ይህንንም፡የመሰለ ሌላ፡ነገር፡የለበትም፡እንላለን፤ተዋሕዶው፡ እውነተኛ፡ስለሆነ፡ተቀላቀለ፡ማለት፡አይ[ገባ] ማማውምና።

Scanned by CamScanner

በ፳፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፤ ወሶበ፡ንቤ፡ዋሕድ፡ወልድ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር፡ተሠገወ፡ወኮነ፡ሰብአ፡ወበእንተ፡
ዝንቱሂ፡ነገር፡ኢይበውዕ፡ቱሳሔ፡ውስቴቱ፡
ዘከመ፡የአምኑ፡እልክቱ፡ወኢተወለጠ፡
ህላዌ፡ቃል፡ኀበ፡ህላዌ፡ትስብእት፡ወህላዌ፡
ትስብእት፡ኀበ፡ህላዌ፡ቃል፡ዳእሙ፡
ይሔልዉ፡፪ቱ፡ህላዌያት፡በተዋሕዶ፡በበህላ
ዌሆሙ፡እንበለ፡ውላጤ።

፳፩፤ ወንጤይቅ፡ንሕነ፡ዘነበብናሁ፡ቅድመ፡ወአ
እመርነ፡ተዋሕዶተ፡ዘኢይትረከብ፡ወዘኢይ
ትነገር፡፩ዱ፡ህላዌሁ፡ለወልድ፡ዘተሠገወ፡
በከመ፡ይቤ።

## አዮክንድዮስ።

ምዕ፤፵፬፤፩–፱።

፩፤ ይቤ፡አዮክንድዮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሮሜ፡
ውስተ፡መልእክቱ፡ዐቢይ፡ኀበ፡ቅዱስ፡ሳዊር
ያኖስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘኤላ።
፪፤ አመ፡ጊዜ፡ወረደ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡እም
ሰማያት፡ወኀደረ፡ውስተ፡ከርሣ፡ለእግዝ
እትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡
ወተሰብአ፡እምኔሃ፡ኢያምጽአ፡ሥጋ፡
ምስሌሁ፡እምሰማያት፡ወመለኮቱሂ፡ኢኮነ፡
እምድር፡አላ፡አምላክ፡ውእቱ።

፫፤ ወለሊሁ፡ሐነፀ፡ሥጋሁ፡ውስተ፡ከርሠ፡
ድንግል፡ወኢተሳተፎ፡መኑሂ፡በፈጢረ፡
ሥጋሁ፡አላ፡ለሊሁ፡ባሕቲቱ፡ፈጠሮ።
፬፤ ወንትአመን፡ከመ፡በኵሉ፡ዘገብሮ፡
ትስብእት፡ኢተፈልጠ፡እምኔሁ፡መለኮት፡
ኢአሐተ፡ሰዓተ፡ወንትአመን፡እስመ፡አመ፡
ጊዜ፡መጽአ፡እግዚእነ፡ወመድኃኒነ፡አኀበረ፡
መለኮቶ፡ምስለ፡ትስብእቱ፡በተዋሕዶ።

፭፤ ወእምድኅረ፡ተዋሐደ፡መለኮት፡ምስለ፡
ትስብእት፡ኢተፈልጠ፡እንከ፡ተዋሕ
ዶቶሙ፡በምንትኒ፡እምነ፡ግብራት፡እስመ፡
ኢይትፈለጡ፡ወበከመ፡ለመለኮቱ፡አልቦቱ፡
ጥንት፡ከማሁ፡እምድኅረ፡ትንሣኤሁ፡
እሙታን፡አልቦቱ፡ለትስብእት፡ተፍጻሜት።
፮፤ ወጠበወ፡ሐሊበ፡እምብእሲት፡ድንግል፡

ሰኞ፡መዓልት፡በ፳፡ሰዓት።

፳፤ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ወልድ፡ዋሕድ፡ነፍስን፡
ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡ሆነ፡ባልን፡ጊዜም፡
ስለዚህም፡ነገር፡ቢሆን፡እነዚያ፡እንደሚ
ያምኑ፡መቀላቀል፡የለበትም፤የቃል፡ባሕርይ፡
የሥጋን፡ባሕርይ፡ወደመሆን፡የሥጋ፡ባሕርይ፡
የቃል፡ባሕርይን፡ወደመሆን፡አልተለወጠም።
ሁለቱ፡ባሕርያት፡ያለመለዋወጥ፡ባለመቀ
ላቀል፡ምንታዌን፡አጥፍተው፡በተዋሕዶ፡
ጸንተው፡ይኖራሉ፡እንጂ።
፳፩፤ አስቀድመን፡የተናገርነውን፡እንረዳለን፤
ሰው፡የሆነ፡የወልድ፡አካሉ፡አንድ፡ነው፡
ብለን፡እንደተናገርንም፡የማይመረመር፡የማ
ይነገር፡ተዋሕዶውን፡እናውቃለን።

## አዮክንድዮስ።

ምዕ፤፵፬፤፩–፱።

፩፤ ወደ፡ኤላ፡ኤጲስቆጶስ፡ወደ፡ቅዱስ፡ሳዊር
ያኖስ፡በላከው፡በደገኛው፡መልእክቱ፡የሮም፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡አዮክንድዮስ፡እንዲህ፡አለ።
፪፤ እግዚአብሔር፡ቃል፡ከሰማይ፡በወረደ፡ጊዜ፡
በእመቤታችን፡በቅድስት፡ድንግል፡
ማርያም፡ማኅፀንም፡በአደረ፡ጊዜ፡ከእር
ስዋም፡ሥጋን፡ነፍስን፡ነሥቶ፡ሰው፡በሆነ፡
ጊዜ፡ከሰማይ፡ሥጋን፡ይዞ፡አልመጣም፤
መለኮቱም፡ከምድር፡አልተገኘም፤ቀዳማዊ፡
አምላክ፡ነው፡እንጂ።
፫፤ እርሱም፡ሥጋውን፡በድንግል፡ማኅፀን፡ፈጠረ፤
ሥጋውንም፡በመፍጠር፡ማንም፡ማን፡አጋዥ፡
አልሆነውም፤እርሱ፡ራሱ፡ፈጠረው፡እንጂ።
፬፤ ሥጋ፡በሠራው፡ሥራ፡ሁሉ፡መለኮት፡
አንዲት፡ሰዓት፡ስንኳ፡በማናቸውም፡ሥራ፡
ከርሱ፡እንዳልተለየ፡እናምናለን፤ጌታችን፡
መድኃኒታችን፡ሰው፡በሆነ፡ጊዜ፡መለኮቱን፡
ከሥጋ፡ጋር፡በተዋሕዶ፡አንድ፡እንደ፡
አደረገም፡እናምናለን።
፭፤ መለኮትም፡ከትስብእት፡ጋር፡ከተዋሐደ፡
በኋላ፡ከሥራ፡በማናቸው፡ሥራ፡አንድነ
ታቸው፡ፈጽሞ፡አልተለየም፤መለየት፡የለባ
ቸውምና፤ለመለኮት፡ጥንት፡እንደሌለው፡
ከትንሣኤው፡በኋላ፡ለትስብእትም፡እንዲሁ፡
ፍጻሜ፡የለውም።
፮፤ መለኮት፡በማይመረመር፡ተዋሕዶ፡ከሥጋ፡

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

እንዘ ፡ ይትዋሐድ ፡ መለኮት ፡ ምስለ ፡
ትስብእት፡ በተዋሕዶ ፡ ዘኢይትረከብ ፡
ኢተነሊ፡ጥንተ፡ለመለኮት፡እምአመ፡ሖረ፡
እግዚአብሔር፡ቃል፡ኀበ፡ዮርዳኖስ፡ከመ፡
ይጠመቅ፡እምዮሐንስ፡ወመጽአ፡ሎቱ፡ቃለ፡
አብ፡እምሰማይ፡ወሰምዐ፡ዮሐንስ፡አኮ፡
ከመዝ፡አላ፡እንዘ፡አልቦቱ፡ጥንት፡አመ፡
ጊዜ፡ኀደረ፡ውስተ፡ከርሣ፡ለማርያም፡
ድንግል፡ወኮነ፡አሐደ፡ሥጋ፡ምስለ፡
መለኮት፡ወተሳተፎ፡መለኮት፡ለትስብእት፡
በአሐዱ፡ተዋሕዶ፡ዘእንበለ፡ውላጤ፡ወዘእ
ንበለ፡ፍልጠት።

፲፯፤ አልቦቱ ፡ ለመለኮት ፡ ፍልጠት ፡ እምትስ
ብእት፡ እንዘ፡ስቁል፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡
ኢተፈልጠ፡መለኮቱ፡እምትስብእቱ፡ኢ፡
አሐተ፡ሰዓተ፡ወኢ፡ከመ፡ቅጽበተ፡ዓይን፡
ወእንዘሂ፡ውስተ፡መቃብር፡ኢተፈልጠ፡
መለኮት፡እምትስብእቱ።

፲፰፤ ወዐርገ፡ውስተ፡ሰማያት፡በሥጋ፡ዘነሥአ፡
እምእግዝእትነ፡ድንግል፡ማርያም፡ወነበረ፡
በየማነ፡አቡሁ፡ኄር፡ዝንቱ፡ውእቱ፡
አርትዖ፡ሃይማኖት።

፲፱፤ እመቦ፡ዘኢየአምን፡ከመዝ፡እስመ፡ቅድስት፡
ቤተ፡ክርስቲያን፡ጉባኤ፡እንተ፡ሐዋርያት፡
ታወፅኦ፡ወእግዚአብሔርሂ፡ፈጣሪሃ፡ያወግዞ።

## ናጣሊስ።

ምዕ፤፴፯፡፩–፰።

፩፤ ይቤ፡ናጣሊስ፡ማኅቶት፡ብሩህ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ዘሮሜ፡ዓባይ፡ሀገር።

፪፤ አአምን፡ካዕበ፡በእንተ፡ሥርዓተ፡መድኃኒነ፡
በሥጋ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ነበረ፡
በዘዚአሁ፡እንዘ፡ኢይትዌለጥ፡ወእንዘ፡ኢይ
ትመየጥ፡ኮነ፡ሥጋ፡ከመ፡የሐድሶ፡ለዕጓለ፡
እመሕያው።

፫፤ ውእቱ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡በልደት፡
ቀዳማዊ፡እምእግዚአብሔር፡አብ፡ወኮነ፡
ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡በልደት፤ዘይእዜ፡
እምድንግል።

፬፤ አሐዱ፡ውእቱ፡አምላክ፡ፍጹም፡ዕሩይ፡
ምስለ፡አብ፡በመለኮት፡ወውእቱ፡ከመ፡

ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ጋር፡አንድ፡ሁኖ፡ከድንግል፡ጡትን፡ጠባ፤
የመለኮት፡መገኘት፡እግዚአብሔር፡ቃል፡
በዮሐንስ፡እጅ፡ይጠመቅ፡ዘንድ፡ወደ፡
ዮርዳኖስ፡ሂዶ፡የአብ፡ቃልም፡ከሰማይ፡ከተነ
ገረለት፡ዮሐንስም፡ከሰማ፡ወዲህ፡ነው፡
አትበል፤እንዲህ፡አይደለም፤ጥንት፡
ሳይኖረው፡በእመቤታችን፡በቅድስት፡
ድንግል፡ማርያም፡ማኅፀን፡በአደረ፡ጊዜ፡
ሥጋ፡ከመለኮት፡ጋራ፡በተዋሕዶ፡አንድ፡
ሆነ፡እንጂ፤መለኮትም፡ትስብእትን፡
መለወጥ፡መለየት፡በሌለበት፡ተዋሕዶ፡
ተዋሐደው፡እንጂ።

፲፯፤ በመስቀል፡ተሰቅሎ፡ሳለ፡ለመለኮት፡ከሥጋ፡
መለየት፡የለበትም፤አንዲት፡ሰዓት፡የዓይን፡
ጥቅሻ፡ያህል፡እንኳ፡ቢሆንም፡መለኮት፡ከት
ስብእት፡አልተለየም፤በመቃብር፡ውስጥ፡
ሳለም፡መለኮት፡ከትስብእት፡አልተለየም።

፲፰፤ ከእመቤታችን፡ከቅድስት፡ድንግል፡
ማርያም፡በነሣው፡ሥጋም፡ወደ፡ሰማይ፡
ዐረገ፤በአባቱም፡ዕሪና፡ተቀመጠ፤የቀና፡
ሃይማኖት፡ይህ፡ነው።

፲፱፤ እንዲህ፡ብሎ፡የማያምን፡ቢኖር፡ሐዋርያት፡የሰ
በሰበዋት፡ቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ትለየ
ዋለች፤ፈጣሪዋ፡እግዚአብሔርም፡ይለየዋል።

## ናጣሊስ።

ምዕ፤፴፯፡፩–፰።

፩፤ የሚአበራ፡ፋና፡የታላቂቱ፡ሀገር፡የሮሜ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡ናጣሊስ፡እንዲህ፡አለ።

፪፤ መድኃኒታችን፡በሥጋ፡ያደረገውን፡
ተዋሕዶ፡አምናለሁ፤እግዚአብሔር፡ቃል፡
በአካሉ፡በባሕርዩ፡ጸንቶ፡ኖሮአልና፤ሰውን፡
ያድን፡ዘንድ፡ሳይለወጥ፡ባሕርዩን፡ሳይለቅ፡
ሰው፡ሆነ።

፫፤ ከእግዚአብሔር፡አብ፡በተወለደው፡
በቀዳማዊ፡ልደቱ፡የእግዚአብሔር፡አብ፡
ልጅ፡ነው፤ከድንግል፡በተወለደው፡
በደኃራዊ፡ልደቱ፡የሰው፡ልጅ፡ሆነ።

፬፤ እርሱ፡አንዱ፡በመለኮት፡ከአብ፡ጋር፡አንድ፡
የሚሆን፡የሚተካከል፡ፍጹም፡አምላክ፡ነው፡

Scanned by CamScanner

| በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት። |
|---|---|
| ብእሲ፡ፍጹም፡በልደት፡እምድንግል፡ዕሩይ፡ምስለ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡በሥጋ። | እርሱም ፡ ከድንግል ፡ በተወለደው ፡ ልደት ፡ በሥጋ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ መቼም፡መች፡ፍጹም፡ሰው፡ነው። |
| ፩፤ እመቦ ፡ ዘይብል ፡ ከመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አውረደ ፡ ሥጋ ፡ እምሰማይ ፡ አው ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ ሥጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በጥንተ፡ህላዌ፡ውጉዘ፡ለይኩን። | ፩፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሰማይ ፡ ሥጋን፡ ይዞ ፡ እንደመጣ ፡ የሚናገር ፡ ወይም ፡ የተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ በቅድምና ፡ በመኖር ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ የተወገዘ፡የተለየ፡ይሁን። |
| ፪፤ እመቦ ፡ ዘኢየአምን ፡ ከመ ፡ ሥጋ ፡ እግዚእነ ፡ ውእቱ ፡ እምድንግል ፡ ወውእቱ ፡ ዕሩይ ፡ ምስሌነ፡ውጉዘ፡ለይኩን። | ፪፤ ጌታችን ፡የተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ከድንግል ፡እን ደተገኘ ፤ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማያምን፡ቢኖር፡የተለየ፡ይሁን። |
| ፫፤ እመቦ ፡ ዘይብል ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ዘተሰብአ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ በሥጋ ፡ ከመ ፡ ሥጋሁ ፡ እንበለ ፡ ነፍስ ፡ አው ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ፡ አው ፡ ኢነባቢ ፡ ውእቱ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን። | ፫፤ በግብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ሥጋው ፡ ነፍስ፡ የሌለው ፡ ነው ፤ ምትሐት ፡ ነው፤ ወይም ፡ የማይናገር ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር፡የተለየ፡ይሁን። |
| ፬፤ እመቦ ፡ ዘይትህበል ፡ ወይብል ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ሐመ ፡ በመለኮት ፡ ወአኮ ፡ በሥጋ ፡ ኅዲጎ ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ፡በእንቲአነ፡በሥጋ፡ውጉዘ፡ለይኩን። | ፬፤ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ስለእኛ ፡ ታመመ ፡ የሚለውን፡የመጽሐፍን፡ቃል፡ትቶ፡ደፍሮ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ያይደለ፡ በመለኮት፡ታመመ፡የሚል፡ቢኖር፡ የተወገዘ፡የተለየ፡ይሁን። |
| ምዕ፤፵፯፤፩–፲። | ምዕ፤፵፯፤፩–፲። |
| ፲፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ማር ፡ ኤፍሬም ፡ ሶርያዊ፡በተፍጻሜተ፡ዝንቱ፡ድርሳን። | ፲፤ የሶርያው ፡ መምህር ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡ በዚህ ፡ ድርሳን፡መጨረሻ፡ዳግመኛ፡እንዲህ፡አለ። |
| ፲፩፤ እምደብረ፡ሲና፡ወሀበ፡እግዚአብሔር፡፪ኤ፡ጽላተ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ቦቶን ፡ ትእዛዘ ፡ በእዴሁ ፡ ወእምኔሁ ፡ ፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽላተ ፡ ቅዱሰ፡ዘውእቱ፡ሥጋሁ። | ፲፩፤ እግዚአብሔር፡ዐሥሩን፡ቃላት፡በእጁ፡የጻፈባቸውን ፡ ሁለቱን ፡ ጽላት ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ሰጠ፤ ከእንቷም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ጽላትን፡ፈጠረ፤ይኸውም፡ሥጋው፡ነው። |
| ፲፪፤ እምደብረ፡ሲና፡ወፅአ፡እሳት፡ወጽልመት፡ወእምኔሁ፡ወፅአ፡ለነ፡አምላክ፡ወሰብእ። | ፲፪፤ ከደብረ፡ሲና፡እሳት፡ጨለማ፡ወጣ፤ከእንቷ፡ግን፡ሰው፡የሆነ፡አምላክ፡ተገኘልን። |
| ፲፫፤ እምደብረ፡ሲና፡ወፅአ፡ድንጋጼ፡ወሀውከ፡ላዕለ፡አይሁድ፡ወእምኔሁ፡ወፅአ፡ሁከት፡ወድንጋጼ፡ዓቢይ፡ላዕለ፡አይሁድ፡ወሄሮድስ፡ወዲያብሎስ፡ምስለ፡አጋንንቲሁ። | ፲፫፤ በደብረ ፡ ሲና ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ ድንጋጤና ፡ ሽብር ፡ ወጣ ፤ ከእንቷም ፡ በአይሁድ ፡ በሔሮድስ፡በዲያብሎስና፡በሠራዊቱ፡ላይ፡ጽኑ፡ድንጋጤ፡ሆነ። |
| ምዕ፤፵፰፤፴፩–፴፫። | ምዕ፤፵፰፤፴፩–፴፫። |
| ፴፩፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኤራቅሊስ ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት ፡ ዘቍስጥንጥንያ ፡ በውስተ ፡ ድርሳኑ፡ዘደረሰ፡በእንተ፡ሃይማኖት። | ፴፩፤ የቍስጥንጥንያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ይህ፡ቅዱስ፡ኤራቅሊስ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት፡ድርሳኑ፡ዳግመኛ፡እንዲህ፡አለ። |

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፴፯፤ ዘአልቦቱ ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ዘእንበለ ፡ ውላጤ፡ወዘአልቦቱ፡ጥንት፡ልህቀ፡በበሕቅ፡ በሥጋ፡እንዘ፡ፍጹም፡ውእቱ፡በኵሉ።

፴፰፤ በህላዌሁ ፡ ዘኢይቀርቦ ፡ ሕማም ፡ ተወክፈ ፡ ሕማመ ፡ ወኢነሥአ ፡ ትእምርተ ፡ ሕማም ፡ በዘሀሎ፡ቦቱ፡አላ፡ተወክፈ፡ሕማመ፡በሥጋ፡ በዘኮነ፡ቦቱ።

በረከተ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ለእሉ ፡ መምህራን ፡ የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡በል፤ወኵሎ፡ሥርዓተ፡አብጽሕ፡ ከመ፡ቀዳሚ።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

፩፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ቀሲስ ፡ በደብረ ፡ አባ ፡ መቃርስ፡ዘስሙ፡ዮሐንስ፡ወፈራሄ፡እግዚአ ብሔር፡ውእቱ።

፪፤ ወዘልፈ፡ታስተርእዮ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወትትናገሮ ፡ ገሀደ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ያፈቅራ፡ፈድፋደ፡ወይትቀነይ፡ላቲ፡በኵሉ፡ ኃይሉ።

፫፤ ወአሐተ፡ዕለተ፡እንዘ፡ሀሎ፡ውስተ፡በአቱ፡ ምስለ ፡ ረድኡ ፡ ወካልእኒ ፡ መነኮስ ፡ ምስሌሆሙ።

፬፤ ቦአ፡ብርሃን፡ውስተ፡በአቱ፡ወኮነ፡እምሳለ፡ ድንግል፡እንተ፡ባቲ፡ክንፍ፡ከመ፡ንስር።

፭፤ ወሰፍሐት ፡ ክነፊሃ ፡ ላዕለ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወጸለለቶ።

፮፤ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ረድኡ ፡ ወዝኩኒ ፡ መነኮስ ፡ ዘሀሎ፡ምስሌሆሙ፡አንከሩ፡ፈድፋደ።

፯፤ ወሰብሕዎ፡ለእግዚአብሔር፡ወወደስዋ፡ለእ ግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ዘታስተፌ ሥሕሙ ፡ ለእለ ፡ ይትለአክዋ ። ጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፴፯፤ ሥጋ፡ያልነበረው፡ቃል፡ያለመለወጥ፡ሥጋ፡ ተዋሐደ፤ጥንት፡የሌለው፡ቃል፡በሁሉም፡ ፍጹም፡ሲሆን፡በሥጋ፡በየጥቂቱ፡አደገ።

፴፰፤ በባሕርዩ ፡ ሕማም ፡ የሌለበት ፡ እርሱ ፡ መከራን፡በሥጋ፡ተቀበለ፤ቀድሞ፡በነበረበት፡ ባሕርዩ፡መከራ፡አልተቀበለም፤ዛሬ፡ሰው፡ በሆነበት፡በሥጋ፡መከራ፡ተቀበለ፡እንጂ።

የእነዚህ፡መምህራን፡የጸሎታቸው፡በረከት፡ ከሁላችን፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ምንተኑ ፡ በል ፤ ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ እንደ[illegible] ለፊው፡አድርስ።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለም፡ ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ኅሊና፡ የጸናች፡ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያም፡ ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ በአባ ፡ መቃርስ ፡ ገዳም ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚፈራ፡ስሙ፡ዮሐንስ፡የሚባል፡አንድ፡ ቄስ፡ነበረ።

፪፤ በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የምትሆን፡እመቤ ታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሁልጊዜ፡ተገልጻ፡ታነጋግረው፡ነበር፤እርሱ፡ እጅግ፡ይወዳትና፡በፍጹም፡ችሎታው፡ያገለ ግላትም፡ነበርና።

፫፤ አንድ፡ቀንም፡ከረድኡ፡ጋራ፡በበአቱ፡ሳለ፡ ሌላ፡መነኵሴም፡ከሳቸው፡ጋራ፡ሳለ።

፬፤ ወደ ፡ መኖሪያውም ፡ ብርሃን ፡ ገባ ፤ እንደ ንስርም፡ክንፍ፡ያላት፡የድንግል፡አምሳል፡ሆነ፡

፭፤ ክንፏንም ፡ ዘርግታ ፡ አባ ፡ ዮሐንስን ፡ ጋረደችው።

፮፤ ረድኡና፡ያ፡ከእሳቸው፡ጋራ፡ያለ፡መነኵሴ፡ በአዩ፡ጊዜ፡እጅግ፡አደነቁ።

፯፤ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑት ፤ የሚያገለግ ሏትን ፡ ደስ ፡ የምታሰኛቸውን ፡ አምላክን፡ የወለደች፡በሁለት፡ወገን፡ድንግል፡የሆነች፡ ክብርት፡እመቤታችን፡ማርያምንም፡አከ[illegible] ሩዋት ፤ አመሰገኗትም ። ልመናዋ ፡ በረከቷ፡

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ዓለም፡አሜን።

ለተአምርኪ፡ናከብሮ፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ ወበአሐቲ፡ዕለት፡ዐርገ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኢየሩሳሌም፡ወቦአ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወምስሌሁ፡ብዙኃን፡አሕዛብ፡እምአይሁድ፡ወእምጸሐፍቶሙ።

፪፡ ወአኀዙ፡አይሁድ፡ይትናገሩ፡በበይናቲሆሙ፡ወያነክሩ፡በእንተ፡ሕንጻሃ፡ለቤተ፡መቅደስ፡ወዕበያ፡ወጽንዓ።

፫፡ ወእምዝ፡ይቤልዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡አ፡ሊቅ፡ትሬኢኑ፡ለዛቲ፡መቅደስ፡ዕበያ፡ወክብራ፡ወሠርጓ።

፬፡ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡እወ፡ሠናይት፡በከመ፡ትቤሉ፡ወባሕቱ፡እመ፡ፈቀድክሙ፡አንህልዋ፡ወአነ፡አነሥአ፡በሠሉስ፡ዕለት።

፭፡ ወይቤልዎ፡አይሁድ፡በእንተ፡ዝንቱኬ፡ነገር፡ያስተአብዱከ፡ሕዝብ።

፮፡ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡እመሰ፡ያስተአብዱ፡ነገርየ፡ቦኑ፡ትክሉ፡ታስተሐቅሩ፡ነገርየ፡ወተአምራተ፡ዘእገብር።

፯፡ ወይቤልዎ፡እመ፡ገበርከ፡መንክረ፡ንሬኢ፡ወኢናስተሐቅር፡ቃለከ፡እስመ፡ትትናገር፡ዘኢይደሉ፡ወትሬሲ፡ርእሰከ፡አምላከ።

፰፡ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡እመሰ፡ኢገበርኩ፡ዘይመስል፡ግብሮ፡ለአቡየ፡ኢትእመኑኒ።

ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እመ፡ትመጽእ፡በል።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

ተአምርሽን፡እናከብረዋለን፡ይበል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ጌታችን፡አምላካችን፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

፩፡ በአንዲት፡ዕለትም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ወጣ፤ወደ፡ቤተ፡መቅደስም፡ገባ፤ከርሱ፡ጋራም፡ከአይሁድና፡ከጸሐፍቶቻቸው፡ብዙ፡ሕዝብ፡ነበር።

፪፡ አይሁድም፡ስለ፡ቤተ፡መቅደስ፡ሕንጻና፡ስለ፡ክብርዋ፡ስለ፡ጽናቷም፡እርስ፡በርሳቸው፡በማድነቅ፡ይነጋገሩ፡ጀመሩ።

፫፡ ከዚህ፡በኋላ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡መምህር፡ሆይ፡የዚችን፡መቅደስ፡ክብርዋን፡ታላቅነቷን፡ጌጥዋን፡ሽልማቷን፡ታያለህን፡አሉት።

፬፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡እንደምትሉት፡አወን፡መልካም፡ናት፤ነገር፡ግን፡ብትወዱ፡አፍርሰዋት፤እኔ፡በሦስተኛው፡ቀን፡አነሣታለሁ፡አላቸው።

፭፡ አይሁድም፡ስለዚህ፡ነገር፡ሕዝቡ፡ያቃልሉሃል፡(ያስተሐቅሩሃል)፡አሉት።

፮፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ነገሬን፡የሚአቃልሉ፡ከሆነ፡የምሠራውን፡ተአምራትና፡የማስተምረውን፡ትምህርቴን፡መንቀፍ፡በውኑ፡ትችላላችሁን፡አላቸው።

፯፡ ድንቅ፡ተአምራት፡ከአደረግህ፡እናያለን፤ቃልህን፡እናቃልልም፤ነገር፡ግን፡የማይገባ፡ትናገራለህ፤ሰው፡ስትሆን፡አምላክ፡ነኝ፡ትላለህና።

፰፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡የአባቴን፡ሥራ፡የሚመስል፡ሥራ፡ካልሠራሁ፡አትመኑብኝ፡አላቸው።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

እመ፡ትመጽእ፡በል።

### በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፻፳፩፡፫።

እስመ፡ህየ፡ዐርጉ፡አሕዛብ።

ሕዝበ፡እግዚአብሔር፡ ስምዐ፡እስራኤል።

ከመ፡ይግነዩ፡ለስምከ፡እግዚኦ።

ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፡፪፡፲፪-፳፪።

፲፪፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ወረደ ፡ ቅፍርናሆም ፡ ውእቱ ፡ ወእሙ ፡ ወአኀዊሁ ፡ ወአርዳኢሁ ፡ ወነበሩ፡ህየ፡ኅዳጠ፡መዋዕለ፡ወአኮ፡ብዙኀ።

፲፫፡ ወቀርበ ፡ በዓለ ፡ ፋሲካሆሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ወዐርገ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ኢየሩሳሌም።

፲፬፡ ወረከበ ፡ በምኵራብ ፡ እለ ፡ ይሠይጡ ፡ ወይሣየጡ፡አልሕምተ፡ወአባግዐ፡ወአርጋበ፡ ወመወልጣነ፡እንዘ፡ይነብሩ።

፲፭፡ ወገብረ ፡ መቅሠፍተ ፡ ጥብጣቤ ፡ ዘሐብል ፡ ወሰደደ፡ኵሎ፡እምኵራብ፡አባግዐኒ፡ወአልህምተኒ ፡ ወዘረወ ፡ ወርቆሙ ፡ ለመወልጣን ፡ ወገፍትዐ፡ማዕዳቲሆሙ፡ወመናብርቲሆሙ፡ ለእለ፡ይሠይጡ፡ርግበ፡ገንጸለ።

፲፮፡ ወይቤሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይሠይጡ ፡ አርጋበ ፡ አሰስሉ፡ወአውፅኡ፡ዘንተ፡እምዝየ፡ወኢትረስዩ፡ቤተ፡አቡየ፡ቤተ፡ምሥያጥ።

፲፯፡ ወተዘከሩ፡አርዳኢሁ፡ከመ፡ጽሑፍ፡ውእቱ፡ ዘይብል፡ቅንዓተ፡ቤትከ፡በልዐኒ።

፲፰፡ ወአውሥእዎ፡አይሁድ፡ወይቤልዎ፡ምንተ፡ ትእምርተ፡ታርኢ፡ዘዘንተ፡ትገብር።

፲፱፡ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ ንሥትዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወበሠሉስ፡ዕለት፡አነሥእ።

፳፡ ወይቤልዎ፡አይሁድ፡በአርብዓ፡ወስድስቱ፡ ዓመት ፡ ተሐንጸ ፡ ዝንቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወአንተሰ፡በሠሉስ፡መዋዕል፡ታነሥእ።

፳፩፡ ወውእቱሰ ፡ በእንተ ፡ ቤተ ፡ ሥጋሁ ፡ ይቤሎሙ።

፳፪፡ ወአመ፡ተንሥአ፡እምነ፡ምውታን፡ተዘከሩ፡ አርዳኢሁ ፡ ከመ ፡ በእንተዝ ፡ ይቤሎሙ ፡ ወአምኑ ፡ በቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ወበቃለ ፡ እግዚእ፡ኢየሱስ፡ዘይቤሎሙ።

### ስኞ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፡፻፳፩፡፫።

የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ እስራኤል ፡ ወደ ፡ ኢየሩ ሳሌም፡ወጥተዋል።

ለእስራኤልነታቸው፡ምስክር፡የሚሆኑ፡የእግ ዚአብሔር፡ ወገኖች፡ናቸው።

አቤቱ፡ ለስምህ፡ይገዙ፡ዘንድ፡ይበል።

የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፪፡፲፪-፳፪።

፲፪፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እርሱ ፡ እናቱ ፡ ወንድሞቹና፡ ደቀ፡መዛሙርቱ፡ወደ፡ቅፍርናሆም፡ወርደው፡ በዚያ፡ብዙ፡ያይደለ፡ጥቂት፡ቀን፡ተቀመጡ።

፲፫፡ የአይሁድ፡የፋሲካቸው፡በዐል፡ቀርቦ፡ነበርና፡ ጌታ፡ኢየሱስ፡ ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ወጣ።

፲፬፡ በምኵራብም፡ላሙን፡በጉን፡ርግቡን፡የሚሸ ጡትንና፡የሚገዙትን፡ለዋጮችንም፡ገበያ፡ አድርገው፡አገኘ።

፲፭፡ ከገመድ ፡ የተሠራ ፡ አለንጋ ፡ ይዞ ፡ በጉንም፡ ላሙንም፡ሁሉንም፡ከምኵራብ፡አስወጣ፡የለ ዋጮችን ፡ ወርቅ ፡ በተነ ፡ ድርድራቸውንም፡ አፈረሰ ፡ የርግብ ፡ ሻጮች ፡ ወንበርንም፡ ገለበጠ።

፲፮፡ ርግብ ፡ ሻጮችንም ፡ ይህን ፡ ከዚህ ፡ አውጡ፡ ወዲያ ፡ በሉ ፡ የአባቴን ፡ ቤት ፡ የገበያ ፡ ቤት፡ አታድርጉ፡አላቸው።

፲፯፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ የቤትህ ፡ ቅናት ፡ በላኝ፡ የሚል፡ቃል፡ተጽፎ፡እንዳለ፡አሰቡ።

፲፰፡ አይሁድም ፡ መልሰው ፡ ይህን ፡ የምታደርግ፡ ምን፡ምልክት፡ታሳያለህ፡አሉት።

፲፱፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ይኸን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ አፍርሱት ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አነሣዋለሁ፡ ብሎ፡መለሰላቸው።

፳፡ አይሁድም ፡ ይኸ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በአርባ፡ ስድስት፡ዓመት፡ተሠራ፡አንተ፡ግን፡በሦስት ቀኖች፡ውስጥ፡ትሠራዋለህን፡አሉት።

፳፩፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ቤት ፡ ስለተባለ ፡ ሥጋው፡ ነገራቸው።

፳፪፡ ከሙታን፡በተነሣም፡ጊዜ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ ስለዚህ ፡ እንደነገራቸው ፡ አሰቡና ፡ በመጻ ሕፍት፡ቃልና፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ በነገራቸው፡ ነገርም፡አመኑ።

### በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፫፤ ወእንዘ፡ሀሎ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኢየሩሳሌም፡ በበዐለ፡ፋሲካ፡ብዙኃን፡አምኑ፡ቦቱ፡ሶበ፡ ርእዩ፡ተአምረ፡ዘገብረ።
፳፬፤ ወውእቱሰ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኢአምኖሙ፡ እስመ፡የአምሮ፡ለኵሉ፡ለለአሐዱ።
፳፭፤ ወኢይፈቅድ፡ይንግርዎ፡ግዕዞ፡ለሰብእ፡ እስመ፡ለሊሁ፡የአምሮ፡ለሰብእ።

### ድኅረ፡ወንጌል፡በስድስቱ፡ሰዓት፡ እምዕለተ፡ሰኑይ።

፩፤ አ፡ለሃቲ፡ድፍረት፡እንተ፡ገበርካሃ፡ሕዝበ፡ እስራኤል፡ዘጥኑይ፡ቀዲሙ፡ለእግዚአ ብሔር፡ወፆረ፡ልበ፡ካህናቲከ።

፪፤ መካነ፡ሥርየት፡ኮነ፡መካነ፡ኃጢአት፡ ወመካነ፡አልሕምት፡ወረሰይክምዎ፡ ማኅደረ፡ዐመፃ፡ወትዕግልት፡ወማኅደረ፡ አባግዕ፡ወመወልጣን፡ወእለ፡ይሠይጡ፡ አርጋበ።
፫፤ ምንት፡ውእቱ፡ረባሕ፡ዘምሉዕ፡ኵሎ፡ነውረ፡ ወዘንተ፡ዐምፃ፡እንተ፡ገበርክምዎ፡ሶበ፡ ርዕየ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ኀበ፡ቤተ፡ አቡሁ፡እንዘ፡ይገብሩ፡ዘንተ፡በውስቴታ፡ እስመ፡እሙንቱ፡ረሰይዎ፡ማኅደረ፡ለፈያት፡ ወመሠጥ፡ወዓማፅያን፡ወቤተ፡መንግድ።
፬፤ ወአውፅአ፡አልሕምተ፡ወአባግዐ፡ወመናብር ቲሆሙ፡ለእለ፡ይሠይጡ፡አርጋበ፡ወማዕዳ ቲሆሙ፡ለመወልጣን፡ገንጸለ።
፭፤ ወሶበ፡ርእዩ፡አርዳኢሁ፡ዘንተ፡አእመሩ፡ ከመ፡ጽሑፍ፡በእንቲአሁ፡ዘይቤ፡እስመ፡ ቅንዓተ፡ቤትከ፡በልዓኒ።
፮፤ ገብረ፡ከመዝ፡ዘእንበለ፡ፍርሀት።ሥልጣንከ፡ በሰማይ፡ወበምድር።ወፍርሀትከ፡እግዚእ፡ አንቀልቀለ፡አድባረ።
፯፤ ወለእስራኤልሰ፡አብድ፡ናሁ፡ከደነት፡ ላዕሌሁ፡ረድኤቱ።ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡ መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።ወኵሉ፡ ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።
(ይ፡ካ)፡ሑሩ፡ወዕትው፡በሰላም።
እግዚአብሔር፡የሃሉ፡ምስሌክሙ።

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፳፫፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡በፋሲካ፡በዓል፡በኢየሩ ሳሌም፡ሳለ፡ብዙ፡ሰዎች፡ያደረገውን፡ ተአምራት፡ባዩ፡ጊዜ፡አመኑበት።
፳፬፤ እሱ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ግን፡ኢያምናቸውም፡ ነበር፤ሁሉንም፡እያንዳንዱን፡ያውቀዋልና።
፳፭፤ የሰውንም፡ሥራውን፡ሊነግሩት፡አይሻም፤ እሱ፡ሰውን፡ያውቀዋልና።

### ከወንጌል፡በኋላ፡ሰኞ፡በስድስት፡ሰዓት የሚነበብ።

፩፤ የእስራኤል፡ወገን፡ሆይ፡ላደረግሃት፡ለዚች፡ ድፍረት፡ወዮ፤አስቀድሞ፡የእግዚአብሔር፡ ገንዘብ፡የሆነውን፡ለመድፈር፡የካህናቶችህ፡ ልቡና፡ደነደነ።
፪፤ የሥርየቱ፡ቦታ፡የኃጢአት፡ቦታ፡ሆነ፤ የላሞችም፡ማደሪያ፡ሆነ፤የዓመፅና፡የቅሚያ፡ ቦታ፡የበጎችም፡ማደሪያ፡አደረጋችሁት፤የለ ዋጮችና፡የርግብ፡ሻጮች፡ቦታ፡አደረጋ ችሁት።
፫፤ ነውርን፡ሁሉና፡የሠራችሁትን፡ይህን፡ አመፅ፡የተመላ፡ጥቅሙ፡ምንድን፡ነው?የእግ ዚአብሔር፡ልጅ፡በአባቱ፡ቤት፡በውስጥዋ፡ የማይገባ፡ሥራ፡ሲሠሩ፡በአየ፡ጊዜ፡እነሱ፡ የነጣቂ፡ወንበዴ፡ማደሪያና፡የዓመፀኞች፡ መነገጃ፡ቤት፡አድርገውታልና።
፬፤ ላሞችንና፡በጎችን፡አስወጣ፡የርግብ፡ ሻጮችንም፡ወንበራቸውን፡ገለበጠ፤የለዋ ጮችንም፡ድርድራቸውን፡አፈረሰ።
፭፤ ደቀ፡መዛሙርቱም፡ይህን፡ባዩ፡ጊዜ፡ የቤትህ፡ቅናት፡በላኝ፡የሚለው፡ስለርሱ፡ የተጻፈ፡እንደሆነ፡አወቁ።
፮፤ በሰማይና፡በምድር፡የመላ፡ሥልጣንህ፡ያለ፡ መፍራት፡እንደዚህ፡አደረገ።መፈራትህም፡ አቡቱ፡ተራራዎችን፡አናወጠ።
፯፤ ሰነፍ፡እስራኤልን፡ግን፡እነሆ፡ረድኤቱ፡ ጋረደችው።መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ ሁኖ፡መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል፡ሥርዓቱ፡ሁሉ፡እን ደፊተኛው፡ነው።
ካህኑ፡በሰላም፡ሂዱና፡ግቡ፤እግዚአብሔር፡ ከእናንተ፡ጋር፡ይሁን፡ይበል።

## ምዕራፍ፡፲፫።

ትዕዛዝ፡ወይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በጊዜ፡ተሰዐቱ፡ሰዓት፡ዘሰኑይ።

ወይጸልዩ፡መዝሙረ፡ዳዊት፡ዘይቤ፡እግዚአብሔር፡ቆመ፡ውስተ፡ማኅበረ፡አማልክት፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡ወስብሐቲሁኒ፡ይነብር፡ለዓለም።

ወውዳሴ፡ማርያም፡ዘኀሙስ።

ወይበል ፡ መራሒ ፡ በ፫ ፡ ስምዕዎኬ ። ወእምዝ ፡ ይበሉ ፡ ዐሠርተ ፡ ወ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ ለከ ፡ ኃይል።

### ክፍል፡፩።

### ምንባብ፡ዘተሰዐቱ፡ሰዓት።

### ኦሪት፡ዘልደት።

ምዕ፥፪፥፲፭–፳፭።

፲፭፤ ወነሥአ፡እግዚአብሔር፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡ዘገብሮ ፡ ወሤሞ ፡ ውስተ ፡ ገነት፡ ከመ ፡ ይትገበራ፡ወይዕቀባ።

፲፮፤ ወአዘዞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ወይቤሎ ፡ እምኵሉ፡ዕፅ፡ዘሀሎ፡ውስተ፡ገነት፡ብላዕ።

፲፯፤ ወእምዕፅ፡ዘያርኢ፡ወያሌቡ፡ሠናየ፡ወእኩየ፡ኢትብላዕ፡እምኔሁ፡እስመ፡በዕለተ፡ትበልዕ፡እምኔሁ፡ሞተ፡ትመውት።

፲፰፤ ወይቤ፡እግዚአብሔር፡ኢኮነ፡ሠናየ፡ለዕጓለ፡እመሕያው፡ይንበር፡ባሕቲቶ፡አላ፡ንግበር፡ሎቱ፡ቢጸ፡ዘትረድኦ።

፲፱፤ ወገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓዲ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም፡እምድር፡ወኵሎ፡አዕዋፈ፡ሰማይ፡ወአምጽኦሙ ፡ ኀበ ፡ አዳም ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ወምንተ ፡ ይሰምዮሙ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሰመዮሙ ፡ አዳም ፡ ለለነፍሰ ፡ ሕይወት ፡ ውእቱ ፡ ይኩን ፡ ስሞሙ።

፳፤ ወሰመየ ፡ አዳም ፡ ኵሎ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለኵሉ፡ እንስሳ ፡ ወለአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወለኵሉ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፡ ወለአዳምሰ ፡ ኢተረክበ፡ሎቱ፡ረድኤቱ፡ዘከማሁ።

## ምዕራፍ፡፲፫።

ሰኞ ፡ ከቀኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን፡ውስጥ፡ካህናት፡ይሰብሰቡ።

እግዚአብሔር ፡ ቆመ ፡ የሚለውን ፡ የዳዊት፡ መዝሙር ፡ ወስብሐቲሁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም፡ እስከሚለው፡ድረስ፡ይጸልዩ።

ውዳሴ፡ማርያም፡የኀሙስን፡ይድገሙ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለከ ፡ ኃይል ፡ ይበሉ ፤ አሥራ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መሪውም ፡ በሦስት ፡ ሃሌታ፡ ስምዕዎኬ፡ይበል።

### ክፍል፡፩።

### የዘጠኝ፡ሰዓት፡ንባብ።

### ኦሪት፡ዘፍጥረት።

ምዕ፥፪፥፲፭–፳፭

፲፭፤ እግዚአብሔር ፡ ያበጃትም ፡ ይጠብቃትም፡ ዘንድ ፡ የፈጠረውን ፡ አዳምን ፡ አምጥቶ፡ በገነት፡አኖረው።

፲፮፤ እግዚአብሔርም ፡ አዳምን ፡ በገነት ፡ ውስጥ፡ ካለው፡ዕንጨት፡ሁሉ፡ብላ፡ብሎ፡አዘዘው።

፲፯፤ ክፉና ፡ በጎን ፡ ለይቶ ፡ ከሚአስታውቅ ፡ ከዕፀ፡ በለስ፡ግን፡አትብላ፡ብሎ፡አዘዘው፡ከእሱ፡በም ትበላበት፡ቀን፡የሞት፡ሞትን፡ትሞታለህና።

፲፰፤ የምትረዳው፡ሔዋንን፡እንፍጠርለት፡እንጂ፡ ብቻውን ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለአዳም ፡ አግባብ፡ አይደለም፡አለ፡እግዚአብሔር።

፲፱፤ ዳግመኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አው ሬዎችን ፡ ከምድር ፡ ፈጠረ ፤ የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ፤አይቶ ፡ ማንም፡ ማን፡ እያለ ፡ ስም ፡ ያወጣላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ፡ አዳምም ፡ አመጣቸው ፤ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያዋን፡ ለሆኑት ፡ ሁሉ ፡ አዳም ፡ ስም ፡ ያወጣ ላቸው፡ይጠሩበት፡ዘንድ፡ነው።

፳፤ አዳምም፡ለእንስሳ፡ለሰማይ፡ወፎችም፡ሁሉ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬዎችም ፡ ሁሉ ፡ ስማቸውን ፡ አወጣላቸው ፤ ለአዳም ፡ ግን፡ እንደሱ፡ያለ፡ረዳት፡አልተገኘለትም።

Scanned by CamScanner

### በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፳፩፤ ወአምጽአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድቃሰ ፡ ላዕለ ፡ አዳም ፡ ወኖመ ፡ ወነሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሐደ ፡ እምአጽመ ፡ ገቦሁ ፡ ወመልአ ፡ ሥጋ ፡ መካና።

፳፪፤ ወነደቃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይእቲ ፡ ዓፅመ ፡ ገቦሁ ፡ እንተ ፡ ነሥአ ፡ እምአዳም ፡ ወረሰያ ፡ ብእሲተ ፡ ወአምጽአ ፡ ኀበ ፡ አዳም።

፳፫፤ ወይቤ ፡ አዳም ፡ ሶቤሃ ፡ ዛቲ ፡ ዐፅም ፡ እምዐ ዕምየ፡ ወሥጋ ፡ እምሥጋየ ፡ ለትኩነኒ ፡ ብእሲትየ፡እስመ፡እምታ፡ወፅአት፡ይእቲ።

፳፬፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ የኀድግ ፡ ብእሲ ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ ወይትልዋ ፡ ለብእሲቱ ፡ ወይከውኑ ፡ ፪ሆሙ፡፩ደ፡ሥጋ።

፳፭፤ ወሀለዉ ፡ አዳም ፡ ወሔዋን ፡ ብእሲቱ ፡ ዕራቃ ኒሆሙ፡ወኢይትኀፈሩ።

ምዕ፤፫፡፩–፳፬።

፩፤ ወአርዌ ፡ ምድርሰ ፡ ትጠበብ ፡ እምኵሉ ፡ አራዊተ፡ ገዳም ፡ ዘገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትቤላ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ለብእሲት ፡ ምንትኑ፡ ውእቱ ፡ ዘይቤለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትብልዑ፡እምኵሉ፡ዕፅ፡ዘውስተ፡ገነት።

፪፤ ወትቤላ ፡ ብእሲት ፡ ለአርዌ ፡ ምድር ፡ እምዕፅ፡ ዘይፈሪ፡ዘሀሎ፡ማዕከለ፡ገነት፡ንበልዕ።

፫፤ ወእምዕፅሰ ፡ ባሕቲ ፡ ዘሀሎ ፡ ማዕከለ ፡ ገነት ፡ ይቤለነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢንብላዕ ፡ እምኔሁ ፡ ወከመ ፡ ኢንግሥሥ ፡ ወከመ ፡ ኢንሙት፡ይቤ።

፬፤ ወትቤላ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ለብእሲት ፡ አኮ ፡ ሞተ፡ዘትመውቱ።

፭፤ አላ ፡ እስመ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ አመ ፡ ዕለተ ፡ ትበልዑ ፡ እምኔሁ ፡ ይትፈታሑ ፡ አዕይንቲክሙ ፡ ወትከውኑ ፡ ከመ ፡ እግዚአ ብሔር፡ ወተአምሩ፡ሠናየ፡ወእኩየ።

፮፤ ወሶበ ፡ ርእየት ፡ ብእሲት ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ዕፁ ፡ ለበሊዕ ፡ ወሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ለአዕይንት ፡

### ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፩፤ እግዚአብሔርም፡በአዳም፡ላይ፡እንቅልፍን፡ አመጣበት፤ ተኛም እግዚአብሔርም፡ከጎኑ፡ አንዲት ፡ አጥንትን ፡ ነሣ ፡ ቦታዋንም ፡ ሥጋ ፡ መላ።

፳፪፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህቺን ፡ ከአዳም ፡ ጎን ፡ የነሣትን ፡ አጥንት ፡ ሕዋሳትን ፡ ቀረፀላት ፡ ሴትም፡አደረጋት፤ወደ፡አዳምም፡አመጣት።

፳፫፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ አዳምም ፡ እሷ ፡ ከባሏ ፡ ተገኝታ ለችና ፡ ያጥንቴ ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋዬ ፡ ቁራጭ ፡ ናት፡ሚስት፡ትሁነኝ፡አለ።

፳፬፤ ስለዚህም፡ነገር፡ሰው፡እናት፡አባቱን፡ትቶ፡ ሚስቱን፡ይከተላል፤ሁለቱም፡አንድ፡አካል፡ ይሆናሉ።

፳፭፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ዕራቁታቸውን ፡ ነበሩ፤ አይ ተፋፈሩም፡ነበር።

ምዕ፤፫፡፩–፳፬።

፩፤ የምድር ፡ እባብ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈጠ ራቸው ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬዎች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ፡ተንኰለኛ፡ነበረችና፡ሔዋንን፡እግዚአ ብሔር፡በገነት፡ካለ፡እንጨት፡ሁሉ፡አትብሉ፡ ያላችሁ፡ለምንድር፡ነው፡አለቻት።

፪፤ ሔዋንም ፡ የምድር ፡ እባብን ፡ በገነት ፡ መካከል፡ካለ፡ከሚአፈራው፡እንጨት፡ሁሉ፡ እንበላለን፡አለቻት።

፫፤ ነገር ፡ ግን ፡ በገነት ፡ መካከል ፡ ካለ ፡ ከበለስ ፡ እንጨት ፡ ፍሬ ፡ እንዳንበላ ፡ እግዚአብሔር ፡ አትብሉ፡አለን፡አለቻት፤ስንኳን፡ልንበላው፡ እንዳንነካው ፡ አትንኩ ፡ አለን፤ ነገር ፡ ግን ፡ ነፍጎን፡አይደለም፡እንዳንሞት፡ብሎ፡ነው።

፬፤ የምድር ፡ እባብም ፡ ሔዋንን ፡ ሞትን ፡ የምትሞቱ፡አይደለም፡አለቻት።

፭፤ ከሱ ፡ በበላችሁበት ፡ ቀን ፡ ዐይነ ፡ ልቡናችሁ ፡ እንደሚበራ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ምትሆኑ፤ ክፉና ፡ በጎንም ፡ እንደምታውቁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃልና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሞትን፡የምትሞቱ፡አይደለም፡አለቻት።

፮፤ ሔዋንም ፡ ዕንጨቱ ፡ ለመብላትና ፡ ለማየትም፡ ለዓይንም፡ያማረ፡የተወደደ፡እንደ፡ሆነና፡በጎ፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ወለርእይ ፡ ወሠናየ ፡ ያጤይቅ ፡ ነሥአት ፡
እምፍሬሁ፡ወበልዐት፡ወወሀበቶ፡ለብእሲሃ፡
ምስሌሃ፡ወበልዐ።
፯፡ ወተፈትሐ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ወአእመሩ ፡
ከመ፡ዕራቃኒሆሙ፡እሙንቱ፡ወኀፍሩ።
ወሰፈዩ ፡ ቆጽለ ፡ በለስ ፡ ወገብሩ ፡ ሎሙ ፡
መዋርዕተ።
፰፡ ወሰምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡
ያንሶሱ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ፍና ፡ ሠርክ ፡
ወተኀብኡ፡አዳም፡ወብእሲቱ፡እምቅድመ፡
እግዚአብሔር፡ማዕከለ፡ዕፀዊሃ፡ለገነት።
፱፡ ወጸውዖ፡እግዚአብሔር፡ለአዳም፡ወይቤሎ፡
አይቴ፡ሀሎከ፡አዳም።
፲፡ ወይቤ ፡ አዳም ፡ ቃለከ ፡ ሰማዕኩ ፡ እንዘ ፡
ታንሶሱ፡ውስተ፡ገነት፡ወፈራህኩ፡እስመ፡
ዕራቅየ፡አነ፡ወተኀባዕኩ።
፲፩፡ ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡መኑ፡አይድዓከ፡
ከመ፡ዕራቅከ፡አንተ፡እምዕፅኑ፡ዘአዘዝኩከ፡
ከመ፡ኢትብላዕ፡እምኔሁ፡በላዕከኑ?
፲፪፡ ወይቤ፡አዳም፡ብእሲት፡እንተ፡ወሀብከኒ፡
ምስሌየ ፡ ትንበር ፡ ይእቲ ፡ ወሀበተኒ ፡
ወበላዕኩ።
፲፫፡ ወይቤላ፡እግዚአብሔር፡ለብእሲት፡ለምንት፡
ገበርኪ ፡ ዘንተ ፡ ወትቤ ፡ ብእሲት ፡ አርዌ ፡
ምድር፡አስፈጠተኒ፡ወበላዕኩ።
፲፬፡ ወይቤላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአርዌ ፡ ምድር ፡
እስመ፡ገበርኪዮ፡ለዝንቱ፡ግብር፡ርግምት፡
ኩኒ፡እምኵሉ፡እንስሳ፡ወእምኵሉ፡አራዊተ፡
ምድር ፡ ወበዕንግድዓኪ፡ ሑሪ ፡ ወመሬተ ፡
ብልዒ፡ኵሎ፡መዋዕለ፡ሕይወትኪ።
፲፭፡ አስተፃርር፡ማእከሌኪ፡ወማእከለ፡ብእሲት፡
ወማእከለ፡ዘርዕኪ፡ወማዕከለ፡ዘርዓ፡ውእቱ፡
ለይዕቀብ ፡ ርእሰኪ ፡ ወአንቲኒ ፡ ዕቀቢ ፡
ሰኰናሁ።
፲፮፡ ወለብእሲትኒ ፡ ይቤላ ፡ እግዚአብሔር ፡
አብዝኆ፡አበዝኆ፡ለኃዘንኪ፡ወለሥቃይኪ፡
ወበፃዕር፡ለዲ፡ኵሎ፡መዋዕለ፡ሕይወትኪ፡
ወወሊድኪ፡ኀበ፡ምትኪ፡ይኩን፡ምግባዕኪ፡
ወውእቱ፡ይቅንይኪ።
፲፯፡ ወለአዳምኒ፡ይቤሎ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡
ሰማዕከ ፡ ቃለ ፡ ብእሲትከ ፡ ወበላዕከ ፡ እም
ውእቱ ፡ ዕፅ ፡ ዘአዘዝኩከ ፡ ከመ ፡ ኢትብላዕ ፡

ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ነገርንም ፡ እንዲአስረዳ ፡ በአየች ፡ ጊዜ፡
ከፍሬው፡አምጥታ፡በላች፤ለባሏም፡እንደ[illegible]፡
ሰጠችው፤በሉም።
፯፡ ዐይነ፡ልቡናቸውም፡በራ፡እነሱም፡ዕራቁታ
ቸውን፡እንደ፡ሆኑ፡አውቀው፡አፈሩ።
የበለስ ፡ ቅጠልን ፡ ሰፍተው ፡ ለራሳቸው፡
መሸፈኛ፡ግልድም፡አደረጉ።
፰፡ በማታ፡ጊዜ፡በገነት፡ውስጥ፡ሲመላለስ፡እ
ግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ አዳምና፡
ሔዋን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በገነት፡
ዕንጨቶች፡መካከል፡ተሸሸጉ።
፱፡ እግዚአብሔርም ፡ አዳምን ጠርቶ ፡ አዳም፡
ወዴት፡አለህ፡አለው።
፲፡ አዳምም ፡ በገነት ፡ ውስጥ ፡ ስትመላለስ፡
ቃልህን፡ሰምቼ፡ፈራሁ፤ዕራቁቴን፡ነኝና፡
ተሸሸግሁ፡አለ።
፲፩፡ እግዚአብሔርም፡እራቁትህን፡እንደሆንክ፡
ማን ፡ ነገረህ? ከሱ ፡ እንዳትበላ ፡ካዘዝኩህ፡
እንጨት፡በላህን፡አለው።
፲፪፡ አዳምም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትቀመጥ ፡ዘንድ፡
የሰጠኸኝ፡ሴት፡ሰጥታኝ፡በላሁ፡አለ።

፲፫፡ እግዚአብሔርም ፡ ሔዋንን ፡ ይህን ፡ ለምን፡
ሠራሽ፡አላት፤ሔዋንም፡የምድር፡እባብ፡አሳ
ተችኝና፡በላሁ፡አለች።
፲፬፡ እግዚአብሔርም፡የምድር፡እባብን፡ይህን፡
ሥራ፡ሠርተሻልና፡ከምድር፡አውሬዎችና፡
ከእንስሶች፡ተለይተሽ፡የተረገምሽ፡ሁኚ፡በደ
ረትሽም፡ሂጂ። በሕይወትሽ፡ዘመን፡ሁሉ፡
አፈርን፡ብዪ፡አላት።
፲፭፡ በአንችና፡በሴቲቱ፡መካከል፡ጠላትነትን፡
አጸናለሁ፤ በዘርሽና ፡ በዘርዋ ፡ መካከልም፡
እርሱ ፡ ራስሽን ፡ ይቀጥቅጥ ፤ አንቺም ፡
ሰኰናውን፡ጠብቂ፡አላት።
፲፮፡ እግዚአብሔርም ፡ ሴቲቱን ፡ መከራሽንና፡
ሐዘንሽን፡ማብዛትን፡አበዛዋለሁ፤በሕይወት
ዘመንሽ ፡ ሁሉ ፡ በምጥ ፡ ውለጂ ፤ በፃር፡
በጋርም፡ ወልደሽ ፡ መመለሻሽም ፡ ወደ፡
ባልሽ፡ይሁን፤እሱም፡ይግዛሽ፡አላት።
፲፯፡ እግዚአብሔርም ፡ አዳምን ፡ የሚስትህን፡
የሔዋንን ፡ ቃል ፡ ሰምተህ ፡ እንዳትበላ፡
ካዘዝኩህ ፡ እንጨት ፡ በልተሃልና ፡ ምድር፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ርግምተ ፡ ትኩን ፡ ምድር ፡ በተግባርከ ፡ ወበፃዕር፡ብላዕ፡ኵሎ፡መዋዕለ፡ሕይወትከ።

፲፰፤ አስዋከ ፡ ወአሜከላ ፡ ይብቊልከ ፡ ወብላዕ ፡ ሣዕረ፡ገዳም።

፲፱፤ ወበሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ብላዕ ፡ ኅብስተከ ፡ እስከ ፡ ትገብእ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ እንተ ፡ እምኔሃ ፡ ወፃእከ ፡ እስመ ፡ መሬት ፡ አንተ ፡ ወውስተ ፡ መሬት፡ትገብእ።

፳፤ ወሰመየ ፡ አዳም ፡ ስማ ፡ ለብእሲቱ ፡ ሔዋን ፡ እስመ፡ይእቲ፡እሞሙ፡ለሕያዋን።

፳፩፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ወለብእሲቱ፡አዕዳለ፡ዘማዕስ፡ወአልበሶሙ።

፳፪፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ አዳም ፡ ኮነ ፡ ከመ፡ አሐዱ ፡ እምኔነ ፡ ያእምር ፡ ሠናየ ፡ ወእኩየ ፡ ወይእዜኒ ፡ ዮጊ ፡ ያሌዕል ፡ እዴሁ ፡ ወይነሥእ ፡ እምዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ወይበልዕ ፡ ወየሐዩ፡ለዓለም።

፳፫፤ ወአውፅኦ፡እግዚእ፡እግዚአብሔር፡ለአዳም፡እምገነተ፡ተድላ፡ከመ፡ይትገበራ፡ለምድር፡እንተ፡እምኔሃ፡ወፅአ፡ወአኅደሮ፡ቅድመ፡ገነተ፡ትፍሥሕት።

፳፬፤ ወአዘዞሙ ፡ ለኪሩቤል ፡ ወለሱራፌል ፡ ዘውስተ፡እደዊሆሙ፡ሰይፈ፡እሳት፡እንተ፡ትትመየየጥ ፡ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ ፍኖተ ፡ ዕፀ ፡ ሕይወት።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፵፥፩–፫።

፩፤ ገሥዕዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር።

፪፤ ካህናቲሃኒ፡ንብብዋ፡ለኢየሩሳሌም፡ውስተ፡ልባ ፡ ወገሥፅዋ ፡ እስመ ፡ በዝኀ ፡ ኃሣራ ፡ ወተርፈ፡ኃጢአታ፡ወተፈድየት፡እምእደ፡እግዚአብሔር፡ካዕበተ፡ኃጢአታ።

፫፤ ቃለ፡ዓዋዲ፡በገዳም፡ጺሑ፡ፍኖቶ፡ለእግዚአብሔር፡ወዓርዩ፡መጽያሕቶ፡ለአምላክነ።

ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

በሥራህ፡የተረገመች፡ትሁን፡በሕይወትህ፡ዘመን፡ሁሉ፡በፃር፡በጋር፡ብላ፡አለው።

፲፰፤ እሾኽ ፡ አሜከላም ፡ ይብቀልብህ፤ በምድረ ፡ በዳ፡ያለ፡እህልንም፡ብላ፡አለው።

፲፱፤ አንተ፡አፈር፡ነህና፡ወደ፡አፈርነትም፡ትመለሳለህና፡ከሷ፡ወደ፡ተገኘህባት፡ወደ፡መሬት፡እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡ እንጀራህን ፡ ጥረህ ፡ ግረህ፡ብላ፡አለው።

፳፤ በነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ለሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እናት ፡ ናትና ፡ አዳም ፡ የሚስቱን ፡ ስም ፡ ሔዋን፡አላት።

፳፩፤ እግዚአብሔርም ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ የቁርበት፡ልብስ፡አለበሳቸው።

፳፪፤ እግዚአብሔርም፡እንዲህ፡አለ። ክፉና፡በጎን፡ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡ አዳም ፡ ከኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ሆነ ፡ አሁንም ፡ ፡ ወይም ፡ እኮ ፡ እጁን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ከዕፀ ፡ ሕይወት ፡ በልቶ ፡ ዘለዓለም፡እንዳይኖር፤

፳፫፤ ከስዋ ፡ የተገኘባት ፡ ምድርን ፡ ያርሳት ፡ ይቆፍራት ፡ ዘንድ ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምን፡ ከገነት ፡ አውጥቶ ፡ በገነት ፡ አንፃር ፡ አኖረው።

፳፬፤ ቦግ ፡ ቦግ ፡ የምትል ፡ የእሳት ፡ ሰይፍ ፡ በእጃቸው፡ ያለች ፡ ኪሩቤልና ፡ ሱራፌልንም ፡ የዕፀ ፡ ሕይወት ፡ መንገድን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው።

የነቢዩ፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፵፥፩–፫።

፩፤ እግዚአብሔር ፡ ነቢያትን ፡ ወገኖቼን ፡ ምከሩዋቸው፡አለ።

፪፤ ካህናቱን ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ከልቧ ፡ የሚገባ ፡ ነገርን፡ንገርዋት፤ ገሥቍልናዋ፡በዙ፡ነውና፡ኃጢአቷም፡በዝቷልና፡የኃጢአቷንም፡ፍዳ፡ከእግዚአብሔር፡እጅ፡ዕዕፍ፡አድርጋ፡ተቀብላለችና፡ምከርዋት፡አለ።

፫፤ የዓዋጅ፡ነጋሪ፡ቃል፡በምድረ፡በዳ፡የእግዚአብሔርን ፡ ጐዳና ፡ ጥረጉ ፤ የፈጣሪያችሁንም ፡ ጥርጊያ፡ጐዳና፡አስተካክሉ።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፬፥ ኲሉ ፡ ማዕምቅ ፡ ይምላዕ ፡ ወኲሉ ፡ ደብር ፡ ወወግር፡ይትሐት፡ወይኩን፡ኲሉ፡መብእስ፡ መጽያሕተ፡ወይኩን፡ቈላተ፡ምድር፡ርኂበ።

፭፥ ወያስተርኢ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይርአይ፡ኲሉ፡ዘነፍስ፡መድኃኒተ፡እግዚአብሔር።

፮፥ እስመ፡እግዚአብሔር፡ነበበ፡ቃለ፡ዘይብል፡ ክላህ፡ወበል፡ወእቤ፡ምንተ፡እኬልህ፡ኲሉ፡ ዘሥጋ፡ከመ፡ሣዕር፡ወኲሉ፡ክብሩ፡ለሰብእ፡ ከመ፡ፍሬ፡ሣዕር።

፯፥ ወይየብስ፡ሣዕሩ፡ወይወድቅ፡ፍሬሁ፡እስመ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይነብብ ፡ ቦቱ ፡ አኮኑ፡ሣዕር፡ሕዝብ።

፰፥ ይየብስ፡ሣዕር፡ወይትነገፍ፡ጽጌ፡ወቃለ፡እግዚአብሔርሰ፡ይነብር፡ለዓለም።

ምዕ፤፩፡፩–፱።

፩፥ ምሳሌያተ፡ሰሎሞን፡ወልደ፡ዳዊት፡ዘነግሠ፡ ለእሥራኤል፡በኢየሩሳሌም።
፪፥ ለአእምሮ ፡ ጥበብ ፡ ወተግሣፅ ፡ ወለአእምሮ ፡ ቃለ፡ጥበብ።

፫፥ ወለተወክፎ ፡ መይጠ ፡ ቃል ፡ ወለአእምሮ ፡ ጽድቅ፡ዘበአማን።
፬፥ ወለአርትዖ ፡ ፍትሕ ፡ ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ ጥበበ ፡ ለየዋሃን ፡ ለሕፃናት ፡ ወለወራዙት ፡ ተዐውቆ ፡ ወአእምሮ።

፭፥ ዘንተ ፡ እምከመ ፡ ሰምዐ ፡ ጠቢብ ፡ ይዌስክ ፡ ጥበበ።
፮፥ ወዘሰ ፡ አጥረየ ፡ ሐዳፌ ፡ የአምር ፡ ምሳሌ ፡ ወሥውረ፡ነገረ፡ነገረ፡ጠቢባን፡በቅጽበት።

፯፥ ቀዳሚሃ ፡ ለጥበብ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአእምሮ፡ሠናይት፡ለኵሉ፡ዘይገብራ፡ፈሪሀ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳሚ ፡ ተዐውቆ ፡ ጥበበ ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፬፥ የጐደጐደው ፡ ሁሉ ፡ ይምላ ፤ ተራራው ፡ ኰረብታው፡ሁሉ፡ይስተካከል፤ጐጣጉጡም፡ ሁሉ ፡ ጥርጊያ ፡ ጐዳና ፡ ይሁን፤ የቈላው ፡ ምድር፡ሁሉ፡ሜዳ፡ይሁን።
፭፥ የእግዚአብሔር ፡ ጌትነት ፡ ይገለጥ ፤ ሥጋዊ፡ ደማዊ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚአደርገውን፡ድኅነት፡ይይ፤የሚል፡ይሰማል።
፮፥ እግዚአብሔር ፡ አሰምተህ ፡ ተናገር ፡ የሚል፡ ቃል ፡ ተናግሮዋልና ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ ልናገር፡ አልሁ ፤ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሣር፡ ነው፤የሰውም፡ሁሉ፡ክብሩ፡እንደ፡ሣር፡ፍሬ ነው።
፯፥ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወቱ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ ይናገርበታልና ፡ ሣሩ ፡ ይደርቃል፤ ፍሬውም፡ ይረግፋል። ይኸውም ፡ ሣር ፡ ያልሁት ፡ ሰው፡ ነውና።
፰፥ ሰው፡ይጠፋል፤አበባም፡ይረግፋል፤የእግዚአብሔር፡ቃል፡ግን፡ለዘላለም፡ጸንቶ፡ይኖራል፡ ብለህ፡አስተምር፡አለኝ።

ምዕ፤፩፡፩–፱።

፩፥ ለእስራኤል፡በኢየሩሳሌም፡የነገሠ፡የዳዊት፡ ልጅ፡ሰሎሞን።
፪፥ ጥበብንና ፡ ተግሣፅን (ዘጠኙን ፡ ሕግጋትና፡ ኢ.ታምልክን) ፡ ለማወቅ ፡ የፈሊጥን ፡ ነገር፡ ለማሳወቅ።
፫፥ የቃል ፡ መልስን ፡ ለመቀበል ፡ እውነተኛ፡ ነገርንም፡ለማወቅ።
፬፥ ላልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ጥበብን ፡ ለሕፃናት፡ ማወቅን ፡ ለጐልማሶች ፤ ዕውቀትን ፡ ያስተምራቸው፡ዘንድ፡ፍርድን፡ለማቅናት፡ሰሎሞን፡ የተናገረው፡ነገር፡ይህ፡ነው።
፭፥ ብልህ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በጥበብ፡ ላይ፡ጥበብን፡ይጨምራል።
፮፥ መምህርን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ሥውር፡ ነገርንና፡ምሳሌን፡ያውቃል፤የመምህራንም፡ ነገራቸው፡በዓይን፡ጥቅሻ፡ነው።
፯፥ የጥበብ ፡ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔርን፡ መፍራት ፡ ነው ። ለሚያደርጋትም ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ በጎ ፡ ዕውቀት ፡ ናት። እግዚአብሔርን፡ መፍራት፡የዕውቀት፡መጀመሪያ፡ናት።የጥ

| በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ወተግሣፀ፡ይሜንኑ፡ረሲዓን። | ዘኢአብሔርንም ፡ ሕግ ፡ የዘነጉ ፡ ሰዎች ፡ ተግሣፅን ፡ ምክርን ፡ ትምህርትን ፡ ይንቃሉ ፤ ይጠላሉ። |
| ፫፤ ስማዕ ፡ ወልድየ ፡ ሕገገ ፡ አቡከ ፡ ወኢትት ሐየይ፡ትዕዛዘ፡እምከ። | ፫፤ ልጄ ፡ የአባትህን ፡ ሕግ ፡ ስማ፤ የእናትህንም ፡ ትዕዛዝ፡ቸል፡አትበል። |
| ፬፤ አክሊለ ፡ ክብር ፡ ትነሥእ ፡ ለርእስከ ፡ ወባዝግና፡ወርቅ፡ለክሣድከ። | ፬፤ ለራስህ፡ክብር፡ያለው፡ዘውድን፡ትቀዳጃለህ፤ ለአንገትህም፡ዝርግፍ፡ወርቅ፡ታሥራለህ። |
| ክፍል፡፪። | ክፍል፡፪። |
| ድርሳን ፡ ዘይትነበብ ፡ በተሰዐቱ ፡ ሰዓት ፡ ዘዕለተ፡ሰኑይ። | ሰኞ ፡ ከቀኑ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ የሚነበብ ፡ ድርሳን። |
| ፩፤ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ እለ ፡ ያነብቡ ፡ መጽሐፈ ፡ ጥበብ፡ ዘአፍአ ፡ ወዜና ፡ ገድል ፡ ዘበዓለም ፡ ይበጽሑ ፡ በተጠናቅቆ ፡ ምንባብ ፡ ለአእምሮ ፡ ፍካሬ፡ቃላት። | ፩፤ አፍአዊ ፡ ጥበብን ፡ የሚአሳውቁ፡ መጻሕፍትን፡ የሚአነቡ ፡ ከሆኑ ፡ በዓለምም ፡ የሚሆነውን፡የተጋድሎ፡ዜና፡ጠንቅቆ፡በማንበብ፡ የቃላትን፡ትርጓሜ፡ለማወቅ፡ይደርሳሉ። |
| ፪፤ እፎኬ ፡ ይደሉ ፡ ለእለ ፡ ይሰምዑ ፡ መጻሕፍተ ፡ ዘመለኮት ፡ ወያነብቡ ፡ ነገራተ ፡ ዘእግዚእ ፡ ከመ ፡ ይትጋደሉ ፡ በእስተፋጥኖ ፡ ለሰሚዖታ፡ ወጽሒቅ ፡ ለለብዎ ፡ ቃላቲሃ ፡ ወሐቲት ፡ ለፍካሬ ፡ ነገራ፡ ኅቡእ ፡ ወተመይጦ ፡ ለረኪበ ፡ ፍናዊሃ፡ሥውር። | ፪፤ የጌታን ፡ ነገር ፡ የሚናገሩ ፡ አምላክ ፡ ያጻፋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ለሚአነቡና ፡ ለሚሰሙ ፡ እርስዋን ፡ ሰምቶ ፡ ለማወቅ ፡ ተግቶ ፡ ቃሏን ፡ ለማስተዋል ፡ የተሠወረ ፡ ምሥጢርዋንም ፡ መርምሮ ፡ ተመልሶም ፡ ሥውር ፡ መንገዷን ፡ ለማግኘት፡እንዲጋደሉ፡እንዴት፡በይበልጥ፡ ይገባ፡ይሆን። |
| ፫፤ ወስማዕ፡ይእዜኒ፡አ፡ፍቁር፡ዘይቤ፡መጽሐፍ፡ አምላካዊ ፡ ወሶበ ፡ በልዑ ፡ እምዕፀ ፡ ተፈትሐ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ ወአእመሩ ፡ ከመ ፡ ዕራቃኒሆሙ፡ወነሥኡ፡እምቈጽለ፡በለስ፡ወገብሩ፡ ዐጽፈ። | ፫፤ የተወደድህ ፡ ወንድም ፡ ሆይ ፡ አሁንም ፡ አምላካዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ከዕፀ ፡ በለስ ፡ ፍሬ ፡ በበሉ፡ ጊዜ ፡ ዐይናቸው ፡ ተገልጦ ፡ ራቁታቸውን ፡ እንደሆኑም ፡ አወቁ ። ከዕፀ ፡ በለስም ፡ ቅጠል ፡ ወስደው ፡ ለዕርቃናቸው ፡ መሸፈኛ ፡ (መከለያ)ሠሩ፡ያለውን፡ስማ፤ |
| ፬፤ ወሰምዑ፡ድምፀ፡እግዚእ፡አምላክ፡ በውስተ፡ ገነት ፡ በጊዜ ፡ ምሴት ፡ ወተኀብኡ ። ነጽሩኬ ፡ ላዕለ ፡ ዕበየ ፡ ጸጋ ፡ ተአዛዚያን ፡ ወብዝኀ ፡ ነውረ፡ዐላውያን። | ፬፤ የእግዚአብሔር ፡ አምላክንም ፡ ድምፅ ፡ በምሽት ፡ ጊዜ ፡ በገነት ፡ ውስጥ ፡ ሰምተው ፡ ተሸሸጉ። የታዛዦችን ፡ የጸጋ ፡ ልዕልና ፡ የዐመፀኞችንም፡የነውር፡ብዛት፡ተመለከቱ። |
| ፭፤ እስመ ፡ ሔኖክ ፡ ወኤልያስ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ በሥጋ ፡ መዋቲ ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ትዕዛዘ ፡ ፈጣሪሆሙ ፡ ወኮኑ ፡ ተላውያነ ፡ በፍኖት ፡ ትሩፍ ፡ ግዕዘ ፡ እምዘይረክቦ ፡ ለፍጥረት ፡ ሥጋዊ፡እሞት፡ወሙስና። | ፭፤ በመዋቲ ፡ ሥጋ ፡ የተወለዱ ፡ ሔኖክና ፡ ኤልያስ፡የፈጣሪያቸውን፡ትዕዛዝ፡ሰምተው፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ሥርዓት ፡ ተከታዮች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ፡ሥጋዊ፡ደማዊ፡የሆነ፡ፍጥረትን፡ከሚአገኘው፡ሞትና፡ጥፋት፡ነጻ፡ሆኑ። |
| ፮፤ ወተለዓሉ ፡ እምድር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወተሳተፉ ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ እለ ፡ ኢይመውቱ። | ፮፤ ከምድርም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ። ሞት ፡ ከሌላባቸው ፡ መላእክትም ፡ ጋራ ፡ አንድ፡ሆኑ። |

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፯፡ ወእሉሰ፡እለ፡ተፈጥሩ፡ዘኢይመውቱ፡በፍጥረቶሙ ፡ ሶበ ፡ ተዐደዉ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር፡ አምጽኡ ፡ ሞተ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወተዐርቁ ፡ እምልብሰ ፡ ክብር ፡ ወተሰዱ ፡ እምገነተ፡ተድላ፡ወተወግሩ፡በምንዳቤ። | ፯፡ በተፈጥሮአቸው ፡ የማይሞቱ ፡ ሁነው ፡ የተፈጠሩ፡እኒህ፡አዳምና፡ሔዋን፡ግን፡የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ በተላለፉ ፡ ጊዜ ፡ በላያቸው፡ሞትን፡አመጡ፤ከክብር፡ልብስ፡ተራቆቱ፡ከተድላ፡ገነት፡ወጥተው፡በመከራ፡ተጣሉ። |
| ፰፡ አ ፡ ለዛቲ ፡ ዐቢይ ፡ አምጣኒሃ ፡ ወለእለ ፡ መንክር፡ክዋኔሆሙ። | ፰፡ ወዮ ፡ ለዚች ፡ መጠኗ ፡ ታላቅ ፡ አንክሮ፡ ይገባል፤ሁኔታቸውም፡ድንቅ፡ለሆነው። |
| ፱፡ ወሶበ፡ዐለዉ፡አስተርአየት፡ታሕጻጺሆሙ፡ ወተወለጠት ፡ ተመይጦሙ ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ ተንብአ ፡ እምፈጣሬ ፡ ፍጥረታት ፡ ዘህልው፡በኵሉ፡መካን፡ዘየአምር፡ምክረ፡ኅሊና፡ዓለም፡ወኵሎ፡ኅሊና፡ዘአልባብ። | ፱፡ ባመፁም ፡ ጊዜ ፡ ፍጥረታትን ፡ ከፈጠረ፡ በሁሉ፡ቦታ፡ምሉዕ፡ከሆነ፡የሰውን፡ምክርና፡የልብን፡ኀሳብ፡መርምሮ፡ከሚአውቅ፡ጌታ፡ፊት፡መሸሸግ፡እስከ፡ፈለጉ፡ድረስ፡ደርሰው፡ውርደታቸው ፡ ተገለጸች። መመለሻቸውም፡ተለወጠች። |
| ፲፡ ሰምዐ፡ዘይቤ፡እግዚአ፡ዓለም፡አ፡አዳም፡ አይቴኑ፡ሀሎከ፡አንተ፡እስመ፡ሶበ፡አስተርአየ፡ዕራቆ፡እምጸዳለ፡ብርሃን፡ኅፍረ፡እምርእየተ፡ፈጣሪሁ፡ወተሠወረ፡በአቍጽለ፡ዕፅ፡በፈሪህ ፡ በዘሀሎ ፡ ይኩን ፡ ዕልወት ፡ እንዘ ፡ ይጐይይ፡እምኵነኔ፡ወተንበአ፡በአጕናደ፡ዕፅ። | ፲፡ አዳም፡ሆይ፤አንተ፡ወዴት፡አለህ፡ያለውን፡ የዓለምን ፡ ፈጣሪ ፡ ቃል ፡ ሰሙ ፤ ከብርሃን፡ ልብስ፡ተራቁቶ፡በታየ፡ጊዜ፡የፈጣሪውን፡ፊት ፡ ከማየት ፡ በመፍራት ፡ በዕንጨት፡ቅጠል፡ ተሠወረ ፤ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ባለው፡ ጥፋት፡ ከፍርድ ፡ ሊሸሽ ፡ በዛፍ ፡ ግንድ፡ ተሸሸገ። |
| ፲፩፡ ይቤ፡እንዘ፡ያወሥእ፡ለእግዚአ፡ ሰማዕኩ፡ ምጽአተከ፡ውስተ፡ገነት፡ወፈራህኩ፡ወተኀባእኩ። አጽምዕኬ፡ይእዜ፡ወሠናየ፡ለቡ፡ርቱዐ፡ከመ፡ታእምር፡መጠነ፡ኅሊና፡ቃል፡ዘእግዚአ፡ ወአርትዖ ፡ ፍትሕ ፡ ዘልዑል ፡ ወተማሣጸ ፡ ዘጽልሑት፡ወምሕረተ፡ዘዐባይ፡አምጣኒሃ። | ፲፩፡ ለጌታ፡ ሲመልስ፡ወደ፡ገነት፡መምጣትህን፡ሰማሁ፤ፈርቼም፡ተሸሸግሁ፡አለ። አሁንም ፡ አድምጥ ፤ በጎውን ፡ በትክክል፡ አስተውል ፤ የጌታን ፡ የቃሉን ፡ የአሳብ፡ መጠን፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ የልዑልን ፡ ፍርድ፡ ማቅናት፡የሸንገላን፡ተግሣፅ፡መጠኗ፡ታላቅ፡ የሆነውን ፡ ይቅርታ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ፡ አስተውል። |
| ፲፪፡ እስመ፡ብሂሎቱ፡አይቴ፡አንተ፡ፍካሬሁ፡ አኮ፡ ኢያእሚሮ ፡ መካኖ ፡ ሐሰ፤ ዳእሙ ፡ ፍካሬሁ፡እስመ፡አነ፡ፈጠርኩከ፡ሥርግወ፡ በኵሉ፡ላሕይ፡ልቡሰ፡አክሊለ፡ስብሐት፡ዘኢይረክቦ፡ሙስና። ወኅደጉከ፡ውስተ፡ገነት፡መኰንነ፡ወሤምኩከ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ሠናያት፡ወረሰይኩከ፡ክቡረ፡ወርሱየ። | ፲፪፡ ወዴት ፡ ነህ ፡ ማለቱ ፡ እኮ ፡ ትርጓሜው፡ ቦታውን፡ባለማወቅ፡አይደለም፤እውነተኛ፡ትርጓሜው፡በውበት፡ሁሉ፡አስጊጬ፡ፈጥሬሃለሁና ፡ ጥፋት ፡ የማያገኘው ፡ የክብር፡ ልብስን፡ አጐናጸፍኩህ ፤ በገነትም ፡ ገዥ፡ አድርጌ፡ተውኩህ፤በስነ፡ፍጥረት፡ላይ፡ሁሉ፡ ስለሾምኩህ፡የተሸለመ፡የከበረ፡አደረኩህ፡ ማለት፡ነው፡እንጂ። |
| ፲፫፡ ወናሁ፡አንተ፡ይእዜ፡ከመ፡አሐዱ፡እምአራዊት ፡ ንስቲተ ፡ ትጐይይ ፡ እምእለ ፡ የኀሥሡከ፡ ወትሜወር፡በአዕፁቀ፡ፆም፡ዕሩቀከ፡ እምልብሰ፡ስብሐት፡ወክብር፡ዘያደነግፅ። | ፲፫፡ እነሆ፡አንተ፡አሁን፡ከአራዊት፡እንደ፡አንዱ፡ በጥቂቱ፡ትሸሻለህ፤ከሚአስደነግጥ፡የክብር፡ የጌትነት፡ ልብስ ፡ ተራቁተህ ፡ በዛፍ፡ ቅርንጫፍ፡ውስጥ፡ከሚሹህ፡ትሠወራለህ። |

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፲፬፡ አጠይቀኒ፡ይእዜኒኬ፡አይቴ፡ሀሎከ፡ወእፎኑ፡ አንተ፡ወምንትኑ፡ዘአብጽሐከ፡ይእዜኒ፡ኀበ፡ ዝንቱ፡ውላጤ፡ዐቢይ። | ፲፬፡ አሁንም ፡ አስረዳኝ ፡ እስኪ ፡ ወዴት ፡ አለህ? አንተ ፡ ምንድነህ ? ወደዚህ ፡ ታላቅ ፡ ለውጥ ፡ ዛሬ፡ምን፡አደረሰህ? |
| ፲፭፡ ወመኑ ፡ ዘአፍለሰከ ፡ እምዕረፍት ፡ ኀበ ፡ ፃማ ፡ ወእምኑዛዜ ፡ ኀበ ፡ ትካዝ ፡ ወእምትውክልት ፡ ኀበ ፡ ፍርሀት ፡ ወረዐድ ፡ ወድንጋጼ ፡ ወእምተ ሠንዮ ፡ በክብር ፡ ወበጸዳል ፡ ኀበ ፡ ክፍአት ፡ በአቍጽለ፡ዕፅ። | ፲፭፡ ከዕረፍት ፡ ወደ ፡ ድካም ፡ ከመረጋጋት ፡ ወደ ፡ ትካዜ ፡ ከመተማመን ፡ ወደ ፡ ፍርሀት ፡ ወደ ፡ መንቀጥቀጥና ፡ ወደ ፡ መደንገጥ ፡ በክብር ፡ በብርሃን ፡ ከመሸለም ፡ ወደሚአስከፋ ፡ በዕንጨት፡ቅጠሎች፡ወደ፡መሸጎጥ፡ማን፡ አፈለሰህ? |
| ፲፮፡ ወምንትኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ውላጤ፡ዘወረደ፡ ላዕሌከ፡ግብተ። ወእፎኑ ፡ ተዓረርከ ፡ ወገፀየይከ ፡ እምፈጣሪከ ፡ ወተሠወርከ ፡ እምዘ ፡ ይጤይቅ ፡ ፍጥረተከ ፡ ወፈራህከ፡እምዘ፡አሠነየ፡ለከ። | ፲፮፡ ይህ፡በአንተ፡ላይ፡ድንገት፡የወረደ፡ለውጥ፡ ምንድነው? ከፈጣሪህ፡ተጣልተህ፡ተፈጥሮህንም፡ከሚአ ውቅና፡ከሚረዳው፡በልጅነትም፡ከአከበረህ፡ ፈጣሪህ፡ፈርተህ፡ለምን፡ሸሸህ? |
| ፲፯፡ አይ ፡ ኆህልያ ፡ ሰረቀ ፡ መዝገበከ ፡ ስቡሐ ፡ ወአይ፡ኃያል፡ተዐገለ፡ንዋየ፡ብዕልከ፡ወአይ፡ ነፋስ ፡ ጽኑዕ ፡ ገንጸለ ፡ ሐመረከ ፡ ግብተ ፡ ወረሰየከ፡ነዳየ፡ወምኑነ። | ፲፯፡ ምን ፡ ተንኰለኛ ፡ የከበረ ፡ መዝገብህን ፡ ሰረቀህ? ምን ፡ ኃይለኛስ ፡ የብልጽግናህን ፡ ገንዘብ፡ነጠቀህ?ምን፡ጽኑ፡የሆነ፡ነፋስ፡መር ከብህን፡በድንገት፡ገልብጦ፡የተናቅህና፡የተ ዋረድክ፡ድኃ፡አደረገህ? |
| ፲፰፡ ወአውሥአኒ ፡ እስኩ ፡ ይእዜ ፡ ምንት ፡ ዘአፍ ርሀከ ፡ ወአይ ፡ አርዌ ፡ ዘነሰከከ ፡ ወበአይ ፡ ግብር፡ዘተኀባእከ፡እምፍርሀት፡ወኀፍረት። | ፲፰፡ እስኪ ፡ መልስልኝ ፡ ዛሬ ፡ ያስፈራህ ፡ ምንድነው? ምን ፡ አውሬስ ፡ ነከሰህ ? ከመፍ ራትና ፡ ከማፈር ፡ የተነሣ ፡ የተሸሸግኸው ፡ በምን፡ሥራ፡ነው? |
| ፲፱፡ ይቤ ፡ አዳም ፡ ሰማዕኩ ፡ ሰኰናከ ፡ እንዘ ፡ ተሐውር፡ውስተ፡ገነት፡ወፈራህኩ፡እስመ፡ እነ፡ዕሩቅ፡ወተኀባእኩ። | ፲፱፡ አዳምም፡በገነት፡ውስጥ፡ስትሄድ፡ዱካህን፡ ሰማሁ ፡ ራቁቴን ፡ ስለሆንኩ ፡ ፈርቼ ፡ ተሸሸግሁ፡አለ። |
| ፳፡ ወይቤሎ፡እግዚእ፡መኑ፡ነገረከ፡ዘንተ፡ከመ፡ አንተ፡ዕሩቅ፡ወመኑ፡ከሠተ፡ለከ፡ሕሠመ፡ ዐጽፍከ። | ፳፡ ጌታም ፡ እንዲህ፡አለው፡አንተ፡ራቁትህን፡ መሆንህን፡ይህን፡ማን፡ነገረህ?የልብስህንስ፡ መበላሸት፡ማን፡ገለጠልህ? |
| ፳፩፡ አይቴ፡ልብስከ፡ስቡሕ፡ወአይቴ፡ዐጽፍከ፡ ብሩህ ፡ ወአይቴ ፡ አክሊለ ፡ ክብርከ ፡ ዘያንጸ በርቅ። | ፳፩፡ የከበረው፡ልብስህ፡ወዴት፡ነው?የብርሃን፡ መጐናጸፊያህ ፡ ወዴት ፡ ነው ? የሚአንፀባ ርቀው፡የክብር፡አክሊልህስ፡ወዴት፡አለ? |
| ፳፪፡ ሶበ ፡ አኮ ፡ ዘበላዕከ ፡ እምዕፅ ፡ ዘአዘዝኩከ ፡ ከመ፡ኢትብላዕ፡እምኔሁ። | ፳፪፡ እንዳትበላ ፡ ከዘዝኩህ ፡ ዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ከእርሱ ፡ ባትበላ፡ኖሮ፡ይህ፡ባልሆነ፡ነበር። |
| ፳፫፡ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ አውሥአ ፡ አዳም ፡ በአመ ክንዮ ፡ ወይቤ ፡ ብእሲት ፡ ዘረሰይከ ፡ ትኩን ፡ ምስሌየ ፡ ይእቲ ፡ ወሀበተኒ ፡ ወበላዕኩ ፡ እምኔሁ። | ፳፫፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አዳም ፡ በማመካኘት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ፡መለሰ፡ከእኔ፡ጋራ፡እንድትሆን፡ያደረ ግሃት፡ሴት፡ሰጥታኝ፡ከእርሱ፡በላሁ። |
| ፳፬፡ ኀለየ፡በዝንቱ፡ቃል፡ያምሥጥ፡እምንዳቤ፡ ወይፃእ፡እምዘሀሎ፡ኵነኔ፡ይትከሎነን። | ፳፬፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ይፈረድበት ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ ፍርድና፡ቅጣት፡፡መልጥ፡ዘንድ፡አሰበ። |
| ፳፭፡ ዳእሙ፡ሰማዕ፡ዘይብል፡እግዚእ፡ዓለም፡አይ፡ ምንዳቤ ፡ ይደልወከ ፡ ይእዜ ፡ ወአይ ፡ ኵነኔ ፡ | ፳፭፡ ነገር ፡ ግን ፡ የዓለም ፡ ጌታ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ፋ ፡ይጋባህ ፡ ይገባህ ፡ ይሆን? ዛሬ ፡ የምትዘጋጅ |

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ዘትዴሎ፡ላቲ፡ይእዜ።

፳፮፤ በእንተ፡ዘተዓደውከ፡ትዕዛዝየ፡ወሥርዓትየ፡ ወዐለውከ፡ሕግየ፡ወኀደገ፡ፍናውየ፡እስመ፡ ብእሲትሰ፡ሶበ፡አስተአደመት፡ለከ፡ትብላዕ፡ እምዕፅ፡ወመጠወተከ፡እምፍሬሃ፡ለምንት፡ ኢቀደምከ ፡ በትእዛዝየ ፡ ዘገሠፅኩከ ፡ እምቅድመ ፡ ገቢሮታ ፡ በነጽሮ ፡ ወኢያፍ ራህከ፡ሥጋከ፡በዙኀኔ።

፳፯፤ ዳእሙ፡ኮንከ፡አብደ፡በምግባሪከ፡አኮኑ፡እም ተደለውከ ፡ ከመ ፡ ታእምር ፡ ወትዕቀብ ፡ ትእዛዘ ፡ ፈጣሪከ ፡ ወትትከላእ ፡ እምዘከላ ፡ ዕኩከ ። ኢያእምረከኑ ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ላቲ ፡ ወይእቲ፡እምዐፅምከ፡ዐፅም።

፳፰፤ ወእሮ፡ደለወከ፡እንዘ፡አንተ፡ፈታሒ፡ከመ፡ ይፍትሖ፡ላዕሌከ፡ወረሰይከ፡ዘመትሕቴከ፡ መልዕልቴከ፡ወረሰይከ፡ዘነበ፡ርእሰከ።

፳፱፤ መኑ ፡ ይክል ፡ ይላሖ ፡ ኀፍረተ ፡ ድቀትከ ፡ ወአይ፡ዐይን፡ይክል፡ይግበር፡ብካየ፡በእንተ፡ ክዋኔከ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ። እስመ ፡ አንተ ፡ አኅሰርከ ፡ ርእሰከ ፡ ወአፈድፈድከ ፡ ኀሳረ ፡ ሲሳይከ፡ወሀጐልከ፡እምሠናይት፡ዘእዝዝት፡ ለከ፡ዛቲ፡ዐባይ፡አምጣኒሃ።

፴፤ ወለእመ፡ኮነ፡አፍቅሮ፡ሥሥዕት፡ወኀሢሠ፡ ሢመት ፡ ይዌግሩ ፡ ውስተ ፡ ሀጕል ፡ ወይመትሩ፡ ሐብለ ፡ ትእዛዝ ፡ ወያበጽሖ ፡ ሐብለ፡ተዓድዎ፡ወያርሕቅ፡እምሕረተ፡እግ ዚአብሔር፡ወያቄርቦ፡ለአጋንንት።

፴፩፤ ይደልወነኬ፡ከመ፡ንጕየይ፡እምፍትወትነ፡ ወከመ፡ናስተፋጥን፡ለገቢረ፡ፈቃዱ፡ለእግዚ አብሔር፡ዘሎቱ፡ስብሐት፡እስከ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሚን።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ላትን ፡ ፍርድ ፡ እንዴት ፡ ያለች ፡ ትሆን ያለውን፡ስማ፡እንጂ።

፳፮፤ ትዕዛዜን፡ስለ፡ተላለፍክ፡ሥርዓቴን፡ሕጌን፡ አፍርሰህ፡መንገዴን፡ስለ፡ተውክ፡ዛሬ፡የም ትዘጋጅላት፡ፍርድ፡እንዴት፡ያለች፡ትሆን ከዛፊቱ፡ፍሬ፡ትበላ፡ዘንድ፡ሴቲቱ፡ብታማ ጥልህ ፡ ከፍሬዋም ፡ ብትሰጥህም ፡ ከመ ራትህ ፡ በፊት ፡ በማስጠንቀቅ ፡ ያዘዝኩህን፡ አስቀድመህ፡ለምን፡አላሰብህም? ሥጋህን፡ ከቅጣት፡ለምን፡አላስፈራኸውም?

፳፯፤ ነገር፡ግን፡በሥራህ፡ሰነፍ፡ሆንክ፡የፈጣሪህን፡ ትእዛዝ፡ታውቅ፡ዘንድ፡ትጠብቀውም፡ዘንድ፡ ከከለከልኩህስ ፡ ነገር ፡ ትከለከል ፡ ዘንድ፡ በተገባህ፡ነበር፡አንተ፡የእርስዋ፡ጌታዋ፡እንደ ሆንክ ፡ እርሷም ፡ ከዓፅምህ ፡ ዐፅም ፡ እንደ ሆነች፡አላወቅህምን?

፳፰፤ አንተ፡ፈራጅ፡ስትሆን፡በአንተ፡ላይ፡ይፈር ዱብህ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፤ የበታችህን፡ የበላይህ ፡ አደረግህ ፤ ራስህን ፡ ጅራት፡ አደረግህ።

፳፱፤ ስለ ፡ መውደቅህ ፡ ኀፍረት ፡ ማን ፡ ያለቅሳል! ስለ፡ሁኔታህስ፡እንደሚገባ፡ልቅሶ፡ያደርግ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ምን ፡ ዓይን ፡ ነው? አንተ፡ ራስህን ፡ አጐሳቈለሃልና ፡ በምግብህ፡ መከራን፡ አበዛህ ፤ መጠንዋ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ፡ ላንተ፡የታዘዘችልህን፡በጎ፡ዕድል፡አጠፋህ።

፴፤ ሥሥስትና ፡ ዓለማዊ ፡ ሹመትን ፡ መውደድ፡ ከሆነ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይጥላል ፤ የጌታንም፡ ትእዛዝ ፡ አስትተው ፡ ሕግን ፡ ከመተላለፍ፡ አድርሰው ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ይቅርታ፡ አውጥተው፡ወደ፡አጋንንት፡ያቀርባሉ።

፴፩፤ ከዓለማዊ ፡ ፍላጎታችን ፡ እንርቅ ፡ ዘንድ፡ ይገባልና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውንም፡ ለመሥራት ፡ እንፋጠን ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል፡ ክብር፡ምስጋና፡ገንዘቡ፡የሚሆን፡ለዘላለም፡ አሜን።

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፺፩፡፮-፲።

፮፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አፍሮስዮስ፡ ርእሰ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘሀገረ ፡ አርማንያ።

፯፤ ይብሐሙ ፡ እንከሰ ፡ ወይትገሠፁ ፡ ነባብያን ፡ ከንቱ ፡ እምነገሮሙ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ እስመ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኮ ፡ ይእቲ ፡ በሥምረተ ፡ ሰብእ ፡ አላ ፡ በዘከሠተ ፡ ኀይለ ፡ መንፈስ።

፰፤ ንትዐቀብ ፡ እንከ ፡ ወኢንክፍል ፡ መለኮተ ፡ እምሥጋ ፡ እንዘ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትነገር ፡ በክልኤቱ ፡ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ክልኤቱ ፡ ህላዌያት ፡ ወአሐዱ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ።

፱፤ አሐደ ፡ጊዜ ፡ ይትናገር ፡ ዘከመ ፡ ስብሐተ ፡ መለኮት ፡ ወአሐደ ፡ ጊዜ ፡ ዘከመ ፡ ሕማመ ፡ ትስብእት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሜህር ፡ በመለኮት ፡ ወውእቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከመ ፡ ሰብእ ፡ ይብል ፡ በእንተ ፡ ትስብእት ፡ እንዘ ፡ አሐዱ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ።

፲፤ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ኅብስተ ፡ሕይወት ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ኅብስትሰ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋሁ ፡ ዘነሥአ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ኅብስት ፡ ዘወሀበ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ሥጋየ ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ዘአንጽሖ ፡ አብ ፡ ወፈነዎ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወአኮ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘይነግር ፡ ከመ ፡ መለኮት ፡ ይፈቅድ ፡ ንጽሐ ፡ አላ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ሥጋ።

ምዕ፤፺፪፡፩-፲።

፩፤ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘኢየሩ ሳሌም ፡ በሥርዓተ ፡ ትባሬ ፡ ሃይማኖት።

፪፤ ነአምን ፡ በአሐዱ ፡ መለኮት ፡ ወአሐዱ ፡ ሕላዌ ፡ ዘሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘንሰግድ ፡ ሎሙ ፡ በአሐዱ ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፺፩፡፮-፲።

፮፤ የአርማንያ ፡ አገር ፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ አለቃ ፡ ይህ ፡ ክቡር ፡ አባት ፡ አፍሮስዮስ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አለ።

፯፤ እንኪያስ ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገሩ ፡ እሊህ ፡ ከአነጋ ገራቸው ፡ የተነሣ ፡ መልስ ፡ ይጡ ፤ ይገሠፁ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የእግዚአብሔር ፡ሕግ ፡ ወንጌል ፡ የምትነገር ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሀብት ፡ በገለጠው ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ ልባምነት ፡ አይደለምና።

፰፤ እንግዲህ ፡ እንጠበቅ ፤ መለኮትንም ፡ ከሥጋ ፡ አንለይ ፤ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ተብሎ ፡ ይነገራል ። ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነው።

፱፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የጌትነቱን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ የሕማሙን ፡ የሞቱን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ። እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ የጌትነቱን ፡ ነገር ፡ ያስተምራል ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ሰውም ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ የሰውነቱን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሲሆን።

፲፤ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ኅብስተ ፡ ሕይወት ፡ ይህ ፡ ነው። ይህም ፡ ኅብስት ፡ የነሣው ፡ ሥጋው ፡ ነው። ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ ኅብስት ፡ አብ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ የላከው ፡ ያከበረው ፡ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ሥጋዬ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እንዳለ ፡ መለኮት ፡ ክብርን ፡ እንዲሻ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚናገር ፡ አይደለም ፤ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ተናገረ ፡ እንጂ።

ምዕ፤፺፪፡፩-፲።

፩፤ በኢየሩሳሌም ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ የተሾመ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ መጽሐፉ ፡ እንዲህ ፡ አለ።

፪፤ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ የምንሰግድላቸው ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ በባሕርይ ፡ በመለኮት ፡ አንድ ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

አምላኮ ፡ ዘውእቶሙ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ፡ቅዱስ።

፫፤ ወነአምን ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ሠለስቱ ፡ አካላት ፡ ፍጹማን ፡ በገጻት ፡ ወዕሩያን ፡ በመለኮት ፡ ወበህላዌ ፡ ወበብሉየ ፡ መዋዕልና ፡ በስብሐት ፡ ወኃይል ፡ ወበህልዎ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወዘኢየአምን ፡ ዘንተ ፡ ከመዝ ፡ ንህነ ፡ ናወግዞ።

፬፤ ወበእንተ ፡ ትስብእቱ ፡ ወትሥግውቱ ፡ ለእግዚእነ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንብል፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ቀዳማዊ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መለኮታዊ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒተ ፡ ትዝምደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ተወልደ፡እምእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ ማርያም፡ወወፅአ፡እምብእሲት፡በከመ፡ይቤ፡ ሐዋርያ።

፭፤ ወሶበ ፡ ተሠገወ ፡ እምኔሃ ፡ ተዐረየ ፡ ምስሌነ ፡ ወተዐገሠ ፡ ሕማመ ፡ በእንቲአነ ፡ ዘበአማን ፡ ወአኮ ፡ በምትሐት ፡ ወደከመ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት፡ ዘከማነ ፡ ወአኮ ፡ በምትሐት።

፮፤ ወሶበሂ፡ቀሠፍዎ፡ወተወክፈ፡ሕማመ፡በእንቲአነ ፡ እምጲላጦስ ፡ ተዐውቆ ፡ ሕማም ፡ ወዝብጠት ፡ ዘከማነ ፡ ወሶበሂ ፡ ፀፍዕዎ ፡ ወቀነውዎ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ በቅንዋት ፡ ኮነ፡ይትዓወቆ፡ሕማም፡ዘተወክፎ።

፯፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኢሳያስ ፡ ነቢይ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ደዌነ ፡ ወፆረ ፡ ሕማመነ፡ ወውእቱ ፡ ትኩዝ ፡ በእንቲአነ ፡ ወንሕነ ፡ ርኢናሁ ፡ ድውየ ፡ ወሕሙመ ፡ ወኅሡረ ፡ ወቅኑሉ ፡ በእንተ ፡ ኃጣውኢነ ፡ ወተዐገሠ፡ዘንተ፡በእንተ፡ጌጋይነ፡ወካዕበ፡ ይቤ ፡ ብእሲ ፡ ቅኑል ፡ ወሥጠ ፡ ሕማመነ ፡ ዲቤሁ።

፰፤ ወካዕበ፡ንስምዖ፡ለጳውሎስ፡እንዘ፡ይብል፡ በእንቲአሁ፡ከመ፡ውእቱ፡ሊቀ፡ካህናቲነ፡ ወይክል፡ይሕምም፡ሕማመነ፡ወተመክረ፡ ከማነ፡በኵሉ፡ግብር፡ዘእንበለ፡ኃጢአት፡ ባሕቲታ።

፱፤ ወንትአመን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ነፍሰ ፡ ነባቢተ፡እንተ፡ትመስል፡ነፍሳቲነ፡በሕማመ፡ ዘሐመ፡በእንቲአነ፤ወካዕበ፡ተዐገሠ፡ሕማመ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እንደሆኑ ፡ እናምናለን ። እሊህም ፡ አብ፡ ወልድ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ናቸው።

፫፤ እሊህም ፡ ሦስቱ ፡ አካላት ፡ በገጽ ፡ ፍጹማን፡ እንደሆኑ ፡ በሥልጣን ፡ በባሕርይ ፡ ከዘመን፡ አስቀድሞ ፡ በመኖር ፡ በጌትነት ፡ በመፍጠር፡ ሳይለወጡ፡በመኖር፡አንድ፡እንደሆኑ፡እናምናለን፤ይህን፡እንዲህ፡ብሎ፡የማያምነውን፡ እኛ፡እናወግዘዋለን።

፬፤ ጌታችን ፡ አምላካችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ነፍስና፡ሥጋን፡ተዋሕዶ፡ ሰው፡ስለመሆኑም፡በቅድምና፡የነበረ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ጌትነት፡ገንዘቡ፡የሆነ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ሰውን፡ለማዳን፡ከእመቤታችን፡ከቅድስት፡ድንግል፡ማርያም፡እንደ፡ ተወለደ ፡ እንናገራለን ፤ ጳውሎስ ፡ እንደተ ናገረ፡ከድንግልም፡ተወለደ።

፭፤ ከእርሷም፡ሥጋን፡ነፍስን፡በተዋሐደ፡ጊዜ፡ እኛን ፡ መሰለ ፡ በምትሐት ፡ ያይደለ ፡ በእውነት፡ ስለእኛ፡መከራን፡ወዶ፡ተቀበለ፡ መንገድ፡በመሄድም፡እንደእኛ፡ደከመ፤በምትሐትም፡አይደለም።

፮፤ በግርፋትም ፡ ጊዜ ፡ ስለእኛም ፡ ከጲላጦስ ፡ መከራን፡በተቀበለ፡ጊዜ፡እንደእኛ፡መከራው፡ ግርፋቱ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ፤ ፊቱን ፡ በፀፋት፡ ጊዜም፡እጁን፡እግሩን፡በችንካር፡በቸነከሩት፡ ጊዜም፡የተቀበለው፡መከራ፡ይሰማው፡ነበር።

፯፤ እርሱ፡ደዌያችንን፡ወሰደ፤ሕማማችንንም፡ ተሸከመ ፤ እርሱ ፡ ስለእኛ ፡ አዘነ ፤ ተከዘ፡ የእኛን፡ኃጢአት፡ለማስተስረይ፡የታመመ፡ የቈሰለ፡ሁኖ፡አየነው፡በደላችንን፡ለማስተ ስረይ፡ይህን፡ወዶ፡ተቀበለ፡ብሎ፡ኢሳይያስ፡ እንደተናገረ፡ዳግመኛም፡በችንካር፡በጦር፡ የቆሰለው፡ሰው፡የእኛን፡መከራ፡ተቀበለ፡ ብሏል።

፰፤ ዳግመኛ ፡ አስታራቂያችን ፡ እንደሆነ ፡ የእኛንም ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ እንዲችል ፡ ከኃጢአት፡በቀር፡በሥራ፡ሁሉ፡እንደ፡እኛ፡ እንደተፈተነ፡ስለርሱ፡ሲናገር፡ጳውሎስን፡ እንሰማው።

፱፤ ስለእኛ፡በታመመው፡ሕማም፡የእኛን፡ነፍስ፡ የምትመስል፡ነባቢት፡ነፍስን፡እርሱ፡እንደ፡ ተዋሐደ ፡ እናምናለን ፤ ዳግመኛም ፡ የነፍሳ

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ነፍሳቲነ ፡ እሙነ ፡ ዘውእቱ ፡ ሁከት ፡ ወትካዝ ፡ ወሐዘነ ፡ ልብ ፡ ወዮሐንስኒ ፡ ወንጌላዊ ፡ ነገረነ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወዘከረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ተከዘት ፡ ነፍስየ ፡ እስከ ፡ ለሞት ፤ ወዓዲ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ወንጌለ ፡ ማርቆስ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አኀዘ ፡ ይኅዝን ፡ ወይተክዝ።

፲፤ ወበዝ ፡ ንትአመን ፡ እስመ ፡ በሕማመ ፡ ሥጋ ፡ ሐመ ፡ እሙነ ፡ ወአኮ ፡ በምትሐት።

፲፩፤ ወእለሰ ፡ ይብሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኢሐመ ፡ ሶበ ፡ ቀሠፍዎ ፡ ወኢደክመ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ሰቀልዎ ፡ ወኢረከበ ፡ ሕማም ፡ በጊዜ ፡ ቀነውዎ ፡ በቅንዋት ፡ ንህነ ፡ ናወግዞሙ ፡ ከመ ፡ ዐላውያን።

በረከቶሙ ፡ ለእሉ ፡ መምህራን ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ወኵሎ፡ሥርዐተ፡ከመ፡ቀዳሚ፡አብጽሕ።

ተአምሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ። ጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

፩፤ ቅዱስ ፡ ደቅስዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘጥልጥልያ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ቀዊሞ ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ርእየ ፡ ሥዕለ ፡ ዘእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ እንዘ ፡ ይውኅዝ ፡ ሐፍ ፡ እምገጸ።

፪፤ ወአንከሩ ፡ ሰብአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወትቤሎ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ለደቅስዮስ ፡ አንሥእ ፡ ለዛቲ ፡ ወለተ ፡ ዘሀለወት ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ወንሣእ ፡ ግልባቤ ፡ ርእሳ ፡ ይኩን ፡ መድኃኒተ ፡ ለዘሐመ።

፫፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘንተ ፡ ተአምረ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ደቅስዮስ ፡ ወይቤሎ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ናሁ ፡ ሀሎ ፡ ወልድየ ፡ ዘአኀዞ ፡ ጋኔን ፡ ወአምጽእዎ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአኀዝዎ ፡ ዐሠርቱ ፡ ዕደው ፡ ወስሐንዎ ፡ አማሕፀንኩከ ፡ ኪያሁ ፡ አ ፡ እግዚእየ።

፬፤ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ደቅስዮስ ፡ ሰገደ ፡ ኀበ ፡ ሥዕላ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ችንን ፡ ሕማም ፡ በእውነት ፡ ወዶ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ እናምናለን ፤ ይኸውም ፡ ሁከት ፡ ትካዝ ፡ የልብ ፡ ሐዘን ፡ ነው ፡ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስም ፡ የእርሱን ፡ ነገር ፡ ነገረን ፡ እርሱ ፡ ነፍሴ ፡ ከሥጋዬ ፡ እስከ ፡ መለየት ፡ ደርሳ ፡ አዘነች ፤ እንዳለም ፡ አስረዳ ፤ ዳግመኛም ፡ እንዳዘነ ፡ እንደተከዘ ፡ በማርቆስ ፡ ወንጌል ፡ ተጽፎአል።

፲፤ በምትሐት ፡ ያይደለ ፡ በእውነት ፡ የሥጋ ፡ ሕማምን ፡ እንደታመመ ፡ በዚህ ፡ እናምናለን።

፲፩፤ በገረፉት ፡ ጊዜ ፡ አልተሰማውም ፤ በሰቀሉትም ፡ ጊዜ ፡ አልደከመም ፤ በችንካርም ፡ በቸነከሩት ፡ ጊዜ ፡ ሕማም ፡ አላገኘውም ፡ ብለው ፡ ስለእርሱ ፡ የሚናገሩትን ፡ ግን ፡ መናፍቃን ፡ እንደመሆናቸው ፡ እኛ ፡ እናወግዛቸዋለን።

የእኒህ ፡ መምህራን ፡ በረከታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር ፡ አሜን።

### ምንተኑ፡በል።

ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ እንደፊተኛው ፡ አድርስ።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ በእኛ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይደርብንና ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ የምትሆን ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ያደረገችው ፡ ተአምር ፡ ይህ ፡ ነው።

፩፤ የጥልጥልያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ደቅስዮስ ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ቁሞ ፡ ሳለ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ የሆነች ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ የክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ሥዕልን ፡ ወዝ ፡ ከፊቷ ፡ሲፈስ ፡ (ሲንጸፈጸፍ) ፡ አየ።

፪፤ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ አደነቁ ፤ እመቤታችንም ፡ ደቅስዮስን ፡ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ያለችውን ፡ ይቺን ፡ ብላቴና ፡ አንሣት ፤ በራስዋም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መሸፈኛዋን ፡ ለታመመ ፡ መድኃኒት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ውሰድ ፡ አለችው።

፫፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ይህን ፡ ተአምር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ደቅስዮስ ፡ ቀርቦ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ጋኔን ፡ ያደረበት ፡ ልጅ ፡ እነሆ ፡ አለኝ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አምጥተውታል ፤ ዐሥር ፡ ሰዎችም ፡ ይዘውታል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ተስኗቸዋል ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እርሱን ፡ ታድነው ፡ ዘንድ ፡ ተማጽኜ ፡ በሃለሁ ፡ አለው።

፬፤ ደቅስዮስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ ድንግል ፡ ከሆነች ፡ የአምላክ ፡ እናት ፡ ከእመቤ

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ወአኀዘ፡ይእተ፡
ግልባቤ ፡ በእዴሁ ፡ ወአልበሶ ፡ ለውእቱ ፡
ዘጋኔን፡ወሐይወ፡ወበርሀ፡ገጹ፡ወአንከሩ፡
ሰብአ፡ሀገር፡ዘንተ፡ተአምረ።
፳፫፡ ወሐይዉ ፡ በውእቱ ፡ ግልባቤ ፡ ምውታን ፡
ወድውያን፡መጠነ፡ሰብዓ፡ወተሰዓቱ፡ምእት።
፳፬፡ ወይቤሉ ፡ ሰብእ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ በሰማያት ፡ ወለወላዲቱ ፡ ድንግል ፡
ማርያም።
ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
ለተአምርኪ፡ማርያም፡ክብር፡ይደሉ፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

፳፭፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተጋብኡ ፡ ሊቃነ ፡
ካህናቲሆሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ወይቤልዎ ፡ አ ፡
ሊቅነ፡ኄር፡ነአምር፡ከመ፡እምኀበ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ተፈኖከ፡ወአንተ፡ትሬሲ፡ዘበሕግ፡
ጥበበ ፡ ንግረነ ፡ በአይ ፡ ሥልጣን ፡ ትገብር ፡
ዘንተ።
፳፮፡ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አነሂ፡ካዕበ፡
እሴአለክሙ ፡ ጥምቀቱ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወልደ ፡
ዘካርያስ፡ሰባኪ፡እምአይቴ፡ውእቱ፡እምኀበ፡
እግዚአብሔርኑ፡ወሚመ፡እምኀበ፡ሰብእ፡
ወተደሙ፡አውሥእቶ።
፳፯፡ ወይቤሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ለእመ ፡ ንብሎ ፡
እምሰብእ ፡ ንፈርሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እስመ ፡
ይሬስይዎ፡ለዮሐንስ፡ከመ፡ነቢይ። ወለእመ፡
ንብሎ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡ይብሉነ፡እሉ፡
ሕዝብ፡ለምንት፡ኢተለውክምዎ።
፳፰፡ ወይቤልዎ፡ኢነአምር፡ጥምቀቶ፡እምአይቴ፡
ውእቱ።
ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አነሂ ፡
ኢይነግረክሙ ፡ በአይ ፡ ሥልጣን ፡ እገብር ፡
ዘንተ።
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
እመ፡ትመጽእ፡ለኰንኖ፡በል።
ወዘሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ታችን፡ክብርት፡ማርያም፡ሥዕል፡ፊት፡ሰገደ፤
ያንንም ፡ መሸፈኛ ፡ ወስዶ ፤ ጋኔን ፡ የያዘውን፡
ሰው፡አለበሰው፤ድኖ፡ፊቱም፡በራ፤የሀገሩም፡
ሰዎች፡ይህን፡ተአምር፡አደነቁ።
፳፫፡ በዚያም፡መሸፈኛ፡ሰባት፡ሺህ፡ዘጠኝ፡መቶ፡
ያህል፡ሙታኖችና፡በሽተኞች፡ዳኑ።
፳፬፡ ሰዎችም፡በሰማይ፡ለእግዚአብሔር፡ምስጋና፡
ይሁን ፤ ለወለደችው ፡ ለማርያምም ፡ ክብር፡
ይሁን፡አሉ።
ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ
ይኑር፡አሜን።
ለተአምርኪ፡ማርያም፡ክብር፡ይደሉ፡በል።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ለዘላለሙ፡ ይኑርና ፡ ጌታችን ፡ አምላካችን ፡
መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፳፭፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአይሁድ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናቶ
ቻቸው ፡ ተሰብስበው ፡ ቸር ፡ መምህር ፡ ሆይ፤
አንተ፡ከእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ተልከህ፡እን
ደመጣህ ፡ እናውቃለን ፤ ትምህርትንም ፡
በሕግ፡ ታስተምራለህ ፤ ይኸን ፡ በማን ፡
ሥልጣን፡እንደምትሠራ፡ንገረን፡አሉት።
፳፮፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡እኔም፡ደግሞ፡አንዲት፡ቃልን፡
እጠይቃችኋለሁ፤ ሰባኪው ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ፡
የዮሐንስ ፡ ጥምቀቱ ፡ ከወዴት ፡ ነው ? ከእግዚአ
ብሔር፡ ነውን?ወይስ፡ከሰው፡አላቸው።
በመልስ፡ጥያቄው፡ተደነቁ።
፳፯፡ እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ከሰው ፡ ነው ፡ ብንለው፡
ሕዝቡን ፡ እንፈራቸዋለን ፤ ዮሐንስን ፡ እንደ፡
ነቢይ ፡ ያደርጉታልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ዘንድ፡ነው፡ብንለው፡ሕዝቡ፡ለምን፡አልተከ
ተላችሁትም፡ይሉናል፡አሉ።
፳፰፡ ጥምቀቱ ፡ ከወዴት ፡ እንደሆነ ፡ አናውቅም፡
አሉት።
ጌታ፡ኢየሱስም፡ በምን፡ሥልጣን፡ይኸንን፡
እንደምሠራ ፡ እኔም ፡ አልነግራችሁም ፡
አላቸው።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።
እመ፡ትመጽእ፡በል።
ወዘሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|

ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፳፬፡፭፡፬።

ስምዐነ ፡ አምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ተስፋሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ። ብፁዕ ፡ ዘኀረይኮ፡ ወዘተወ ከፍኮ።

(ይ፡ዲ)፡ቊሙ፡ወአጽምዑ፡ይበል።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፩፡፳፫—፳፯።

፳፫፤ ወበዊአ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዘ ፡ ይሜህር ፡ መጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወመላ ህቅተ፡ሕዝብ፡ወይቤልዎ፡በመባሕተ፡መኑ፡ ትገብር ፡ ዘንተ ፡ ወመኑ ፡ ወሀበከ ፡ ዘንተ ፡ ሥልጣነ።

፳፬፤ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡ እሴአለክሙ፡አነሂ፡አሐተ፡ቃለ፡ወእምከመ፡ ነገርክሙኒ ፡ አነሂ ፡ አየድዓክሙ ፡ በአይ ፡ ሥልጣን፡እገብር፡ዘንተ።

፳፭፤ ጥምቀቱ፡ለዮሐንስ፡እምአይቴ፡ውእቱ፡እም ሰማይኑ፡ወሚመ፡እምሰብእ፡ወኀለዩ፡በበይ ናቲሆሙ ፡ ወይቤሉ ፡ እመ ፡ ንብሎ ፡ እምሰማይ፡ ይብለነ ፡ በእፎኬ ፡ ዘኢአመንክምዎ።

፳፮፤ ወእመሂ ፡ ንብሎ ፡ እምሰብእ ፡ ንፈርሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እስመ ፡ ከመ ፡ ነቢይ ፡ ይሬእይዎ ፡ ለዮሐንስ።

፳፯፤ ወአውሥእዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወይቤልዎ ፡ ኢነአምር ፡ ወይቤሎሙ ፡ ውእቱኒ፡ አነሂ ፡ ኢያየድዐክሙ ፡ በአይ ፡ ሥልጣን፡እገብር፡ዘንተ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በተሰዓቱ፡ሰዓት፡እምዕለተ፡ ሰኑይ።

ዘዮሐንስ፡ምስለ፡ትንቢት

፩፤ በእዴከ ፡ ንጽሕት ፡ እግዚእ ፡ ፈጠርከኒ ፡ ወለሐኰኒ፡እስመ፡ለብሐዊ።

፪፤ ወወሀብከኒ ፡ ገነተ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወሀብከኒዮሙ ፡ ሊተ ፡ ጸግዎ።

፫፤ ወሀብከኒ፡ኃይለ፡ሥልጣንከ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ ፍጥረትከ፡እንተ፡ታሕተ፡ሰማይ።

ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፡፳፬፡፭፡፬።

ድኅነት ፤ የምታደርግልን ፡ ፈጣሪያችን ፡ ልመና ችንን፡ስማን፤በምድር፡ዳርቻ፡ላሉት፡ሁሉ፡አለኝ ታቸው፡የምትሆን፡አንተ፡ነህ፤የመረጥከውና፡የተ ቀበልከው፡የተመሰገነ፡ነው፡ይበል።

ዲያቆኑ፡ቊሙ፡ወአጽምዑ፡ይበል።

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፩፡፳፫—፳፯።

፳፫፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ ገብቶ ፡ ሲያስተምር የካህናት ፡ አለቆችና ፡ የሕዝቡ ፡ አለቆች ፡ ወደርሱ፡መጥተው፡በማን፡ሥልጣን፡ነው፡ ይህን ፡ የምታደርገው ? ይህንንስ ፡ ሥልጣን ፡ ማን፡ሰጠህ?አሉት።

፳፬፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እኔም ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ እጠይቃችኋለሁ ፡ የነገራችሁኝም ፡ እንደሆነ፡እኔም፡በምን፡ሥልጣን፡ይህን፡እን ደማደርግ፡እነግራችኋለሁ፡አላቸው።

፳፭፤ የዮሐንስ ፡ ጥምቀቱ ፡ ከየት ፡ ነው ? ከሰማይ ፡ ነውን?ወይስ፡ከሰው?እርስ፡በርሳቸው፡ተነ ጋግረው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፤ ከሰማይ ፡ ነው ፡ ብንለው ፡ ያላመናችሁት ፡ ለምን ፡ ነው ? ይለናል።

፳፮፤ ከሰው ፡ ነው ፡ ብንለውም ፡ ሕዝቡን ፡ እን ፈራቸዋለን፤ዮሐንስን፡እንደ፡ነቢይ፡ያዩት፡ ነበርና።

፳፯፤ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አናውቅም ፡ ብለው ፡ መለሱለት ፤ እርሱም ፡ እንኪያስ፡እኔም፡በምን፡ሥልጣን፡ይህን፡እን ደማደርግ፡አልነግራችሁም፡አላቸው።

ሰኞ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ከወንጌል ፡ በኋላ ፡ የሚነበብ።

ከትንቢት፡ቃል፡ጋር፡አንድ፡የሚሆን፤

፩፤ አቤቱ ፡ በንጽሕት ፡ እጅህ ፡ ሠራኸኝ ፡ ፈጠር ከኸኝም፡ፈጣሪ፡ነህና።

፪፤ ተድላ፡ደስታ፡የሚገኝበት፡ገነትን፡ሰጠኸኝ፤ የአትክልቱን ፡ ሁሉ ፡ ፍሬ ፡ ለእኔ ፡ ስጦታ ፡ አድርገህ፡ሰጠኸኝ።

፫፤ ከሰማይ፡በታች፡ባለ፡ፍጥረትህ፡ሁሉ፡ላይ፡ የሥልጣንህን፡ኃይል፡ሰጠኸኝ።

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፬፡ ወረሰይከ ፡ ኵሎ ፡ ዘመደ ፡ ተሐዋስያን ፡ ታሕቴየ፡ ወኢኀደገኒ ፡ እኅጣእ ፡ ምንተኒ ፡ እምክብር። | ፬፡ የተንቀሳቃሽን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ በበታቼ፡ አደርግህ፤ከክብር፡ምንም፡ምን፡አጣ፡ዘንድ፡ አላደረግኸኝም። |
| ፭፡ ወረሰይከ፡ኵሎ፡ይግርር፡ሊተ።ወአዘዝከኒ፡ ትዕዛዘ ፡ ወወፃእኩ ፡ እምኔሃ ፡ (ስእለተ ፡ አዳም)። | ፭፡ ሁሉም፡እንዲገዛልኝ፡አደረግህ።ትእዛዝን፡ አዘዝከኝ፤ከትእዛዝህም፡ወጣሁ፤(የአዳም፡ ልመና)። |
| ፮፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ እስእለከ ፡ አ ፡ ኄር ፡ ግበር ፡ ምስሌየ ፡ በከመ ፡ ዕበየ ፡ ምሕረትከ። | ፮፡ ጌታዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ሆይ ፡ እለምንሃለሁ፤ቸር፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ፡ ቸርነትን፡አድርግ። |
| ፯፡ ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡ከመ፡አነ፡መሬት፡ወከመ፡ ሣዕር፡ዘሀሎ፡ውስተ፡ሐቅል። | ፯፡ አቤቱ ፡ እኔ ፡ ዐፈር ፡ እንደሆንኩ ፡ በዱር፡ እንዳለም፡ሣር፡እንደሆንኩ፡አስበኝ። |
| ፰፡ ወወሀብከኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጽንዐ ፡ ኃይልከ ፡ ለአሕጽጾ፡ንዴትየ።ለእሐቲ፡ዕፅ፡አዘዝከ፡ በእንቲአሃ። | ፰፡ ለደካማው፡ተፈጥሮዬ፡አቤቱ፡የኀይልህን፡ ጽናት ፡ ሰጠኸኝ ፤ ችግሬንም ፡ ለማቃለል፡ ለአንዲት፡ፍሬ፡ዕጽ፡ስለእርሷ፡አዘዝከ። |
| ፱፡ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ። | ፱፡ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ይቅርታህ፡ብዛት፡ከእኔ፡ ጋራ፡ቸርነትን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ። |
| ፲፡ እፎ ፡ ኮንከ ፡ ዘኢሰማዒ ፡ ለትእዛዝየ ፡ አውፃእከ፡ዐመፃ፡ላዕለ፡ብእሲት። | ፲፡ እንዴት፡ትእዛዜን፡የማትሰማ፡ሆንክ?ስህተ ትህን፡በሔዋን፡አመካኘህ? |
| ፲፩፡ ወለይእቲሰ፡ኢአዘዝክዋ፡ዘከማከ፡ወሰማዕከ፡ እምኔሃ ፡ ወገደፍከ ፡ ቃላትየ ፡ ወተኀባእከ ፡ ውስተ፡ዕፅ፡ከመ፡ኢይርአይከ፡አነ። | ፲፩፡ እርሷን፡እንዳንተ፡አላዘዝኳትም፤የእርሷን፡ ቃል፡ሰምተህ፡በደልከ፤ቃሌንም፡ጣልከው፤ እኔ፡እንዳላይህም፡በዛፍ፡ውስጥ፡ተሸሸግህ። |
| ፲፪፡ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ። | ፲፪፡ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብየ፡እለምንሃለሁ። |
| ፲፫፡ ተሐዘብከ፡ከመ፡ትዕርግ፡ኀበ፡እምላካዊት፡ ግብር፡ከመ፡እግዚእከ፡በፍሬ፡ዕፅ። | ፲፫፡ በዕፅ፡ፍሬ፡እንደ፡ፈጣሪህ፡ወደ፡አምላካዊ፡ ሥራ፡የምትደርስ፡መስሎህ፡ተጠራጠርህ፤ |
| ፲፬፡ አእመርከ ፡ ሠናየ ፡ ወእኩየ ፡ ወኮንከ ፡ አምላከ። | ፲፬፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ለይተህ ፡ የምታውቅ ፡ አምላክ፡ ሆንክ። |
| ፲፭፡ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ። | ፲፭፡ ቸር ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ምሕረትህ ፡ ብዛት ፡ ከእኔ፡ ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ። |
| ፲፮፡ አ ፡ አዳም ፡ አይቴኑ ፡ ስብሐት ፡ ዘኮነ ፡ ለከ ፡ ዐረቀ፡ እምልብስከ ፡ እንተ ፡ አልበስኩከ ፡ ኪያከ። | ፲፮፡ አዳም ፡ ሆይ ፡ ተደርጎልህ ፡ የነበረ ፡ ክብር፡ ወዴት ፡ ነው ? አንተን ፡ አልብሼህ ፡ ከነበ ረውም፡ልብስ፡ተራቆትህ። |
| ፲፯፡ ነሣእከ ፡ ቈጽለ ፡ እምዕፅ ፡ ወተከደንከ ፡ ኀፍረተከ፡እምገጽየ። | ፲፯፡ ከዛፍ፡ቅጠልን፡ወስደህ፡ከፊቴ፡ለመሠወር፡ ኀፍረትህን፡ሸፈንክ። |
| ፲፰፡ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ። | ፲፰፡ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ይቅርታህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ። |
| ፲፱፡ አንሰ ፡ አእምር ፡ ኪያከ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ፈጠርኩከ፡ ወአእመርኩከ ፡ እምቅድመ ፡ ከዊኖትከ፡ወእምቅድመ፡እመ፡ገቢሮትከ። | ፲፱፡ እኔ ፡ አንተን ፡ አውቅሃለሁ ፤ ፈጥ ሬሃለሁና ፡ ከመሆንህም ፡ በፊት ፡ አው ቅሃለሁ። |

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፳፤ ወሀብኩከ ፡ ቃለ ፡ ትእዛዝየ ፡ ከመዝ ፡ ነገርኩከ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ዕፅ ፡ ዘእንበለ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀው ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ እስመ ፡ ለዛቲ ፡ ፍሬሃ ፡ ምረረ ፡ ሞት ፡ ይእቲ። | ፳፤ በገነት ፡ ካሉት ፡ ዛፎች ፡ ሁሉ ፡ በቀር ፡ ዕፀ ፡ በለስን፡አትንካ፡ብዬ፡እንደዚህ፡ስነግርህና፡ የትእዛዝ ፡ ቃል ፡ ስሰጥህ ፡ የበለስ ፡ ፍሬዋ ፡ መራራ ፡ ሞት ፡ ናትና ፡ ከማድረግህ ፡ በፊት ፡ እንደምትሳሳት፡አውቅ፡ነበር። |
| ፳፩፤ ወሶበ ፡ በላዕከ ፡ እምኔሃ ፡ ሞተ ፡ ትመውት ፡ አንተ ። አንሰ ፡ ኢየኀድገከ ፡ ትኩን፡አብደ። | ፳፩፤ ከእርሷ ፡ በበላህ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ሞትን ፡ እንድ ትሞት፡አውቃለሁና፡ሰነፍ፡አላዋቂ፡ትሆን፡ ዘንድ፡እኔ፡አልተውኩህም፡ነበር። |
| ፳፪፤ ወባሕቱ ፡ አነ ፡ አእመርኩከ ፡ በዝንቱ ፡ እምቅድመ፡ይኩን፡አጽመምከ፡እዝነከ፡ወተ አዘዝካሃ፡አነ፡አመጽእ፡ላዕሌከ፡ኵነኔ። | ፳፪፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዚህም ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ አወቅሁህ ፤ ጆሮህን ፡ አደንቁረህ ፡ ሔዋንን ፡ ታዘዝካት፤እኔ፡ፍርድን፡እፈርድብሃለሁ። |
| ፳፫፤ እስእለከ ፡ አ ፡ ኄር ፡ ግበር ፡ ምስሌየ ፡ በከመ ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ። | ፳፫፤ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብየ፡እለምንሃለሁ። |
| ፳፬፤ አ፡አዳም፡መሬት፡አንተ፡ወአነ፡አገብአከ፡ ውስተ፡መሬት፡ህየንተ፡ምግባራት፡እንተ፡ ደፈርከ፡ላዕሌሆን። | ፳፬፤ አዳም፡ሆይ፤አንተ፡ዐፈር፡ነህ፤ደፍረህ፡ስለ ሠራሃቸው፡ሥራዎች፡እኔ፡ወደ፡ዐፈርነት፡ እመልስሃለሁ። |
| ፳፭፤ እስእለከ ፡ አ ፡ ኄር ፡ ግበር ፡ ምስሌየ ፡ በከመ ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ። | ፳፭፤ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ። |
| ፳፮፤ ለምንት ፡ ሔዋን ፡ ኮንኪ ፡ ከመዝ ፡ ወወፃእኪ ፡ እምትእዛዝየ ፡ አኮ ፡ መልአክ ፡ ዘተናገረኪ ፡ ወኢ ፡ ያፍ ፡ እምአየር ፡ ወአርዌ ፡ ዘከይሲ ፡ ፍጥረታ፡ሰማዕኪ፡እምኔሃ። | ፳፮፤ ሔዋን፡ሆይ፡ለምን፡እንደዚህ፡ሆንሽ?ከትእ ዛዜስ፡ለምን፡ወጣሽ?የተናገረሽ፡መልአክ፡ አይደለም፤ወይም፡ወፍ፡ከአየር፡አልተናገ ረሽም ፡ ፍጥረቷ ፡ እባብ ፡ ከሆነች ፡ አውሬ ፡ ከእርሷ፡ሰማሽ፡እንጂ። |
| ፳፯፤ ሚ፡መጠን፡እምሕማማት፡እንተ፡ትከውን፡ ለኪ፡ሐዘናት፡ወገዐር፡ዐቢይ። | ፳፯፤ ከመከራዎች ፡ ወገን ፡ ለአንቺ ፡ የሚሆንብሽ ፡ መከራ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይበዛ ፡ ይሆን ? ፃር ፡ ጋርሽ፡ታላቅ፡ሐዘን፡ነውና። |
| ፳፰፤ ወአነ ፡ አነሥእ ፡ ተፃርሮተ ፡ ማእከሌኪ ፡ ወማእከለ፡ከይሲ፡ደቂቃ፡ምስለ፡ደቂቅኪ፡ ወውእቶሙ ፡ የኀሥሡ ፡ ርእሶሙ ፡ ወእሙንቱ፡ይእኀዙ፡እገሪሆሙ። | ፳፰፤ እኔም ፡ በአንቺና ፡ በከይሲ ፡ መካከል ፡ በልጆቿና፡በልጆችሽ፡መካከል፡ፀብን፡አስነ ሣለሁ፤ልጆችሽ፡ራሳቸውን፡ይቀጠቅጣሉ፡ እነዚያም፡እግራቸውን፡ይነድፋሉ። |
| ፳፱፤ ወጸውዓ ፡ እግዚእ ፡ ለከይሲ ፡ ወረገማ ፡ ወይቤላ፡ ርግምት ፡ አንቲ ፡ እማእከለ ፡ ኵሉ ፡ አራዊት ፡ ወሑሪ ፡ በእንግድዓኪ ፡ ወሐመደ ፡ ብልዒ ፡ ህየንተ ፡ ዘኮንኪ ፡ ስሕተተ ፡ እስመ ፡ ጸላኢ ፡ ረከበ ፡ መካነ ፡ ውስቴትኪ ፡ ወኮንኪ ፡ ቤተ፡ለእኩይ። | ፳፱፤ ጌታም ፡ ከይሲን ፡ ጠርቶ ፡ ከአራዊት ፡ ሁሉ ፡ መካከል፡ተለይተሽ፡አንቺ፡የተረገምሽ፡ሁኚ፤ በደረትሽ፡እየተሳብሽ፡ሂጂ፤ትቢያንም፡ብዪ፤ ለስህተት ፡ ምክንያት ፡ ስለሆንሽ ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስ፡በአንቺ፡ውስጥ፡ቦታ፡አግኝቷልና፡ ለክፋም፡ማደሪያ፡ሁነሻልና። |
| ፴፤ ወአጽነነ ፡ ብእሲ ፡ እዝኖ ፡ ኀቤኪ ። ናሁ ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡ ትትረገም ፡ ምስ ሌሁ። | ፴፤ አዳምም ፡ አንቺን ፡ ለመስማት ፡ ጆሮውን ፡ ዘንበል፡አደረገ፤እነሆ፡ምድር፡ሁሉ፡ከርሱ፡ ጋራ፡እንደ፡እሱ፡ትረገማለች። |

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፴፩፤ እስእለከ ፡ አ ፡ ኄር ፡ ግበር ፡ ምስሌየ ፡ በከመ ፡ ዕበየ፡ምሕረትከ።

፴፪፤ ወካዕበ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘውእቱ ፡ አዳም ፡ ዘኮነ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ሰማዕከ ፡ እምብእሲትከ ፡ ርግምት ፡ ምድር ፡ በእንቲአከ ፡ ወተሐዩ ፡ በሐዘን ፡ አ ፡ አዳም ፡ ምድርኒ ፡ ታበቍል ፡ ለከ ፡ አሜከላ ፡ ወሦከ ። እስእለከ ፡ አ ፡ ኄር ፡ ግበር ፡ ምስሌየ ፡ በከመ ፡ ዕበየ ፡ ምሕረትከ።

፴፫፤ ወይቤላ፡ለሔዋን፡አንቲ፡ትወልዲ፡ወልደ፡በፃዕር፡ወበሕማም፡ወትገብኢ፡ኀበ፡ምትኪ፡ወውእቱ፡ይሜለጥ፡ላዕሌኪ፡ወኢይከውን፡ላዕሌኪ፡ዕረፍት፡በሕይወትኪ።

፴፬፤ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ዕበየ፡ምሕረትከ።

፴፭፤ ወይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ አዳም ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ እምኔነ ፡ ዘየአምር ፡ ሠናየ ፡ ወእኩየ ፡ ኢየኅድጎ ፡ ውስተ ፡ ገነት ፡ ከመ ፡ ኢያንሥእ ፡ እዴሁ ፡ ወኢይብላዕ ፡ እምዕፀ ፡ ሕይወት።

፴፮፤ ወእምዝ፡አውፅአሙ፡ለአዳም፡ወለብእሲቱ፡ምስሌሁ፡እምገነተ፡ትፍሥሕት።

፴፯፤ ወረሰየ፡ሱራፌሃ፡ምስለ፡ኵናቱ፡እሳታዊት፡ከመ፡ይዕቀብ፡አንቀጸ፡ገነት።

፴፰፤ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ዕበየ ፡ ምሕረትከ ። አይቴኑ ፡ አሐውር ፡ እምቅድመ፡ገጽከ፡ወአይቴ፡እጉይይ፡እመንፈስከ።

፴፱፤ እመኒ ፡ ዐረጉ ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ፡ አው ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ታሕቲት ፡ ህየኒ ፡ እረክበከ።

፵፤ እስእለከ፡አ፡ኄር፡ግበር፡ምስሌየ፡በከመ፡ዕበየ፡ምሕረትከ።

፵፩፤ ወሖረ ፡ አዳም ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ታሕታዊ ፡ ቅድመ፡ አንቀጸ ፡ ገነት ፡ ሐረሰ ፡ ምድረ ፡ ወበልዐ፡እምፍሬሃ።

፵፪፤ ወነበረ፡ውስተ፡ስሕተት፡ዘአውከከ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፴፩፤ ቸር፡ሆይ፡እንደቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ጋራ፡ቸርነትን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ።

፴፪፤ ዳግመኛም ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ እርሱም ፡ በገነት ፡ የነበረ ፡ አዳምን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለው፤የሚስትህን፡ቃል፡ሰምተሃልና፡ስለ፡አንተ፡ምድር፡የተረገመች፡ናት፤በሐዘንም፡ትኖራለህ፤አዳም፡ሆይ፡ምድርም፡አሜከላና፡እሾኽን፡ታበቅልብሃለች፡አለው።ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ጋራ፡ቸርነትን፡አድርግ፡ብየ፡እለምንሃለሁ።

፴፫፤ ሔዋንንም፡በፃር፡በጋር፡ልጅን፡ትወልጃለሽ፡ከወለድሽም፡በኋላ፡ወደ፡ባልሽ፡ትመለሻለሽ፡እርሱም፡በላይሽ፡ይሠለጥናል፤በዘመንሽም፡ሁሉ፡ዕረፍትን፡አታገኚም፡አላት።

፴፬፤ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ።

፴፭፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እነሆ፡አዳም፡ከእኛ፡እንዳንዱ፡ክፉና፡በጎ፡ለይቶ፡የሚአውቅ፡ሆነ፤እንግዲህ፡እጁን፡ዘርግቶ፡ከዕፀ፡ሕይወት፡እንዳይበላ፡በገነት፡ውስጥ፡አልተወውም።

፴፮፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አዳምንና ፡ ሚስቱን ፡ ከርሱ፡ጋራ፡ከተድላ፡ገነት፡አወጣቸው።

፴፯፤ የገነትንም፡በር፡ይጠብቅ፡ዘንድ፡ከእሳታዊት፡ሰይፉ፡ጋር፡ሱራፌን፡ከዚያ፡አደረገው።

፴፰፤ ቸር፡ሆይ፡እንደ፡ቸርነትህ፡ብዛት፡መጠን፡ከእኔ፡ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብየ፡እለምንሃለሁ። ከፊትህ፡ወዴት፡እሄዳለሁ? ከሥልጣንህስ፡ሸሽቼ፡ወዴት፡እደርሳለሁ?

፴፱፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ብወጣ ፡ አንተ ፡ ከዚያ ፡ አለህ፤ ወደ፡ምድር፡በታችም፡ብወርድ፡በዚያ፡አገኝሃለሁ።

፵፤ ቸር፡ሆይ፡እንደቸርነትህ፡ብዛት፡ከእኔ፡ጋራ፡ቸርነትህን፡አድርግ፡ብዬ፡እለምንሃለሁ።

፵፩፤ አዳምም ፡ በገነት ፡ መግቢያ ፡ ፊት ፡ ለፊት፡ወደ፡ዝቅተኛ፡ቦታ፡ወርዶ፡ምድርን፡እያረሰ፡ፍሬዋን፡የሚመገብ፡ሆነ።

፵፪፤ በአጠፋውም፡ገንዘብ፡በስሕተት፡ውስጥ፡ኖረ፡

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፵፫፤ ወተፈጸመ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወላዕለ ፡ ብእሲቱ ፡ ዘጽሑፍ ፡ ለግብርናት ፡ በእንተ ፡ ዘኢሰምዐ ፡ ትዕዛዝ ። ወኵሎሙ ፡ ደቂቁ ፡ እስከ ፡ ኅልቀተ፡ ዓለም።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ወኵሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

እንበለ፡ደዌ፡ወሕማም፡በል።

## ምዕራፍ፡፲፬።

ትእዛዝ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ በጊዜ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘሰኑይ ፡ ወይጸልዩ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ዘይብል ፡ ብፁዕ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈርሆ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡ እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ። ወውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ዘዐርብ ። ወይበል ፡ መራሒ ፡ (ም) ፡ በ፩ ፡

ስብሐት፡ለአብ፤

ወእምዝ፡ይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

### ክፍል፡፩።

ምንባብ፡ዘዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት፡ዘሠኑይ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ።

ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፶፡፩–፫።

፩፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይኑ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፈ፡ኅዳጋቲሃ፡ለእምክሙ፡ዘፈነውኩ፡ ላቲ ፡ ወለመኑ ፡ እፈዲ ፡ ዕዳ ፡ ዘሤጥኩክሙ ፡ አኮኑ፡በእንተ፡ኃጢአትክሙ፡ሤጥኩክሙ፡ ወበእንተ ፡ ጌጋይክሙ ፡ ፈነውክዋ ፡ ለእምክሙ።

፪፤ ናሁ ፡ መጻእኩ ፡ ወአልቦ ፡ ሰብእ ፡ ጸዋዕኩ ፡ ወአልቦ ፡ ዘተሠጥወኒ ፡ ኢትክልኑ ፡ አድኅኖ ፡ እዴየ ፡ ወኢይክልኑ ፡ ባልሐ፡ናሁ፡በተግሣጽየ፡አነጽፍ፡ለባሕር፡ ወአየብሶሙ ፡ ለአፍላግ ፡ ወይመውቱ ፡ ዓሣቲሆሙ ፡ በኀጢአ ፡ ማይ ፡ ወየኀልቁ ፡ በጽምእ።

፫፤ ወእገለብባ፡ለሰማይ፡በጽልመት፡ወአለብሳ፡ሠቀ።

ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፵፫፤ ትእዛዝን ፡ ስለአልሰማ ፡ ለተገገርነት ፡ የተጻፈባቸው ፡ በእርሱና ፡ በሚስቱ ፡ ላይ ፡ ተፈጸመ ፡ በልጆቹም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ።

መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ መጥቶ ፡ ሰው ፡ ሁኖ፡ መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።

ሥርዓቱ፡ሁሉ፡እንደፊተኛው፡ነው።

እንበለ፡ደዌ፡ወሕማም፡በል።

## ምዕራፍ፡፲፬።

ሰኞ ፡ ከቀኑ ፡ በአሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ በቅድስት፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ውስጥ፡ካህናት፡ ተሰብስበው፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘይፈርሆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከሚለው፡እምይእዜ፡ወእስከ፡ለዓለም፡እስከ ሚለው፡ድረስ፡የዐርብንም፡ውዳሴ፡ማርያም፡ ይድገሙ ፤ መሪውም ፡ በአንድ፡ ሃሌታ ፡ ስብሐት፡ ለአብ ፡ የሚለውን ፡ መዝሙር ፡ ይምራ።

ከዚህ፡በኋላ፡ለከ፡ኃይል፡ይበሉ።

### ክፍል፡፩።

ሰኞ፡በአሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡የሚነበብ።

የነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፶፡፩–፫።

፩፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ለእናታችሁ ፡ የላከሁላት ፡ የመፈቻዋ ፡ ደብዳቤ ፡ ወዴት ፡ ነው ? የሸያጫችሁንስ ፡ ዕዳ ፡ ለማን ፡ እከፍላለሁ ? በኃጢአታችሁ ፡ የሸጥኋችሁ ፡ አይደለምን ? እናታችሁንስ ፡ በበደላችሁ ፡ አሰማርኩ፡የሰደድኋት፡አይደለምን።

፪፤ እነሆ ፡ በረድኤት ፡ መጣሁ ፤ ዕውቀት ፡ ያለው፡ሰው፡የለም፤አስተምሩ፡ብዬ፡ተናገርሁ፡ የሰማኝ ፡ የለም፤ በውኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ ማዳን ፡ አትችልምን?እነሆ፡በተግሣጼ፡ባሕርን፡አደረቅኋት፤ፈሳሾችንም፡አደረቅኋቸው፤ዓሦቻቸውም፡ውኃ፡በማጣት፡ይሞታሉ፡በውኃ፡ጥምም፡ያልቃሉ።

፫፤ ሰማይን፡(ባቢሎንን)፡በጨለማ፡እሸፍናታለሁ፤ ማቅን፡አለብሳታለሁ፡(መከራ፡አመጣባታለሁ)።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፮፡፪–፳።

፪፡ ወአርኅዉ ፡ አናቅጸ ፡ ወይባእ ፡ ሕዝብ ፡ ዘየዓቅብ ፡ ጽድቀ ፡ ወይትዌ ከፍ ፡ ርትዐ፡ ወይትመኃፀን ፡ ሰላመ ፡ እስከ፡ለዓለም።

፫፡ ኪያከ፡ተወከልኩ፡እግዚኦ፡አምላክ፡ዐቢይ፡ ዘለዓለም።

፬፡ ዘአትሐትኮሙ ፡ ወአውረድኮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ አርያም ፡ ወትነጽሖን ፡ ለአህጉር ፡ ጽኑዓት ፡ ወታወርዶን ፡ እስከ ፡ ምድር።

፭፡ ወይከይዶን፡እግረ፡የዋሃን፡ወትሑታን፤

፮፡ ወይከውን ፡ ፍኖተ ፡ ርቱዐ ፡ ለጻድቃን ፡ ወትጸያሕ፡ፍኖተ፡ራትዓን።

፯፡ እስመ ፡ ርቱዕ ፡ ውእቱ ፡ ፍኖቱ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ወተወከልነ ፡ በስሙ ፡ ቅዱስ ፡ ወረከብነ፡ዘፈተወት፡ነፍስነ።

፰፡ በሌሊት ፡ ትገይሥ ፡ መንፈስየ ፡ ኀቤከ ፡ እግዚኦ፡ አምላኪየ ። እስመ ፡ ብርሃን ፡ ትእዛዝከ፡በዲበ፡ምድር ። ተመሀሩ፡ገቢረ፡ ጽድቅ፡እለ፡ትነብሩ፡ውስተ፡ዓለም።

፱፡ እስመ፡ኀልቀ፡ኃጥእ፡ዘኢይትሜሀር፡ገቢረ፡ ጽድቅ፡በዲበ፡ምድር፡ወኢይገብር፡ሠናየ፡ ያእትትዎ ፡ ለኃጥእ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ስብሐተ፡እግዚአብሔር።

፲፡ እግዚኦ፡ልዑለ፡መዝራዕተከ፡ኢያእመሩ ። እምከመሰ፡አእመሩ፡ይትኃፈሩ፡ቅንአት፡ አኀዞሙ ፡ ለሕዝብ ፡ አብዳን ፡ ወይእዜኒ ፡ እሳት፡ትበልዖሙ፡ለፀር።

፲፩፡ እግዚኦ፡አምላክነ፡ሰላመ፡ሀበነ ፡ እስመ ፡ ኵሎ፡ወሀብከነ።

፲፪፡ እግዚኦ፡አምላክነ፡አጥርየነ ፡ እግዚኦ፡ዘእን በሌከ፡ባዕደ፡ኢነአምር፡ወስመ፡ዚአከ፡ ንጼውዕ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

የነቢዩ፡የኢሳይያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከኛ፡ ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፳፮፡፪–፳።

፪፡ በሮችን፡ክፈቱ፡ሕግን፡የሚጠብቅ፡የቀና፡ ሥራንም፡የሚቀበል፡እስከ፡ዘላለሙ፡ድረስ፡ ፍቅር ፡ አንድነትን፡ ገንዘብ ፡ የሚአደርግ፡ ወደ፡ትምህርት፡ይግባ።

፫፡ ለዘላለሙ፡ገናና፡ፈጣሪ፡የምትሆን፡አቤቱ፡ አንተን፡አመንኩ፤

፬፡ በልዕልና፡የሚኖሩትን፡ፈጽመህ፡ያዋረድ ኻቸው፡ጽኑ፡ጽኑ፡የሆኑ፡አምባዎችንም፡ያፈ ረስኻቸው፡ምድር፡እስከ፡መሆን፡ድረስም፡ ያጠፋኻቸው፡አንተ፡ነህ።

፭፡ የተዋረዱ፡ሰዎችና፡የየዋሃን፡እግር፡ይረግጣቸዋል።

፮፡ ለደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ የቀና ፡ ጐዳና ፡ ይሆናል፤ ለቅኖችም፡ጐዳና፡ትጠረጋለች።

፯፡ የእግዚአብሔር ፡ ጐዳና ፡ የቀና ፡ ነውና፡ በከበረ፡ስሙ፡አምነን፡የልቡናችንን፡ፈቃድ፡ አገኘን።

፰፡ ሕግህ፡በዚህ፡ዓለም፡ብርሃን፡ነውና፡አቤቱ፡ ፈጣሪዬ፡ሰውነቴ፡በሌሊት፡ወዳንተ፡ትገሠ ግሣለች ። በዚህ፡ዓለም፡የምትኖሩ፡ሰዎች፡ የጽድቅን፡ሥራ፡ተማሩ።

፱፡ በዚህ፡ዓለም፡ደግ፡መሥራትን፡የማይማር፡በጎ፡ ሥራንም ፡ የማይሠራ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሰው፡ ጠፍቷልና። የእግዚአብሔርን፡ክብር፡እንዳያይ፡ ኃጥኡን፡ሰው፡በሞት፡ያስወግዱታል።

፲፡ አቤቱ ፡ ገናና ፡ ሥልጣንህን ፡ አላወቁም፡ ካወቁስ፡ይፈሩ፤ሰነፎች፡ወገኖችን፡ቅንአት፡ ያዛቸው፤አሁንም፡ጠላቶችን፡እሳት፡ትበላቸ ዋለች።

፲፩፡ አቤቱ፡ፈጣሪያችን፡ሰላምን፡ስጠን፤ተድላ፡ ደስታውን፡ሰጥተኸናልና።

፲፪፡ አቤቱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ገንዘብ ፡ አድርገን፤ አቤቱ፤ ካንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ፡ አናውቅም፤ስምህንም፡እንጠራለን።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፫፤ ሙታንሰ ፡ ኢይሬእይዋ ፡ ለሕይወት ። ወዓቀብተ፡ሥራይኒ፡ኢያነሥኡ።በእንተዝ፡ አምጸእኮሙ ፡ ወአጥፋእኮሙ ፡ ወአእተትከ ፡ ዙሎ፡ትዕቢቶሙ።

፲፬፤ ወስኮሙ፡እግዚእ፡እኪተ።ወስኮሙ፡እኪተ፡ ለክቡራነ፡ምድር።

፲፭፤ እግዚእ፡በምንዳቤየ፡ተዘከርኩከ።ወበኅዳጥ፡ ሕማም፡ገሠፅከኒ።

፲፮፤ ከመ ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ ማሕምም ፡ እንተ ፡ አልጸቀት፡ለወሊድ፡ወአውየወት፡በሕማማ፡ ከማሁ፡ኮነ፡ለፍቁርከ።

፲፯፤ በእንተ ፡ ፈሪሆትከ ፡ እግዚእ ፡ ጸነስነ ፡ ሐመምነሂ፡ወወለድነ፡መንፈሰ፡አድኅኖትከ፡ በዲበ፡ምድር፡ወይወድቁ፡እለ፡ይነብሩ፡ዲበ፡ ምድር።

፲፰፤ ሙታንሰ ፡ ይትነሥኡ ፡ ወየሐይዉ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ። ወይትፌሥሑ ፡ እለ ፡ ውስተ፡ምድር።እስመ፡ጠል፡ዘእምኀቤከ፡ ሕይወቶሙ፡ውእቱ።ወታጠፍእ፡ምድሮሙ፡ ለኃጥአን።

፲፱፤ ሑር ፡ ሕዝብየ ፡ ወባእ ፡ ቤተከ ። ወዕፁ ፡ ኆኅተከ። ወተኀባእ፡ኅዳጠ፡ምዕረ።እስከ፡ የኀልፍ፡መዓቱ፡ለእግዚአብሔር።

፳፤ ናሁ፡እግዚአብሔር፡ያመጽእ፡መቅሠፍተ፡ እምነ፡መቅደሱ፡ዲበ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ ምድር፡ወትከሥት፡ምድር፡ደማ፡ወኢትከ ድኖሙ፡ለቅቱላን።

ምዕ፤፳፯፡፩።

፩፤ ውእተ፡ አሚረ፡ ያመጽእ፡ እግዚአብሔር፡ መጥባሕተ፡ ቅዱሰ፡ ዐቢየ፡ ወጽኑዐ፡ ላዕለ፡ ከይሲ ፡ ወአርዌ ፡ ዘየአኪ ፡ እምከይሲ ፡ ወይቀትሎ ፡ ለከይሲ ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ። ውእተ፡ጊዜ።

ዘሆሴዕ፡ ነቢይ፡ በረከቱ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፲፬፡፩-፱።

፩፤ ተመየጥ፡ እስራኤል፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክከ ፡ እስመ ፡ ደከምከ ፡ በአመፃከ ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፫፤ ሙታን፡ግን፡ሕይወትን፡አያዩዋትም፤ባለመ ድኃኒቶችም ፡ አያስነሡዋቸውም ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አምጥተህ ፡ አጠፋኻቸው ፤ ትዕቢታቸ ውንም፡ሁሉ፡አራቅህ።

፲፬፤ አቤቱ ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራን ፡ ጨምር ባቸው።በዚህ፡ዓለም፡በከበሩ፡ሰዎች፡ላይም፡ መከራ፡አምጣባቸው።

፲፭፤ አቤቱ፡በመከራዬ፡ጊዜ፡አሰብኩህ።በጥቂት፡ መከራም፡ገሠፅከኝ።

፲፮፤ ምጥ፡የተያዘች፡ለመውለድ፡የደረሰች፡ሴት፡ በምጥዋ ፡ ጊዜ ፡ እንደምትጨነቅ ፡ አቤቱ ፡ በፊትህ፡ለወዳጅህ፡እንዲሁ፡ሆንን።

፲፯፤ አቤቱ፡አንተን፡ፀንሰናል፤መከራ፡ተቀብለን ወለድን።የድህነት፡መንፈስ፡በምድር፡ላይ፡ ነው ። በምድር ፡ ላይ ፡ (በሰማርያ) ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች፡ይጠፋሉ።

፲፰፤ ሙታን ፡ ይነሣሉ ፤ በመቃብር ፡ ያሉ ፡ ይድናሉ፤በምድር፡ያሉትም፡ደስ፡ይላቸዋል፤ ከአንተ ፡ የተገኘ ፡ ጠለ ፡ ረድኤት ፡ ሕይወ ታቸው፡ ነውና ። የኃጥአንን ፡ አገር ፡ ግን ፡ ታጠፋለህ።

፲፱፤ ሕዝቤ፡ሂድ፡ወደቤትህም፡ግባ፡ደጃፍህን፡ ዝጋ ፤ ጥቂት ፡ ጊዜም ፡ ተሸሸግ ፡ የእግዚአ ብሔር፡ቁጣው፡እስኪያልፍ፡ድረስ።

፳፤ እነሆ፡እግዚአብሔር፡በዚህ፡ዓለም፡በሚኖሩ፡ ሰዎች፡ከማደሪያው፡ከሰማይ፡መቅሠፍትን፡ ያመጣል፤(ለኪሶ)፡ምድርም፡ደሟን፡ትመል ሳለች፤የሞቱትንም፡አትሠውራቸውም።

ምዕ፤፳፯፡፩።

፩፤ ያን፡ጊዜ፡እግዚአብሔር፡ልዩ፡ገናና፡ጽኑ፡ የሆነ፡ሾተልን፡በእባብ፡ላይ፡ያመጣል፤(ናቡ ከደነፆር) ፡ ከእባብ ፡ የሚከፋ ፡ የምድር ፡ አውሬንም፡ያመጣል፤ያን፡ጊዜም፡በባሕር፡ ያለ፡አውሬን፡ይገድላል፤(ኪራም)።

የነቢዩ ፡ ሆሴዕ ፡ ትንቢት ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፲፬፡፩-፱።

፩፤ እስራኤል ፡ ወደ ፡ ፈጣሪህ ፡ ወደ ፡ እግዚአ ብሔር፡ተመለስ፤በበደልህ፡ወድቀሃልና።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ለምንት ፡ ትተክሉ ፡ ኃጢአተ ፡ ወትቀሥሙ ፡ ፍሬ፡ሞት።

፪፤ ወንሥኡ ፡ ሠናያተ ፡ ዘነዓሥዮ ፡ ለእግዚአብሔር፡ፍሬ፡ከናፍሪነ።

፫፤ ወበሉ ፡ አሦርሂ ፡ ኢያድኅነ ፡ ወአፍራሰኒ ፡ ኢንጼዓን ፡ ወኢንብሎሙ ፡ እንከ ፡ አማልክቲነ፡ለግብረ፡እደዊነ።

፬፤ ወበእንተዝ፡ይሣሃል፡ዕጓለ፡ማውታ፡ወይፌውሶሙ ፡ ለሕሙማኒሆሙ ፡ ወያፈቅሮሙ ፡ እሙነ ፡ ወናሁ ፡ እመይጥ ፡ መዐትየ ፡ እምኔሆሙ።

፭፤ ወእከውኖሙ፡ከመ፡ዝናም፡ለእሥራኤል፡ ወይሠርፅ፡ከመ፡ጽጌ፡ወይጸንዕ፡ሥረዊሁ፡ ከመ፡ሊባኖስ።

፮፤ ወይወፍሩ ፡ አዕጹቂሁ ፡ ወይከውን ፡ ከመ ፡ ዘይት፡ሥሙር፡ወመዐዛሁ፡ከመ፡ሊባኖስ።

፯፤ ወይትመየጡ፡ወይነብሩ፡ታሕተ፡ጽላሎቱ፡ ወየሐይዉ ፡ ወይጸግቡ ፡ እምሥርናይ ፡ ወይሠርፅ ፡ ከመ ፡ ወይን ፡ ዝክሩ ፡ ወከመ ፡ ወይነ፡ሊባኖስ።

፰፤ ለኤፍሬም፡ለምንት፡እንከ፡ሎቱ፡ጣዖት፡ ወናሁ፡አነ፡አድከምክዎሂ፡ወአነ፡አጽናዕክዎሂ፡ወአነ፡አፈርዮ፡ከመ፡ዘይት፡ሥሙር፡ ወይትረከብ፡ፍሬሁ፡በኀቤየ።

፱፤ መኑ፡እንከ፡ጠቢብ፡ዘይኄልዮ፡ለዝንቱ፡ ወመኑ ፡ ዘይሌብዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወየአምሮ ፡ እስመ፡ርቱዓት፡ፍናዊሁ፡ለእግዚአብሔር፡ ጻድቃን ፡ የሐውርዎን ፡ ወኃጥአንሰ ፡ ይስእንዎን።

ጥበበ ፡ ሢራክ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፩፤፳-፳፩።

፳፤ ሥርዋ፡ለጥበብ፡ፈሪሃ እግዚአብሔር፡ወአዕፁቂሃኒ፡ያነውህ፡መዋዕለ፡ሕይወት።

፳፩፤ ኢይክል፡መዐትም፡ወዓማፂ፡ጸዲቀ፡እስመ፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ኃጢአትን ፡ ለምን ፡ ትተክላላችሁ? የሞት፡ ፍሬንስ፡ለምን፡ትለቅማላችሁ።

፪፤ ለእግዚአብሔር ፡ የምናቀርበው ፡ የከንፈሮ ችንን፡ዋጋ፡ምስጋናን፡ያዙ።

፫፤ አርበኛው ፡ አያድንም ፡ በፈረሶች ፡ ተቀም ጠንም ፡ አናመልጥም ፤ የእጆቻችን ፡ ሥራ፡ (ጣዖቶቻችንን) ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ፈጣሪዎ ቻችን፡ናቸው፡አንላቸውም፡በሉ።

፬፤ ስለዚህ፡ሰው፡ሁሉ፡ይቅር፡ይባላል፤በሽተኞ ቻቸውንም፡ያድናቸዋል፤በእውነትም፡ይወዳ ቸዋል ፤ እነሆ ፡ ቁጣዬንም ፡ ከእነሱ ፡ እመል ሳለሁ።

፭፤ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ ዝናም ፡ እሆናቸዋለሁ፡ እንደ ፡ አበባም ፡ በረድኤት ፡ ይለመልማል፡ ሥሩም፡እንደ፡ደጋ፡ዛፍ፡ይጸናል።

፮፤ ጫፎቹ፡(ልጆቹ)፡ይወፍራሉ፤እርሱም፡እንደተ ወደደ፡ዘይት፡ይሆናል፤መዐዛው፡(ሃይማኖቱ)፡ እንደ፡ሊባኖስ፡ይሆናል፤(አባትነቱ)።

፯፤ ከተማረኩበትም ፡ ተመልሰው ፡ በረድኤቱ፡ ጥላ፡ተጠብቀው፡ይኖራሉ፤ከአሕዛብ፡ባለጠ ግነት ፡ ይጠግባሉ ፤ ስም ፡ አጠራሩም ፡ እንደ ወይን፡ይለመልማል፤እንደ፡ደጋ፡ወይንም፡ ደስ፡ያሰኛል።

፰፤ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ለኤፍሬም ፡ ጣዖት ፡ ምን፡ ነው? እኔ ፡ አደከምኩት ፤ እኔም ፡ አጸናሁት፤ እንደ ፡ አማረ ፡ ዘይትም ፡ እኔ ፡ አበዛዋለሁ፡ ፍሬውም፡በእኔ፡ዘንድ፡ይገኛል።

፱፤ ይህንን ፡ አስተውሎ ፡ የሚያስበው ፡ ብልህ፡ ማነው? ይህንንስ ፡ ልብ ፡ የሚያደርገው፡ ማነው? ይህንን ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቀው፡ ማነው? የእግዚአብሔር ፡ መንገዶቹ ፡ የቀኑ፡ ናቸውና ፡ ጻድቃን ፡ ይሄዱባቸዋል ፤ ኃጥአን ግን፡ያጧቸዋል።(አይፈጽሟቸውም)።

የሲራክ ፡ የጥበብ ፡ መጽሐፍ ፡ በረከቱ ፡ ከእኛ፡ ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፤፩፤፳-፳፩።

፳፤ የጥበብ ፡ ሥርዋ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ነው፤ቅርንጫፎችዋም፡የሕይወት፡ዘመንን ያረዝማል።

፳፩፤ ቁጠኛ፡ዓመፀኛ፡ሰው፡መጽደቅ፡አይችልም

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

በጊዜ፡ይትመዓዕ፡ይከውን፡ድቀቱ።

፳፪፤ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ ጊዜሃ ፡ ተዓገሣ ፡ ለመዓት ፡ ወድኅረ፡ታስተፌሥሐከ።

፳፫፤ እስከ፡ትረክብ፡ጊዜሁ፡ኀባዕ፡ነገረከ፡ወይት ናገሩ፡ብዙኃን፡በጥበብከ።

፳፬፤ ውስተ ፡ መዛግብቲሃ ፡ ለጥበብ ፡ ትምህርተ ፡ አምሳል ፡ ያስቆርሮ ፡ ኃጥእ ፡ ለፈራሂ ፡ እግዚአብሔር።

፳፭፤ ለእመ ፡ ታፈቅራ ፡ ለጥበብ ፡ ዕቀብ ፡ ትእዛዛ ፡ ወእግዚአብሔር፡ ይሁበከሃ።

፳፮፤ ጥበብኒ ፡ ወአእምሮኒ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ፡ወፈቃዱኒ፡ሃይማኖት፡ወየዋሃት።

፳፯፤ ኢትርሳእ፡ፈሪሃ፡እግዚአብሔር።

፳፰፤ ወኢትጸመዶ፡በ፪ኤ፡ልብ፡እንዘ፡ትናፍቅ።

፳፱፤ ወኢትደቅ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ሰብእ ፡ ወዕቀብ ፡ ከናፍሪከ።

፴፤ ወኢታዕቢ ፡ ርእሰከ ፡ ከመ ፡ ኢትሕሥር ፡ ወከመ፡ኢትደቅ፡ነፍስከ፡ወይከሥተከ፡እግዚአብሔር፡ኅቡዓቲከ፡ወበማእከለ፡ብዙኃን፡ያወድቀከ፡እስመ፡በፍርሀተ፡እግዚአብሔር፡ ኢመጻእከ ፡ ወምሉዕ ፡ ጕሕሉት ፡ ውስተ ፡ ልብከ።

### ክፍል፡፪።
### ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፶፫፤፳፫–፳፯።

፳፫፤ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎዶጦስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘእንቄራ፡በውስተ፡ዝንቱ፡ድርሳን፡ዘደረሰ።

፳፬፤ በእንተ ፡ ምንት ፡ ረሰየ ፡ ሕማመ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ዘሎቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ፈቂዶ ፡ ያጥፍእ ፡ ሕማመ ፡ በሕማሙ ፡ ወያብጥል፡ሞተ፡በሞቱ።

፳፭፤ ወወለጠ ፡ ዘሀሎ ፡ በዝንቱ ፡ አምሳል ፡ በዘዚአሁ ፡ አምሳል ፡ ወበዝንቱ ፡ አምሳል ፡ ሞዐ፡ባሕቲቶ፡ውእተ፡ሕማመ።

፳፮፤ ወተዐገሠ፡ስቅለተ፡ወረሰየ፡ጽፍዐተ፡ሎቱ፡ ወለሕማምሂ ፡ ረሰዮ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ወአመ፤ኮነ፡ሕማም፡ለእግዚአብሔር፡ዝንቱ፡ ሕማም፡ረከበ፡ሥልጣነ፡በዲበ፡ምድር፡ከመ፡ ያብጥል፡ሕማማተ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

በተቆጣ፡ጊዜ፡ፈጥኖ፡ይጠፋልና።

፳፪፤ ጊዜዋ፡እስኪያልፍ፡ድረስ፡ቁጣን፡ታገሣት፤ ኋላ፡ግን፡ደስ፡ታሰኝሃለች።

፳፫፤ ጊዜ ፡ እስከታገኝ ፡ ድረስ ፡ ነገርህን ፡ ሠውር ፤ ብዙዎች፡ሰዎችም፡ጥበብህን፡ይናገራሉ።

፳፬፤ በጥበብ ፡ መዛግብት ፡ የምሳሌ ፡ ትምህርት ፡ አለ፤ኃጢአተኛ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚ ፈራውን፡ይጸየፈዋል።

፳፭፤ ጥበብን፡ከወደድሃት፡ትእዛዟን፡ጠብቅ፤እግዚአብሔርም፡እርሷን፡ይሰጥሃል።

፳፮፤ ጥበብም ፡ ዕውቀትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ፤ ፈቃዱም ፡ ሃይማኖትና ፡ የዋህነት፡ነው።

፳፯፤ እግዚአብሔርን፡መፍራት፡አትርሳ።

፳፰፤ እየተጠራጠርህ፡በሁለት፡ልብ፡አታገልግለው።

፳፱፤ በሰው ፡ አፍ ፡ እንዳትወድቅ ፡ ከንፈርህን ፡ ከሐሜት፡ከአሉባልታ፡ጠብቅ።

፴፤ ራስህን ፡ አታኵራ ፤ እንዳትዋረድ ፡ ሰውነ ትህም፡እንዳትጠፋ፡ሠውረህ፡የሠራኸውን፡ እግዚአብሔር፡ ይገልጥብሃልና፡በብዙዎች፡ ሰዎች፡መካከልም፡ያዋርድሃልና፡እግዚአብሔርንም ፡ በመፍራት ፡ አልመጣህምና ፡ በልብህም፡ሽንገላ፡መልቷልና።

### ክፍል፡፪።
### የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፶፫፤፳፫–፳፯።

፳፫፤ የዕንቆራ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ ቴዎዶጦስ፡በዚህ፡አንቀጽ፡እንዲህ፡አለ።

፳፬፤ ለእሱ ፡ እንደሚገባ ፡ አድርጎ ፡ ሰብአዊ ፡ ሕማምን ፡ ስለምን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ? በሕማሙ፡ ሕማምን ፡ ሊአጠፋ ፡ በሞቱም ፡ ሞቱን፡ያጠፋ፡ዘንድ፡ወዶ፡ነው፡እንጂ።

፳፭፤ በዚህ፡በሥጋ፡ባሕርይ፡ያለ፡ሥራን፡በእርሱ፡ ባሕርይ፡ባለ፡ሥራ፡ለወጠ፤በዚህም፡ባሕርይ፡ ያለን፡ሕማም፡ብቻውን፡ድል፡ነሣ።

፳፮፤ ስቅለትን ፡ ታገሠ ፡ በጥፊ ፡ መመታትንም ፡ ለራሱ፡ገንዘብ፡አደረገ፤ሕማምንም፡ለራሱ፡ ብቻ ፡ አደረገ ፤ ሕማም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ ሊሆን ፡ በተገባው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ሕማም፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሕማማትን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ፡ሥልጣንን፡አገኘ።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፺፰፤ ወህላዌሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢተወክፈ ፡ ሕማመ ፡ በግብር ፡ በርእሱ ፡ አመ ፡ ረሰየ ፡ ሕማመ ፡ ሥጋ ፡ ለመለኮቱ ፡ አላ ፡ ሕማም ፡ ረከበ፡ ኀይለ ፡ በዘይመስሎ ፡ ወሞትሂ ፡ ሶበ ፡ ኮነ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አብጠለ ፡ ሞተ ፡ ወእምድኅረ ፡ ሞቱሂ ፡ ነሠተ ፡ ሙዐተ ፡ ሞት።

ምዕ፤፶፩፡፺፱—፻፫።

፺፱፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ዘቆጵሮስ ፡ ንህነሰ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ መድኀኒነ ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ኢየሐምም ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ወኮነ ፡ በሥጋሁ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወደለዎ ፡ ከመ ፡ ይሕምም ፡ በሥጋሁ ፡ ኢተሃሊ፡ከመ፡ውእቱ፡ምትሐት፡ዘአልቦቱ፡ ሥጋ፡ዘበአማን፡አላ፡ቦቱ፡ኵሉ፡አምሳላት፡ ዘዘከርነ፡በዕጓለ፡እመሕያው።

፻፤ ወዓዲ ፡ ተወክፈ ፡ ሕማማተ ፡ ዘዘከርነ ፡ ዘውእቱ ፡ ንዋም ፡ ወረኃብ ፡ ወጽምዕ ፡ ወድካም፡ ወኵሎ ፡ አምሳለ ፡ ዘይትዐወቅ ፡ በህላዌ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘረከቦ፡በትስብእት።

፻፩፤ ወዘይቤ፡በወንጌል፡ቅዱስ፡ናሁ፡ረከብናሁ፡ ለማስያስ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ሙሴ ፡ በእንቲአሁ ፡ በአይቴ፡ተረክበ፡ዘእንበለ፡ዳእሙ፡በህላዌ፡ ዘዘከርነ ፡ ወዘይትዐወቅ ፡ ዘውእቱ ፡ አስተር እዮቱ፡በሥጋ፡ዘይትረከብ።

፻፪፤ ወበእንተ፡ዝንቱ፡ተብህለ፡እስመ፡ወዐልት፡ አኀዝዎ፡ወመጠወ፡ዘባኖ፡ለቅሥፈት፡ወመ ልታሕቶ፡ለጽፍዐት፡ወኢሜጠ፡ገጾ፡እምኀ ፍረተ፡ምራቅ፡ወበከየ፡ወተከዘ፡ወኵሎ፡ ዘተብህለ፡በእንቲአሁ፡ተወክፈ።

፻፫፤ ወመኑ፡ውእቱ፡ዘይክል፡ይቅሥፍ፡ቃለ፡እግ ዚአብሔር፡አው፡ይጽፍእ፡አው፡ይውርቅ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ዘኢይት ረከብ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፺፰፤ የሥጋን፡ሕማም፡ለመለኮት፡ገንዘብ፡በአደረ ጊዜ፡የእግዚአብሔር፡አካል፡በባሕርዩ፡በግ ሕማምን ፡ አልተቀበለም ። ሕማም ፡ በሚ ማማው፡ባሕርዩ፡ኀይልን፡ነሣ፡እንጂ፤ሞትም በሥጋ፡ለእግዚአብሔር፡ቃል፡ገንዘብ፡በሆነ ጊዜ፡ሞትን፡አጠፋ፤ከሞትም፡በኋላ፡ፈርሶ በስብሶ፡መቅረትን፡አጠፋ።

ምዕ፤፶፩፡፺፱—፻፫።

፺፱፤ ዳግመኛ ፡ የቆጵሮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይህ ቅዱስ፡ኤጲፋንዮስ፡እንዲህ፡አለ፤እኛ፡ግን መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ በባሕርዩ፡ መለኮቱ ፡ ሕማም ፡ ሳይኖርበት በሥጋ፡እንደታመመ፡እናውቃለን፤ከሰማይ የወረደ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሥጋ ፡ የተገለጠ እርሱ፡ቃል፡ነው።በሥጋ፡ይታመም፡ዘንድ ተገባው ። እውነተኛ ፡ ሥጋ ፡ የሌለው ምትሐት፡ነው፡አትበል፤በሰው፡እንዳለ፡የተ ናገርነው፡ሁሉ፡ገንዘቡ፡ነው፡እንጂ።

፻፤ ዳግመኛ ፡ የተናገርናቸው ፡ ሕማማትን ተቀበለ ፡ ስንል ፡ መተኛት ፡ ረሀብ ፡ ጽም ድካም፡ነው።በሰው፡ባሕርይ፡እንዳለ፡የሚ ታወቀውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ይህ፡ሁሉ፡ያገኘውም፡ሰው፡በመሆኑ፡ነው።

፻፩፤ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ሙሴ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የጻፈ ለትን ፡ ማስያስን ፡ እነሆ ፡ አገኘነው ያለ በሚታወቅ ፡ በተናገርነው ፡ ባሕርይ ፡ ነው እንጂ ፡ በምን ፡ ባሕርይ ፡ ተገኘ? ይኸውም በሚታይ፡ሥጋ፡መታየቱ፡ነው።

፻፪፤ ስለዚህም ፡ የአይሁድ ፡ ሎሌዎች ፡ እን ያዙት፡ ጀርባውን ፡ ለግርፋት ፡ ፊቱንም በጥፊ፡ ለመመታት ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ምራቅን ከመጸየፍ፡የተነሣ፡ፊቱን፡እንዳልመለሰ፡እን ዳለቀሰ፡እንዳዘነ፡ስለ፡እርሱ፡የተነገረውን ሁሉ፡እንደተቀበለ፡ተነገረ።

፻፫፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ይገርፍ ፡ ዘንድ በጥፊም፡ይመታው፡ዘንድ፡ወይም፡በማይያዝ በማይዳሰስ ፡ በመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ በፊቱ እንትፍ፡ይልበት፡ዘንድ፡የሚችል፡ማነው?

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፴፯፤ እስመ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳማዊ ፡ ተወክፈ፡ዘንተ፡አኮኑ፡በሥጋሁ፡ተወክፈ፡ሕማመ፡ወበመለኮቱሰ፡ዘኢየሐምም፡እንዘ፡ኢይትፈለጥ ፡ እምሥጋሁ ፡ ወበፈቃዱ ፡ ኀለቈ፡ሕማማተ፡ከመ፡ዘሎቱ።

፴፰፤ ዘከመ፡ደም፡ዘውስተ፡ልብስ፡ብእሲ፡ወአኮ፡ደም፡ቅቡዕ፡በዘይለብሶ፡ከማሁ፡እግዚአ፡ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ወኢረከቦ ፡ ሕማም ፡ ለመለኮቱ፡ አላ፡ኀለቈ፡ሕማማተ፡ከመ፡ዘሎቱ ፡ እስመ ፡ ተወክፎ ፡ በሥጋሁ ፡ አምላካዊ፡ እስመ ፡ መለኮት ፡ ይትወሐድ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ ይኩነነ ፡ መድኃኒተ ፡ በመለኮት ፡ ዘይትወሐድ ፡ ምስለ ፡ ሥጋሁ ። በረከተ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ለእሉ ፡ መምህራን ፡ የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ተግሣጽ፡ዘአቡነ፡አባ፡ሲኖዳ።

በረከቱ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፤ እስመ ፡ ትትረከብ ፡ ምግባር ፡ ዘትመስል፡ሠናይተ ። ወይእቲ፡እኪት፡በኀበ፡እግዚአብሔር።

፪፤ ወናሁ ፡ ሶበ ፡ ንኔጽር ፡ አሐደ ፡ ዘይገብር ፡ ኃጢአተ ፡ በውስተ ፡ መካናት ፡ ቅዱሳት ። ንትዓገሥ፡ላዕሌሁ፡ወንጼር፡ድካሞ፤እስመ፡እግዚአብሔር፡ሶበ፡ተከለ፡ገነተ፡ኢነሥአ፡እምዕፀው፡ሠናያተ፡ባሕቲቶሙ፡አላ፡ዕፀወ፡እኩያተ፡ተከለ፡ቦቱ።

፫፤ ወኢተከለ፡ቦቱ፡ዕፀ፡ዘእንበለ፡ፍሬ፤ወኢዕፀ ፡ ዘእኩይ ፡ ፍሬሁ ፡ ኢይኩን ፡ ዝንቱ ፡ ባሕቲቱ።

፬፤ ወለሰብእ፡ድኅረ፡ገብሮ፡ወሤሞ፡ውስተ፡ገነት፡ሶበ፡ኀደገ፡ትእዛዞ፡ኢኀደጎ፡ወኢተዓገሦ፡አላ፡አውጽኦ፡እምገነት።

፭፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አእምሩ ፡ አ ፡ አኀው ፡ ዘኢኮነ፡ሠናየ፡ኢትምልዑ፡ቤተ፡እግዚአብሔር፡ወመካኖ፡እምሰብእ፡እኩያን፡ወእምሰብእ፡ሠናያን፡ከመ፡ካልአት፡መካናት፡ዘይመልዑ፡ኃጥአን፡ወዓማዕያን፡ሠናያን፡

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፴፯፤ በቅድምና፡የነበረ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ይህን፡ከተቀበለ፡መከራን፡የተቀበለ፡በሥጋ፡አይደለምን? በመለኮቱስ ፡ የማይታመም ፡ ነው፤ከሥጋው፡ሳይለይ፡ገንዘቡ፡እንደሆነ፡አድርጎ፡ሕማምን፡በፈቃዱ፡ተቀበለ፡እንጂ።

፴፰፤ ደም፡በሰው፡ልብስ፡ላይ፡እንዲረጭ፡ደም፡ከለባሹ ፡ እንዳይደርስ ፡ እንዲሁም ፡ ጌታ ፡ በሥጋው፡ታመመ፤በመለኮቱ፡ግን፡ሕማም፡የለበትም ፤ መለኮት ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ ስለተዋሐደ፡አምላክ፡በሆነ፡ሥጋው፡ተቀብሎ ታልና፡ሕማምን፡ገንዘብ፡አደረገ፡እንጂ፡ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ በተዋሐደ ፡ መለኮት ፡ መድኃኒት፡ይሆነን፡ዘንድ። የእኒህ፡መምህራን፡ጸሎታቸው፡በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

### የአባታችን፡የአባ፡ሲኖዳ፡ምክርና፡ተግሣጽ፡ይህ፡ነው።

በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትሁን፤አሜን።

፩፤ መልካም ፡ ሥራ ፡ የምትመስል ፡ ምግባር ፡ ትገኛለች፤እርሷም፡በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡የከፋች፡ናት።

፪፤ እነሆ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በተቀደሱ ፡ ቦታዎች ፡ ውስጥ ፡ ኃጢአት ፡ ሲሠራ ፡ ባየን ፡ ጊዜ ፡ በእርሱ፡ላይ፡ታግሠን፡እናጽናናው፤እግዚአብሔር፡ገነትን፡በአትክልት፡በአዘጋጀ፡ጊዜ፡በጎ፡የሆኑ፡ዕፀዋትን፡ብቻ፡ወስዶ፡አላዘጋጀም፤ክፉዎቹንም፡ጭምር፡ተከለ፡እንጂ።

፫፤ ተክሉንም ፡ ያለ ፡ ፍሬ ፡ አልፈጠረውም ፤ ፍሬው ፡ መራራ ፡ የሆነውንም ፡ እንጨት ፡ ብቻውን፡እንዲሆን፡አላደረገውም።

፬፤ ሰውንም፡ፈጥሮ፡በገነት፡ከሾመው፡በኋላ፡ትእዛዙን ፡ ባፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ታግሦ ፡ አልተወውም፤ከገነት፡አወጣው፡እንጂ።

፭፤ ስለዚህም ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ አስተውሉ ፤ በጎ፡ያልሆነውን፡የእግዚአብሔርን፡ቤትና፡ቦታውንም ፡ በክፉዎች ፡ ሰዎችና ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች፡(በመናፍቃን)፡አትምሉት።ደጎችና፡ክፉዎች፡ዓመፀኞችና፡ኃጥአን፡እንደሞሉ

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ወእኩያን ፤ አላ ፡ ሶበ ፡ ንኔጽር ፡ አሐዱ ፡ እንዘ ፡ ይገብር ፡ ኃጢአተ ፡ ናውፅኦ ፡ እመካናት ፡ ቅዱሳት፡ፍጡነ።
፳፩ አነ ፡ አአምር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልአ።
፳፪ ወሶበ፡ንሬስዮ፡ለቤቱ፡ከመ፡ካልእት፡ምድር፡ በምንት፡እንከ፡ናከብሮ፡ለቤቱ።

፳፫ ወእመሰ፡አነ፡ሶበ፡እገብር፡ኃጢአተ፡እኪተ፡ በከመ፡ይገብሩ፡ካልአን፡እለ፡ይነብሩ፡ዲበ፡ ምድር ፡ በምንት ፡ ይሰምዩኒ ፡ ካህነ ፤ እስመ ፡ ዝንቱ፡ይከውን፡ለነ፡ደይነ።
፳፬ እስመ ፡ አሐዱ ፡ ኢይክል ፡ ይምላዕ ፡ ቤተከ ፡ ርስሐተ፡ዘእንበለ፡ፈቃድከ።
፳፭ ወወዓልተ፡ንጉሥኒ፡ኢይትሀበሉ፡ይጸውዑ፡ ይባኡ፡ኵሉ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ውስተ፡ጽርሐ፡ ንጉሥ ፡ እምእለ ፡ ይገብሩ ፡ ፈቃዶ ። ወእለ ፡ የዐብዩ ፡ ለእመ ፡ ገብሩ ፡ ዘንተ ፡ በተዓድዎ ፡ ይደልዎሙ፡ዐቢይ፡ኵነኔ፡እስከ፡ለሞት።

ምንተኑ፡በል።

ተአምሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፩ ዘከመ ፡ ጸለየት ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ።
፪ ወትቤ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ዘይገብር ፡ ኵሎ፡ዘፈቀደ፡በሰማይኒ፡ወበምድርኒ፡ባርካ፡ እግዚኦ ፡ ለይእቲ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ይትገበር ፡ በዓል፡በስመ፡ዚአየ።
፫ ተወከፍ፡ጸሎትየ፡ወባርክ፡ርስተከ፡ሕዝበከ፡ ወመሲሐከ፡እለ፡ያቄርቡ፡ለከ፡መሥዋዕተ፡ በስመ፡ዚአየ።

፬ ወአውሥአ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይቤላ ፡ ናሁ ፡ ገበርኩ ፡ ለኪ ፡ ወእምይእዜሰ ፡ ተፈሥሒ ፡ እስመ ፡ ተውህበኪ ፡ እምነቢየ ።

ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ባቸው ፡ እንደሌሎች ፡ ቦታዎች ፡ አንዱ ፡ ኃጢአ
ትን ፡ ሲሠራ ፡ በተመለከትን ፡ ጊዜ ፡ ከቅዱሳ
ቦታዎች፡ፈጥነን፡እናውጣው፡እንጂ።
፳፩ ምድር ፡ በመላዋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ እንደሆነች፡እኔ፡አውቃለሁና።
፳፪ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ምድራዊት ፡ ቤት ፡ ካደረግነው ፡ እንግዲህ ፡ ያከበርነው ፡ በምንድር፡ነው?
፳፫ በዓለም ፡ ያሉ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እንደሚ ሠሩት፡ እኔ ፡ የከፋ ፡ ኃጢአትን ፡ በምሠራ ፡ ጊዜ፡ እንዴት ፡ ካህን ፡ ብለው ፡ ሊጠሩኝ ፡ ይችላሉ?ይህ፡ያስፈርድብናልና።
፳፬ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ያለ ፡ ፈቃድህ ፡ በቤትህ ፡ ውስጥ፡ቁሻሻ፡ይመላ፡ዘንድ፡አይችልምና።
፳፭ የንጉሥ ፡ ጭፍሮችም ፡ ፈቃዱን ፡ ከሚ ጽሙት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አዳራሽ ፡ ይገቡ፡ ዘንድ ፡ አንዱንም ፡ አንዱን ፡ ይጠሩ ዘንድ፡አይደፍሩም።እምቢ፡ተኞችም፡በመ ላለፍ ፡ ይህን ፡ ቢአደርጉ ፡ ለሞት ፡ እስከሚ ደርስ፡ታላቅ፡ቅጣት፡ይገባቸዋል።

ምንተኑ፡በል።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለ
ይደርብንና ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በሁለ
ወገን ፡ ድንግል ፡ የሆነች ፡ ቅድስት ፡ እመ
ታችን፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይ
ነው።
፩ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በሁለት ፡ ወገ ድንግል ፡ የሆነች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን እንደጸለየች።
፪ እንዲህም፡አለች፡ጌታዬ፡ሆይ፡የልዑል፡እ
ዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶ
በሰማይም፡በምድርም፡የፈቀድከውን፡ሁሉ
ማድረግ ፡ የምትችል አቤቱ ፡ በእኔ ፡ ስም
በዐል፡የሚደረግባትን፡ይቺን፡ቦታ፡ባርካት
፫ ልመናዬንም ፡ ተቀብለህ ፡ ርስት ፡ ትሆንህ
በልጅነት ፡ ያከበርካቸውን ፡ ወገኖችህ
በእኔ፡ ስም ፡ መሥዋዕትን ፡ የሚአቀርቡልህ
ሁሉ፡ባርክ።
፬ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ መልሶ
እንዲህ ፡ አላት ፤ እነሆ ፡ ያልሺውን ፡ አደረ
ሁልሽ ፤ ከእኔም ፡ ከአባቱም ፡ ከመንፈ

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

ኵሉ፡ሀብት፡ወእምኀበ፡አቡየ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ።

፭፡ ወኵሉ፡ዘይዜክር፡ስመኪ፡ወይጼውዕ፡ ኢይማስን፡በኀበ፡ገዘ፡ዓለም፡ወኢበከሃኒ፡ አላ፡ይረክብ፡ጸጋ፡በኀበ፡አቡየ፡ዘበሰማያት።

፮፡ ወእምዝ፡ተመይጠ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ኀበ፡ጴጥሮስ፡ወይቤሎ፡ናሁኬ፡ በጽሐ፡ጊዜ፡አንብቦ፡ወዘምሮ።

፯፡ ወእምዝ፡አኀዘ፡ጴጥሮስ፡ያንቦብ፡ ወይዘምር፡ምስለ፡መላእክት፡ውእተ፡ጊዜ፡ ሠረቀ፡ዲበ፡ገጸ፡ለቅድስት፡ዐቢይ፡ብርሃን።

፰፡ ወአንሥአት፡እደዊሃ፡ወባረከቶሙ፡ለአርድእት።

፱፡ ወእምዝ፡ሰፍሐ፡እደዊሁ፡እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወተመጠወ፡መንፈሳ፡ ወሶቤሃ፡ተፈልጠት፡እምሥጋሃ፡ወመልአ፡ ውስተ፡ውእቱ፡መካን፡ብርሃን፡ዐቢይ።

፲፡ ወወፅአ፡ጼና፡መዐዛ፡ሠናይ፡ዘእልቦ፡ ዘከማሁ።

፲፩፡ ወመጽአ፡ቃል፡እምሰማይ፡ዘይብል፡ብፅዕት፡ አንቲ፡ንግሥት፡ወቡርክት፡እምአንስት።

፲፪፡ ወሰገደ፡ጴጥሮስ፡ምስለ፡አርድእት፡ታሕተ፡ እገሪሃ፡ለቅድስት፡ድንግል።

፲፫፡ እፎኬ፡መድምም፡ክብር፡ዘውድስት፡በአፈ፡ አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ ወስብሐት፡በአፈ፡መላእክት፡ወሰብእ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ወኵሎ፡ሥርዓተ፡ከመ፡ቀዳሚ፡አብጽሕ።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ዘከመ፡ቦአ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወረከበ፡ሥዕለ፡ ራዕዩ፡ለሕዝቅኤል፡ወዘከመ፡አመክርዎ፡ አይሁድ፡ወዘከመ፡አደንገፆሙ፡በገቢረ፡ ተአምራት፡ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ቅዱስም፡ዘንድ፡ከዛሬ፡ጀምሮ፡ፍጹም፡ ሀብት፡ተሰጥቶሻልና፡ደስ፡ይበልሽ።

፭፡ ስምሽን፡የሚአስታውስና፡የሚጠራው፡ በዚህ፡ዓለምም፡ሆነ፡በወዲያኛውም፡ጥፋት፡ አያገኘውም፤ከአባቴ፡ዘንድ፡በሰማይ፡ጸጋ፡ ክብርን፡ያገኛል፡እንጂ።

፮፡ ከዚህም፡በኋላ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወደ፡ጴጥሮስ፡ተመልሶ፡እነሆ፡የማንበብና፡ የመዘመር፡ጊዜ፡ደረሰ፡አለው።

፯፡ ከዚህ፡በኋላ፡ጴጥሮስ፡ከመላእክት፡ጋራ፡ ያነብና፡ያመሰግን፡ይዘምር፡ዘንድ፡ጀመረ፤ በቅድስት፡ድንግል፡ፊቷ፡ላይ፡ታላቅ፡ ብርሃን፡በራ።

፰፡ እጆቿንም፡አንሥታ፡ሐዋርያትን፡ባረከቻቸው።

፱፡ አሁንም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ እጆቹን፡ዘርግቶ፡ነፍስዋን፡ተቀበለ፤ ያንጊዜም፡ከሥጋዋ፡ተለየች፡በዚያ፡ቦታም፡ ታላቅ፡ብርሃን፡መላበት።

፲፡ እንደርሱ፡ያለ፡የሌለ፡መልካም፡መዓዛ፡ ወጣ።

፲፩፡ ከሰማይም፡አንቺ፡ከሴቶች፡ተለይተሽ፡የተባረክሽ፡ንዕድ፡ክብርት፡ንግሥት፡ነሽ፡የሚል፡ ቃል፡መጣ።

፲፪፡ ጴጥሮስም፡ከሐዋርያት፡ጋራ፡ለቅድስት፡ ድንግል፡ከእግርዋ፡በታች፡ሰገደ።

፲፫፡ በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡አንደበት፡ የተመሰገነች፡በሰውና፡በመላእክት፡አንደበትም፡የከበረች፡ይህ፡ለእርስዋ፡የሆነ፡ ክብር፡ምንኛ፡ታላቅና፡ድንቅ፡ነው።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ሥርዓቱን፡ሁሉ፡እንደፊተኛው፡አድርስ።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይደርብንና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወደ፡ቤተ፡ መቅደስ፡ገብቶ፡የሕዝቅኤልን፡የራዕዩን፡ ሥዕል፡እንዳገኘ፡አይሁድ፡እንደ፡ተፈታተኑትና፡በገቢረ፡ተአምራት፡እንዳስደነገጣቸው፡ያደረገው፡ድንቅ፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፩፤ ወበአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ቦአ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወርእየ ፡ ሥዕለ ፡ ራእዩ፡ ለሕዝቅኤል ፡ ዘውእቱ ፡ ሠረገላ ፡ ዘይጸውርዎ ፡ አርባዕቱ ፡ እንስሳ ፡ እሙንቱኒ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ፡ ወገጸ ፡ እንስሳ ፡ ገጸ ፡ ንስር ፡ ወገጸ ፡ አንበሳ።

፪፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ምንትኑ ፡ ውእቱ፡ዝ፡ሥዕል፡ወይቤልዎ፡ሥዕለ፡ራእዩ፡ለሕዝቅኤል፡ነቢይ፡ዘርእየ።

፫፤ ወይቤሎሙ ፡ አኮኑ ፡ ዝንቱ ፡ ሥዕል ፡ ግቡር ፡ በዘዘዚአሁ፡ሥርዓት፡ወይቤልዎ፡እወ፡ንህነ፡ነአምር፡ዘንተ።

፬፤ ወእምዝ፡ይቤ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለእመ፡አነ፡እኤዝዞሙ፡ለእሉ፡አምሳላተ፡እንስሳ፡ከመ፡ይኩኑ፡ነባብያነ፡ኢተአምኑሁ፡ከመ፡ወልደ፡ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ፡ወአልቦ፡ሥሉጥ፡ዘእንበሌሁ።

፭፤ ወይቤልዎ ፡ አይሁድ ፡ ይእዜ ፡ አእመርነ ፡ ከመ፡ ጠፍአ ፡ ኀሊናከ ፡ ወዘንግዐ ፡ ልቡናከ ፡ አማን ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ፡ አንተ ። (ሎቱ ፡ ስብሐት)።

፮፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እመሰ ፡ ኢገበርኩ፡በከመ፡እቤለክሙ፡ወእመ፡ኢረከብክምዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ሥዕላት ፡ ሕያዋነ ፡ አእምሩ፡ጥዩቀ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡ወልደ፡ዮሴፍ፡ጸራቢ፡በከመ፡ትቤሉ።

፯፤ ወይቤልዎ፡ግበር፡እስኩ፡ንርአይ፡ለእመ፡ገበርከ፡ዘንተ፡ነአምን፡ብከ፡ከመ፡አንተ፡ውእቱ፡ኢየሱስ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ዘይሴፈውዎ፡ለመድኀኒተ፡ዓለም።

፰፤ ወተመይጠ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኀበ፡እሉ፡ሥዕላት፡ለክሙ፡እብለክሙ፡አ፡ሥዕላት፡ብሉያት፡የሀሉ፡ውስቴትክሙ፡መንፈስ፡ወይኩን ፡ ለክሙ ፡ ሥጋ ፡ ወንዑ ፡ እመካንክሙ፡ዲበ፡ምድር፡ኀበ፡ሀሎነ፡ንህነ።

፱፤ ወእምዝ፡ሖሩ፡ኀበ፡መቃብር፡ዘሀለዉ፡አብርሃም፡ይሥሐቅ፡ወያዕቆብ፡ወኀበ፡ኵሉ፡ዘተቀብረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እምደቂቆሙ ፡ ለአበው፡እምቀዳሚ፡መዋዕል።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፩፤ በአንዲት ፡ ዕለትም ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ሳለ ፡ ሕዝቅኤል፡ በፈለገ ፡ ኮቦር፡ በአየው ፡ አምሳል ፡ አርባዕቱ፡ እንስሳ ፡ የተሸከሙትን ፡ የሠረገላ ፡ ሥዕል፡ አየ፤ እነርሱም ፡ የሰውና ፡ የላም ፡ የንስርና፡ የአንበሳ፡መልክ፡ያላቸው፡ናቸው።

፪፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ ይህ ፡ ሥዕል ፡ ምንድንነው፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ ነቢዩ ፡ ሕዝቅኤል፡ በራዕይ፡አይቶ፡የሣለው፡ሥዕል፡ነው፡አሉት፡

፫፤ ይህ ፡ ሥዕል ፡ በየራሱ ፡ አሠራርና ፡ ሥርዓት፡ የተሠራ ፡ አይደለምን? አላቸው ። እነርሱም፡ አወን፤ይህን፡እኛ፡እናውቃለን፡አሉት።

፬፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ እነዚህን፡ የእንስሳ ፡ ሥዕሎች ፡ ተናጋሪዎች ፡ ይሆኑ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ባዛቸው ፡ የሰው ፡ ልጅ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ እርሱም ፡ ሥልጣን፡ እንደሌለ፡በእኔ፡ታምናላችሁን?አላቸው።

፭፤ አይሁድም ፡ አእምሮህ ፡ እንደተዛባ፡ ልቡናህም፡እንደ፡ዘነጋ፡ገና፡ዛሬ፡አወቅን፡ በእውነት፡አንተ፡የዮሴፍ፡ልጅ፡ነህ፡አሉት፡ የክብር፡ባለቤት፡እርሱን።

፮፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡እንዳልኳችሁ፡ካላደረግሁ፡ እነዚህንም፡ሥዕሎች፡ሕያዋን፡ሁነው፡ካላ ኛችኋቸው ፡ እናንተ ፡ እንዳላችሁት፡ የጸራቢው ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ እንደሆንኩ፡ በእውነት፡ታውቃላችሁ፡አላቸው።

፯፤ እነርሱም፡እስኪ፡አድርግ፤እንይ፡ይህንንም፡ ካደረግህ ፡ ዓለምን ፡ ለማዳን ፡ ይመጣል፡ ብለው፡ ተስፋ ፡ የሚአደርጉት ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ እንደሆንክ፡ እናምናለን፡አሉት።

፰፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ሥዕሎቹ ፡ መለስ፡ ብሎ፡ እናንተ ፡ ያረጃችሁ ፡ ሥዕሎች ፡ ሆይ፡ በውስጣችሁ ፡ መንፈስ ፡ ያድር ፡ ዘንድ፡ ሥጋንም ፡ ትለብሱ ፡ ዘንድ ፡ እናንተን፡ ተናገርኩ፤ከቦታችሁም፡ተነሥታችሁ፡እኛ ወዳለንበት፡ወደምድር፡ኑ።

፱፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አብርሃም ፡ ይሥሐቅ፡ ያዕቆብና፡ከቀድሞ፡ዘመን፡ጀምሮ፡ከአበው፡ ልጆች፡ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ወደተቀበሩበት ሄዱ።

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፤ ወበልዎሙ፡ ወልደ፡እግዚአብሔር፡ፈጣሬ፡
ቀዳማዊ ፡ ይኤዝዘክሙ ፡ ከመ ፡ ትምጽኡ ፡
ኵልክሙ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወይምጻእ፡
ምስሌክሙ፡አሐዱ፡እምውሉድክሙ፡ዘኮነ፡
የአምር፡ምሥጢራትየ፡ወዜና፡ምጽአትየ፡
ውስተ፡ዓለም፡ከመ፡ታጠይቅዎሙ፡ለውሉ
ድክሙ፡አይሁድ፡ኵሎ፡ከመ፡መኑ፡አነ፡ወእ
ምአይቴ፡መጻእኩ፡ወኀበ፡አይቴ፡አሐውር።
፲፩፤ ወሶበ፡ይቤ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ዘንተ፡ነገረ፡
ላዕለ፡ሥዕላት፡ኮነ፡ዲበ፡ምድር፡ወውስተ፡
ኢየሩሳሌም፡ጽልመት፡ዐቢይ፡ወድልቅልቅ፡
ወሙብረቀ፡ኃይል፡ወነፋሰ፡ዐውሎ፡እስከ
ወድቁ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
በገጾሙ።
፲፪፤ ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ተአተተ፡ጽልመት፡ወር
እይዎሙ፡ለእሉ፡ሥዕላት፡ዘኮኑ፡እንስሳ፡ዘይ
ትሐወሱ፡ወሪዶሙ፡ምድረ።
፲፫፤ ወእምዝ፡ሖሩ፡ወአፍጠኑ፡ገጸ፡ሰብእ፡ወገጸ፡
አንበሳ፤ገጸ፡ንስር፡ወገጸ፡እንስሳ፡ውስተ፡
መካነ፡መቃብሪሆሙ፡ለአብርሃም፡ወለይ
ሥሐቅ፡ ወለያዕቆብ፡ ወኀበ፡ ዐሥርቱ፡
ወክልኤቱ፡ደቂቆሙ፡ለአበው።
፲፬፤ ወንስርሰ፡ሖረ፡ኀበ፡መቃብሪሁ፡ለሙሴ፡ወጸ
ውዕዎሙ፡ ወአብጽሕዎሙ፡ ኀበ፡ ቤተ፡
መቅደስ፡ በከመ፡ አዘዞሙ፡ እግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወበጽሑ፡ ፍጡነ፡
በቅጽበት፡ ወርእይዎሙ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡
ሀለዉ፡ህየ፡እምደቂቀ፡እስራኤል።
፲፭፤ እስመ፡ርእይዎሙ፡ለአብርሃም፡በሢበቱ፡
ወለይሥሐቅ፡በአምሳሉ፡ዘያስተርኢ፡ዘኮነ፡
ቦቱ፡እምቅድመ፡ይሙት።ወለያዕቆብሂ፡በት
እምርት፡ዘገብረ፡ቦቱ፡መልአከ፡እግዚአ
ብሔር፤ሶበ፡ተራከቦ፡በመካነ፡ራዳን፡ዳርም፡
ዛ፡ ይእቲ፡ ሐቅለ፡ ካራን። ወለሙሴሂ፡
ርእይዎ፡እንዘ፡ይሴባሕ፡ገጹ፡ወአእመርዎ፡
በለትቶ፡ልሳኑ።
፲፮፤ ወአኀዘ፡አብ፡አብርሃም፡ይትናገር፡ወይቤ፡
አ፡ማኅበረ፡አይሁድ፡አነ፡አቡክሙ፡ወእሉ፡
ክልኤቱ፡ ደቂቅየ፡ ይሥሐቅ፡ ወያዕቆብ፡
ወዝንቱኒ፡ ሙሴ፡ ነቢይ፡ ዐቢይ፡ እምው
ሉድየ፡[illegible]

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፤ እንዲህም፡በሉአቸው፤አስቀድሞ፡የነበረ፡
ፈጣሪ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ሁላችሁም፡
ወደ፡ቤተ፡መቅደስ፡ትመጡ፡ዘንድ፡የመም
ጣቴንና፡ሰው፡የመሆኔን፡ምሥጢሬን፡የሚአ
ውቀውን፡ከልጆቻችሁ፡አንዱ፡ከእናንተ፡
ጋራ፡ይምጣ፤እኔ፡ማን፡እንደሆንኩ፡ከየት፡
እንደመጣሁ፡ወዴትም፡እንድሄድ፡ለልጆ
ቻችሁ፡ለአይሁድ፡ታስረዱአቸው፡ዘንድ።
፲፩፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ለሥዕሎች፡ይህን፡ነገር፡
በተናገረ፡ጊዜ፡በኢየሩሳሌምና፡በምድር፡
ሁሉ፡ታላቅ፡ጨለማ፡ሆነ፤የኢየሩሳሌምም፡
ሰዎች፡ሁሉም፡በግንባራቸው፡ተደፍተው፡
እስቲወድቁ፡ድረስ፡የምድር፡ንውጽውጽታ፡
የኃይል፡መብረቅና፡ጥቅል፡ነፋስ፡ሆነ።
፲፪፤ ከዚህ፡በኋላ፡ጨለማው፡ተወግዶ፡ተንቀ
ሳቃሽ፡ የሆኑትን፡ ሥዕሎች፡ ከምድር፡
ወርደው፡አዩአቸው።
፲፫፤ ከዚህ፡በኋላም፡የሰው፡የእንስሳ፡የንስርና፡
የአንበሳ፡ፊት፡ያላቸው፡ሥዕሎች፡እነአብር
ሃምና፡ይሥሐቅ፡ያዕቆብም፡አሥራ፡ሁለቱ፡
ልጆቻቸውም፡ ወደ፡ ተቀበሩበት፡ ቦታ፡
ፈጥነው፡ሄዱ።
፲፬፤ ንስር፡ግን፡ሙሴ፡ወደተቀበረበት፡ቦታ፡ሄደ፤
ጌታ፡ኢየሱስም፡እንዳዘዛቸው፡ጠርተው፡
ወደ፡ቤተ፡መቅደስ፡አደረሱአቸው፤እንደ፡
ዓይን፡ጥቅሻም፡ፈጥነው፡ደረሱ፤ከእስራ
ኤልም፡ ልጆች፡ በዚያ፡ ያሉት፡ ሁሉ፡
አዩአቸው።
፲፭፤ አብርሃምን፡ በሺበቱ፡ ይሥሐቅንም፡
ከመሞቱ፡አስቀድሞ፡ይታይ፡በነበረበት፡
ምልክት፡ ያዕቆብንም፡ ራዳን፡ ዳርም፡
በሚባል፡ቦታ፡እርሷም፡የካራን፡በረኻ፡ናት፤
በዚያ፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ በተገ
ናኘው፡ ጊዜ፡ በአደረገለት፡ ምልክት፡
ሙሴንም፡ፊቱ፡ሲበራ፡አይተው፡በአንደ
በቱም፡ለንባዳነት፡አወቁት።
፲፮፤ አባት፡አብርሃምም፡ይናገር፡ዘንድ፡ጀመረ፤
እንዲህም፡አለ፤የአይሁድ፡ወገኖች፡ሆይ፡እኔ፡
አባታችሁ፡ነኝ፤እነዚህም፡ሁለቱ፡ልጆቼ፡
ይሥሐቅና፡ያዕቆብ፡ናቸው።ይኸም፡ከልጆቼ፡
ወገን፡ታላቅ፡ነቢይ፡የሆነው፡ሙሴ፡ነው።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።

፲፯፤ ወናሁ፡በጸሕነ፡ኀቡረ፡ዘምስለ፡አበው፡እለ፡ትሬእይዎሙ፡ምስሌነ፡በኃይሉ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡ዘከሀድክሙ፡መለኮቶ።

፲፰፤ ኦ፡ደቂቅየ፡ሎቱ፡ስምዕዎ፡ወተአዘዙ፡ለቃለ፡ዚአሁ።

፲፱፤ ወዓዲ፡ተንሥአ፡ሙሴ፡ከመ፡ይትናገር፡ወይቤሎሙ፡ኦ፡አኀውየ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡አነ፡ውእቱ፡ሙሴ፡ዘአውፃእኩ፡አበዊክሙ፡እምድረ፡ግብጽ፡በእደ፡ጽንዕት፡ወበመዝራዕት፡ልዕልት።

፳፤ አነ፡ውእቱ፡ዘቀሠፍክዎሙ፡ለግብጽ፡በመቅሠፍት፡አነ፡ውእቱ፡ዘነፈቅዋ፡ለባሕረ፡ኤርትራ፡ወአውፃእክዎሙ፡ለአበዊክሙ፡ወአስጠምክዎ፡ለፈርዖን፡ወለሠራዊቱ፡ውስቴታ።

፳፩፤ ወኵሎ፡መንክረ፡ዘገበርኩ፡በኃይሉ፡ለዝንቱ፡ብእሲ፡ዘይቀውም፡ማእከሌክሙ፡ገበርኩ።

፳፪፤ ወሰፍሐ፡ሙሴ፡እደዊሁ፡ኀበ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ወይቤ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘተናገረኒ፡እምዕፀ፡ጳጦስ።

፳፫፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘአውረደ፡ለክሙ፡መና፡በገዳም።
ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘአውፅአ፡ለክሙ፡ማየ፡እምኰኵሕ፡ጽንዕት።

፳፬፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘአብርሀ፡ለክሙ፡ጽልመተ፡በዓምደ፡እሳት፡እንዘ፡ተሐውሩ።

፳፭፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘነገረኒ፡ስሞ፡መልዕልተ፡ደብር፡እንዘ፡ይብል፡አህያ፡ሸራህያ፡ዝ፡ብሂል፡ዘሀሎ፡ወይሄሉ፡ዘውእቱ፡እግዚአ፡ኀይላት፡ጸባኦት።

፳፮፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘተነበይኩ፡አነ፡በእንተ፡ምጽአቱ፡ወእቤለክሙ፡ያነሥእ፡ለክሙ፡እግዚአብሔር፡እምአኀዊክሙ፡ነቢየ፡ዘከማየ።

፳፯፤ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘአብአኒ፡በአተ፡መልዕልተ፡ደብር።
ዝ፡ውእቱ፡ዘለሐኮ፡ለአቡነ፡አዳም፡ቅድመ፡በእደዊሁ፡ወገብሮ፡በአርአያሁ፡ወበአምሳሊሁ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፯፤ እነሆ፡ከእኛ፡ጋራ፡ከምታዩአቸው፡አባቶች፡ጋራ፡አምላክነቱን፡በካዳችሁት፡በዚህ፡ሰው፡ኃይል፡በአንድነት፡መጣን።

፲፰፤ ልጆቼ፡ሆይ፡ቃሉን፡ስሙት፡ለእርሱም፡ታዘዙ።

፲፱፤ ዳግመኛም፡ሙሴ፡ተነሥቶ፡ይናገር፡ዘንድ፡ጀመረ፤እንዲህም፡አላቸው፤ወንድሞቼ፡የእስራኤል፡ልጆች፡በፀናች፡እጅ፡በበረታች፡ክንድ፡ከግብጽ፡ምድር፡አባቶቻችሁን፡ያወጣሁ፡እኔ፡ሙሴ፡ነኝ።

፳፤ ግብጻውያንን፡በመቅሠፍት፡የቀጣኋቸው፡እኔ፡ነኝ፤የኤርትራን፡ባሕር፡ከፍዬ፡አባቶቻችሁን፡ያወጣሁ፡ፈርዖንንና፡ሠራዊቱን፡በውስጥዋ፡ያሰጠምኩ፡እኔ፡ነኝ።

፳፩፤ ተአምራቱን፡ሁሉ፡ያደረግሁት፡ከመካከላችሁ፡በቆመው፡በዚህ፡ሰው፡በሆነው፡አምላክ፡ኃይል፡ነው።

፳፪፤ ሙሴም፡እጆቹን፡ወደ፡ጌታችን፡ወደ፡ኢየሱስ፡ዘርግቶ፡እንዲህ፡አለ፤ከዕፀ፡ጳጦስ፡ውስጥ፡የተናገረኝ፡ይህ፡ነው።

፳፫፤ በበረኻ፡ውስጥ፡ሳላችሁ፡መና፡ያወረደላችሁ፡ይህ፡ነው።
ከጸናች፡ዓለትም፡ውኃ፡ያፈለቀላችሁ፡ይህ፡ነው።

፳፬፤ ስትጓዙም፡በእሳት፡ዓምድ፡ጨለማውን፡ያበራላችሁ፡ይህ፡ነው።

፳፭፤ በደብረ፡ሲና፡ላይ፡አህያ፡ሸራህያ፡ነኝ፡ብሎ፡ስሙን፡የነገረኝ፡ይህ፡ነው፤ትርጓሜውም፡አስቀድሞ፡የነበረ፡ዛሬም፡ያለ፡ከዓለም፡ኅልፈት፡በኋላም፡የሚኖር፡ማለት፡ነው፡እርሱም፡የሠራዊት፡ጌታ፡ነው።

፳፮፤ ስለ፡እርሱ፡ትንቢት፡የተናገርኩለት፡ከወንድሞቻችሁ፡ውስጥ፡እንደ፡እኔ፡ያለ፡ነቢይን፡እግዚአብሔር፡ያስነሣላችኋል፡ያልኋችሁ፡እርሱ፡ይህ፡ነው።

፳፯፤ በተራራው፡ላይ፡ወደዋሻ፡ያስገባኝ፡ይህ፡ነው።
አስቀድሞ፡አባታችን፡አዳምን፡በእርሱ፡ያውና፡በምሳሌው፡የፈጠረው፡ይህ፡ነው።

| በ፲ወ፭፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘሠኑይ። | ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፭፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ፳፰፡ ወይእዜኒ ፡ መጽአ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ያድኅኖ ፡ ለአዳም ፡ እምኵነኔ ፡ ኃጢአት ፡ ዘስሕተት። | ፳፰፡ አሁንም፡ስቶ፡ኃጢአት፡ሠርቶ፡ከመጣበት፡ፍዳ፡አዳምን፡ያድነው፡ዘንድ፡ሰው፡ሆነ። |
| ፳፱፡ አ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ስምዑ ፡ ወተአዘዙ ፡ ሎቱ።<br>ወኵላ፡ነፍስ፡እንተ፡ኢትሰምዖ፡ትትሀጐል፡እምውስተ፡ሕዝባ። | ፳፱፡ የእስራኤል፡ልጆች፡ሆይ፡ቃሉን፡ስሙ፤ታዘዙለትም።<br>የማትሰማውና ፡ የማትታዘዝለት ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ ከወገንዋ ፡ ተለይታ ፡ ትጠፋለች ፡ አላቸው። |
| ፴፡ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ሙሴ ፡ ነጊረ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ተሰብሐ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ፡ ወፈድፈደ ፡ ብርሃኑ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ። | ፴፡ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መናገሩን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የጌታችን ፡ ፊቱ ፡ ቦግ ፡ ብሎ ፡ በራ፤ብርሃኑም፡ከፀሐይ፡እጅግ፡የሚበልጥ፡ሆነ። |
| ፴፩፡ ወሶበ፡ርእይዎ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡እለ፡ነበሩ፡ ህየ ፡ ወድቁ ፡ በገጾሙ ፡ ወኮኑ ፡ ከመ ፡ አብድንት፡ወአንሥአሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወአጽንዐ፡አልባቢሆሙ። | ፴፩፡ ከዚያ፡የነበሩ፡የእስራኤል፡ልጆች፡በአዩት፡ጊዜ ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፍተው ፡ ወደቁ፤ እንደ ፡ በድንም ፡ ሆኑ ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ አነሣቸው፤ልቡናቸውንም፡አጸናናቸው። |
| ፴፪፡ ወይቤሎሙ ፡ ትትካሀዱኑ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ኢኮንኩ ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ እንዘ ፡ እሉ ፡ አበው፡ይከውኑኒ፡ስምዐ፡ወእሙንቱስ፡ኢተ ክሀሎሙ ፡ ያውሥእዎ ፡ አሐተ ፡ ቃለ ፤ ወአምኑ፡ቦቱ፡ብዝኆሙ። | ፴፪፡ እንዲህም፡አላቸው፤እኔ፡የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እንዳልሆንኩ፡አሁንም፡ትከራከሩላችሁን፡እነዚህ፡አባቶች፡እየመሰከሩልኝ፡አላቸው። እነርሱ፡ግን፡አንዲት፡ቃል፡ይመልሱለት፡ዘንድ ፡ አልተቻላቸውም ። ብዙዎቹም ፡ አመኑበት። |
| ፴፫፡ ወእምዝ ፡ ይቤሎሙ ፡ ኢትትመከሑ ፡ ከመ ፡ አብርሃም ፡ አቡክሙ ፡ እስመ ፡ ብየ ፡ ክሂል ፡ አንሥኦ፡እምእላንቱ፡አዕባን፡ውሉደ፡ለአብ ርሃም። | ፴፫፡ ከዚህ፡በኋላ፡አብርሃም፡አባታችሁ፡ስለሆነ፡አትመኩ ፤ ከእነዚህ ፡ ደንጊያዎች ፡ ለአብ ርሃም፡ ልጆች ፡ አድርጌ ፡ አስነሣ ፡ ዘንድ ፡ ችሎታ፡አለኝና፡አላቸው። |
| ፴፬፡ ወነበሩ ፡ አበው ፡ አብርሃም ፡ ይሥሐቅ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወሙሴ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተንሥኡ፡እመቃብሪሆሙ፡በምድረ፡ኢየሩ ሳሌም፡ሠሉሰ፡መዋዕለ፡እንዘ፡ይጼውዑ፡ሰብአ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወይሰብኩ፡በስሙ። | ፴፬፡ አባቶች ፡ አብርሃምና ፡ ይሥሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ ሙሴና፡ከመቃብራቸው፡የተነሡት፡አበው፡ሁሉም፡በኢየሩሳሌም፡ምድር፡ሦስት፡ቀን፡ያህል ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደማመን፡ሰውን፡እየጠሩ፡በስሙም፡እያስ ተማሩ፡ሰነበቱ። |
| ፴፭፡ አይሁድሰ ፡ ኢተወከፍዎሙ ፡ ወኢአም ንዎሙ፡ከመ፡እሙንቱ፡አበው፡ወባሕቱ፡ኮኑ፡ይዌግርዎሙ፡በአዕባን። | ፴፭፡ አይሁድ፡ግን፡እነርሱ፡አባቶች፡እንደሆኑ፡አልተቀበሉአቸውም ፤ አላመኑአቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በድንጋይ ፡ ሊወግሯቸው ፡ ጀመሩ። |
| ፴፮፡ ወይቤልዎሙ ፡ አንትሙ ፡ መሠርያን ፡ አብያጺሁ፡ለኢየሱስ፡ከመ፡ኢያኔስ፡ወኢያ ንበሬስ፡መሠርያን፡ግብጽ፡ኮኑ፡ይገብሩ፡ዘይበዝኀ፡እምዝ፡ግብር፡ዘይገብሮ፡ወልደ፡ጸራቢ።(ሎቱ፡ስብሐት) | ፴፮፡ የጸራቢው ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ይሠራው ፡ ከነበረው፡ሥራ፡ይልቅ፡አብዝተው፡ይሠሩ፡እንደነበሩ፡እንደግብጽ፡ጠንቋዮች፡እንደ፡ኢያኔስ ፡ እንደ ፡ ኢያንበሬስ ፡ የክርስቶስ ፡ ጓደኞች ፡ የሆናችሁ ፡ ጠንቋዮች ፡ ናችሁ ፡ አሉአቸው ። (ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና) ፡ |

**በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘሠኑይ።**

፴፯፤ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እመሰ ፡ አነ ፡ መሠርይ ፡ ቦኑ ፡ እሉኒ ፡ አበው ፡ ንጹሐን ፡ መሠርያንኑ ፡ እሙንቱ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ከመ ፡ አነሥእ ፡ እምኔክሙ ፡ ዘይፈትሑ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ወይትዋቀሡክሙ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ፡ ዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ እመ ፡ እመጽእ ፡ በስብሐትየ ፡ ወስብሐተ ፡ ሐራ ፡ መላእክትየ፡ንጹሐን።

፴፰፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ነገሮ ፡ ወገርዎ ፡ ካዕበ ፡ በአዕባን።

፴፱፤ ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ጸረቶ፡ደመና፡ወአብጽሐቶ፡ፈለገ፡ዮርዳኖስ።

፵፤ ወመጽኡ፡አበው፡ኀበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤልዎ፡አ፡እግዚእነ፡እስመ፡ርኢነ፡ስብሐቲከ፡ወይእዜኒ፡ምንተ፡ትኤዝዘነ።

፵፩፤ ወይቤሎሙ፡ተመየጡ፡መካነክሙ፡እንተ፡ተንሣእክሙ፡እምኔሃ፡በሰላም፡ወተመይጡ፡መካናቲሆሙ፡እንዘ፡የአኵትዎ፡ለእግዚአብሔር።

፵፪፤ ወእሙንቱኒ፡ሥዕላተ፡አርባዕቱ፡እንስሳ፡እለ፡ለብሱ፡ሥጋ፡መጽኡ፡ገጸመ፡ኀበ፡ሀሉ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወሰገዱ፡ሎቱ።

፵፫፤ ወለእሙንቱኒ ፡ ሥዕላት ፡ ይቤሎሙ ፡ ተመየጡ ፡ መካነክሙ ፡ በከመ ፡ ኮንክሙ ፡ ቀዳሚ፡ውስተ፡ቤተ፡መቅደስ።

፵፬፤ ወተመይጡ ፡ እሉ ፡ ሥዕላት ፡ በከመ ፡ ኮኑ ፡ ቀዳሚ ። ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡በል።

## ክፍል፡፫።

**ይዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።**

መዝ፡፲፱፡፪።

ወትጼዕረኒ ፡ ልብየ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ። እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ ይትዔበዩ ፡ ጸላእትየ ፡ ላዕሌየ ። ነጽረኒ፡ ወስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ።

ይሕ፡ ሕዝብኒ፡ይሰጠዉ፡ዘንተ።

ይ፡ዲ፡ ቁሙ፡ወአጽምዑ።

ይ፡ካ፡ ወንጌል፡ቅዱስ፡ይበል።

**ወንጌል፡ዘዮሐንስ።**

ምዕ፡፰፡፶፩–፶፱።

፶፩፤ አማን፡አማን፡እብለክሙ፡ዘዐቀበ፡ቃልየ፡ኢይጥዕም፡ለሞት፡ለዓለም።

፶፪፤ ወይቤልዎ ፡ አይሁድ ፡ ይእዜኬ ፡ አእመርናከ ፡ (ሎቱ፡ ስብሐት) ፡ ከመ ፡ ጋኔን ፡ ብከ ፡ አብርሃም ፡ ጥቀ ፡ ሞተ ፡ ወነቢ

**ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።**

፴፯፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡እኔስ፡መሠርይ፡ከተባልሁ፡ በውኑ ፡ እነዚህ ፡ ንጹሐን ፡ አባቶች፡ መሠርያን፡ይባላሉን?በፍርድ፡ቀን፡ሙታን፡ በሚነሡበት ፡ ቀን፡ በክብሬና ፡ በጌትነቴ፡ በንጹሐን ፡ መላእክቶቼም ፡ ምሥጋና፡ በምመጣ፡ጊዜ፡በእናንተ፡ላይ፡የሚፈርዱ፡ የሚያስፈርድባችሁ፡ከእናንተ፡ውስጥ፡እነ ማስነሣ ፡ በእውነት ፡ እነግራችኋለሁ፡ አላቸው።

፴፰፤ ነገሩንም፡በሰሙ፡ጊዜ፡ሁለተኛ፡ደንጊያ ወረወሩበት።

፴፱፤ ከዚህም፡በኋላ፡ደመና፡ተሸክማ፡ከዮርዳኖስ ወንዝ፡አደረሰችው።

፵፤ አባቶችም፡ወደ፡ጌታ፡ኢየሱስ፡መጥተው፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ክብርህን ፡ አይተናልና፡ እንግዲህ፡አሁን፡ምን፡ታዘናለህ፡አሉት፡

፵፩፤ ወደ ፡ ተነሣችሁበት ፡ ቦታችሁ፡ በሰላም ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰገኑ ፡ ወደቦታቸው፡ ተመለሱ።

፵፪፤ ሥጋ፡የለበሱ፡እነዚያም፡የአርባዕቱ፡እንስሳ ሥዕሎች፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ወዳለበት፡በረኛ ቦታ፡መጥተው፡ሰገዱለት።

፵፫፤ እነዚያን፡ሥዕሎችም፡አስቀድሞ፡ትኖሩ ወደ፡ነበራችሁበት፡ወደ፡ቦታችሁ፡ወደ ቤተ፡መቅደስ፡ተመለሱ፡አላቸው።

፵፬፤ እነዚያም ፡ ሥዕሎች ፡ እንደቀድሞው ኑሮአቸው፡ተመለሱ። ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለም ይኑር፡አሜን።

አመ፡ትመጽእ፡በል።

## ክፍል፡፫።

**ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።**

መዝ፡፲፱፡፪።

ልቡናዬም ፡ ሁልጊዜ ፡ ታስጨንቀኛለች፡ ጠላቶቼስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይታበዩብኛል፡ አቤቱ፡ፈጣሪዬ፡ ልመናዬን፡ስማኝ፡ተመለከ ተኝም፡ይበል።

(ሕ) ይህንንይቀበሉ።

ዲያቆኑ፡ ቁሙ፡ወአጽምዑ፡ይበል።

ይ፡ካ፡ ወንጌል፡ቅዱስ፡ይበል።

**የዮሐንስ፡ወንጌል።**

ምዕ፡፰፡፶፩–፶፱።

፶፩፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡ ቃሌን የጠበቀ፡ለዘለዓለም፡ሞትን፡አይቀምስም።

፶፪፤ አይሁድም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፡ (ሎቱ ስብሐት)፡ ገና ፡ ዛሬ ፡ ጋኔን ፡ እንዳለብህ አወቅን ፡ እኮ ፡ አብርሃም ፡ ሰማ

በ፩፡ሰዓተ፡ሌሊት፡ዘሠሉስ፡ንዋም።

፶፮፤ አንትሙ ፡ ተዐቢ ፡ እምአቡነ ፡ አብርሀም ፡
ዘጥዕመ፡ሞተ።ኢኮነ፡ለከ፡ዓዲሁ፡፶፡ዓመት፡
እመዋዕል ፡ አብርሃምሃ ፡ እፎ ፡ ርኢከ ፡ መነ ፡
ትሬሲ፡ርእሰከ።
፶፯፤ ወይቤ ፡ መድኅን ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ከመ ፡
አነ፡ሀሎኩ፡እምቅድመ፡አብርሃም።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ወኵሉ፡ሥርዓቱ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፲፫።

ትእዛዝ ፡ ወእምዝ ፡ ይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡
ውስተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ በቀዳሚ ፡
ሰዓተ፡ ሌሊት፡ዘሠሉስ፡ዘውእቱ፡፩፡ሰዓት፡
(ንዋም።)
ወይጸልዩ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ዘይብል ፡
ተዘከሮ፡እግዚኦ፡ለዳዊት፡እስከ፡ኀበ፡ይብል፡
ወእሰሰልኩ፡ጽዕለተ፡እምደቂቀ፡እስራኤል።
ወውዳሴ፡ማርያም፡ዘቀዳሚት።

### ክፍል፡፩።

ዘዘካርያስ፡ነቢይ፡በረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፩፡፩–፬።

፩፤ በካልእ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለዳርዮስ ፡
በሳምን ፡ ወርኀ ፡ ኮነ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
ኀበ፡ዘካርያስ፡ወልደ፡በራክዩ፡ወልደ፡ሐዶ፡
ነቢይ፡እንዘ፡ይብል።
፪፤ ተምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ አበዊክሙ ፡
ዐቢየ፡መዓተ።
፫፤ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡
ይመልክ፡ተመየጡ፡ኀቤየ፡አነኒ፡እትመየጥ፡
ኀቤክሙ።
፬፤ ወኢትኩኑ፡ከመ፡አበዊክሙ፡እለ፡ገሠፅዎሙ፡
ነቢያት ፡ ቀደምት ፡ ወይቤልዎሙ፡ ከመዝ ፡
ይቤ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ፡
ተመየጡ ፡ እምፍኖትክሙ ፡ እኩይ ፡ ወእም
እከየ፡ምግባሪክሙ፡ወአበዩ፡ሰሚዖትየ፡ይቤ፡
እግዚአብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ።

ማክሰኞ፡ሌሊት፡በ፩፡ሰዓት።

፶፮፤ አንተ ፡ ከሞተው ፡ ከአባታችን ፡ ከአብርሃም
ትበልጣለህን፡ከዘመናት፡ገና፡ሃምሳ፡ዓመት
አልሆነህ ፡ አብርሃምን ፡ እንዴት ፡ አየህ
ራስህን፡ማንን፡ታደርጋለህ?
፶፯፤ መድኅንም ፡ ከአብርሃም ፡ በፊት ፡ እኔ
እንዳለሁ፡በውነት፡እነግራችኋለሁ፡አለ፡
መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ መጥቶ ፡ ሰው
ሆኖ፡መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን፡

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ሥርዓቱ፡ሁሉ፡እንደ፡ፊተኛው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፲፫።

ትእዛዝ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በከበረች ፡ ቤተ
ክርስቲያን ፡ ማክሰኞ ፡ ከሌሊቱ ፡ በ
ጀመሪያው ፡ ሰዓት ፡ ካህናት ፡ ይ
ብሰቡ።
ተዘከሮ ፡ እግዚኦ ፡ የሚለውን ፡ የዳዊት
መዝሙር ፡ ወእሰሰልኩ ፡ ጽዕለተ ፡ እስ
ሚለው፡ድረስ፡ጸልዩ።
ውዳሴ፡ማርያምም፡የቀዳሚትን፡ይድገሙ

### ክፍል፡፩።

የነቢዩ፡የዘካርያስ፡ትንቢት፡በረከቱ፡ከእኛ
ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።

ምዕ፡፩፡፩–፬።

፩፤ ዳርዮስ፡በነገሠ፡በሁለተኛው፡ዘመን፡በስ
ንተኛው ፡ ወር ፡ በኅዳር ፡ የእግዚአብሔር
ቃል፡ ወደ ፡ ሐዶ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ በራክዩ ፡ ልጅ
ወደ፡ነቢዩ፡ዘካርያስ፡እንዲህ፡ሲል፡መጣ
፪፤ እግዚአብሔር ፡ በአባቶቻችሁ ፡ ላይ ፡ ጽኑ
ቁጣ፡ተቆጣ።
፫፤ ሁሉን፡የሚገዛ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ
እናንተ፡በንስሓ፡ወደኔ፡ተመለሱ፤እኔም፡ወደ
ቅርታዬ፡ወደ፡እናንተ፡እመለሳለሁ።
፬፤ ሁሉን፡የሚገዛ፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ
ከክፉ ፡ ሥራችሁ ፡ ከክፉም ፡ ምግባራችሁ
ተመለሱ ፤ እኔንም ፡ መስማት ፡ እምቢ ፡ አሉ
ብለው፡ቀድሞ፡የነበሩ፡ነቢያት፡እንደ፡መከ
ሩአቸው ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር
እንደ፡አባቶቻችሁ፡አትሁኑ፡አለ።

## በ፲ወ፩፡ሰዓተ መዓልት፡ዘሠኑይ።

ያትኒ ፡ ሞቱ ፡ ወአንተሰ ፡ ትብል ፡ ዘዓቀበ ፡
ቃልየ፡ኢይጥዕም፡ለሞት፡ለዓለም።
፶፫፡ አንተኑ፡ተዐቢ፡እምአብርሃም፡አቡነ፡ዘሞተ፡
ወእምነቢያትኒ ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ መነ ፡ ትሬሲ ፡
ርእሰከ።
፶፬፡ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡
እመሰ፡ለልየ፡ሰባሕኩ፡ርእስየ፡ኢይበቍዓኒ፡
ስብሐትየ፡ወኢምንተኒ፡አላ፡ሀሎ፡አቡየ፡ዘይ
ሴብሐኒ ፡ ዘአንትሙ ፡ ትብልዎ ፡ አምላክነ ፡
ውእቱ፡ወኢተአምርዎ።
፶፭፡ ወአንሰ፡አአምሮ፡ወእመሰ፡እቤ፡ኢየአምሮ፡
እከውን ፡ ከማክሙ ፡ ሐሳዌ ፡ ወአንሰ ፡
አአምሮሂ፡ወቃሎሂ፡አዐቅብ።
፶፮፡ አብርሃም፡አቡክሙ፡ተመነየ፡ከመ፡ይርአይ፡
ዕለትየ፡ወርእየሂ፡ወተፈሥሐ።
፶፯፡ ወይቤልዎ ፡ አይሁድ ፡ ሃምሳ ፡ ዓመት ፡
አልብከ፡አብርሃምሃ፡ርኢከ።
፶፰፡ ወይቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አማን ፡
አማን፡እብለክሙ፡እምቅድመ፡ይትወለድ፡
አብርሃም፡ሀሎኩ፡አነ።
፶፱፡ ወነሥኡ ፡ እብነ ፡ ከመ ፡ ይውግርዎ ፡ ወተኀ
ብአሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወወፅአ፡እምኵራብ፡
ወኀለፈ፡እንተ፡ማእከሎሙ፡ወሖረ።

### ድኅረ፡ወንጌል።

በዐሥርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡
ዘሰኑይ።

፩፡ ብርሃን ፡ ዘእምብርሃን ፡ ዘአብርሀ ፡ ላዕለ ፡
ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ወመልአ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡
ዘውእቱ፡እግዚእ፡ኢየሱስ።
፪፡ አይሁድሰ ፡ ኢቀርቡ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ብርሃን ፡
ከመ፡ይርአይዎ።
፫፡ አስተርአየ ፡ ውስቴቱ ፡ ምሥጢሩ ፡ እስመ ፡
ዘአምነ፡ቦቱ፡ኢይመውት፡ለዓለም።
፬፡ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ አብዳን ፡ አይሁድ ፡ ይቤሉ ፡
አብርሃም፡ሞተ፡ወነቢየትኒ፡ሞቱ፡እፎ፡ዘኢ
ይመውት፡ዘየአምን፡ብከ።
፭፡ ይቤሎሙ ፡ ለእመ ፡ ሰባሕኩ ፡ ርእስየ ፡ ኢኮነ ፡
ስብሐትየ ፡ ምንተኒ ፡ እስመ ፡ ህየ ፡ ሊተ ፡ ዘይሴ
ብሐኒ።

## ሰኞ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ሞቷል ፤ ነቢያትም ፡ ሙተዋል ፤ አንተ ፡ ግን ፡
ቃሌን፡የጠበቀ፡ለዘላለም፡አይሞትም፡ትላለህ።
፶፫፡ ከሞተው ፡ ከአባታችን ፡ ከአብርሃም ፡ ከሞቱ ፡
ከነቢያትስ ፡ አንተ ፡ ትበልጣለህን ? ራስህን ፡
ማንን፡ታደርጋለህ?
፶፬፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤ እኔ ፡
ራሴን፡በራሴ፡ባመሰግን፡ምሥጋናዬ፡ምንም፡
አይጠቅመኝም ፤ እናንተ ፡ አምላካችን ፡ ነው ፡
የምትሉትና፡የማታውቁት፡የሚአመሰግነኝ፡
አባቴ፡አለ።
፶፭፡ እኔ ፡ ግን ፡ አውቀዋለሁ ፡ አላውቀውም ፡ ብል ፡
እንደናንተ ፡ ሐሰተኛ ፡ እሆናለሁ ፤ እኔስ ፡ አው
ቀዋለሁ ፤ ቃሉንም፡እጠብቃለሁ።
፶፮፡ አባታችሁ ፡ አብርሃም ፡ የእኔን ፡ ቀን ፡ ሊያይ ፡
ተመኘ ፤ አይቶም፡ደስ፡አለው።
፶፯፡ አይሁድም ፡ ሃምሳ ፡ ዓመት ፡ ያልሆነህ ፡
እንዴት፡አብርሃምን፡አየህ፡አሉት።
፶፰፡ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ እላች
ኋለሁ ፤ አብርሃም ፡ ሳይወለድ ፡ እኔ ፡ ነበርኩ ፡
አላቸው።
፶፱፡ ሊወግሩትም፡ደንጊያ፡አነሡ ፤ ጌታ፡ኢየሱስ፡
ግን ፡ ተሠውሮአቸው ፡ ከምኵራብ ፡ ወጣና ፡
በመካከላቸው፡አልፎ፡ሄደ።

### ከወንጌል፡በኋላ።

ሰኞ ፡ ከቀኑ ፡ በአሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡
የሚነበብ።

፩፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የሚያበራ ፡ ዓለምን ፡
ሁሉ ፡ የመላ ፡ ከብርሃን ፡ የተገኘ ፡ ብርሃን ፡
ይኸውም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ነው።
፪፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ያዩት ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡
ብርሃን፡አልቀረቡም።
፫፡ በውስጡም ፡ ምሥጢሩ ፡ ተገለጠ ፤ ያመነበት ፡
ለዘላለም፡አይሞትምና።
፬፡ ሰነፎች፡አይሁድም፡በሰሙ፡ጊዜ፡አብርሃም፡
ሙቷል ፤ ነቢያትም ፡ ሙተዋል ፤ ያመነብህ ፡
የማይሞተው፡እንዴት፡ነው፡አሉ።
፭፡ እኔ፡ራሴን፡በራሴ፡ባመሰግን፡ምስጋናዬ፡ምንም፡
አይጠቅመኝም ። የሚአመሰግነኝና ፡ በጌትነት ፡
በክብር፡የሚገልጠኝ፡ከዚያ፡አለና፡አላቸው።